



t.me/OLDBOOKSPDF

# ስውሯ ገዳይ

## AND THEN THERE WERE NONE

Agatha Christie

ትርጉም፡- ዓለም በቀለ

t.me/OLDBOOKSPDF

© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

የመጀመሪያ እትም፡- ነሐሴ 2007 ዓ.ም.

ዋና አከፋፋይ

ዩኒቲ መጻሕፍት መደብር

ኮሜርስ ከቴሌ ባር አጠገብ

ስልክ፡- 0912 028 794

፡- 0911 669 946

የመ.ሳ.ቁ. 4143

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አንድ

በባቡሩ አንደኛ ማዕረግ ፋርጎ ውስጥ በቅርቡ ጡረታ የወጡት ዳኛ ጀስቲስ -ዋርግሬቭ ተሳፍረዋል፡፡ ዳኛው ጥግ ላይ ተቀምጠው ሲጋራቸውን እያጨሱ የታይም መፅሄት ፖለቲካ አምድ ያነባሉ፡፡ መፅሄቱን አስቀምጠው ወደ ውጪ በመስኮቱ በኩል ተመለከቱ፡፡ ባቡሩ ሶመርሴትን አልፎ እየሔደ መሆኑን ተመልክተው የእጅ ሰአታቸውን አየት አደረጉ፡፡ የሁለት ሰዓት ጉዞ ይቀራቸዋል፡፡ ስለ ኢንዲያን ደሴት ያነበቡትን ለማስታወስ ሞከሩ፡፡

በዲቮን የባሕር ዳርቻ የሚገኘውን ኢንዲያ ደሴት የመዝናኛ ጀልባ አፍቃሪ የሆነ የአንድ አሜሪካዊ ቱጃር ንብረት ነበር፡፡ ቱጃሩ ከሶስተኛ ሚስቱ ጋር ባለመስማማቱ ደሴቷን እና በደሴቷ ላይ የተገነባውን የተቀናጣ መኖሪያ ቤት ለመሸጥ ማስታወቂያ አስነገረ፡፡ ስለደሴቷ ሽያጭ በሰፊው ሲዘግቡ የቆዩ ጋዜጦች አውን የተባለ ሰው እንደገዛት ዘገቡ፡፡ በጥቂት ቀናት ውስጥ የበርካታ ገዢዎች ስም ከደሴቷ ጋር ተያያዘ፡፡

ገብርኤል ተርል የተባለች የሆሊውድ ተዋናይት የእረፍት ግዜዋን በደሴቷ ለማሳለፍ በማሰብ እንደገዛቻው ተነገረ፡፡ ከቀናት በኋላ ደግሞ የእንግሊዝ ባሕር ሃይል ለማዘዣ ጣቢያነት እንደገዛው ፣ የንጉሳውያን ቤተሰቦች ለልኡላኑ የጫጉላ ግዜ ማሳለፊያ እንዳሰቡት እና የመሳሰሉት አሉባልታዎች ጋዜጦችን አጣበው ከረሙ፡፡

ጡረተኛው ጀስቲስ ዋርግሬቭ ከኪሳቸው አንድ ደብዳቤ አውጥተዉ ማንበብ ጀመሩ፡፡ ደብዳቤው የተፃፈበት የእጅ ፅሁፍ የሚያምር ባይሆንም ፊደላቱ ግን በግልፅ ይታያሉ፡፡

"ውድ ላውረንስ ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለደህንነትህ ከሰማሁ ብዙ አመታት አልፈዋል፡፡ ወደ ኢንዲያ ዲሲት መምጣት ይኖርብሃል፡፡ ... ደሴቷ እጅግ በጣም ውብ ስትሆን ስለድሮ ትዝታችን ለመጫወት አመቺ ናት፡፡ ... የሚያምር ተፈጥሮ እና ማይ ግባት አላት፡፡ ከፓዲንግተን በሚነሳው የጉዞ መስመር 12፡40 ባቡር ተሳፈር፡፡ ኦክብሪጅ ላይ እንገናኛለን፡፡

ያንተው ኮንስታንስ ከልሚንግተን"

ላኪዋ ሴት በደብዳቤው መጨረሻ ላይ ፊርማዋን አስቀምጣለች፡፡ ጀስቲስ ዋርግሬቭ ወይዘሮዋን ለመጨረሻ ጊዜ መቼ እንዳገኟት ለማስታወስ ሞከሩ፡፡ ከስምንት አመታት በፊት ነበር፡፡ በወቅቱ ወደ ጣሊያን በመሔድ በፀሃያማው የአገሪቷ ክፍል ዘና በማለት ማሳለፏን አስታወሱ፡፡ በመቀጠል ወደ ሶሪያ በማምራት መዝናናቷን ቀጥላ ነበር፡፡ በርግጥም ወ/ሮ ከልሚንግተን የግል ደሴት በመግዛት ምስጢራዊ ህይወቷን መቀጠል የምትፈልግ ሴት እንደሆነች ዳኛው ገመቱ፡፡ የግምታቸውን ትክክለኛነት ለራሳቸው በማረጋገጥ የባቡሩ ምቹ መደገፊያ ላይ ተንጋልለው ተኙ፡፡

• • •

ቬራ ክሌይትሮን በባቡሩ ሶስተኛ ማዕረግ ፉርጎ ውስጥ ከአምስት ተሳፋሪዎች ጋር በመጓዝ ላይ ናት፡፡ የባቡሩን ሙቀት ስታስበው በባህር ላይ የእረፍት ጊዜዋን ለማሳለፍ የሚያስችል ጊዜያዊ ስራ ማግኘቷ አስደሰታት፡፡ ብዙውን ጊዜ የእረፍት ጊዜ ስራ የሚያገናኛት ወኪል የሞግዚትነት ስራ ብቻ ነበር የሚሰጣት፡፡ በዚህኛው እረፍቷ ያጋጠማት የፀሃፊነት ስራ አስደስቷታል፡፡

አይናቿን ከድና ስለ ደብዳቤው ማሰላሰል ጀመረች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ስምሽን ያገኘሁት ከሴት ሰራተኞች አገናኝ ወኪል ደብዳቤ ላይ ነው፡፡ ወኪሎቹ በግል እንደሚያውቁሽ ተረድቻለሁ፡፡ በደብዳቤው የተገለፀውን ደሞዝ ለመክፈል የተስማማሁ ሲሆን ስራሽን ነሐሴ 8 መጀመር ትችያለሽ፡፡ በፓዲንግተን 12:40 ባቡር ተሳፍረሽ አክብሪጅ ስትደርሺ የሚቀበልሽ ሰው አዘጋጅቻለሁ፡፡ ለአንዳንድ ወጪ የሚሆንሽ አምስት ፓውንድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ልኬልሻለሁ ያንቺው ኡና ናንሲ አውን"

በፖስታው እናት ላይ የተፃፈው አድራሻ ኢንዲያን ደሴት ፣ ስቲክልሃቨን ፣ ዴቮን የሚል ነበር፡፡ ስለ ደሴቷ በቅርቡ የተፃፈ ነገር ከጋዜጦች ላይ አለመመልኳት አስታወሰች፡፡ ቀድሞ ያነበበቻቸው አንዳንድ ታሪኮች ምናልባትም እውነተኛ ላይሆኑ እንደሚችሉ አሰበች፡፡ አንድ ሚሊየነር በደሴቷ ላይ የገነባው መኖሪያ ቤት አቻ የሌለው እና የተቀናጣ እንደሆነ ሰምታለች፡፡

ቬራ ክሌይትሮን አድካሚ የት/ቤት ስራዋን በማስታወስ «የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማጫወት አስደሳች ስራ አይደለም» በማለት አሰበች፡፡ ቀዝቀዝ ባለ ስሜት «ይህንን ስራ ማግኘቴ በራሱ ጥሩ እድል ነው፡፡ ማንም ቀጣሪ በግድያ የተጠረጠችን ሴት መቅጠር አይፈልግም፡፡ ዳኛው በነፃ ቢያሰናብተኝም...» በማለት ስለ ስራ እድሏ አሰበች፡፡

አቃቤ ሕጉ ስለ ድፍረቷ ያለውን አድናቆት በገለፀላት ወቅት የተሰማትን ደስታ አሰበች፡፡ ከአንድ ወንጀል መርማሪ የማትጠብቀው መልካምነት ነበር፡፡ ወ/ሮ ሃሚልተንም ለእርሷ መልካም ነበሩ፡፡ ሁጎ ብቻ ነበረ የጨከነባት፡፡ አሁን ግን ስለ እርሱ ማሰብ አትፈልግም፡፡ የባቡሩ ሙቀት እየተሰማት ቢሆንም ባህር ላይ ለመስራት እየሔደች መሆኗን ስታስታውስ በድንገት ቀፈፋት፡፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በድንገት አእምሮዋ ውስጥ የመጣባት ምስል ነበር እስፈሪ ስሜት የፈጠረባት፡፡ ባህር ላይ ብቅ ጥልቅ የሚለው የሴሪል ጭንቅላት ምስል ታያት፡፡ ህይወቱን ለማትረፍ ወደ ዳር ለመዋኘት የሚታገለው ሲሪል... ወደ እርሱ በቀስታ እየዋኘች ስትሔድ የራሷን ምስል አሰበች፡፡ በሞት ሽረት ብቅ ጥልቅ ወደሚለው ሲሪል እየዋኘች ብትጠጋም በፍጥነት ደርሳ ልትታደገው እንደማትችል ግን እርግጠኛ ነበረች፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ የሰማያዊው ባህር ምስል እንዲሁም ከባህሩ ዳርቻ አሸዋ ላይ የተኛው የሁጐ ምስል ድቅን አለባት፡፡ እንደሚያፈቅራት የነገራት የሁጐ ምስል!

ስለ ሁጐ ማሰብ የለባትም...

አይኖቿን ገልጣ ከእርሷ ወንበር በተቃራኒ የተቀመጠውን ሰው አየች፡፡ ረጅም ቁመቱ ፣ የገረጣ ፊቱ እና ቀዝቃዛ ስሜት የሚያሳዩ አይኖቹ የተለየ ውበት እንደሰጡት አሰበች፡፡ ጠባብ አፉን ስታይ ደግሞ ጨካኝ ሰው መሰላት፡፡ «የሚወደው ስራ ያለው እና በአለም ላይ አስደሳች ስፍራዎችን በመዞር የተመለከተ ሰው ይመስላል» በማለት አሰበች፡፡ እርሷም አንድ ቀን ማለፊያ ስራ እንዲኖራት ተመኘች...

• • •

ፊሊፕ ሎምባርድ ከፊትለፊቱ የተቀመጠችውን ሴት በፈጣን አይኖቹ ከላይ እስከታች ገምግሞ ጨረሳት፡፡ «መስህብ ያላት - መምህርት መሳይ ናት» ሲል አሰበ፡፡ ከፍ ያለ ደረጃ ያላት ቀጣሪ እንደምትመስል ገመተ፡፡ ቀረብ ብሎ ሊያናግራት አሰበና ወዲያውኑ ሃሳቡን ቀየረ፡፡ የመጣበት ስራ ላይ ብቻ ማተኮር እንዳለበት አስታወሰ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሆኑ የስራው አይነት ምንድን ነው? አጭሩ አይሁድ አሰሪው ምስጢራዊ ነው፡፡ «ከፈለግህ ስራ ፤ ካልሆነ ግን ልትተወው ትችላለህ - መቶ አለቃ ሎምባርድ » የሚል መልስ ነበር የሰጠው፡፡

ሎምባርድ በዝግታ «መቶ የወርቅ ሳንቲም ትከፍላለህ?» በማለት ጠየቀው፡፡ ያቀረበው የክፍያ መጠን አነስተኛ እንዲመስል ነበር ዘና ብሎ የጠየቀው፡፡ ነገር ግን ለምግቡ እንኳን የሚበቃ ገንዘብ ስላልነበረው ከጠየቀው በታችም ሊቀበል ይችላል፡፡

አጭሩን አይሁድ ሊያታልለው እንደማይችል ያውቃል፡፡ አይሁዳውያን በተለይ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ፈጽሞ እንደማይታለሉ ያውቃል፡፡

ዘና እንዳለ ጥያቄውን ቀጠለ፡- «ተጨማሪ መረጃ አትሰጠኝም?» አይሁዱ አይዛክ ሞሪስ መላጣ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ስለ ስራው ሰፊ መረጃ እንደማይሰጠው ገለጸለት፡፡

«አይቻልም መቶ አለቃ ሎምባርድ፡፡ ደንበኞቹ በከፍተኛ አክብሮት እንደሚንከባከቡህ ነግረውኛል፡፡ ስቲክልሃቨን ፣ ዴቮን ድረስ ለምትጓዝበት ስራ ደግሞ ያልከውን መቶ ፍራንክ እከፍልሃለሁ፡፡ አክብሪጅ ጣቢያ ስትደርስ መኪና ይጠብቅህና ስቲክልሃቨን ያደርስሃል፡፡ ወደ ኢንዲያን ደሴት የሚወስድህም የሞተር ጀልባ ይጠብቅሃል፡፡ ስትደርስ ደንበኞቹ ይቀበሉሃል»

«ምን ያህል ቀናት ነው የምቆየው?» በማለት ሎምባርድ ጠየቀው፡፡

«ቢበዛ አንድ ሳምንት»

ሎምባርድ ፂሙን እያፍተለተለ «ህገ-ወጥ የሆነ ነገር ውስጥ እንደማልገባ ታውቃለህ አይደል» በማለት አይሁዱን ጠየቀው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሞሪስ ስስ ከናፍሮቹን በመጠኑ ከፊት አድርጎ ፈገግ አለና ‹‹ህግ ጣ ትዕዛዛ ካቀረቡልህ ስራውን ማቋረጥ ትችላለህ›› በማለት መለሰለት፡፡

የአይሁዱ ፈገግታ የነገር እንደሆነ ሎምባርድ ስለገባው እሱም ፈገግ አለ፡፡ ሎምባርድ ስለ ህጋዊነት የሚጨነቅ ሰው እንዳልሆነ ሁለቱም ያውቃሉ፡፡

ሎምባርድ በነፋሻማ ስፍራ ለመጨረሻ ግዜ የተዝናናበትን ወቅት ለማስታወስ ሞከረ፡፡ በኢንዲያ ደሴት ጥሩ የእረፍት ግዜ እንደሚጠብቀው አሰበ፡፡

* * *

የ65 አመቷ ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት ማጨስ በማይፈቀድበት የባቡሩ ሶስተኛ ማዕረግ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የጦር ሰራዊት አባል የነበሩት አባታቸው በከፍተኛ ስነ-ስርአት ስለነበር ያሳደጎቻቸው ከቤት ውጪ ስላለው አለም በብዛት አያውቁም፡፡ በመሆኑም የተሳፋሪው ስርአት-የለሽ አቀማመጥ እና ጩኸት ከሙቀቱ ጋር ተዳምሮ ረብሿቸዋል፡፡

የዚህ ዘመን ወጣቶች ስለ አቀማመጣቸው የማይጨነቁ ናቸው ሲሉ ወይዘሮዋ አሰቡ፡፡ ጥርሳቸውን ለማስነቀል ማደንዘዣ የሚወጉ እንዲሁም ለእንቅልፍ የሚሆን ኪኒን የሚጠብቁ ብልሹ ወጣቶች መብዛታቸውን በማሰብ የራሳቸውን ዘመን አስተዳደግ አመሰገኑ፡፡ ባቡሩ ውስጥ የተመለከቷቸው ሴቶች እጅ እና እግራቸውን ሳያስተካክሉ የሚቀመጡ ስርአት አልባ በመሆናቸው ወይዘሮዋ አፈሩ፡፡

ወ/ሮ ብሬንት ትኩረታቸውን ከተሳፋሪዎቹ ስርአት-አልባነት ላይ በማንሳት ስላለፈው አመት የበጋ እረፍት አስታወሱ፡፡ የዚህኛውን አመት እረፍት በኢንዲያ ደሴት ለማሳለፍ መቻላቸው የፈጠረላቸውን ደስታ በማሰብ ደጋግመው ያነበቡትን ደብዳቤ በድጋሚ አስታወሱት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለውድ ወ/ሮ ብሬንት

እንደሚያስታውሱኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ከአመታት በፊት ነሐሴ ወር ላይ ቤልሂቨን የእንግዶች ማረፊያ ተገናኝተን ነበር፡፡ ሁለታችንም ብዙ የምንጋራቸው ነገሮች እንዳሉን አስታውሳለሁ፡፡ በአሁኑ ወቅት ከዴቮን የባህር ዳርቻ በቅርብ ርቀት በሚገኝ ደሴት ላይ የራሴን የእንግዶች መቀበያ ከፍቻለሁ፡፡

እንደ እርስዎ የቀድሞውን ስርአት ለሚወድ ሰው የሚሆን ቦታ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ለእይታ የማይመችም ሆነ የሚረብሽ ድምፅ የማይኖርበት የበጋ እረፍት ያለ ምንም ክፍያ በኢንዲያን ደሴት ቢያሳልፉስ?

ነሐሴ 8 ለእርስዎ ተስማሚ እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡

የእርስዎ አክባሪ

ዩ.ኤን."

ወ/ሮ ብሬንት ስለ ላኪዋ ሴት ስም ለማስታወስ ሞከሩ፡፡ የፀሃፊዋን የማይነበብ ፊርማ እና የስም ምህፃረ-ቃል በመመልከት ብቻ ለማወቅ ባለመቻላቸው በስጨት ብለው "ለምንድን ነው ብዙ ሰዎች የሚነበብ ፊርማ የማይፅፉት?" በማለት ራሳቸውን ጠየቁ፡፡

ቤልሂቨን የተዋወቋቸውን ሰዎች ለማስታወስ ሞከሩ፡፡ ሁለት ተከታታይ የበጋ እረፍታቸውን ባሳለፉበት አጋጣሚ የተዋወቋትን በመካከለኛ እድሜ የምትገኝ ሴት ስም ለማስታወስ ሲጣጣሩ ቆዩ፡፡ የሴትየዋ ስም ኦሊቨር እንደነበር በመጨረሻ አስታወሱ፡፡

ኢንዲያን ደሴት በተደጋጋሚ በጋዜጦች የተጠቀሰ ስም ነበር፡፡ የፊልም ተዋናይ አሊያም ሚሊኒየር ሰው በባለቤትነት እንደያዘው ስለ ሽያጩ ካነበቡት ላይ አስታወሱ፡፡፡ በርካታ ቱጃሮች የግል ደሴት ለመግዛት



t.me/OLDBOOKSPDF

ይጣደፉና ጥቂት ግዜ ከኖሩበት በኋላ ጉዳቱን በመረዳት በርካሽ ዋጋ ለመሸጥ እንደሚወስኑ በተደጋጋሚ ወይዘሮዋ ሰምተዋል፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት ያለ ክፍያ የተቀናጣ የበጋ እረፍት ማሳለፋቸውን በማሰብ ተደስተዋል፡፡ ክፍያቸው ከአመት አመት በመቀነሱ ያጋጠማቸውን የገንዘብ እጥረት በማሰብ የቀረበላቸው ግብዣ እጅግ አስደሳች ነበር፡፡ የጋባዣቸውን ሴት ማንነት የበለጠ ለማስታወስ ከአእምሮአቸው ጋር መታገል ቀጠሉ፡፡

* * *

ጀነራል ማካርተር በባቡሩ መስታወት በኩል ወደ ውጪ ተመለከተ፡፡ ቀርፋፋው ባቡር ጀነራሉ ወደ ሚወርድበት ኤክስተር እየቀረበ ነበር፡፡ የሚሄድበት ኢንዲያን ደሴት ብዙ እንደማይርቅ የተሰማው ጀነራል በባቡሩ ቀርፋፋነት ተበሳጭቷል፡፡ ለመሆኑ እውን የተባለው ጋባዡ ማን ነው? ምናልባት የጎደኞቹ ስፑፍ ሌጋርድ ወይም ጆን ዳየር ሊሆን እንደሚችል ገመተ፡፡

'አንድ ወይም ሁለት የጥንት ጎደኞችህ ስለቀድሞው ግዜ በማውራት እረፍታቸውን ካንተ ጋር ለማሳለፍ ጎጉተዋል' የሚለውን የደብዳቤውን ክፍል አስታወሰ፡፡ ስለጥንቱ ግዜ ለመጫወት ከፍተኛ ጉጉት ቢኖረውም ወዳጆቹ ግን ርቀውታል፡፡ እድሜ ለዚያ የአሉባልታ ወሬ!

በፈጣሪ! ወጣቱ አርሚቴጅ ከሰላሳ አመታት በኋላ ነበር ለመጀመሪያ ግዜ ያናገረው፡፡ ለመሆኑ ምን አውርቶ ይሆን? ምንስ አውቆ ይሆን? መቼም መልካም ወሬ ከብዙ አመታት በኋላ ለመስማት አይጠብቅም፡፡ ነገር ግን ይህ ኢንዲያን ደሴት  የሚሉት ቦታ ብዙ ስለተወራለት ጀነራሉ ለማየት ጎጉቷል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ደሴቱ የባህር ሃይል አሊያም የአየር ሃይል ማዘገር ጣቢያ እንደሆነ የተነገረውን ወሬ ጀነራሉ ያስታውሳል፡፡ ወጣቱ አሜሪካዊ ሚሊኒየር ኤልመር ሮብሰን ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት ደሴቷን እንዳሳመራት የተነገረውን አስታወሰ፡፡ በርግጥም መዝናኛ ስፍራው አቻ የሌለው የቅንጦት ስፍራ ሆኗል፡፡ ኤክስተር ለመድረስ ተጨማሪ አንድ ሰአት በቀርፋፋው ባቡር ላይ ማሳለፉን በማሰብ ተቁነጠነጠ፡፡ ደሴቷን ለማየት ቸኮለ፡፡

* * *

ዶ/ር አርመስትሮንግ በዝግታ እያሽከረከረ የሳሊስቤሪን ሜዳ በማለፍ ላይ ነው፡፡ የስራ ጫና እንዳዳከመው ፊቱ ያሳብቅበታል፡፡ ዝነኛነት ያመጣበትን የስራ ውጥረት አስታወሰ፡፡ ሃርሌይ ጐዳና ላይ የሚገኘው ቢሮው በውድ ቁሳቁስ የተሞላ ሲሆን በተመሳሳይ ላይ የእርሱን እርዳታ በሚፈልጉ በርካታ ደምበኞቹ የተጣበበ ነበር፡፡ ይህንን መሰል እረፍት ዘወትር ያልም ነበር፡፡

የስነ-ልቦና አማካሪ የሆነው ዶ/ር አርመስትሮንግ በስራው ጉበዝ ከመሆኑም በላይ ዕድለኛ ጭምር ነው፡፡ የእርሱን እርዳታ በመፈለግ ቢሮውን የሚያጣብቡ ባለ ሃብት እና ዝነኛ ሴቶችን መመልከት የስኬታማነቱ ምስክር ነበር፡፡ ብዙዎች ስለ እርሱ ሲያወሩ "ወጣት ቢሆንም አስገራሚ ችሎታ አለው፡፡ ጣቱን ያሳረፈበት ችግር ወዲያውኑ ይፈታል" ይላሉ፡፡

ከስራ ውጥረቱ የገላገለውን ግብዣ ያበሰረው ደብዳቤ እጁ የገባው ከነሐሴ ወር በአንዱ ጠዋት ነበር፡፡ ደብዳቤው ግልፅ ባይሆንም ከዴቨን ጠረፍ አቅራቢያ ወደሚገኝ ደሴት የተደረገለትን ጥሪ ወጣቱ ዶ/ር ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ የተቀበለው ከደብዳቤው ጋር የተላከለትን ዳጐስ ያለ የገንዘብ ቼክ በመመልከት ነበር፡፡

የእውን ቤተሰቦች የተንደላቀቁ ሃብታሞች ናቸው!



t.me/OLDBOOKSPDF

ምናልባትም የሚስቱ ጤና ያሳሰበው ባል ሚስትየዋ ሃኪም ጋር ሊኖራት ከሚችለ መቅረቧን ሳታውቅ እንድትታከምለት ፈልጎ ሊሆን ይችላል በማለት አሰበ፡፡ ሴቶች ለአእምሮ መቃወስ ተጋላጭ ናቸው በማለት ቅንድቡን ከፍ አደረገ፡፡ የሴቶቹ መታመም ለስራ ጥሩ እንደሆነለት በማሰብ ስላማከራቸው ህመምተኛ ሴቶች አሰበ፡፡ የብዙዎቹ ችግር ተመሳሳይ ሲሆን መጠነኛ ድብርት ነበር፡፡ ነገር ግን ችግራቸውን በቀላሉ መንገድ ሲረዱ ስለማያስደስታቸው ዶ/ሩ በተወሳሰበ መንገድ ነበር ለህመምተኞች የሚያስረዳቸው፡፡

የሚያዝላቸው መድሃኒት በፍጥነት የሚፈውስ ባይሆንም ስለሚያምኑት ግን በቶሎ ይሻላቸዋል፡፡ ለአስራ አምስት አመታት ያህል ትርፋማ ስራ መስራቱን ሲያስብ እድለኛ መሆኑን ያምናል፡፡ ከአስራ አምስት አመት በፊት ያጋጠመው አስደንጋጭ ነገር ህይወቱን ወዳልጠበቀው መስመር እንዳዞራት ያውቃል፡፡ ከዚያ ጀምሮ መጠጥ የተባለ ነገር አቁሟል፡፡

ዶ/ሩን ከሃሳቡ ያባነነው እያጓራ አልፎት የሔደው የውድድር መኪና ድምፅ ነበር፡፡ ዶ/ሩ በድንጋጤ የራሱን መኪና ወደ መንገዱ ጠርዝ አወጣት፡፡ እንደዚህ ያሉ ችኩል አሽከርካሪዎች በከተማ ብቻ ያሉ ይመስለው ነበር፡፡

ቶኒ ማርስተን የውድድር መኪናውን እያከነፈ ስለ እንግሊዝ ጠባብ የመኪና መንገዶች እና አሽከርካሪዎች በብስጭት አሰበ፡፡ "ብዙ መኪና ባይኖርም መካከለኛውን መንገድ ይዘው ሌላ ሰው አያሳልፉም፡፡ የፈረንሳይ የመንገድ ስርአት የተሻለ ነው፡፡"

ለመጠጥ መቆም ፈልጎ ነበር፡፡ ነገር ግን ኢንዲያን ደሴት ለመድረስ የቀረውን መቶ ኪሎሜትር በጀመረው ፍጥነት ለመጨረስ በማሰብ ሃሳቡን



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀየረ፡፡ ለመሆኑ የደሴቱ ባለቤቶች የሆኑት የእውን ቤተሰቦች ምን ያህል ሃብታም ቢሆኑ ነው ህዝብ በስፋት ያወራላቸው በማለት አሰበ፡፡ በሚጠብቀው አስደሳች ግዜ በመደሰት መጠጥ በብዛት እንደሚኖር ተስፋ አደረገ፡፡

የደሴቷ ባለንብረት ተዋናይቷ ገብርኤል ተርል አለመሆኗ ያሳዝናል፡፡ ደሴቷ በበርካታ የፊልም ባለሙያዎች መጣበቧ አስደሳች እንደሚሆን በመገመት ብዙ ሴቶች ሊኖሩ ይችሉ እንደነበር በቁጭት አሰበ፡፡

ስለሴቶች ባሰበበት ቅፅበት ነበር መጠጥ በድጋሚ ያማረው፡፡ መንገድ ዳር ወዳ'ገኘው ሆቴል ገብቶ አንድ ሁለት ካለ በኋላ በር ላይ ወዳ'ቆማት ዳልሜይን መኪናው አመራ፡፡ የመኪናዋን በር ከፍቶ ሲገባ ሴቶች በአድናቆት እየተመለከቱት እንደነበር ታውቆታል፡፡ ረጅም ቁመቱ ፣ የቆመ ፀጉሩ ፣ ቀጥ ያለ አፍንጫውና ሰማያዊ አይኖቹ የማንንም እይታ እንደሚስቡ ያውቃል፡፡

የውድድር መኪናዋን እያስጮኸ ወደ መንገዱ ሲገባ መንገደኞች በሙሉ አንጻዱን በአግራሞት አዩ፡፡ አንቶኒ ማርስቶን በጉጉት ወደሚጠብቀው የደሴት መዝናኛ ተጣደፈ፡፡

* * *

አቶ ብሎር የተሳፈሩበት ቀርፋፋ ባቡር ከፕሊይማውዝ ነበር የተነሳው፡፡ እርሳቸው በነበሩበት ፉርጎ ውስጥ ሌላ አንድ ተሳፋሪ ብቻ ነበር፡፡ ተሳፋሪው ሽማግሌ ሲሆኑ መርከበኛ የሚያስመስል አለባበስ ነበራቸው፡፡

አቶ ብሎር በትንሿ ማስታወሻቸው ላይ እየፃፉ ከራሳቸው ጋር ማውራት ጀመሩ፡፡ "ብዙ ናቸው" በማለት በማስታወሻቸው ላይ የተዘረዘሩትን ሙሉ እና የምህፃረ-ቃል ስሞች ለራሳቸው አነበቡ፡፡ "ኤሚሊ ብሬንት ፣ ቬራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሊይትሮን ፣ ደ/ር አርመስትሮንግ ፣ አንቶኒ ማርስተን ፣ ሽማግሌው ጀስቲስ ዋርግሬቭ ፣ ፊሊፕ ሎምባርድ ፣ ጀነራል ማከአርተር ፣ ሲ.ኤም.ጂ ፣ ዲ.ኤስ.አ ፣ ማንሰርቫንት እና ሚስቱ እንዲሁም ሮጀር እና ባለቤቱ፡፡"

ማስታወሻ ደብተራቸውን ወደ ኪሳቸው በመመለስ ማሰላሰል ቀጠሉ፡፡ "ሁሉም ነገር እንከን የለሽ እና ቀላል በሆነ መንገድ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ በማለት በባቡሩ መስታወት የራሳቸውን ምስል ተመለከቱ፡፡ ምጥጥ ያለ ፊታቸው እና ፂማቸው ወታደር አስመስሏቸዋል፡፡ ገፅታቸው ምንም አይነት ስሜት አይነበብበትም፡፡ "ወታደር መሆኔን የሚለይ አይኖርም-" በማለት ለራሳቸው ማረጋገጫ ከመስጠታቸው በፊት በጡረታ የተገለለ መኮንን ከእንግዶቹ መካከል መኖሩን አስታወሱ፡፡

ደቡብ አፍሪካዊ መሆናቸውን በመግለፅ ለመቀላቀል ወሰኑ፡፡ ማናቸውም ስለ ደቡብ አፍሪካ ባለማወቃቸው የተወሰኑ ማስታወሻዎችን ካነበቡ ከሁሉም የተሻለ እውቀት ስለሚኖራቸው ደቡብ አፍሪካን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት እንደሚችሉ ገመቱ፡፡ ኢንዲያን ደሴትን በልጅነታቸው ነበር የተመለከቷት፡፡ መልካም ሽታ ያላቸው ኮረብታዎቿን ፈፅሞ አይረሱትም ነበር፡፡ ከጠረፍ አንድ ማይል ርቀት ላይ የምትገኘው ደሴት ስሟን ያገኘችው የአሜሪካ ኢንዲያ ሰው የፊት ገፅ ከሚመስለው ቅርጿ እንደነበር አስታወሱ፡፡

በዚያች ደሴት ላይ ቤት መስራት የማይታሰብ እንደሆነ ብሎር ገመቱ፡፡ በተለይ የደሴቷን አስቸጋሪ የአየር ፀባይ የሚያውቅ ሰው ቤት መስራት እንደማያስብ አውቀዋል፡፡ በመጨረሻም "ሃብታም ምን ቀልብ አለው?" ሲሉ በፈገግታ አሰቡ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በፉርጎው ወስጥ የነበሩት ሽማግሌ ተሳፋሪ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "የባህር ላይ አየርን መገመት አይቻልም" አሉ፡፡

አቶ ብሎርም በትህትና "ትክክል ብለዋል" በማለት መለሱላቸው፡፡

ሽማግሌውም ደጋግመው ሳሉና "አውሎ ንፋስ እየመጣ ነው" በማለት ተነበዩ፡፡ "አይመስለኝም ወዳጄ፡፡ ቀኑ ብሩህ ነው" በማለት ብሎር መለሱ፡፡ ሽማግሌው ቆጣ ብለው "ስነግርህ - ይሸተኛል!" በማለት ተከራከሩ፡፡ "ምናልባት - ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ" በማለት አቶ ብሎር ንግግሩን በሰላም ለመቋጨት ሞከሩ፡፡

ባቡሩ ሲቆም ሽማግሌው ተሳፋሪ እየተንገዳገዱ ከወንበራቸው ተነሱ፡፡ መራመድ እንዳቃታቸው የተመለከቱት አቶ ብሎር ሽማግሌውን ለመደገፍ ተጠጉ፡፡

"እዚህ ነው የምወርደው" በማለት ሽማግሌው በምስጋና መልኩ ለአቶ ብሎር ፈገግታ አሳዩ፡፡ የባቡሩን በር በሁለት እጃቸው ዘግተው ወደ ኋላ በመዞር "በትጋት ፀልይ ፤ የፍርድ ቀን ደርሳለች" በማለት አቶ ብሎርን አስጠነቀቁ፡፡

የአቶ ብሎር ቸልታ ያበሳጫቸው ሽማግሌ ቆጣ ብለው "አንተን እኮ ነው የምለው - ወጣቱ! የፍርድ ቀን ቀርባለች" በማለት ደገሙለት፡፡

አቶ ብሎር ወንበሩ ላይ ተመቻችቶ በመቀመጥ "ከእኔ ይልቅ እርስዎ ለፍርድ ቀን ቀርበዋል" በማለት የሽማግሌውን ማስጠንቀቂያ ለብቻው ተሳለቀበት፡፡

ነገር ግን ብሎር ተሳስቶ ነበር.....

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሁለት



ከኦክብሪጅ ባቡር ጣቢያ ውጪ ግራ የተጋቡ እንግዶች ሰብሰብ ብለው ቆመዋል፡፡ ከእነርሱ ጀርባ ደግሞ ሻንጣዎቻቸውን የያዙላቸው የጣቢያው ሰራተኞች ቆመዋል፡፡ አንዱ ሰራተኛ ከፍ ባለ ድምፅ "ጂም!" በማለት የታክሲ ሾፌር ጠራላቸው፡፡

"ሁላችሁም ወደ ኢንዲያን ደሴት ናችሁ?" በማለት ባለታክሲው በትህትና ሲጠይቃቸው አራቱ እንግዶች በአንድ ድምፅ መለሰሉለት፡፡ ወዲያውኑ እርስ በርሳቸው ተያዩ፡፡

ባለ ታክሲው ከእንግዶቹ መካከል እድሜያቸው ከፍ ያለውን ጀስቲስ ዋርግሬቭ በመመልከት ገለፃ አደረገላቸው፡፡ "ያሉን ሁለት ታክሲዎች ናቸው፡፡ አንደኛው ከአምስት ደቂቃ በኋላ የሚደርሰውን የኤክስተር ባቡር መጠበቅ አለበት፡፡ አንድ እንግዳ በዚያ ባቡር እየመጣ ነው፡፡ ለተሟላ ምቾታችሁ ሲባል ከእናንተ መካከል አንዳችሁ መቆየት ይኖርባችኋል' በማለት ሶስት ሰዎችን በመጫን ለመሔድ እንደሚችል ነገራቸው፡፡

ፀሃፊዋ ቬራ ክሌይትሮን ሶስቱን እየተመለከተች እናንተ ሂዱ፡፡ እኔ ከሚመጣው እንግዳ ጋር መምጣት እችላለሁ በማለት ስትናገር ወ/ሮ ብሬንት በፍጥነት አመስግነው ወደ ታክሲው ገቡ፡፡ ሽማግሌው ዋርግሬቭ ተከተሉ፡፡

መቶ አለቃ ሎምባርድ ካንቺ ጋር እጠብቃለሁ በማለት ለትውውቅ እጁን ዘረጋላት፡፡

"ቬራ ክሌይትሮን እባላለሁ"

"ፊሊፕ ሎምባርድ"



t.me/OLDBOOKSPDF

የባቡር ጣቢያው ሰራተኞች የእንግዶቹን ሻንጣዎች ታክሲዋ ላይ ጭነው ጨረሱ፡፡ ጡረተኛው ዳኛ ዋርግሬቭ ከበድ ባለ ድምፅ "አስደሳች አየር ነው" አሉ፡፡

"በትክክል" በማለት ወ/ሮ ብሬንት ተስማሙ፡፡ የዳኛውን ድምፅ በአግራሞት አሰቡ እና የደሴቷ ባለቤቶች ወ/ሮ ኦሊቨር እና ባለቤታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወዳጆች እንዳሏቸው ገመቱ፡፡

"ይህንን ስፍራ ከዚህ በፊት ታውቂዋለሽ?"

"ኮርንወል እና ቶርክን አይቻለሁ፡፡ እዚህ ስመጣ ግን የመጀመሪያ ነው፡፡" በማለት ወ/ሮ ብሬንት መለሱላቸው፡፡

ዳኛውም "ይህንን ቦታ እኔም አላውቀውም" በማለት ተስማሙ፡፡ ታክሲያቸውም መንገዱን ቀጠለ፡፡

የሁለተኛው ታክሲ ሾፌር "ባቡሩ እስኪደርስ ወደ ውስጥ ብትገቡስ?" በማለት በትህትና ጠየቃቸው፡፡

ቬራ በተመሳሳይ ትህትና "ግድየለም እንጠብቃለን" በማለት ስትመልስ ሎምባርድም በፈገግታ "ከዚያ ባቡር ከተገላገልን መቼም እዚህ መቆሙ አያስከፋም" በማለት ቬራን እና ሾፌሩን ተራ በተራ በጥያቄ ተመለከታቸው፡፡

"በዚህ ሙቀት በባቡር መጓዝ ከባድ ነው፡፡ አስቸጋሪውን የእንግሊዝ በጋ እዚህ ማሳለፍ መልካም አጋጣሚ ነው" በማለት ቬራ መለሰችለት፡፡

"ከዚህ በፊት ይህንን ስፍራ ታውቂያለሽ?" በማለት ሎምባርድ ጠየቃት፡፡

"የመጀመሪያዬ ነው" በማለት መለሰችለት እና ሰራተኛ መሆኗንም ለማሳወቅ እያደዛ "ቀጣሪዬንም ገና አልተዋወቅኋቸውም" በማለት አከለችበት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"የምን ቀጣሪ?"

"የወ/ሮ እውን ፀሃፊ ነኝ" በማለት መለሰችለት

"ገባኝ... ግን ትንሽ ያልተለመደ ይመስላል" አላት

"ፀሃፊዋ በድንገት ስለታመመችባት ግዜያዊ ሰው እንዲልክላት ለቀጣሪ ወኪሏ ደብዳቤ ፅፋ ነበር

"እዛ ስትደርሺ ስራውን ባትወጂውስ?"

ቬራ ሳቅ ብላ ችግር የለውም ግዜያዊ ስራ ነው፡፡ በሴቶች ት/ቤት ቋሚ ስራ አለኝ፡፡ ደሴቷን ለማየትም ጓጉቻለሁ፡፡ ብዙ ተወርቶለታል፡፡ መቼም ሳታየው አትቀርም፡፡ በማለት በጥያቄ አስተያየት አየችው

"አላየሁትም፡፡" በማለት መለሰላት

"የእውን ቤተሰቦች ደሴቱን እንደሚወዱት እገምታለሁ፡፡ ለመሆኑ አይተሃቸው ታውቃለህ?"

ሎምባርድ ባልጠበቀው ጥያቄ ግራ ተጋባ፡፡ ምን ማለት እንደነበረበት ለማሰብ እየሞከረ ሳለ "እጅሽ ላይ ተርብ አለ፡፡ አትንቀሳቀሺ - አለበለዚያ ይነድፍሻል" በማለት በቀስታ አነሳላት -

"በዚህ በጋ ደግሞ ተርቡ በዝቷል  አመሰግናለሁ" አለችው፡፡ ክርቀት የባቡር ድምፅ ተሰማ፡፡ ሎምባርድም አስጨናቂውን ጥያቄ ለመመለስ ሳይገደድ ቀረ

"ባቡሩ መጥቷል" አላት

* * *

ቀጭን ጉልማሳ ተሳፋሪ ከባቡሩ ጣቢያ ሲወጣ ሎምባርድ እና ቬራ ተመለከቱት፡፡ የሰውየው ተክለ-ሰውነት እና ንቁ አይኖች ወታደር መሆኑን ያሳብቁበታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቬራ እጇቿን ለሰላምታ ዘረጋችለት፡፡ "የወ/ሮ አውን የግል ፀሃፊ ነኝ፡፡ ይህ ደግሞ ሎምባርድ ነው፡፡ መኪና እየጠበቀህ ነው" በማለት አቀባበል አደረገችለት፡፡

እንግዳው ሰው ሎምባርድን በፍጥነት ነበር ገምግሞ የጨረሰው፡፡ 'መልከ-መልካም ቢሆንም የሆነ ነገሩ ይረብሻል' በማለት አሰበ፡፡ ሶስቱም ታክሲ ውስጥ ገቡ፡፡ በፕሌይ ማውዝ መንገድ ላይ ታክሲዋ መክነፍ ጀመረች፡፡

ጀ/ል ማክ አርተር "ይህንን ስፍራ አይቼው አላውቅም፡፡ የትውልድ መንደሬ ምስራቅ ዴቮን ነው" በማለት መልስ ጠበቁ፡፡

"ተራራ እና ሜዳው - በአጠቃላይ ቆንጆ ስፍራ ነው" በማለት ቬራ መለሰችላቸው

"ትንሽ ይጨንቃል፡፡ ሁሉንም ነገር በግልፅ ማየት የሚቻልበት አይነት ስፍራ አይደለም" በማለት ሎምባርድ ተናገረ፡፡

"ብዙ ቦታ ያየህ ይመስለኛል" አሉ ጀ/ሉ፡፡

"እዚህ እዚያ ስል ነው የኖርኩት ጌታዬ" በማለት ሎምባርድ መለሰላቸው፡፡ የጀነራሉን ወታደር መሆን ቀድሞ የገመተው ሎምባርድ የጦርነት ወሬ እንደሚቀጥሉ ቢጠብቅም ጀ/ል ማክ አርተር ዝምታን ነበር የመረጡት፡፡

*          *          *

እንግዶቹን ያሳፈሩት ታክሲዎች ጠመዝማዛውን መንገድ ይዘው ቁልቁል ወደ ስቲክልሃቨን ወረዱ፡፡ በመስመር የተደረደሩ መኖሪያ ቤቶች አንድ ወይም ሁለት የአሳ ማጥመጃ ጀልባ ይታያል፡፡

እንግዶቹ በመግባት ላይ ባለችው የፀሃይ ብርሃን ታግዘው ከባህሩ ደቡባዊ ጫፍ የምትገኘውን ኢንዲያን ደሴት በመጨረሻ ለማየት ቻሉ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሩቅ ነው በማለት ቬራ አግራሞቷን ገለፀች፡፡ በርግጥም ደሴቷ እንደጠበቀችው አላገኘችውም ነበር፡፡ በደሴቷ ዳር ላይ በርካታ ነጫጭ ቤቶችን እና የመዝናኛ ጀልባዎችን ለማየት ጠብቃ ነበር፡፡ ደሴቱ ግን ኮረብታ ሲሆን መላጣ የአሜሪካ ቀይ ህንድ ጭንቅላት ነበር የሚመስለው፡፡ የደሴቱ ምስል ቀፈፋት፡፡ ውስጧን ቢረብሸውም ስሜቷን ለመደበቅ ሞከረች፡፡

እነ ቬራን ያሳፈረችው ታክሲ ባህሩ ዳርቻ ላይ ከሚገኘው አነስተኛ መጠጥ ቤት ደጃፍ ደርሳ ቆመች፡፡ በሩ ላይ ሶስት ሰዎች እየጠበቋቸው ነበር፡፡ ከጡረተኛው ዳኛ እና ወ/ሮ ብሬንት አጠገብ የነበረው ፈርጣማ ሰው እጁን ለሰላምታ ዘረጋላቸው፡፡

"ዴቪስ እባላለሁ፡፡ ከደቡብ አፍሪካ ምስራቃዊ ግዛት ናታል" በማለት በፈገግታ ራሱን አስተዋወቀ፡፡

ዳኛው ዋርግሬቭ ፈርጣማውን ዴቪስ በጥርጣሬ ተመለከቱት፡፡ ወ/ሮ ብሬንት ከቅኝ ግዛት የሚመጡ ሰዎችን ብዙም አይወዱምና ስለ ዴቪስ እርግጠኛ መሆን አልቻሉም፡፡

"መንገዳችንን ከመቀጠላችን በፊት ለምን አንድ ሁለት አንልም፡፡ በማለት ትውውቁን ለማጠናከር ወዳጃዊ ግብዣን አስከተለ፡፡ የእንግዶቹን ስሜት አልባ ፊት በመመልከት ሃሳቡን በፍጥነት አነሳ፡፡ "አክባሪ ጋባዦቻችንን ከምናስጠብቃቸው እንግዲያውስ አሁኑኑ እንንቀሳቀስ" በማለት ሲናገር እንግዶቹ ፊት ላይ ያልጠበቀውን ግራ መጋባት ተመለከተ፡፡

በእንግዶቹ መካከል የተፈጠረውን ግራ መጋባት ለግዜውም ቢሆን ገለል ያደረገው ከኋላቸው የመጣው ሰው ነበር፡፡ የሰውየውን የገረጣ ፊት እና



t.me/OLDBOOKSPDF

ያልተስተካከለ አለባበስ በመመልከት አሳ አጥማጅ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

በአካባቢው የዴቮን ዘዬ ለስለስ ባለ ድምፅ "ክቡራትና ክቡራን ወደ ደሴቷ ለመጓዝ ዝግጁ ናችሁ? ጀልባ ተዘጋጅቶላችኋል፡፡ በራሳቸው መኪና እየመጡ ያሉ ሁለት እንግዶች ቢኖሩም ጋባዣችሁ አቶ ኦውን እናንተን እንዳላጉላላ አደራ ስላሉኝ መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡" በማለት ባህሩ ዳርቻ ወደታሰረችው ጀልባ መራቸው፡፡

"ትንሽ ነች!" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት ጀልባዋ ሁሉንም መቻሏን ተጠራጠሩ፡፡

"በቂ ነች እመቤቴ፡፡ ያለ ምንም ስጋት የፈለጉትን ያህል ርቀት ሊጓዙባት ይችላሉ፡፡ በማለት ባለጀልባው መለሰላቸው

አቶ ዋርግሬቭ "ብዛታችንን አይተኸዋል?" በማለት ጠየቁት፡፡

"የእናንተን ያህል ተጨማሪ ተሳፋሪ የመያዝ አቅም አላት"

ፊሊፕ ሎምባርድ "አየሩም የተረጋጋ ስለሆነ ችግር የለም" በማለት ሊያረጋጋቸው ሞከረ፡፡

ወ/ሮ ብሬንት የጀልባዋን አቅም ባያምኑበትም ለመሳፈር ግን የመጀመሪያ ነበሩ፡፡ በመቀጠል ሁሉም እንግዶች ተሳፈሩ፡፡ በመካከላቸው ፍፁም ፀጥታ ሰፈነ፡፡ መሪያቸው ጀልባዋን ማንቀሳቀስ ሲጀምር የመኪና ድመፅ ሰምቶ ቀና አለ፡፡

ከፍተኛ ጉልበት ያለው የተዋበ መኪና በመንደሯ ጠባብ መንገድ ላይ እየከነፈ ወደ ባህሩ ዳርቻ ሲመጣ ተመለከቱት፡፡ የሾፌሩ ፀጉር በንፋስ ወደኋላ ሲበተን ከርቀት ይታያል፡፡ በምሽቷ ፀሃይ ብርሃን ሲመለከቱት ሰው ሳይሆን በተረት አለም የሚገኝ አንድ አማልክት ነበር የሚመስለው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

መኪናዋ በባህሩ ዳርቻ ያለውን አሸዋ እና ጠጠር እያፈናጠረች ተጠጋቻቸው፡፡ አንቶኒ ማርስተን መኪናው ውስጥ ሳለ ፍፁም ዘላለማዊ ፍጡር ነበር የሚመስለው፡፡ በዚያች ቅፅበት የተመለከቱትን ምትሃታዊ እና የማይሞት ውበት ከግዜ በኋላ ከእንግዶቹ ጥቂቶች ብቻ አስታውሰውታል......

* * *

ፍሬድ ናራኮት ስለ አድካሚ ስራው እያሰበ ነበር የጀልባዋን ሞተር ያስነሳው፡፡ የደሴቷ ባለቤት ሚስተር የጋበዛቸውን እንግዶች እንደጠበቃቸው አላገኛቸውም፡፡ በአግባቡ የለበሱ እንዲሁም በባህር ላይ ለመዝናናት የቻኩሉ ባለጠጋ እንግዶችን ነበር የጠበቀው፡፡ ከኦውን በፊት የደሴቷ ባለቤት የነበረው ቱጃር ኤልመር ሮብሰን የተዋጣለት ደጋሽ እንደነበር በማስታወስ ተጋባዦቹ እንደ እሁኖቹ ተራ እንዳልነበሩ አስታወሰ፡፡

'ይህ ኦውን የተባለ ሰው የተለየ መሆን አለበት' በማለት ባለጀልባው ፍሬድ አሰበ፡፡ አዲሱ ባለቤት ኦውን እንደሚባል ከመስማት በዘለለ እሱንም ሆነ ሚስቱን አላያቸውም፡፡ የደሴቷ ባለቤት ወደ ደሴቷ አንዴም አለመምጣቱ ፍሬድን አስገርሞታል፡፡ ግዢው የተፈፀመው ሞሪስ በተባለ ሰው በኩል ነበር፡፡ ከግዢው ጀምሮ የስራ ትዕዛዝ እና ዳጉስ ያለ ክፍያ የሚሰጠውም ሞሪስ የተባለው ሰው ነበር፡፡

ጋዜጦች ሚስተር ኦውን ምስጢራዊ ሰው እንደሆነ በፃፉት ለመስማማት የተገደደው ባለ ጀልባ ከጋባዡ ቀድሞ ተጋባዦቹን ማወቁ አስገርሞታል፡፡ የፊልም ተዋናይቷ ገብርኤል ተርል በምስጢር ደሴቷን እንደገዛች ተገምቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ጀልባው ላይ የሚገኙትን እንግዶች ተመልክቶ ነበር ግምቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሳሳተ እንደሆነ የደመደመው፡፡ ምክንያቱም አንዳቸውም የፊልም ተዋንያን አይመስሉም፡፡

ፍሬድ ናርኮት ለእንግዶቹ የራሱን ግምት በመስጠት ስለማንነታቸው አሰበ፡፡ "አሮጊቷ ሴት አንዲት አመለ-ቢስ የወጥ ቤት ሰራተኛ መሆን አለባት፡፡ ወጣቷ ሴት ቆንጆ ብትሆንም የሆሊውድ ፊልም ተዋናይት ሳትሆን ተራ ሴት እንደሆነች ግልፅ ነው፡፡ በጉራ የተወጠረው ሰውዬም ቢሆን ከፍ ያለ ደረጃ ያለው ሳይሆን ስራ ያቆመ ነጋዴ ነው፡፡ ሌላኛው ሰውዬ ደግሞ አይኖቹ ፈፅመው አይቆሙም ፤ ሌባ ወይም ሰዶም ይመስላል፡፡ ሽማግሌው ደግሞ በጡረታ የተገለሉ የጦር ሰራዊት መኮንን ይመስላሉ..." በማለት የእንግዶቹን ምስል አሰበ፡፡

ባለጀልባው ፍሬድ ምናባዊ ግምቱን ቀጠለ፡፡ "ከእንግዶቹ መካከል የሃብታም ገፅ ያለው በመጨረሻ የመጣው ብቻ ነው" በማለት በተቀናጣ መኪናው ስለመጣው እንግዳ በአድናቆት አሰበ፡፡ የእርሱ አይነት መኪና እጅግ በጣም ውድ እንደሆነ እርግጠኛ በመሆን በመንደሩ ታይቶ የማይታወቅ መኪና የሚያሽከረክረው ሰው ከገንዘብ መሃል የተወለደ መሆን አለበት፡፡ ምናልባትም ለመዝናናት የመጣው እርሱ ብቻ መሆን አለበት በማለት ፍሬድ ገመተ፡፡

ግራ የሚያጋባ ግብዣ .... በተለይ ደግሞ ስለተጋባገሮቹ ሲታሰብ ሁሉም ነገር ግራ የሚያጋባ ነበር....

• • •

ጀልባዋ ወደ ደሴቱ ዳርቻ ስትቃረብ ቤቱ ሙሉ በሙሉ ታያቸው፡፡ የደሴቷ ደቡባዊ ጫፍ አስገራሚ ውበት ነበረው፡፡ ቤቱ ፊቱን ወደ ባህሩ አድርጎ የተሰራ ነበር፡፡ ከብ ቅርፅ ያለው ዘመናዊ ግንባታ ሲሆን በዙሪያው


t.me/OLDBOOKSPDF

ያሉት ከብ መስኮቶች ብርሃን በደንብ እንዲያስገቡ የታሰበባቸው እንደሆነ ያስታውቃል፡፡ በርግጥም ቤቱ ከሚገመተው በላይ ውብ እና የተቀናጣ ነበር፡፡

በሁለት አለቶች መካከል አስገብቶ የጀልባዋን ሞተር አጠፋው፡፡ የጀልባዋ ባለቤት ቀድሞ ወረደ፡፡ ሎምባርድ ተከተለውና የቀሩትን ተሳፋሪዎች ለሁለት እየደገፉ ወደ መሬት አወረዷቸው፡፡

"የአየሩ ጣቢያ ከባድ ሲሆን መቼም ወደዚህ መምጣት አይታሰብም" በማለት ሎምባርድ ግምታዊ ጥያቄ አቀረበ፡፡

"የደቡብ ምስራቁ ንፋስ ከተነሳ ቢያንስ ለሳምንት መንቀሳቀስ አይቻልም" በማለት ፍሬድ መለሰለት፡፡

ምግብ እና ቁሳቁስ ማቅረቡም አስቸጋሪ ይሆናል በማለት ቬራ አሰበች፡፡ ደሴት ላይ መኖር የሚያስቸግረውም በዚህ መሰል የአቅርቦት እና የግንኙነት ችግር ነው፡፡

ፍሬድ ጀልባውን ችካል ላይ አሰረና እንግዶቹን እየመራ በተፈጥሮአዊ ደረጃዎቹ በኩል ወደ ደሴቷ የላይኛው ክፍል ወሰዳቸው፡፡

ጀ/ል ማከአርተር "የሚያምር ገፅታ!" በማለት አደነቁ፡፡ ነገር ግን ቦታው የተለየ ምቾት አልሰጣቸውም ነበር፡፡

ወደ ሰፊው በረንዳ ሲጠጉ ቤቱ የበለጠ ገዘፈባቸው፡፡ በሩ አጠገብ በጥሩ ሁኔታ የለበሰ አስተናጋጅ ቆሞ እየጠበቃቸው መሆኑን ሲመለከቱ በርግጥም ግብዣው ከፍ ያለ ደረጃ እንዳለው ሁሉም ገመቱ፡፡ ጎልማሳው አስተናጋጅ ፀጉሩ በከፊል የሸበተ ሲሆን ለትህትና ጉንበስ ባለበት አጋጣሚ እንኳን የቁመቱ ርዝመት የተጋነነ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በፈገግታ ከተቀበላቸው በኋላ "እባካችሁ ተከተሉኝ" በማለት ወደ ሰፊው እልፍኝ መራቸው፡፡ በእልፍኙ የተደረደሩትን የመጠጥ አይነት እና ብዛት የተመለከተው አንቶኒ ማርስተን ምራቁን ዋጠና 'የመጠጥ አውደ-ርዕይ' በማለት አደነቀ፡፡ ከአድናቆቱ ያባነነው የአስተናጋጁ ንግግር ነበር፡፡

"የተከበሩ አቶ ኦውን እስከ ነገ እንደማይደርሱ አሳውቀውናል.... የምትፈልጉትን ነገር በሙሉ እንድናቀርብ አሳስበውናል.....ወደተዘጋጁላችሁ ክፍሎች እመራችኋለሁ... ራት ሁለት ሰአት ላይ ይቀርባል..."

* * *

ቬራ አስተናጋጁ ወ/ሮ ሮጀርስን ተከትላ በደረጃው ወደ ላይኛው ክፍል ወጣች፡፡ ወ/ሮ ሮጀርስ የተዘጋጀላትን ክፍል በር በመክፈት እንድትገባ በእጆቿ ጋበዘቻት፡፡ ክፍሉ በጥሩ ሁኔታ የተሰናዳ እንደሆነ የተመለከተችው ቬራ ፊቷ በአድናቆት በራ፡፡ የክፍሉ ሁለት መስኮቶች የተከፈቱ ሲሆን አንደኛው የባህሩን ከፊል ገፅታ የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምስራቃዊ የደሴቷን አካል ያሳያል፡፡

"የሚያስፈልግሽን በሙሉ እዚሁ እንደምታገኚ አምናለሁ ፣ ወይዘሪት" በትህትና ነበር ወ/ሮ ሮጀርስ የተናገረችው፡፡

ቬራ ክፍሉን እየተዟዟረች ቃኘችው፡፡ የመታጠቢያ ክፍሉ በር የተከፈተ ሲሆን የውስጡ ግድግዳ በውሃ ሰማያዊ ሸክላ የተለበጠ ነበር፡፡ ከአልጋው አጠገብ የተቀመጡትን የጉዞ ሻንጣዎች በመመልከት ወደ ወ/ሮዋ ዞረችና "በትክክል ፤ የምፈልገውን ሁሉ አግኝቻለሁ" በማለት መለሰችላት፡፡

"ምንም ነገር ብትፈልጊ ደውሉን በመጫን ልትጠሪኝ ትችያለሽ"

የወ/ሮ ሮጀርስ ድምፅ በፍርሃት የተሸበረች ይመስል የሚርገበገብ ነበር፡፡ ቬራ ወይዘሮዋን በትኩረት ተመለከተቻት እና 'ቀዝቃዛ እና ደም አልባ ጣረ-


t.me/OLDBOOKSPDF

ሞት ትመስላለች' ስትል አሰበች፡፡ የወይዘሮዋ ቀዝቃዛ አይኖች መንቀዥቀዣቸው ምቾት ነሳት፡፡ 'የራሷን ጥላ የምትፈራ ትመስላለች' በማለት ስለ አስተናጋጇ እያሰበች ሳለ ጀርባዋን የፍርሃት ስሜት ወረራት

"የወ/ሮ አውን አዲስ ፀሃፊ ነኝ፡፡ ያወቅሽ ይመስለኛል" በማለት ቬራ ራሷን አስተዋወቀች፡፡

"ፊፅሞ አላወቅሁም፡፡ የእንግዶች ስም ዝርዝር እና የተዘጋጀላቸውን ማረፊያ ክፍል ብቻ ነው የማውቀው"

"ወ/ሮ አውንን እኔ አላገኘኋቸውም፡፡ እዚህ የደረስኩት ከሁለት ቀናት በፊት ነው" በማለት ወ/ሮ ሮጀርስ ከቀጣሪዋ ጋር አለመገናኘቷን ገለፀችላት

"ለመሆኑ ስንት ሰራተኞች አሉ?"

"እኔ እና ባለቤቴ ሮጀርስ ብቻ ነን" በማለት ወ/ሮዋ መለሰችላት፡፡

ስምንት እንግዶች እና ባልና ሚስት ጋባዦቻቸው፡፡ በአጠቃላይ በቤቱ ያሉት አስር ተስተናጋጆች ሲሆኑ የመስተንግዶውን ስራ የያዙት ባልና ሚስቶቹ አስተናጋጆች እንደሆኑ አሰበች፡፡

"እኔ ምግቡን ሳዘጋጅ ሮጀር ደግሞ ቤት ያስተካክላል፡፡ ትልቅ ድግስ እንደሚሆን ሁለታችንም አልገመትንም ነበር" በማለት ወ/ሮዋ አከለች፡፡

"ሁለታችሁ ብቻ?" ቬራ ጠየቀች

"እንበቃለን ብዬ እገምታለሁ፡፡ ስራው ከበዛ ደግሞ ወ/ሮ አውን ተጨማሪ አጋዥ ማምጣታቸው አይቀርም"

"እንደ'ዛ መሆን አለበት" በማለት ቬራ ተናገረች እና ወደ መስኮቱ አመራች፡፡ ወ/ሮ ሮጀርስ ኮቴዋን ሳታሰማ ከክፍሉ ወጣች፡፡

ቬራ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ ወደ ውጪ እየተመለከተች በሃሳብ ተዋጠች፡፡ ሁኔታዎቹ በሙሉ አስፈሪ ሆነውባታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የቤቱ ባለቤቶች አለመኖር ፤ የአስተናጋጇ ጣረ-ሞት መምሰል እና የእንግዶቹ ሁኔታ በአጠቃላይ ረብሿታል፡፡

"የአውን ባልና ሚስት ምን እንደሚመስሉ ቀድሜ ባውቅ ጥሩ ነበር... በሃሳቧ ስለቀጣሪዎቿ ማንነት እያሰላሰለች ክፍሉ ውስጥ መዘዋወር ጀመረች፡፡

የተዘጋጀላት ማረፊያ ክፍል እጅግ የተዋበ ነበር፡፡ በእምነበረድ እና መስታወት ያጌጠ ግድግዳ እንዲሁም በተለያዩ ቅርፃ ቅርፆች የተዋበ መኝታ ክፍል ነበር፡፡ ግድግዳው ላይ ከተሰቀለው ሰአት አጠገብ የተዋበ የፎቶ መስታወት ፍሬም ተሰቅሏል፡፡ በውስጡም ብራና ላይ የተፃፈ የህፃናት የተረት ግጥም ነበር፡፡

ቬራ ወደ ማሞቂያው ተጠግታ ግጥሙን በቅርበት ተመለከተችው፡፡ ግጥሙ የህፃናት ማስተማሪያ ሲሆን እያነበበችው ስትወርድ የህፃንነት ዘመኗን አስታወሳት፡፡

አስር የህንድ ልጆች ለራት ተጠሩ ፤
አንዱ ታፍኖ ሲሞት ዘጠኙ ቀሩ፡፡
ዘጠኙ ልጆች ሳይተኙ አደሩ ፤
አንዱ ሲያንቀላፋ ስምንቱ ቀሩ፡፡
ስምንቱ ልጆች ወደ ዲቮን ተጓዙ ፤
አንዱ እዚያው ሲቀር ሰባቱ ተመለሱ
ሰባቱ ልጆች እንጨት ሲፈልጡ ፤
አንዱ ራሱን ሲፈልጥ ስድስቱ አመለጡ፡፡
ስድስቱ ልጆች በንብ ቀፎ ሲጫወቱ ፤


t.me/OLDBOOKSPDF

አንዱ ሲነደፍ ተረፉ አምስቱ፡፡
አምስቱ ልጆች ህግ ተፈተኑ ፤
አንዱ ሲመረጥ አራቱ ተበተኑ፡፡
አራቱ ልጆች ባህር ሲቀዝፉ ፤
አንዱን አሳ በላው ፤ ሶስቱ ተረፉ፡፡
ሶስቱ ልጆች በጫካ ሲዞሩ
አንዱን አውሬ በላው ሁለቱ ቀሩ፡፡
ሁለቱ ልጆች ፀሃይ ሲሞቁ ፤
አንዱ አረረ ፤ አንዱ ብቻ ቀረ፡፡
የተረፈውም ልጅ ራሱን አነቀ ፤
የቀረ ልጅ ሳይኖር ተረቱም አለቀ፡፡

ቬራ የተረት ግጥሙን አንብባ ስትጨርስ ፈገግ አለች፡፡ በርግጥም የህንዶቹ ህፃናት ተረት ያስፈገጋት ህንድ ደሴት ላይ ሆና ስላነበበችው ነበር፡፡ ወደ መስኮቱ ተመልሳ ሰፊውን ባህር እያየች በሐሳብ ተጓዘች፡፡

ባህሩ ሰፊ ሲሆን በአቅራቢያው የሚታይ ምድር የለም፡፡ ሰማያዊው ባህር እስከ አድማስ ጥግ ተዘርግቶ ተመለከተች፡፡ ሰማያዊ ባህር .... ሰላማዊ ቢመስልም .... አንዳንዴ ግን ጨካኝ ይሆናል፡፡ ወደ ውስጥ ጐትቶ ያሰጥማል ... ወደ ጥልቅ ያሰጥማል ... መስጠም ... ባህር ውስጥ ሰርጥ መጥፋት..

አይሆንም! አታስታውሰውም፡፡ አሁን ሁሉም ነገር አልፏል፡፡ ፈፅሞ ሊታሰበው አይገባም...

• • •


t.me/OLDBOOKSPDF

ዶ/ር አርመስትሮንግ ደሴቷ ላይ የደረሰው ፀሃይ መግባት ስትጀምር ነበር፡፡ በጀልባ ጉዞው ወቅት ስለጋባገሮቹ የኦውን ባልና ሚስት ለማወቅ ያደረገው ሙከራ አልተሳካለትም፡፡ ባለ ጀልባው ናርኮት በስራ ደክሞ ስለነበር ለዶ/ሩ ጥያቄ መልስ የመስጠት ፍላጐት አልነበረውም፡፡

ዶ/ሩ በጉዞው ወቅት ፀሃይ ግንባሩን ሲያቃጥለው ስለነበር ተዳክሟል፡፡ የጀልባውን ጉዞ የጨረሰውም በተለያዩ ሃሳቦችና እቅዶች ተጠምዶ ነበር፡፡ ይህንን መሰል እረፍት ለብዙ ግዜ ሲመኝ ቢቆይም አልቻለም ነበር፡፡ ገንዘቡ ቢኖረውም ስራውን ለአፍታ የማቆም ፍላጐት አልነበረውም፡፡ ይህ አጋጣሚ ሁሉን ነገር ወደኋላ በመተው ዘና የሚልበት እንደሆነ ተሰምቶታል፡፡

"በዚህ ምሽት ፈፅሞ ወደ ለንደን እንደማልመለስ ለራሴ እነግረዋለሁ፡፡ በሃርሌ ጐዳና ስላደረግሁትም ነገር ሆነ ስለ ማንኛውም ያለፈ ነገር የማላስታውስበት ምሽት ነው" በማለት ለራሱ አረጋገጠ፡፡

ምሽቱን ደሴት ላይ ማሳለፉ በራሱ የተለየ ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ ደሴት ላይ ያለ ሰው ከውጪው አለም ጋር ምንም አይነት ንክኪ አይኖረውም፡፡ ደሴት ራሱን የቻለ ሙሉ አለም ነው - ምናልባትም ወደኋላ የማይመለሱበት ሙሉ አለም፡፡

"ተራ ህይወቴን ትቼው መጥቻለሁ" በማለት በፈገግታ አሰበ፡፡ ፊቱ በሃሴት እንዳበራ የተለያዩ ዕቅዶችን ማሰላሰል ቀጠለ፡፡ ከጀልባው ወርዶ የድንጋይ ደረጃውን በመውጣት ወደ ግዙፉ የኦውን ባልና ሚስት ቤት ሲያመራ ፊቱ በፈገግታ እንደተሞላ ነበር፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ወደ ቤቱ ሲቃረብ በረንዳው ላይ የተቀመጡትን አዛውንት በግልፅ ተመለከታቸው፡፡ በመጀመሪያ የአዛውንቱን ስሜት አልባ



t.me/OLDBOOKSPDF

እና የተዳከመ ፊት የት እንደሚያውቀው ማስታወስ ከብዶት ነበር። በመጨረሻም አዛውንቱ ሰው ዳኛ ዋርግሬቭ እንደሆኑ አወቀ።

ዋርግሬቭን እንዴት ይረሳቸዋል? በእርሳቸው ችሎት ፊት ቀርቦ የህክምና መረጃ ማቅረቡን አስታወሰ። የዳኛው ሰውነት በአነስተኛዋ ወንበር ውስጥ ተጣጥፎ ቢቀመጥም በለንደን ጠበቆች እና አቃቤያን ህግ የሚፈሩ እንደሆኑ ዶ/ሩ ጠንቅቆ ያውቃል። ብዙ የህግ ባለሙያዎች 'ሰቃዩ' እና "ገዳዩ ዳኛ" በማለት ነበር የሚጠሯቸው። እኚህን ዳኛ በዚህ ከአለም ውጪ በሚገኝ ስፍራ ሲያገኛቸው ተገርሟል።

ዳኛው ጀስቲን ዋርግሬቭም በሃሳብ ተውጠው ተመለከቱት። "አርመስትሮንግ አይደለም እንዴ? በምስክሮች ሳጥን ውስጥ ሆኖ በጥንቃቄ የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ዶክተር ..." በማለት ዳኛው አስታወሱት። የሃርሊ ጐዳና ዶክተሮችን መጥፎነት ሲያስቡ በቅርቡ ችሎት ፊት ቃለ መጠይቅ ያደረጉለትን ብልህ ሰው አስታወሱ።

"ወደ እልፍኙ ዝለቅ-መጠጥ እዛ ነው ያለው" በማለት ዳኛው ከፍ ባለ ድምፅ ተናገሩ። ዶ/ሩ የዳኛውን ድምፅ ሲሰማ ተገርሟል። ምክንያቱም ከሩቅ ሲመለከታቸው ወንበራቸው ላይ እያንቀላፉ መስሎት ነበር።

"መጀመሪያ ለጋባዦቼ ሰላምታ ማቅረብ አለብኝ" በማለት መለሰላቸው

"የምትችል አይመስለኝም" አሉት በቀዘቀዘ ድምፅ

"ለምን?"

"ጋባዦቻችን የሉም። ግራ የገባው ነገር ነው። የዚህ ቦታ ሁኔታ ሊገባኝ አልቻለም" አሉት ዳኛው

ዶ/ር አርመስትሮንግ ለደቂቃ ያህል አተኩሮ ተመለከታቸው። እንቅልፍ የወሰዳቸው መስሎት ሊሔድ ሲል በድጋሚ የዳኛው ድምፅ አስቆመው


t.me/OLDBOOKSPDF

"ኮንስታንስ ካልሚንግተን የምትባል ሴት ታውቃለህ?" በማለት ጠየቁት፡፡

"በፍፁም" በማለት መለሰላቸው

"እኔም ላስታውሳት አልቻልኩም፡፡ ማንነቷ ግልፅ አይደለም፡፡ በዚያ ላይ የእጅ ፅሁፏ አይነበብም ነበር፡፡ የተጠራሁበትን ቤት ተሳስቼ ወደዚህ ሳልመጣ አልቀረሁም" አሉ ዳኛው፡፡ ዶ/ሩ ራሱን አነቃንቆ አልፏቸው ወደ እልፍኙ ዘለቀ፡፡

ዳኛው ዋርግሬቭ የኮንስታንስ ከልሚንግተንን ማንነት ለማስታወስ ሞከሩ፡፡ ሴት የማያምኑት ዋርግሬቭ ከተጋባዦቹ መካከል የሚገኙትን ሁለት ሴቶች አስታወሱ፡፡ አንዷ ወጣት ሴት ስትሆን ብዙም ትኩረታቸውን አልሳበችውም፡፡ ሌላዋ እንግዳ ሴት ደግሞ አሮጊት ነበሩ፡፡ ሶስተኛ ሴት መኖሯን ዳኛው አስታወሱ - የአስተናጋጁ ባለቤት ወ/ሮ ሮጀርስ፡፡

አገልጋይዋ ወ/ሮ ሮጀርስ ለየት ያለ ፍጥረት እንዳላት አስታወሱ፡፡ ሴትየዋ የደነገጠች ወፍ ነበር የምትመስለው፡፡ ባልና ሚስቶቹ አገልጋዮች ስራቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ እንደሆኑ በማሰብ ቀና ሲሉ ባልየው አገልጋይ ሮጀርስ አጠገባቸው መድረሱን የተመለከቱት፡፡

"ኮንስታንስ ከልሚንግተን የተባለች ሴት ከሚመጡት እንግዶች መካከል አለች እንዴ?" በማለት ጠየቁት፡፡

ሮጀርስም ሽማግሌውን አተኩሮ በመመልከት "እኔ እስከማውቀው ድረስ እንደዚያ የምትባል ሴት የለችም" አላቸው፡፡

ዳኛው በአግራሞት ቅንድባቸውን ከፍ አደረጉ፡፡ "ህንድ ደሴት? የተደበቀ ጥቁር ሰው ከዚህ መኖሩ አይቀርም" ሲሉ አሰቡ፡፡

• • •



t.me/OLDBOOKSPDF

እንቶኒ ማርስተን በድካም የዛለ ሰውነቱን በሙቅ ውሃ ታጥቦ ዘና አለ። ብዙ ነገሮችን ላለማሰብ ሞከረ። በርግጥም ስሜቱን የሚከተል እና የድርጊት ሰውነበርማርስተን።

"ይህንን ነገር የግድ ማድረግ ሳይኖርብኝ አይቀርም" በማለት ለአፍታ ያህል አሰበና ወዲያውኑ ረሳው። ከመታጠቢያ ገንዳው እንደወጣ ፂሙን በአግባቡ ላጨና ራሱን ለታላቁ ራት ግብዣ ዝግጁ አደረገ። ከዚያስ...?

* * *

ብሎር ከረባቱን ለማስተካከል ይሞክራል። የራት ግብዣ እና መሰል መሰናዶ ብዙም አይመቸውም። የተረጋጋ ለመምስሰል ሞከረ። ከእንግዶቹ መካከል እርሱ ላይ አይኑን የጣለበት እንደሌለ አስተውሏል። ሁሉም ተጋባዥ የሚተዋወቅ ይመስል ነበር የሚተያየው። 'የራሱ ጉዳይ' ሲል አሰበ። ስራውን ለማሰናከል አስቦ ያደረገው አልነበረም።

ግድግዳ ላይ በፍሬም የተሰቀለውን የህፃንነት የተረት ግጥም አነበበና ፈገግ አለ። እዚያ ቦታ መገኘቱ የተለየ ስሜት ፈጥሮበታል።

"ይህንን ደሴት በልጅነቴ አውቀዋለሁ። ነገር ግን መቼም ቢሆን እንዲህ አይነት ስራ ሲያውም ቤት ውስጥ ለመስራት እመለሳለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር። ጥሩው ነገር ማናችንም የወደፊቱን ቀድመን አለማወቃችን ነው ...ነገረ ስራቸው ይገርማል..." በማለት አሰበ።

* * *

ጀነራል ማካርተር ግንባሩን ከስከሶ ተቀምጧል። ሁሉም ነገር እንደገመተው አልሆነም። የሚቀፍ ነገር እንዳለ ደመ - ነብሱ ነግሮታል።

ሁለቱ ጋባዦቹን አግኝቶ ይቅርታ በመጠየቅ ለመሔድ ወስኗል። ግብዣውም ሆነ ስራው በአጠቃላይ ቢቀርበት እንደሚሻለው አሰበ። ነገር


t.me/OLDBOOKSPDF

ግን የሞተር ጀልባው ተመልሶ ስለሔደ የግድ ደሴቷ ላይ ማደሩ እንደማይቀር አውቆታል፡፡ ስለዚህ ይቆያል....

ሎምባርድ የሚባለው ሰው የሚረብሽ ነገር አለው በማለት አሰበ፡፡ ጀነራሉ በእርግጠኝነት ሎምባርድ የተደበቀ ተልዕኮ እንዳለው አሰበ...

*          *          *

በተመሳሳይ ቅፅበት ነበር ሎምባርድ ከክፍሉ ወጥቶ ወደ ደረጃዎቹ ያመራው፡፡ አረማመዱ በጥንቃቄ ላይ የተመሰረተ ሲሆን እንደ ነብር ኮቴውን ሳያሰማ ነበር የሚራመደው፡፡ ከአዳኝ ነብር ጋር የሚያመሳስለው ነገር ነበር፡፡ አይኖቹ ንቁ ሲሆኑ ለራሱ ብቻ በሚታይ ፈገግታ ፊቱን ሞልቶ ነበር የሚራመደው፡፡

ሳምንቱ የእርሱ እንደሆነ ተሰምቶታል፡፡

*          *          *

ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት ጥቁር የሃር ቀሚሳቸውን በአግባቡ ለብሰው የራት ሰአት እስኪደርስ መኝታ ቤታቸው ሆነው መፅሃፍ ቅዱስ እያነበቡ ነበር፡፡ ከናፍራቸውን በስሱ "እያንቀሳቀሱ ሃጢያተኞች በቆፈሩት ጉድጓድ ይገባሉ.. ያጠመዱት ወጥመድ እግራቸውን ያይዘዋል... ሃጥአን ገሃነም ይገባሉ..." የሚሉትን ሃረጋት ደጋግመው አነበቡ፡፡

መፅሃፍ ቅዱሳቸውን ዘግተው አስቀመጡ፡፡ በዝግታ ተነስተው የአንገት ልብሳቸውን አስተካከሉና ወደ እራት ስፍራው መውረድ ጀመሩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሶስት

ራት ወደ መጠናቀቁ ነበር፡፡ የቀረበላቸውን ምግብ በጥሩ ሁኔታ ያጣጣሙት እንግዶች መጠጥ እና ጨዋታ ጀምረዋል፡፡ ባልና ሚስት ሮጀርስ በመስተንግዶው በኩል ጥሩ ነበሩ፡፡

ዳኛው ዋርግሬቭ ጣፋጩን ወይን እየተጎነጩ ዶ/ር አርመስትሮንግ እና ቶኒ ማርስተንን በወሬ አፍዝዘዋቸዋል፡፡ ወ/ሮ ኤሚሊ እና ጀነራል ማካርተር ሲጠያየቁ ቆይተው በመጨረሻም የጋራ ጓደኞች እንደነበሯቸው አወቁ፡፡ ቬራ ክሬትሮን በበኩሉ ለዴቪስ በርካታ ጥያቄዎችን ስለ ደቡብ አፍሪካ ስትደረድር እርሱም በአግባቡ ሲመልስላት ቆይተዋል፡፡ ሎምባርድ በአድማጭነቱ ቢቀጥልም አይኑ ግን ከአንዱ ወደ ሌላው መንቀልቀሉን አልተወም ነበር፡፡

በዚያ መሃል ነበር አንቶኒ ማርስተን በድንገት "እነዚህ ነገሮች አይገርሙም?" በማለት የሁሉንም ትኩረት የሳበው፡፡

የምግብ ጠረጴዛው መሃል የተቀመጠው የሸክላ ሰሃን ላይ ትናንሽ የሰው ቅርፅ አሻንጉሊቶች ተደርድረው ይታያሉ፡፡

"የህንዶች ምስል የህንድ ደሴትን ለመወከል መሆን ነው" በማለት ቶኒ ስለ አሻንጉሊቶቹ አስረዳ፡፡

ቬራ ቀረብ ብላ ተመለከተችና "ይገርማል ስንት ናቸው? አስር?" ስትል በአግራሞት ጠየቀች

"አዎ - አስር ናቸው"

ቬራ በአግራሞት እየሳቀች አስሩ የህንድ ህፃናት ቅርፅ መኝታ ቤቷ ግድግዳ ላይ ከተሰቀለው የተረት ግጥም ጋር መመሳሰሉን ለእንግዶቹ ነገረቻቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድ በፍጥነት ተቀብሏት "እኔም ክፍል ውስጥ ግጥሙ ተሰቅሏል" ሲል በመቀጠል ሁሉም "እኔም ጋር - " በማለት ተናገሩ

"በጣም ይገርማል" በማለት ቬራ ስታጋንን ዳኛው ዋርግሬቭ ወይናቸውን ሳብ አድርገው "ተራ የህፃን ጨዋታ - " በማለት ተቆናጠሩ፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ እና ቬራ ለአፍታ ያህል ተያዩና ወዲያውኑ ተያይዘው ከሰፊው እልፍኝ አጠገብ ወደ በረንዳው ወደሚያስወጣው የእንግዶች ማረፊያ ተከታትለው ገቡ፡፡ ወጀብ ያነሳው ውሃ ከባህሩ ዳርቻ ከረብታ ጋር ሲላተም የሚፈጥረው ድምፅ ሁለቱን ሴቶች አስደነገጣቸው፡፡

"ደስ ይላል - " አሉ ወ/ሮ ኤሚሊ

"እንዲህ ያለ ድምፅ ያስጠላኛል" አለች ቬራ፡፡ ወዲያውኑ የወ/ሮ ኤሚሊን ጥያቄያዊ ገፅታ ተመልክታ "ማዕበል ሲኖር ይህ ቦታ የበለጠ አስፈሪ ይሆናል" አለቻቸው፡፡

"በክረምት እዚህ የሚኖሩ አይመስለኝም፡፡ የቤት ሰራተኛም ቢሆን በክረምት አይገኝም"

"በበጋም ቢሆን አገልጋይ ማግኘታቸው ይገርማል" በማለት ቬራ በደሴቷ ለመስራት ስለሚስማሙ የቤት ሰራተኞች አሰበች፡፡

"ወ/ሮ ኦሊቫር እነዚህን ባልና ሚስት አገልጋዮች በማግኘቷ እድለኛ ናት፡፡ ሚስትየዋ ጉበዝ አብሳይ ነች" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ሲናገሩ ቬራ ፈገግ ብላ ተመለከተቻቸው፡፡ ሰዎች እድሜያቸው ሲገፋ ስም እንደሚሳሳቱ አስታወሰች እና ጉሮሮዋን ጠራርጋ፡-

"አዎ፡፡ በርግጥም ወ/ሮ ኦውን እድለኛ ናት" አለቻቸው፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ ግራ ተጋብተው ቬራን አዩዋት፡፡ "ወ/ሮ ኦውን ነው ያልሽው?" በማለት ጠየቋት



t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎን"

"አውን ከምትባል ሴት ጋር በህይወቴ ተገናኝቼ አላውቅም -" አሏት ግራ ተጋብተው

ቬራም አፍጥጣ እያየቻቸው "ስሟን እርግጠኛ ነኝ..." በማለት የጀመረችውን ዓ.ነገር ሳትጨርስ የቀሩት እንግዶች በመግባታቸው አንጠልጥላ ተወችው፡፡

ሮጀርስም የቡና ስኒ የተደረደረበት ትሪ ይዞ እንግዶቹን ተከተላቸው፡፡ ዳኛው ከወ/ሮ ኤሚሊ ጎን ሲቀመጡ ፤ አርመስትሮንግ እና ቬራ ተጠጉ፡፡ ቶኒ ወደ መስኮቱ ተጠጋ ፤ ብሎር ደግሞ ከመስኮቱ አጠገብ የተሰቀለችውን የነሐስ ቅርፅ እየተመለከተ ለምን የፍትህ ምልክት ሴት እንደሆነች አሰበ፡፡ ጀነራል ማካርተር ግድግዳውን ተደግፎ ፂሙን ይፈትላል፡፡ ሎምባርድ ደግሞ ጠረጴዛ ላይ ከተደረደሩት የፋሽን መፅሄቶች መካከል አንዱን እያገላበጠ ነበር፡፡

ሮጀርስ እየዞረ ለሁሉም ቡና አስያዘ፡፡ ቡናው ወፍራም እና ትኩስ ሲሆን በጣዕሙ ሁሉም ረክተዋል፡፡ ከምሽቱ 3፡20 ሲሆን ሁሉም በተመገቡት ራት ተደስተው በየራሳቸው ሃሳብ ተወጥረዋል፡፡ በመካከላቸው የሰፈነውን ዝምታ የሰበረው ድንገተኛ ድምፅ ነበር፡፡ ድምፁ የአንደኛቸውም አልነበረም፡፡

"ክቡራት እና ክቡራን - አንድ ግዜ ፀጥታ!"

ድምፁ ከየት እንደመጣ ግራ የተጋቡት እንግዶች በመጀመሪያ እርስ በርሳቸው ተያዩ፡፡ በመቀጠል ድምፁ ሲያስተጋባ ግድግዳውን በድንጋጤ መመልከት ቀጠሉ፡፡

ድምፁ ከፍ ባለ ጉልበት መደመጥ ቀጠለ፡፡

የእያንዳንዳችሁ የወንጀል ክስ እንደሚከተለው ይገለፃል፡-


t.me/OLDBOOKSPDF

ኤድዋርድ ጆርጅ አርመስትሮንግ የካቲት 11 ቀን 1925 ሊሳ ሜሪ ክሊስን በመግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነህ፡፡

ኤሚሊ ካሮሊን ብሬንት ጥቅምት 5 ቀን 1931 ለተከሰተው የቢትሪስ ቴይለር ሞት ተጠያቂ ነሽ፡፡

ዊሊያም ሄንሪ ብሎር ህዳር 10 ቀን 1928 ለተፈፀመው የጀምስ ስቲፈን ላንደር ሞት ተጠያቂ ነህ፡፡

ቬራ ኤልሳቤጥ ክሌይትሮን ነሐሴ 11 ቀን 1935 ዓ.ም ሳይሪል ኦግሊቭ ሃሚልተንን ገድለሻል፡፡

ፊሊፕ ሎምባርድ በወርሃ የካቲት 1932 ዓ.ም ሃያ አንድ የምስራቅ አፍሪካ ጐሳ አባላትን ወንጀል ፈፅሟል፡፡

ጆን ጐርደን ማካርተን ጥር 4 ቀን 1917 ዓ.ም ሆነ ብለህ የሚስትህ ውሽማ የነበረውን አርተር ሪችሞንድ ገድለሃል፡፡

አንቶኒ ጀምስ ማሪስተን ባለፈው ህዳር 14 ቀን ጆን እና ሉሲ ኮምብስን ገድለሃል፡፡

ቶማስ ሮጀርስ እና ኤተል ሮጀርስ ግንቦት 6 ቀን 1929 ዓ.ም ለተፈፀመው የጀኒፈር ብራዲ ሞት ተጠያቂ ናችሁ፡፡

ላውረን ጆን ዋርግሬቭ ሰኔ 10 ቀን 1930 ለሞተው ኤድዋርድ ሴተን ህይወት ተጠያቂ ነህ፡፡

በእስር ላይ የምትገኙ ወንጀለኞች - ራሳችሁን ለመከላከል የምትናገሩት ነገር ይኖራል?

* * *

አስፈሪው ድምፅ ጠፋ፡፡ በእንግዶቹ መካከል የነገሰውን አስፈሪ ፀጥታ የሰበረው ከአገልጋዩ ሮጀርስ እጅ አምልጦ የወደቀው ትሪ ነበር፡፡ በዚያው



t.me/OLDBOOKSPDF

ቅፅበት ከክፍሉ ውጪ የግጭት እና ለቅሶ ድምፅ ተሰማ፡፡ ደንዝዘው ከተቀመጡት መካከል ሎምባርድ ነበር በፍጥነት ተንቀሳቅሶ በሩን የከፈተው፡፡ አገልጋይዋ ወ/ሮ ሮጀርስ ወለሉ ላይ ተጣጥፋ ወድቃለች፡፡

"ማሪስተን!" በማለት ሎምባርድ ተጣራና ለሁለት አንስተው እንግዳ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ካለው አግዳሚ ሶፋ ላይ አስተኟት፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ አጐንብሶ ከተመለከታት በኋላ "ምንም ጉዳት አልደረሰባትም፡፡ ራሷን ስታ ነው፡፡ በደቂቃ ውስጥ ትነቃለች በማለት በፍጥነት ተናገረ፡፡

"ብራንዲ አምጣ" በማለት ሎምባርድ በድንጋጤ ደርቆ የቆመውን ሮጀርስ አዘዘው፡፡ "እሺ..." በማለት እየተንቀጠቀጠ ክፍሉን ለቅቆ ወጣ፡፡

ቬራ "ድምፁ የማን ነው? ከየት ነበር የሚሰማው ... ?" በማለት በድንጋጤ እየተንዘፈዘፈች ጠየቀች፡፡

ጀነራል ማካርተርም ግራ ተጋብቶ "ምን አይነት ቀልድ ነው?" በማለት ተንተባተበ፡፡ ጀነራሉ በደቂቃዎች ውስጥ ፊቱ የተለዋወጠ ሲሆን እድሜው በ10 አመት የጨመረ መስሏል፡፡ ብሎር ፊቱ ላይ ቸፈፍ ያለውን ላብ በመሃረቡ እየጠራረገ ተንቆራጠጠ፡፡ ዳኛው ጀስቲስ ዋርግሬቭ እና ወ/ሮ ኤሚሊ ብቻ ነበሩ ከተቀመጡበት ቦታ ያልተንቀሳቀሱት፡፡ ወ/ሮዋ በድንጋጤ ፊታቸው ቀልቷል፡፡ ዳኛው ደግሞ ጭንቅላታቸውን ወደ ታች ዘመም አድርገው የተቀመጡ ሲሆን አይኖቻቸው ብቻ ነበሩ የሚንቀሳቀሱት፡፡

አርመስትሮንግ ራሷን ከሳተችው ወ/ሮ ሮጀርስ አጠገብ ቆሟል፡፡ ከመካከላቸው መናገር የቻለው ሎምባርድ ብቻ ነበር፡፡ "ድምፁ ከዚሁ ክፍል የተሰማ ይመስላል" አለ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ቬራ እየተንቀጠቀጠች "ማነው ታዲያ? ከእኛ መካከል አይደለም - " በማለት ተንተባተበች፡፡

ለደቂቃ ያህል መልስ ፍለጋ የሁሉም አይኖች ክፍሉን ማተሩ፡፡ ሎምባርድ ከእሳት ማንደጃው አጠገብ ወደ ነበረው በር በቀጥታ አመራ የሁሉም አይኖች ተከተሉት፡፡ በሩን በዝግታ ከፍቶ ወደ ውስጥ ዘለቀ፡፡

"ሁላችሁም ወደ'ዚህ ኑ" በማለት ሲጣራ የሆነ ፍንጭ ማግኘቱ ያስታውቅ ነበር፡፡ ወንበሯቸው ላይ ደርቀው ከተቀመጡት ወ/ሮ ኤሚሊ በቀር ሁሉም ሎምባርድን ተከትለው ገቡ፡፡

በክፍሉ ውስጥ ከእንግዳ ማረፊያው ግድግዳ አጠገብ የተቀመጠ ጠረጴዛ ነበር፡፡ ጠረጴዛው ላይ አሮጌ ድምፅ መቅረጫ እና ማጫወቻ ግራምፎን ተቀምጧል፡፡ የግራምፎኑ ጡሩምባ ሰፊ አፍ ግድግዳው ላይ ተደግፏል፡፡ ጡሩምባውን ሎምባርድ ወደጐን ሲገፋው ግድግዳው ላይ የተቦረቦሩ ሶስት ቀዳዳዎችታዩ፡፡

ሎምባርድ ጡሩምባውን አስተካክሎ የግራምፎኑን ማጫዋቻ ቁልፍ ተጫነው፡፡ "የእያንዳንዳችሁ የወንጀል ክስ እንደሚከተለው ይገለፃል" የሚለው ድምፅ በድጋሚ አስተጋባ፡፡

"ዝጋው! ያስፈራል" በማለት ቬራ ጮኸች፡፡ ሎምባርድም እንደታዘዘው አደረገ፡፡

"ማነው አጉል ሊቀልድ የሚሞክረው?" አለ ዶ/ር አርመስትሮንግ፡፡

"ቀልድ ይመስልሃል?" ዳኛው ቀዝቀዝ ብለው ጠየቁት

"እና?" በማለት አፍጥጦ ጠየቃቸው፡፡

"ለግዜው አስተያየት መስጠት ይከብደኛል" ሲሉ መለሱለት



t.me/OLDBOOKSPDF

የሁለቱን ሙግት ያቆመው የማሪስትን ጥያቄ ነበር፡፡ "ለመ ግራምፎኑን ምን አይነት ሰይጣን ገብቶ እንደከፈተው የሚነግረን ኣለ በማለት ልብ ያላሉትን ጥያቄ አነሳ

"እሱን ማወቅ ይኖርብናል - " በማለት ዳኛው የቀሩትን አስከትለው ወ እንግዳ ማረፊያው ተመለሱ፡፡

ሮጀርስ የታዘዘውን ብራንዲ ይዞ መመለሱ ነበር፡፡ ወ/ሮ ኤሚሊ ደግ ሶፋው ላይ ተኝታ የምታንቋርረውን ወ/ሮ ሮጀርስ አጐንብሰው እየተመለከ ነበር፡፡

ባልየው እየተጣደፈ ወደ ሶፋው አመራ፡፡ "እስቲ ወይዘሮ አሚሊ በማለት ራሷን ወደሳተችው ሚስቱ ተጠግቶ ቀና ሊያደርጋት ሞከረ "ኤተል ኤተል አይዞሽ፡፡ ኤተል ይሰማሻል? እስኪ ቀና በይ" በማለ ቀሰቀሳት፡፡ የወ/ሮዋ ትንፋሽ ቀስ በቀስ ተመለሰ፡፡ ግራ በተጋቡ አይኖ የክፍሉን ዙሪያ ቃኘች፡፡

"እስኪ ቀና በይ ኤተል" ሲል ባልየው ተደናበረ፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ግራ ወደ ተጋባችው ወ/ሮ ሮጀርስ ጐንበስ ብሎ "አይዞሽ ወ/ሮ ሮጀርስ - ምንም ጉዳት አልደረሰብሽም፡፡ ራስሽን ስተሽ ነበር አላት

"ራሴን ስቼ?"

"አዎን"

"ያ አስፈሪ ድምፅ ነው - የፈራጅ ድምፅ - " በማለት አጉተመተመችና አይኖቿን ከድና ተንጋለለች

t.me/OLDBOOKSPDF

"ብራንዲው የታለ?" በማለት ዶ/ሩ ጮኸና ክሮጀርስ ላይ ተቀብሎ "ይሄንን ጠጪበት ፤ ይሻልሻል" በማለት ደግፎ አጠጣት፡፡ ወዲያውኑ ፊቷ ላይ ለውጥ መታየት ጀመረ፡፡ አይኖቿም ተከፈቱ፡፡

"አሁን ደህና ነኝ፡፡ ድምፁ አስደንግጦኝ ነው የወደቅሁት" አለች፡፡

"እኔንም አስደንግጦኝ እኮ ነው ትሪውን የለቀቅሁት፡፡ ፍፁም የሃሰት ወንጀል ነው! ማን እንደሆነ ማወቅ..." በማለት ሮጀርስ መናገር የጀመረውን ሳይጨርስ የዳኛው ሳል አስቆመው፡፡

ጉሮሮአቸውን ጠራርገው "ለመሆኑ ግራምፎኑን አንተ ነበርክ የከፈትከው ሮጀርስ?" በማለት ጠየቁት "በፈጣሪ ስም እምላለሁ - እንደ'ዛ ሊሆን እንደሚችል ባውቅ ኖሮ አልከፍተውም ነበር፡፡" በማለት መለሰ፡፡

"እውነትህን ሊሆን ይችላል፡፡ በትክክል ብትነግረን ይሻላል" ዳኛው ፈርጠም ብለው ጠየቁት፡፡

አስተናጋጁ ፊቱን በመሃረቡ ጠራርጎ "ጌታዬ እኔ የቀረበልኝን ትዕዛዝ ብቻ ነበር የተቀበልኩት" በማለት መለሰላቸው፡፡

"የማንን ትዕዛዝ?"

"የሚስተር ኦውንን"

"ለመሆኑ ትዕዛዙ በትክክል ምን ነበር?"

"ግራምፎኑን ከመደርደሪያው ውስጥ አውጥቼ እንዳስቀምጥ እና ቡና ይዤ ስገባ ሚስቴ ማጫወቻውን እንድትከፍተው ነበር -" በማለት ሮጀርስ መለሰ፡፡

"ጥሩ መልስ ነው" በማለት ዳኛው አሽሟጠጡ

"በፈጣሪ ስም እምላለሁ እውነቱን ነው የተናገርኩት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሙዚቃ መስሎኝ ነበር፡፡ ሽክላው ላይ ስም ተፅፎበት ነበር ...» በማለት ሮጀርስ መማሉን ቀጠለ፡፡

ዳኛው ወደ ሎምባርድ ዞረው «ሽክላው ላይ የዘፈኑ ርዕስ ነበር?» በማለት ጠየቁት፡፡

ሎምባርድ ፈገግ ለማለት እየሞከረ «በትክክል ፤ ጌታዬ ስዋን ሶንግ የሚል ርዕስ ነበረው» ሲል መለሰላቸው፡፡

ጀነራል ማካርተር በድንገት አቋርጦ «ይሄ ፍፁም እብደት ነው፡፡ ተራ ውንጀላ! የሆነ ነገር ማድረግ አለብን፡፡ ይሄ አውን የተባለ ሰው ማንም ይሁን ብቻ...»

«ትክክል! ለመሆኑ እሱ ማን ነው?» በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ጣልቃ ገብተው ጠየቁ፡፡

ዳኛው በአስፈሪ ድምፃቸው ትዕዛዝ አሰተላለፉ «በትክክል በቀጣይ የምናጣራው እሱን ነው፡፡ አቶ ሮጀርስ ሚስትህን አስተኝተሃት በቶሎ ተመለስ - ስራችንን እንጀምራለን፡፡»

«እሺ ጌታዬ»

«ቆይ ልርዳህ» በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ከባልየው ጋር ሆኖ ወ/ሮ ሮጀርስን ወደ መኝታ ክፍሏ ወሰዷት፡፡

«እኔ በበኩሌ መጠጥ እፈልጋለሁ» በማለት ቶኒ ማሪስተን ሌሎቹን በጥያቄ አስተያየት ተመለከታቸው፡፡

«እኔም እፈልጋለሁ» በማለት ሎምባርድ ተስማማ፡፡ ወዲያውኑ መጠጥ የተቀዳባቸው ብርጭቆዎች የተደረደሩበት ትሪ ይዞ ተመለሰ፡፡ «ተዘጋጅተው ነው ያገኘኋቸው» በማለት ለሁሉም ሲያቀብላቸው ወ/ሮ ኤሚሊ ብቻ ውሃ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጠጣት ወሰኑ፡፡ በዚያ መሃል ነበር ዶ/ር አርመስትሮንግ ወደ እንግዳ ማረፊያው የተመለሰው፡፡

"ደህና ናት፡፡ የእንቅልፍ ኪኒን ሰጥቻታለሁ፡፡ እስኪ ለእኔም መጠጥ ስጠኝ -" አለ፡፡ ወንዶቹ መጠጣቸውን አከታተሉት፡፡ ከአፍታ በኋላ አቶ ሮጀርስ መጣ፡፡ ዳኛውም ትዕዛዝ በማስተላለፍ ምርመራው ተጀመረ፡፡ የተቀናጣው እንግዳ ማረፊያ ክፍልም የፍርድ ቤት መሰለ፡፡

"ሮጀርስ - አሁን የምፈልገው በቀጥታ የአቶ ኦውንስን ማንነት እንድትነግረኝ ነው በማለት ዳኛው ጠየቁት

"የዚህ ቤት ባለቤት ነዋ!" መለሰላቸው፡፡

"እሱንማ ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ስለ ሰውየው የምታውቀውን እንድትነግረን ነው የጠየቅሁህ፡፡" በማለት ዳኛው ጠየቁት፡፡

ሮጀርስ ራሱን ነቅንቀና "መናገር አልችልም ፣ ጌታዬ ሰውየውን አይቼው አላውቅም" በማለት መለሰላቸው

በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ ጄነራል ማካርቱር ግራ ተጋብቶ "ምን ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀው

"እኔ እና ባለቤቴ እዚህ ከመጣን ገና አንድ ሳምንታችን ነው ፣ ጌታዬ ቀጣሪያችን በደብዳቤ ነበር የተገናኘን፡፡ ሬጂና በተባለ የሰራተኛ እና አሰሪ ወኪል ቢሮ ነበር የተላክነው" በማለት ሮጀርስ አስረዳቸው፡፡

"የቆየ የውክልና ቢሮ ነው" በማለት ብሎር አረጋገጠላቸው፡፡

ዳኛ ዋርግሬቭ ጥያቄያቸውን በመቀጠል "ለመሆኑ ደብዳቤው በእጅህ ይገኛል?" አሉ

"የተቀጠርንበት የለም - ጥዬዋለሁ" ሲል መለሰላቸው፡፡

"እሺ ቀጥል" በማለት ታሪኩን እንዲቀጥል ትዕዛዝ ነገር አስተላለፉ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ ጌታዬ፡፡ በደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት በእለቱ እዚህ ደረሰን፤ ሁሉም ነገር ሙሉ ነበር፡፡ ማጀቱ በቂ የሆነ ምግብ ሞልቶትም ነበር፡ ከፅዳት ውጪ የሰራነው ነገር አልነበረም"

"ቀጥሎስ?"

"ቤቱን ለግብዣ ምቹ እንድናደርግ የሚያትት ደብዳቤ ደግሞ ደረሰን፤ ትናንት ከሰአት ደግሞ ሌላው የአቶ አውን ደብዳቤ ደርሶናል፤ በደብዳቤውም ላይ ባልና ሚስቱ በራት ግብዣው ላይ መገኘት እንደማይች፤ ገልፀው ራት እንድናቀርብ ፤ በመቀጠል ደግሞ ቡና ቀርቦ ግራምፎ፤ እንድንከፍት ነበር የታዘዝነው፡፡"

ዳኛው ኮስተር ብለው "እሱኛውንስ ደብዳቤ ይዘኸዋል?" በማለት ጠየቁት

"አዎ" አለና ከኪሱ አውጥቶ ሰጣቸው፡፡

ዳኛው ደብዳቤውን አየት አድርገው "ሪትዝ ሆቴል በሚል አድራሻ ነ የተላከው፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ በታይፕ ነው የተፃፈው" በማለት ሲናገ ብሎር በፍጥነት ወደ ዳኛው ተራምዶ "እስኪ ልየው - " በማለ ተቀብሏቸው አገላብጦ ተመለከተው፡፡

"በአዲስ የፅፈት መኪና የተፃፈ ነው፡፡ ወረቀቱም ቢሆን ተራ እና ሁሉ የሚጠቀምበት ነው፡፡ ከዚህ ላይ ምንም ፍንጭ ማግኘት አንችልም፡፡ ምናልባት አሻራ ካልሆነ በቀር" በማለት ደብዳቤውን ሲመልስላቸው ዳኛ በአግራሞት ነበር ብሎርን የተመለከቱት፡፡

ማሪስተን ደብዳቤውን ተንጠራርቶ አየና "ኡሊክ ኖርማን አውን የላኪው ስም የተለመደ አይነት የክርስቲያን ስም ነው" በማለት የበኩሉ አስተያየት ሰነዘረ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኛውም ቀና ብለው ተመልክተውት "ትኩረት የሚስብ ፍንጭ ነው የሰጠኸን አቶ ማሪስተን" በማለት የቀሩትን ሰዎች ገርመም አድርገው ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡ "ሁላችንም ስለቤቱ ባለቤቶች የምናውቀውን መናገር አለብን፡፡ ሁላችንም ተጋብዘን መጥተናል፡፡ እንግዲህ እንዴት እንደተጋበዝን የምንናገርበት ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡"

ወ/ሮ ኤሚሊ ነበሩ የመጀመሪያዋ ተናጋሪ፡፡ "የማይነበብ ፊርማ ያለበት ደብዳቤ ደርሶኝ ነው የመጣሁት፡፡ ጋባዤ ከሁለት አመታት በፊት የበጋ እረፍት ላይ እንደተገናኘን ጠቅሳልኛለች፡፡ በዚያ ወቅት አግዴን ወይም ኦሊቨር ከተባለች ወ/ሮ ጋር ተዋውቄ ነበር፡፡ ነገር ግን እውን ከተባለች ሴት ጋር ፍፁም አልተዋወቅም"

"ደብዳቤው በእጅዎት አለ?" ሲሉ ዳኛው ጠየቁ

"አዎ፡፡ ከክፍሌ ላምጣው" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ በፍጥነት ደብዳቤውን ይዘው ተመለሱ እና ለዳኛው አቀበሉ፡፡

"ጥሩ፡፡ ወ/ሪት ቬራ?" በማለት ቀጣይ ተናጋሪዋን አስጀመሩ፡፡ ቬራም በፀሃፊነት ተቀጥራ መምጣቷን አስረዳች፡፡ በመቀጠል የተጠየቀው ማሪስተን ነበር፡፡

"የድሮ ወዳጄ ባጀር በርክሌይ ነበር የጋበዘኝ፡፡ ወደ'ዚህ መጥቼ እንዳገኘው እና ስለ ጥንቱ ግዜ እንድንጫወት ነበር የገለፀልኝ" በማለት አስረዳ፡፡ ዳኛው ምንም ስሜት አልሰጣቸውም፡፡ በመቀጠል ዶ/ር አርመስትሮንግ ተጠራ፡፡

"ለህክምና ስራ ነበር የተጠራሁት"

"ከቤቱ ባለቤቶች ጋር የግል ትውውቅ የለህማ?" በማለት ዳኛው ጠየቁት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"የለኝም፡፡ ደብዳቤው ላይ ግን የአንድ ወዳጄ ስም ተጠቅሶ ነበር"

"ቆይ እስኪ ልገምት፡፡ ወዳጅህን ካገኘኸው ብዙ አመታት ሆኗ አይደል?" በማለት ዳኛው ፈገግ ብለው ጠየቁት

"አዎን " በማለት ዶ/ሩ መለሰላቸው፡፡

ሎምባርድ ጣልቃ በመግባት "እዚህ ጋር የምናገረው ነገር አለ" በማለት ተጣደፈ፡፡ ዳኛው በእጃቸው ምልክት አስቆሙት፡፡ "ሁሉም ሰው በተራ ነው የሚናገረው፡፡ አሁን ደግሞ ጀነራል ማካርተር ይቀጥሉ" በማለት ዳኛው ስርአት አስያዙት፡፡

ጀነራሉ ፂሙን እየፈተለ መናገር ጀመረ፡፡ "አውን የተባለው ሰውዬ የድሮ ወዳጆቼን ስም ጠቅሶ ነው የጋበዘኝ፡፡ ደብዳቤውን ግን ጥየዋለሁ" በማለት አስረዳ፡፡

"ሎምባርድ አሁን ቀጥል" አሉት ዳኛው

ለደቂቃዎች ያህል የሚናገረውን የፈጠራ ታሪክ ሲያዘጋጅ ቆይቶ ነበር፡፡ በመጨረሻም በጥድፊያ ተናገረ፡፡ "እንደ ሁላችሁም የድሮ ጓደኞቼ ስም ባለበት ደብዳቤ እዚህ እንድመጣ ተነገረኝ፡፡ ደብዳቤውን አልያዝኩትም"

ዳኛው ፊታቸውን ወደ ብሎር አዞሩ፡፡ አፋቸውን ጠራረጉና "አሁን ውጥረት ላይ ደርሰናል፡፡" በማለት ተረጋግተው መናገር ጀመሩ፡፡ የሰማነው ድምፅ ሁላችንንም በስማችን በመጥራት ክስ እንዳቀረበብን ሰምተናል፡፡ ክሱን በተመለከተ እንመለስበታለን፡፡ ለግዜው ግን አንድ ነገር አስታውሱ፡፡ በግራምፎኑ ከተጠሩት መካከል ዊሊያም ሄንሪ ብሎር ይገኝበታል፡፡ በመካከላችን ደግሞ ብሎር የተባለ ሰው የለም፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የዴቪስ ስም አልተጠራም፡፡ ስለዚህ ነገር የምትነግረን አለህ ፣ አቶ ዴቪስ?" በማለት ጠየቁት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎር እንደማፈር ብሎ መለሰላቸው፡፡ "የተደበቀችው ድመት ተገኘች ማለት ነው፡፡ ስሜ ዴቪስ አለመሆኑን ማመን አለብኝ" አለ

"አንተ ዊሊያም ሄንሪ ብሎር ነህ?"

"አዎን"

"ቆይ አንዴ " በማለት ሎምባርድ አቋርጦት መናገር ጀመረ፡፡ "አቶ ብሎር የሃሰት ስም ከመጠቀምህ በላይ ምሽቱን በሙሉ ስትዋሽ ነበር፡፡ ከደቡብ አፍሪካዋ ናታል እንደመጣህ ስታወራ ነበር፡፡ እኔ ደቡብ አፍሪካን በደንብ አውቃታለሁ፡፡ አንተ ናታል እንዳልነበርክ እርግጠኛ ነኝ" አለ፡፡

የሁሉም አይኖች በቁጣ ወደ ብሎር ዞሩ፡፡ አንቶኒ ማሪስተኝ እጆቹን ጨብጦ ወደፊት በመራመድ "ለመሆኑ መልስ አለህ?" በማለት ሲያፈጥበት ብሎር ወደ ኋላ ፈንጠር ብሎ ቆመና ማስረዳት ጀመረ

"ክቡራን ዋሽቼ ስለያዛችሁኝ ይቅርታ፡፡ በኪሴ መታወቂያ ይዣለሁ፡፡ የቀድሞው ብሔራዊ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ባልደረባ ነኝ፡፡ በአሁኑ ወቅት የግል ምርመራ ስራ እሰራለሁ፡፡ ወደ'ዚህ የመጣሁትም ለስራ ነው" በማለት ብሎር አስረዳ፡፡

"ማን ነው የላከህ?" በማለት ዳኛው ጠየቁት፡፡

"አውን የተባለ ሰው ነው ደብዳቤ የላከልኝ፡፡ ትዕዛዙን ከፈፀምኩለት ዳጐስ ያለ ገንዘብ እንደሚሰጠኝ ነበር የገፈልኝ፡፡ ወደ'ዚህ በመምጣትም ድግሱ ላይ እንደ እንግዳ እንድገኝ እና ሁላችሁንም እንድጠብቅ የስም ዝርዝራችሁን ሰጥቶኛል"

"ምክንያትስ ሰጥቶሃል?"

"አዎ፡፡ የባለቤቱን ጌጣጌጦች ለመጠበቅ ነበር የቀጠረኝ፡፡ የሚገርም ሰው ነው፡፡ አጃጅሎኛል፡፡" በማለት የተቀጠረበትን ተግባር አስረዳ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኛው ፂማቸውን እየፈተሉ መናገር ጀመሩ፡፡ "በአጠቃላይ የደረስንበትን ግዜያዊ ድምዳሜ እንመልከት፡፡ የወ/ሮ ብሬንት ደብዳቤ ላይ ያለው ስም ባይነበብም ኡሊክ ኖርማን አውን አሊያም የተጠቀመው የክርስቲያን ስም ኡና ናንሲ መሆኑን መገመት እንችላለን፡፡ እነዚህን ስሞች አሳጥሮ የፈረመው ላኪ "ዩ.ኤን. አውን" በማለት ራሱን ገልጿል፡፡ ይህ ስም ደግሞ "Unkonown" በማለት የማይታወቅ ሰው መሆኑን የገለፀበትም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ጋባዣችን አይታወቅም ማለት እንችላለን ...." በማለት ዳኛው ያልተቋጨ ግምታቸውን አስቀመጡ፡፡

"ይሄ ፍፁም እብደት ነው" በማለት ቬራ በቁጣ ተናገረች፡፡

ዳኛው በተረጋጋ ሁኔታ ወደ ቬራ ዞረው "ትክክል ነሽ፡፡ ሁላችንንም ወደ'ዚህ የጋበዘን ሰው እብድ መሆኑን እኔም አምናለሁ፡፡ አደገኛ እብድ ምናልባትም ግድያ የተጠናወተው እብድ" በማለት አጠናከሩላት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አራት

ውይይቱ ተቋረጠ እና አስፈሪ ፀጥታ በቦታው ተተካ፡፡ ከአፍታ በኋላ የጡረተኛው ዳኛ ቀሰስተኛ ንግግር መሰማት ጀመረ፡፡ "ምርምራችንን እንቀጥላለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን እንደሁላችሁም የእኔን አመጣጥ አስረዳለሁ፡፡" በማለት ከኪሳቸው ደብዳቤ አውጥተው ጠረጴዛው ላይ ወረወሩት እና ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

"ለእኔ የደረሰኝ የግብዣ ደብዳቤ ላይ የቀድሞ ወዳጄ ወ/ሮ ኮንስታንስ ከልሚንግተን ስም ተጠቅሷል፡፡ ለመጨረሻ ግዜ ያገኘኋት ከአመታት በፊት ወደ ምስራቅ ከመሄዱ በፊት ነበር፡፡ ጋባዣችን ስለ ሁላችንም የጠለቀ መረጃ እንዳለው ነው፡፡ ለምሳሌ በእኔ እና በወ/ሮ ኮንስታንስ መካከል ያለውን ወዳጅነት ብቻ ሳይሆን የደብዳቤ አፃፃፏንም ያውቃል፡፡ የዶ/ር አርመስትሮንግ የቀድሞ ወዳጆች በአሁኑ ሰአት የት እንዳሉ ፤ የማሪስተንን ቅፅል ስም እና ጓደኞች ፤ ወ/ሮ ኤሚሊ ከሁለት አመታት በፊት በእረፍት ላይ የተዋወቋቸውን ሰዎች እንዲሁም የጀነራል ማካርተርን የቀድሞ ባልደረባዎች ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነው ወደ'ዚህ የጠራን፡፡ ስለሚያውቀንም ይመስለኛል በልበ-ሙሉነት የወነጀለን፡፡"

የዳኛውን ገለፃ ተከትሎ ጀነራል ማከርተር "ይሄ ፍፁም የሃሰት ውንጀላ ነው!" በማለት አምባረቀ፡፡

"እብደት ነው!" በማለት ቬራ ተከተለች

"ፍፁም ሃሰተኛ! እንዳችንም ወንጀለኞች አይደለንም" በማለት ሮጀርስ ሲናገር ማሪስተን ከአፉ ተቀብሎ "ምን አይነት የሞኝ ጨዋታ እንደሆነ አልገባኝም" አለ፡፡ ጡረተኛው ዳኛ ዋርግሬቭ እጃቸውን ከፍ አድርገው



t.me/OLDBOOKSPDF

የቤቱን ሁካታ አስቆሙ፡፡ በመቀጠልም ቃላት በመምረጥ በጥንቃቄ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

"ሁላችንም እንደሰማነው የማይታወቀው ጌደኛችን ለኤድዋርድ ሴተን ሞት ተጠያቂ አድርጎኛል፡፡ ኤድዋርድን የማውቀው በአንዲት ሴት ሞት ተከስሶ ሰኔ 1930 ፍርድ ቤት በቀረበበት ወቅት ነበር፡፡ ወጣቱ ክሱን ለማስተባበል የተቻለውን ያህል መሞከሩን አስታውሳለሁ፡፡ ነገር ግን በወቅቱ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ስለነበሩ የማያሻማ የጻኝነት ውሳኔዬን አስተላለፍኩኝ፡፡ በሞት እንዲቀጣ ፈረድኩበት፡፡ ያቀረበውም ይግባኝ በቂ ባለመሆኑ የፍርድ ውሳኔው ፀንቶ በሞት ተቀጥቷል፡፡ በወቅቱ ያስተላለፍኩት ውሳኔ ትክክለኛ እንደነበር ለሁላችሁም ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡"

ዶ/ር አርመስትሮንግ ዳኛው ስለሚያወሩት ነገር ግልፅ ሆነለት፡፡ ከአመታት በፊት ስለነበረው የኤድዋርድ ሴተን ክስ መስማት የቻለው ከተከሳሹ ጠበቃ ማቲውስ ነበር፡፡ በወቅቱ ጠበቃው ደንበኛውን ነፃ እንደሚያወጣው እርግጠኛነቱን ለዶ/ር አርምስትሮንግ ገልፆለት ነበር፡፡ ያልጠበቀው ፍርድ ከተበየነ በኋላ ሲያገኘው ግን ዳኛ ዋርግሬቭ በተከሳሹ ላይ የፀና አቋም እንደያዘበት ምናልባትም የግል ፀብ ሳይኖራቸው እንዳልቀረ የነበረውን ግምት ነግሮት ነበር፡፡

"ለመሆኑ ኤድዋርድ ሴተንን በግል ያውቁት ነበር?" በማለት ዶ/ሩ በድንገት ጠየቃቸው፡፡ ዳኛ ዋርግሬቭ በምስጢራዊ አይኖቻቸው አርመስትሮንግን ገርመም አድርገው እንደማያውቁት መለሱለት፡፡

አርመስትሮንግም ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምፅ "ይሄ ሰው እየዋሸ እንደሆነ አውቃለሁ" አለ፡፡

• • •

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀጣይ ቬራ ክሌይትሮን በሚርገበገብ ድምፅ መናገር ጀመረች፡፡ "የእኔን ክስ በተመለከተ የሰማችሁት ፍፁም የተሳሳተ ነው፡፡ የሟቿ ህፃን ሴሪል ሂሚልተን የቤት ውስጥ አስጠኚ በነበርኩበት ወቅት ልጁ እንዳይዋኝ ተነግሮኝ ነበር፡፡ በሃሳብ ውስጥ ሆኜ ወደ ውሃው መሃል መድረሱን ሳላይ ነበር አሰቃቂው አደጋ የተከሰተው፡፡ በተቻለኝ ፍጥነት ልደርስበት ብሞክርም አልቻልኩም፡፡ ፍርድቤቱም በወቅቱ በነፃ ነበር ያሰናበተኝ፡፡ የልጁ እናትም ብትሆን ጥፋተኛ አላዳረገችኝም፡፡ ለመሆኑ ይሄ ሰው ለምን በሃሰት ከሰሰኝ፡፡ ይሄ ፍፁም የተሳሳተ ነው፡፡"

ጀነራል ማካርተር ትከሻዋን ቸብ አድርጎ "ትክክል ነሽ፡ ከሳሻችን ሃሰተኛ ብቻ ሳይሆን እብድም ጭምር ነው፡፡" በማለት አፅናንቷት ከተቀመጠበት ተነስቶ መናገር ቀጠለ፡-

"ይህንን ለመሰለ የሃሰት ውንጀላ መልስ መስጠት በራሱ ክብር ያሳጣል፡፡ ነገር ግን ስለተከሰስኩበት ወጣት መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ሟች አርተር ሪችሞንድ በእኔ ትእዛዝ ስር የነበረ ወጣት መኮንን ሲሆን ቅኝት እንዲወጣ ያዘዝኩትም እኔው ነበርኩ፡፡ በማንኛውም ጦርነት ላይ እንደሚያጋጥመው ሁሉ ወጣቱም በወቅቱ ተገድሏል፡፡ የእሟሟቱን ተፈጥሮአዊነት በተመለከተ በምወዳት ሚስቴ እምላለሁ እጄ የለበትም" በማለት ጀነራሉ ፂሙን እየፈተለ ተቀመጠ፡፡

ሎምባርድ መናገር ሲጀምር አይኖቹ በፍጥነት ነበር የሚዘዋወሩት፡፡ "የጐሳ አባላቱን በተመለከተ የሰማችሁት ታሪክ እውነተኛ ነው፡፡ በግዳጅ ላይ ሳለን በስሬ የነበሩት ጓዶች በርሃብ ሊያልቁ እንደሚችሉ ስለተሰማኝ የነበረውን ስንቅ አስይዤ የጐሳ አባላቱን በመተው የራሴን ጓዶች አትርፌአለሁ".



t.me/OLDBOOKSPDF

ጀነራል ማካርተር ቆጣ ብሎ "በርሃብ እንዲያልቁ ጥለሃቸው ሄድክ" በማለት ጠየቀው

"ራስን የማዳን ጉዳይ ነው። ማንም ሰው ቅድሚያ የሚሰጠው ለራሱ ነው። በዚያ ላይ ደግሞ የአፍሪካ ጐሳ አባላት ሞት ከአውሮፓውያኑ እኩል ሊታይ አይገባም" በማለት በትዕቢት የተሞላ ማስተባበያ ሰጠ።

ቬራ በቁጣ ከወንበሯ ተነስታ "እና ለሞት ጥለሃቸው ሄድክ?" በማለት አፈጠጠችበት።

"በትክክል" በማለት መልሶ አፈጠጠባት።

አንቶኒ ማሪስተን ነበር ቅድሚያ ያስረዳው።. "ጆን እና ሉሲ ኮምብስ ማለት ካምብሪጅ አቅራቢያ በመኪና ገጭቼ የገደልኳቸው ህፃናት ናቸው። መጥፎ ቀን ነበር።"

"መጥፎ ቀን የነበረው ላ'ንተ ነው ወይስ ለህፃናቱ?" በማለት ዳኛው ጠየቁት።

"የእኔ መጥፎ ቀን መስሎኝ ነበር። ነገር ግን ህፃናቱም እድለ-ቢስ ነበሩ። እየሮጡ ነበር መኪና መንገዱ ላይ የገቡብኝ። ለአንድ አመት መንጃ ፍቃዴ ታግዶብኝ ነበር " በማለት መለሰ።

ዶ/ር አርመስትሮንግ ዝግ ባለ ድምፅ "እንደ አንተ ያሉ አሽርካሪዎች ከሩጫ በቀር ሌላ ሃሳብ የላቸውም። የማህበረሰባችን ጠንቆች ናችሁ " አለው።

"የእንግሊዝ መንገዶች በጣም ጠባብ ናቸው ፤ ዶ/ር። ለመሮጥ ባናስብም አይቻልም። በፍጥነት መንገድ መልቀቅ ይኖርብናል።" በማለት ለህፃናቱ ሞት የመንገዶቹን ጠባብነት ተጠያቂ በማድረግ የጨለጠውን መጠጥ ሊሞላ


t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ መደርደሪያው አመራ፡፡ ብርጭቆውን ሞልቶ እየተመለሰ "ለማንኛውም የልጆቹ ሞት አደጋ እንጂ የእኔ ጥፋት አልነበረም" አለ፡፡

• • •

የቤቱ አገልጋይ የነበረው ሮጀርስ በላብ የራሱ ጣቶቹን እያፍተለተለ ለመናገር ፈቃድ ጠየቀ፡፡ የደረቁ ከናፍሮቹን በምላሱ አርጥቦ መናገር ጀመረ፡-

"እኔ እና ባለቤቴ ቀጣሪያችን የነበረችውን እመቤት ብራዲ እንደገደልን ተደርጐ የተነገረው ሃሰት ነው፡፡ ቀጣሪያችን በከፍተኛ ህመም ስትሰቃይ የነበረ ሲሆን እኛም እስከመጨረሻው እለት በታማኝነት ተንከባክበናታል፡፡ በሞተችበት እለት ከፍተኛ ንፋስ ተነስቶ ስለነበር ስልክ ተቋርጦ ነበር፡፡ በድንገት ሲብስባት ዶክተር ለመጥራት በእግሬ ነበር ሄድኩት፡፡ ነገር ግን ዘግይተን ነበር፡፡ ታማኝ አገልጋይነታችንን ማንም ሊመሰክር ይችላል፡፡ ማንም በግድያው አልጠረጠረንም ነበር፡፡"

የደረቁትን የሮጀርስ ከናፍር እና የሚንቀጠቀጡ እጆች የተመለከተው ሎምባርድ ሮጀርስ በድንጋጤ የስኒ ትሪውን የጣለበትን ሁኔታ አስታወሰ፡፡ ነገር ግን ምንም ቃል ሳይተነፍስ በአግራሞት አየው፡፡

ብሎር ለስለስ ባለ ሁኔታ "እመቤታችሁ ስትሞት የወረሳችሁት ነገር ነበር?" በማለት ጠየቀው፡፡

ሮጀርስ ተደናብሮ መለሰለት "አዎን፡፡ ለመልካም አገልጋይነታችን እና ታማኝነታችን ስትል እመቤት ብራዲ ውርስ አስተላልፋልናለች " በማለት መለሰ፡፡

"ያንተም ስም ነበር አቶ ብሎር፡፡ እስኪ ደግሞ ስለ ራስህ ንገረን" በማለት ሎምባርድ ሲጠይቀው ብሎር በድንጋጤ ፊቱ ቀላ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ላንዶር ባንክ ዘርፎ የታሰረ ወንጀለኛ ነበር" በማለት ብሎር የቀረበባ... አጋታ ክሪ...
የግድያ ክስ ማስተባበል ጀመረ

"አስታውሳለሁ፡፡ በወቅቱ የላንዶርን ክስ የያዘው ፖሊስ አንተ ነበርክ
አይደል?" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ ጠየቁት፡፡

"አዎን"

"እድሜ ልክ ተፈርዶበት በእስር ላይ ሳለ ነበር ከአንድ አመት በ...
የሞተው፡፡" በማለት ዳኛው በጥያቄ አስተያየት ተመለከቱት

"ጋጠ-ወጥ ሰው ነበር፡፡ ለማምለጥ ሲሞክር ነበር የገደልኩት" በማለ...
ብሎር መለሰ፡፡

"ከዚያስ?"

"የማዕረግ እድገት ተሰጠኝ፡፡ በወቅቱ ያደርግሁት ነገር ግዴታዬ...
መወጣት እንጂ ወንጀል አልነበረም፡፡" በማለት ብሎር ሲመልስ ሎምባርድ...
ከጣሪያ በላይ ሳቀ፡-

"ሁላችንም ሰው የገደልነው ግዴታችንን ስንወጣ ነበር፡፡ እሺ ዶ/...
ያንተን ደግሞ ንገረን?" እስኪ በማለት ሎምባርድ ወደ ዶ/ር አርመስትሮንግ
ዞሮ "የህክምና ግዳጅ ላይ ሳለህ ነበር የተሳሳትከው?" በማለት ፈገግ እንደ...
ጠየቀው፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ፍፁም ተረጋግቶ ነበር የመለሰላቸው፡፡ "ስለጉ...
የማውቀው ነገር የለም፡፡ ስሙንም አላስታውሰውም፡፡ ግዜው በጣም የ...
በመሆኑ ምናልባትም ከታካሚዎቹ አንዷ ልትሆን ትችላለች፡፡ ብዙ ሰዎች
ኦፕራሲዮን ተደርጐላቸው ካልተረፉ ሃኪሙ ነው የሚወነጀለው፡፡ በጣም
የሚገርም እኮ ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶ/ሩ በሃሳብ ወደኋላ ተመለሰ፡፡ ከአመታት በፊት በሰካር ውስጥ ሆና አፐራሲዮን ያደረጋትን ሴት አስታወሳት፡፡ ህክምናው ቀላል የነበረ ሲሆን በመስከሩ የተነሳ ነበር የገደላት፡፡ በወቅቱ የሟች እህት ብትጠራጠርም ስለ ጉዳዩ አልተነፈሰችም ነበር፡፡ ከአመታት በኋላ የተረሳው ነገር መነሳቱን ሲያስብ ውስጡ በቅዝቃዜ ተሞላ

• • •

ቤቱ በድጋሚ በፀጥታ ተሞላ፡፡ የሁሉም ተሳታፊዎች አይን የነበረው ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት ላይ ነበር፡፡ ወ/ሮዋ እስኪናገሩ እየተጠበቁ እንደሆነ የገባቸው ከሁለት ደቂቃ በኋላ ነበር፡፡

"የምናገረው ነገር ያለ መስሏችሁ እየጠበቃችሁ ነው?" በማለት ተገርመው ጠየቁ፡፡

"ምንም የሚነግሩን የሎትም?" በማለት ጡረተኛው ዳኛ ጠየቋቸው፡፡

"ምንም የለኝም"

"መከላከያ ሃሳቦትን ለማቆየት ፈልገዋል?"

"ምንም የምከላከለው ነገር የለም፡፡ ዘመኔን በሙሉ ያሳለፍኩት በተጠና እና ጤናማ በሆነ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የተሳሳተ ነገር ፈፅሜ አላውቅም" በማለት ፈርጠም ያለ መልስ ሰጡ፡፡ የቀሩት ተሳታፊዎች በምላሹ ባይደሰቱም ወ/ሮዋ ግን ምንም አልመለሱላቸውም፡፡

ዳኛው በረጅሙ ተንፍሰው "እንግዲያው የግል ምርመራችን እዚህ ላይ ያበቃል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በደሴቷ ላይ ከእኛ ውጪ ሌላ ሰው እንዳለ እና እንደሌለ ሮጀርስ ልትነግረን ትችላለህ?" በማለት አገልጋዩን ጠየቁት፡፡

"በፍፁም ሌላ ሰው የለም"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እርግጠኛ ነህ?"

"በጣም እርግጠኛ ነኝ"

ዳኛው ዋርግሬቭ "እንግዲያውስ ወደዚህ ደሴት ያመጣን ሰው እብ ሳይሆን አደገኛ ነው ማለት እንችላለን፡፡ እንደ እኔ አስተሳሰብ ይሄንን ደሴ አሁኑኑ ለቀን መሔድ ይኖርብናል፡፡" በማለት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡

"ምንም ጀልባ የለም እኮ ጌታዬ" አለ ሮጀርስ

"ታዲያ በምንድን ነው ከዋናው ምድር ጋር የምትገናኙት?"

"ፍሬድ ናርኮት ዘወትር ጠዋት ወተት ፣ ዳቦ እና ደብዳቤ ይዞ በመምጣ ሌላ ትዕዛዝ ካለ ይዞ ይመለሳል፡፡"

"ስለዚህ ጠዋት ናርኮት ሲመጣ እንሔዳለና" በማለት ዳኛው ያቀረቡት ብቸኛ ሃሳብ ሁሉም ሲቀበሉት አንቶኒ ማሪስተን ግን ተቃወመ፡፡

"ይሄንን እንቆቅልሽ ሳንፈታ የትም አንሔድም፡፡"

"እኔ በበኩሌ ጀብድ ለመፈፀም የሚያበቃ እድሜ የለኝም " በማለት ዳኛው ቀዝቀዝ ያለ ተቃውሟቸውን አሰሙ፡፡

"ህጋዊ እንቅስቃሴ የሚባለው ነገር አብቆተለታል፡፡ አሁን ወደ ወንጀል የተጠጋንበት ወቅት ነው" በማለት አንቶኒ ማሪስተን የመጠጥ ብርጭቆውን አንስቶ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው፡፡ ወዲያውኑ ወንበሩ ላይ ዘፍ ብሎ ተቀመጠ፡፡ ፊቱ በፍጥነት ነበር የቀላው፡፡ እጆቹ ተዘረጉ፡፡ የመጠጡ ብርጭቆም ከእጁ ላይ ተንሸራትቶ ወለሉ ላይ ወደቀ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አምስት

ፈፅሞ ያልጠበቁት ነገር ነበር የተከሰተው፡፡ አንቶኒ ማሪስተን ተዝለፍልፎ ሲወድቅ በፍጥነት የደረሰበት ዶ/ር አርመስትሮንግ ነበር፡፡ የቀሩት በያሉበት ደንዝዘው ነበር የተመለከቱት፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ቀና ብሎ እየተመለከታቸው "ሞቷል! የፈጣሪ ያለህ" አለ፡፡ ማናቸውም ሊያምኑ አልቻሉም ነበር፡፡ ከሰአታት በፊት በሙሉ ጤንነት ላይ የነበሩ እና አማልክት የመሰላቸው ወጣት በድንገት መሞቱን መቀበል አልቻሉም ነበር፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ በድጋሚ አጐንብሶ የማሪስተንን የገረጣ ፊት ተመለከተ፡፡ ወደ ጐን የተጣመመው የታችኛው ከንፈሩ ሰማያዊ ሆኗል፡፡ ወዲያውኑ ነበር ማሪስተን ሲጠጣበት የነበረውን ብርጭቆ በማንሳት ዶ/ሩ ያሸተተው፡፡

ጀ/ል ማካርተር "እንዴት እንደዚህ በፍጥነት ሊሞት ይችላል? ምን ማለትህ ነው?" በማለት በድንጋጤ ጠየቀው፡፡

"መተንፈስ አቅቶት ነው የሞተው" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ በጣቱ ጫፍ የብርጭቆው ወለል ዳብሶ በቀስታ በምላሱ ጫፍ ቀመሰው፡፡ ወዲያውኑ ፊቱ ተቀያየረ፡፡ "ማሪስተን ተፈጥሮአዊ ሞት አይደለም የሞተው" አለ

ቬራ በቀዘቀዘ ድምፅ "መጠጡ ውስጥ ምን ነበረበት?" በማለት ጠየቀችው፡፡

ዶ/ሩ ግራ ተጋብቶ "በትክክል ምን እንደሆነ ለመናገር ይከብዳል፡፡ ምናልባት ፖታሲየም ሲያናይድ ሊሆን ይችላል፡፡" በማለት ማሪስተን የተመረዘበትን ቅመም ገመተ፡፡

"ብርጭቆው ውስጥ?" በማለት ዳኛው ጠየቁት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶ/ሩ በቀጥታ ወደ መጠጥ መደርደሪያው በመሄድ የውስኪ እና የሲዳሞ ጠርሙስ አሸተተ፡፡ "ሁለቱም ንፁህ ናቸው" አለ፡፡

ሎምባርድ በፍጥነት "እና? በራሱ ብርጭቆ ላይ መርዝ ጨምሯል ማለት ነው?" በማለት ጠየቀው

"ራሱን ሲያጠፋ አይችልም " አለ ብሎር

"ራሱን የሚገድል አይነት ሰው አይደለም፡፡ የመኪና አነዳዱም ሆነ ሁሉ ነገሩ ለመኖር የሚመኝ አይነት እንጂ የሚሞት ፍላጐት ያለው አይመስልም፡፡ ይሄ የማይታመን ነው " በማለት ቬራ አከለች፡፡

"ራሱን ገደለ ከሚለው ውጪ ሌላ መላ-ምት ይኖረናል?" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ግራ ተጋብተው የቆሙትን ሰዎች ጠየቀ፡፡ ሁሉም በአሉታ ራሳቸውን ነቀነቁ፡፡ አንቶኒ ተነስቶ የራሱን መጠጥ ሲቀዳ ስለተመለከቱት መርዝ ቢጨምር እንኳን ራሱ እንደሚሆን አምነዋል፡፡ ነገር ግን እንደ አንቶኒ ያለ ወጣት ራሱን መግደሉ ደግሞ የበለጠ እንቆቅልሽ ሆነባቸው፡፡

* * *

የወጣቱን አስከሬን አፍጥጠው ከመመልከት የተለየ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ በመጨረሻም ዶ/ር አርመስትሮንግ እና ሎምባርድ ተጋግዘው አስከሬኑን ወደ ክፍሉ በመውሰድ አልጋው ላይ አስተኙት፡፡ ወደ እንግዳ ማረፊያው ሲመለሱ የቀሩትን በሙሉ ግራ ተጋብተው እንደቆሙ ነበር ያገኛቸው፡፡

"በጣም መሽቷል፡፡ ብንተኛስ?" በማለት ሃሳብ ያቀረቡት ወ/ሮ ኤሚሊ ነበሩ፡፡ ሁሉም በመዳከማቸው የተነሳ የወ/ሮዋን ሃሳብ መቀበል ቢኖርባቸውም ነገር ግን እርስ በርስ መጠባበቁ የግድ ስለሆነባቸው ለመተኛት አልተስማሙም ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሌሊቱ 6፡30 ቢሆንም ለመተኛት የተዘጋጁት ወ/ሮ ኤሚሊ ብቻ ነበሩ፡፡ በመቀጠል የመተኛት ሃሳቡን የደገፉት ጡረተኛው ዳኛ ዋርግሬቭ ነበሩ፡፡ "ሁላችንም መተኛት አለብን" አሉ፡፡

ሮጀርስ ደግሞ "ምግብ የተበላባቸውን እቃዎች ማነሳሳት አለብኝ" አለ፡፡ ሎምባርድ ቀበል ብሎ "ጠዋት ይነሳል" በማለት እንዲተኛ ሲነግረው ዶ/ር አርመስትሮንግ ደግሞ "ሚስትህ እንዴት ናት?" በማለት ጠየቀው፡፡

"አሁን አይቻት ነበር፡፡ ጥሩ እንቅልፍ ላይ ናት" በማለት መለሰለት፡፡

"ጥሩ፡፡ እንዳትረበሽ ተከታተላት"

"እሺ ፣ ዶ/ር፡፡ መስኮቶቹን ዘጋግቼ ወደ'ሷ እሔዳለሁ" በማለት ወደ ሳሎኑ ገባ፡፡ ሌሎቹም ወደ መኝታ ክፍላቸው ለመሔድ ደረጃውን በሰልፍ መውጣት ጀመሩ፡፡

ቤቱ ሰፊ እና በቂ ብርሃን ያለበት ነበር፡፡ እንደ እንግዶቹ ፍርሃት ቤቱ በጨለማ የተዋጠ ቢሆን ኖሮ ምናልባት የበለጠ እንደሚያስጨንቅ መገመት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የቤቱ ስፋት እና በብርሃን የተሞላ መሆኑ ነበር የበለጠ ያስፈራቸው፡፡

የቤቱ የላይኛው ክፍል ሲደርሱ ሁሉም ተሰነባብተው ወደየክፍላቸው ገቡ፡፡ በተመሳሳይ ፍጥነትም በራቸውን ቆለፉ፡፡

* * *

ዳኛው ዋርግሬቭ ልብሶቻቸውን አወላልቀው ወንበር ላይ በማስቀመጥ ለመኝታ ዝግጅት ማድረግ የጀመሩት እንደገቡ ነበር፡፡ ጡረተኛው ዳኛ የወጣቱ ኤድዋርድ ሴተንን ምስል ከአእምሮአቸው ሊያወጡት አልቻሉም፡፡ የነቁ አይኖቹ ፣ ብሩህ ፈገግታው እና በራስ መተማመኑ የማንንም ዳኛ ቀልብ የሚስብ እንደነበር ታወሳቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በእለቱ በነበረው ችሎት ላይ አቃቤ-ህጉ ሲውሊን አቋሙን አፅንቶ የነበ
ሲሆን የተከሳሹ ወጣት ጠበቃ የነበረው ማቲውስም ፈፅሞ የማይቻል ነበር፡
ተከሳሹ የሁለቱንም መስቀለኛ ጥያቄዎች የመለሰው በአስገራሚ መረጋጋ
ነበር፡፡ ጠበቃው ማቲውስ ደንበኛውን ነፃ እንደሚያወጣው እርግጠኛ ነበር፡፡

ጡረተኛው ዳኛ የእለቱን የፍርድ ውሎ መላልሰው እያሰቡ አልጋቸው ላይ
ተቀምጠዋል፡፡ የእጅ ሰአታቸውን ፈትተው ከትራስጌ መብራታቸው አጠገ
አስቀመጡ፡፡ በመቀጠል ሰው ሰራሽ ጥርሳቸውን አውልቀው የውሃ
ብርጭቆው ውስጥ አስቀመጡት፡፡ ጉንጫቸው ወደ ውስጥ ሰምጦ አስፈሪ
ገፅታ ሰጣቸው፡፡

በሃሳባቸው ተመልሰው የአቃቤ-ህጉንና ጠበቃውን ክርክር መላልሰው
አስታወሱት፡፡ በተለይ የጠበቃው ማቲውስ የመዝጊያ ንግግር የፍርድ
ውሳኔው ምን ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም ነበር፡፡

ዳኛው በጀርባቸው ጋደም በማለት የሴተንን ጉዳይ እንዴት ባልተጠበቀ
መስመር እንዳዞሩት በማስታወስ ፈገግ ብለው ወደ እንቅልፍ አለማቸው
ገቡ፡፡

• • •

ምድር ቤት በሚገኘው የእንግዶች ማረፊያ ክፍል ውስጥ አስተናጋጁ
ሮጀርስ ግራ ተጋብቶ ቆሟል፡፡ የምግብ ጠረጴዛው ላይ በመስታወት ሰሃን
ላይ የተደረደሩትን የቻይና አሻንጉሊቶች በአግራሞት አፍጥጦ እየተመለከተ
ነበር፡፡ "በጣም ይገርማል! ቅድም አስር እንደነበሩ እርግጠኛ ነኝ" በማለት
ለራሱ ተናገረ፡፡

• • •



t.me/OLDBOOKSPDF

ጀነራል ማካርተር አልጋው ውስጥ ይገላበጣል፡፡ ከጭለማው ውስጥ የሚታየው የወጣቱ ወታደር አርተር ሪችሞንድ ፊት ቁልቁል እየተመለከተው መሰለው፡፡

ጀነራሉ ወጣቱን ወታደር ይወደው ነበር፡፡ በይበልጥ ደግሞ ለሌሎች ግድ የሌላት ወጣት ሚስቱ ሌስሊ ስለወደደችው ነበር የወደደው፡፡ የጀነራሉንም ሚስት ከወጣቱ ሪችሞንድ ጋር የበለጠ ተቀራረበች፡፡ ጀነራሉም በመጀመሪያ መቀራረባቸውን በተለየ መንገድ አልተመለከተውም ነበር፡፡ ሚስቱ ለወጣቱ ያላት አመለካከት ከእናታዊ ፍቅር የመነጨ ነበር የመሰለው፡፡ ጀነራሉ ልብ ያላለው ግን ሪችሞንድ የሃያ ስምንት አመት ወጣት ሲሆን ሚስቱ ሌስሊ ደግሞ ሃያ ዘጠኝ አመቷ እንደነበር ነው፡፡

ሪችሞንድ የጀነራሉን ሚስት አፈቀራት፡፡ የልብ ቅርፅ ያለው ፊቷ ፤ የማያርፉ ሰማያዊ አይኖቿ እንዲሁም ወርቃማ ፀጉሯ በፍቅር አንበረከኩት፡፡ ሌስሊን ማፍቀር ብቻ ሳይሆን አመናትም፡፡ ከጀነራሉ ጋር ወደ ፈረንሳይ በዘመቱበት ወቅት ፎቶ ግራፏን ደረት ኪሱ ውስጥ ይዞ ነበር የሚንቀሳቀሰው፡፡

ሌስሊ ዘመቻ ለሚገኙት ባሏ እና ውሽማዋ በተደጋጋሚ ነበር ደብዳቤ የምትፅፈው፡፡ ከበርካታ ደብዳቤዎቿ በኋላ ግን ተሳሳተች፡፡ ለፍቅረኛዋ የፃፈችውን ደብዳቤ በባሏ ፖስታ ውስጥ አሽጋ ላከችለት፡፡ ጀነራሉም የሚስቱን የተሳሳተ ደብዳቤ እንዳነበበ ውስጡ ተሰበረ፡፡ በጣም ተጐዳ፡፡ እንደ ልጁ ያመነው ሪችሞንድ ሚስቱን እንደሚያማግጥበት አልጠረጠረም ነበርና የበለጠ ተጐዳ፡፡

የጀነራሉ ጥላቻ የበለጠ አድርጐ ራሱን ለበቀል እንዲያዘጋጅ አበረታታው፡፡ ጀነራሉም ምስጢሩን አፍኖ በመያዝ ወጣቱን የሚበቀልበትን



t.me/OLDBOOKSPDF

አጋጣሚ መጠበቅ ጀመረ፡፡ በመጨረሻም አጋጣሚው ተገኘ፡፡ አጋጣ ከርሱ ለቅኝት ግዳጅ ላከው፡፡ የጀነራሉን ትዕዛዝ የተጠራጠረው ወጣቱ በወቅቱ በሌ ውስጥ የነበረው ሌላው ወጣት አርሚታጅ ነበር፡፡

የሌስሊ ፍቅረኛ በጀነራሉ ባለቤቷ ትዕዛዝ መሰረት ወደ ግዳጅ ለመሔደ ሲነሳ የተመለከተው አርሚታጅ ወጣቱ ሪችሞንድ በተአምር ካልሆ በስተቀር ከነህይወቱ እንደማይመለስ ያውቅ ነበር፡፡

ወጣቱን ሪችሞንድ ጀነራሉ ሆን ብሎ ነበር ወደ ሞት የላከው፡፡ ድርጊቱ አልፀፀተውም ነበር፡፡ የወጣቱ ሞት ምንም አይነት ጥርጣሬ አልፈጠረም፡፡ በወታደራዊ ዘመቻ ወቅት ግዳጅ የተላከ ወታደር ሊሞት እንደሚችል ሁሉም ይገምታል፡፡ ምናልባት የሚጠራጠር ቢገኝ ሌላው ወጣት ወታደር አርሚታጅ ብቻ ነበር፡፡

ጦርነቱ ተጠናቅቆ ጀነራሉ ወደ እንግሊዝ ሲመለስ ነበር ሌስሊ የፍቅረኛዋን መሞት ያወቀችው፡፡ ጀነራሉም ለሚስቱ ስለ ደብዳቤ ሳይነግራት በዝምታ መኖራቸውን ቀጠሉ፡፡ ነገር ግን ሚስቱ እንደቀድሞው ደስተኛ አልነበረችም፡፡ ከአራት አመታት በኋላ በሳምባ ምች ተሰቃይታ ሞተች፡፡

ጀነራሉም ከሰራዊቱ በጡረታ ተሰናብቶ መኖሪያውን በመቀየር ዴቮን ከተመ፡፡ ከቀድሞ ወዳጆቹ ተለይቶ ምስጢሩን እና ማንነቱን ከማያውቁ እንግዶች ጋር ኑሮውን ቀጠለ፡፡

ከአስራ አምስት አመታት በኋላ የሚስቱም ሆነ የፍቅረኛዋ ሪችሞንድ ምስል ከአእምሮው ቀስ በቀስ መጥፋት ጀምሮ ነበር፡፡ ከአርሚታጅ በቀር ሚስጢሩን የሚያውቅ ሰው እንደማይኖር ነበር ጀነራል ማካርተር



t.me/OLDBOOKSPDF

የተሰማው፡፡ የዛሬ ምሽቱ ድምፅ ነበር ከአመታት በፊት የተቀበረ ምስጢሩን ያወጣበት፡፡

የክሱን እውነተኛነት በተመለከተ አብረውት የነበሩ በሙሉ እንደማያምኑ ይሰማዋል፡፡ በይበልጥ ደግሞ ምንም ከፋት የማያውቁት ወ/ሮ ኤሚሊ በግድያ መከሰሳቸው የበለጠ ተአማኒነቱን ቀንሶታል፡፡ የክሱን ተአማኒነት በአንድ በኩል በመተው ደሴቷን በመልቀቅ ወደ ቤቱ ተመልሶ ብቸኛ ህይወቱን እንደማይቀጥል ተሰማው፡፡

ባህር አቋርጦ አንዴ ደሴት ላይ ከወጣ የማምለጥም ሆነ የመመለስ እድሉ ጠባብ እንደሆነ ጀነራሉ አውቆታል፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ከደሴቷ አምልጦ መመለስ እንደማይፈልግ ተሰማው፡፡

• • •

ቬራ ከሌይትሮን ኮርኒሱ ላይ አፍጥጣለች፡፡ ምንም አይነት እንቅልፍ እንደማይወስዳት ከወዲሁ አውቃዋለች፡፡ ጨለማው ስላስፈራትም መብራቱን እንደበራ ተወችው፡፡

"ሁጎ ... ሁጎ .... ለምንድን ነው አጠገቤ ያለህ ያህል የሚሰማኝ?" በማለት አሰበች፡፡ ለመሆኑ የት ይሆን ያለው? ፈፅሞ ያለበትን አታውቅም፡፡ ማወቅም አትፈልግም፡፡ ከህይወቷ ወጥቶላታል፡፡

ሁጎን ላለማስታወስ ከራሷ ጋር ታገለች፡፡ ነገር ግን ወዲያውኑ ሌላ ምስሎች ተመላለሱባት፡፡ ኮርኔል .... ጥቁር አለት ፣ ወርቃማ የባህር ዳር አሸዋ ፣ ወ/ሮ ሃሚልተን እንዲሁም ህፃኑ ሳይሪል እጇን ሲጉትታት ...

"ወደ ውጪ ነው መዋኘት የምፈልገው ቬራ ... ወደ ውጪ ፣ ወደ ድንጋዩ መዋኘት እፈልጋለሁ" ህፃኑ ሳይሪል ቀና ብሎ ሁጎን ተመለከተው፡፡ ሁጎ ደግሞ ቬራን እያየ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይሪልን ካስተኛት በኋላ ዘወትር ምሽት ሁሉ ወደ ክፍሏ በመምጣት "ሽርሽር መውጣት ትፈልጊያለሽ?" በማለት ይጠይቃታል፡፡ በለስላሳው የባህር ዳርቻ አሸዋ ላይ የአትላንቲክ ውቅያኖስ ሞቃት አየር እየላሰ በጨረቃ ይንሸራሸሩ ነበር

"አፈቅርሻለሁ! እንደማፈቅርሽ ታውቂያለሽ አይደል?" የምታውቀው ይመስላታል፡፡

"እንድታገቢኝ አልጠይቅሽም፡፡ ቢሳቢስቲን የሌለኝ ደሃ ነኝ፡፡ ለሶስት ወራት ያህል ብቻ ሃብታም የመሆን ህልም ነበረኝ፡፡ ሳይሪል የተወለደው ሞሪስ ከሞተች ከሶስት ወራት በኋላ ነበር፡፡ እሱ ሴት ልጅ ቢሆን ኖሮ...!" ልጁ ሴት ቢሆንለት ኖሮ በርግጥም ሁጐ ብዙ ነገር ማድረግ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ወንድ ሆኖ መወለዱ ተስፋ አስቆራጭ ነበር የሆነበት፡፡

"ልቀይር የምችለው አይደለም፡፡ እድሌ ነው፡፡ ሳይሪል ጥሩ ልጅ ነው፡፡ እያደር ደግሞ ወደድኩት" አላት፡፡ በርግጥ ሳይሪል ጠንካራ አልነበረም፡፡ የሚያድግ አይነት ልጅ አለመሆኑን መገመት ቀላል ነበር፡፡

"ቬራ ወደ ዳር መውጣት እፈልጋለሁ፡፡ ወደ ድንጋዩ ልዋኝ?" የህፃኑ ተደጋጋሚ ጥያቄ አድካሚ ነበር፡፡

"ወደ ድንጋዩ አትዋኝም፡፡ ጥልቅ ነው" በማለት ከለከለችው፡፡

"ግን እኮ ቬራ ...."

የሳይሪል ምስል እየተመላለሰ እንቅልፍ ነሳት፡፡ ከአልጋዋ ተነስታ አስፕሪን ለመዋጥ ወደ መደርደሪያው አመራች፡፡ የእንቅልፍ ኪኒን ቢኖር በርከት አድርጋ እንደምትውጥ አሰበችና ወዲያውኑ የወጣቱ ማሪስተን አስከሬን ፊቷ ላይ ድቅን ሲል ቀፈፋት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

አስፕሪኗን ውጣ ከመተኛቷ በፊት ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የህፃናት የተረት ግጥም ቆማ ማንበብ ጀመረች

'አስር የህንድ ልጆች ለራት ተጠሩ ፤
አንዱ ታፍኖ ሲሞት ዘጠኙ ቀሩ

መሞት የሚባል ነገር አስፈራት፡፡ እንደማርስተን ያለ ወጣት መሞት እንደማይገባው ስታስብ ደግሞ የበለጠ ፈራች፡፡ መሞት አትፈልግም፡፡ሞት ለእርሷ ሳይሆን ለሌሎቹ ብቻ እንደሆን አሰበች፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

ዶ/ር አርመስትሮንግ በማይጨበጥ ህልም እና ቅዠት መካከል ሆኖ አልጋው ላይ ይገላበጣል፡፡ በኦፕራሲዮን ክፍል ውስጥ የቀዶ ጥገና ምላጭ ይዞ የቆመ ይመስለዋል፡፡ አንዲት ሴት የቀዶ ጥገናው አልጋ ላይ ተኝታለች፡፡ ፊቷ በጨርቅ ስለተሸፈነ ማንነቷን ማወቅ አልቻለም፡፡ ከአልጋው ጐን የቆመችውን የበሽተኛዋን እህት ሊጠይቃት አስቦ ተወው፡፡

የቀዶ ጥገና ክፍሉ ከፍተኛ ሙቀት ስለነበረው ፊቱ በላብ ተሸፍኖ ነበር፡፡ ነርሷ የበሽተኛዋን ፊት ስትገልጠው የተኛችው ሴት ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት እንደሆኑ አይቶ በአግራሞት ዞር ብሎ ሲመለስ ደግሞ የተኛው ሰው አንቶኒ ማሪስተን ሆነበት፡፡ በአስፈሪው ቅዠት ውስጥ ሆኖ አልጋው ላይ ሲገላበጥ ቆየ፡፡

"ዶ/ር- ዶ/ር" በማለት የሆነ ሰው ቀሰቀሰው፡፡ ከአልጋው ላይ ተስፈንጥሮ በመነሳት ዙሪያውን ቃኘ፡፡ አገልጋዩ ሮጀርስ ነበር ከአስጨናቂው ቅዠት የገላገለው፡፡ አይኖቹን ጠራርጐ በደንብ አየው፡፡

"ምን ሆነሃል?"

"ዶ/ር- ሚስቴ ከእንቅልፏ አልነቃችም" በማለት ሮጀርስ እየተንቀጠቀጠ ነገረው፡፡ ዶ/ር አርመስትሮንግ በፍጥነት የሌሊት ልብሱን ደርቦ ወደ ሮጀርስ መኝታ ክፍል ሮጠ፡፡

ሚስትየዋ አልጋው ላይ ቀጥ ብላ ተኝታለች፡፡ በሰላማዊ እንቅልፍ ውስጥ ያለች ህፃን ነበር የምትመስለው፡፡ ዶ/ር አርመስትሮንግ አንገቷን ጫን ብሎ ተመለከተ፡፡ ምንም ትንፋሽ የላትም፡፡ አጠገቡ የቆመውን ሮጀርስ በጐን ተመለከተው፡፡ ሮጀርስ እየተንቀጠቀጠ "ምንድን ነው ዶ/ር?" በማለት በፍርሃት ጠየቀው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዘግይተናል ሮጀርስ፡፡ አርፋለች"

"ልቧ ጤነኛ ነበር? ምን ሆና ነው?" ባልየው እየተንተባተበ ጠየቀው፡፡

ዶ/ሩም ከአፍታ በኋላ "በደህናው ቀን የአተነፋፈስ ችግር ነበረባት?" በማለት መልሶ ጠየቀው፡፡

"የመገጣጠሚያ ህመም እንጂ ሌላ በሽታ አታውቅም"

"ሃኪም ጋር ወስደሃት ታውቃለህ?"

"በፍፁም፡፡"

"የእንቅልፍ ችግርስ?"

"አንዳንዴ እንቅልፍ እምቢ ይላት ነበር"

"የእንቅልፍ ኪኒን ወስዳ ታውቃለች?"

"እኔ እስከማውቀው ድረስ ወስዳ አታውቅም" የባልየውን መልስ እንደሰማ ዶ/ር አርመስትሮንግ የመልበሻ ጠረጴዛውን መሳቢያ በመክፈት የተደረደሩትን ቅባቶች ፣ ሽቶ እና የጥርስ ብሩሽ ተመለከተ፡፡ ምንም አይነት የእንቅልፍ ኪኒን አልነበረም፡፡

"ዶ/ር አንተ ከሰጠሃት ኪኒን ውጪ ምንም አይነት ነገር አልዋጠችም...." በማለት ሮጀርስ እየተንቀጠቀጠ ለዶ/ሩ ነገረው፡፡

• • •

ከማለዳው ሶስት ሰአት ላይ የቁርሱን መድረስ የሚያሳየው የሰሃን ደወል ሲሰማ ሁሉም ከእንቅልፋቸው ተነስተው ነበር፡፡ ጀነራል ማካርተር እና ጡረተኛው ዳኛ በረንዳው ላይ ተቀምጠው ስለ አንዳንድ የፖለቲካ ጉዳዮች ያወጉ ነበር፡፡

ቬራ እና ሎምባርድ ከቤቱ ጀርባ ቆመው እየተጫወቱ ሳለ ብሎር ባህሩን ቆሞ ሲመለከት አገኙት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከጠዋት ጀምሮ ስመለከት ነበር፡፡ ምንም አይነት ጀልባ አላየሁም" አላቸው፡፡

ቬራ ፈገግ ብላ "የዲቮን ነዋሪዎች በጠዋት አይነሱም፡፡ ሁሉንም ነገር የሚከውኑት አርፍርደው ነው" አለችው፡፡

ሎምባርድ ዙሪያውን ቃኘና "ለመሆኑ አየሩ ጤናማ ሆኖ የሚውል ይመስልሃል?" በማለት ጠየቀው፡፡

"ይመስለኛል"

"አውሎ ንፋሱ መመለሱ አይቀርም"

"ለምን ታሟርታለህ?" በማለት ብሎር ገላመጠው፡፡ ሎምባርድ መልስ ሳይሰጠው የቁርሱ ደወል ተሰማቸው፡፡

"ቁርስ ብንቀምስስ?" በማለት ሎምባርድ ሁለቱን አስከትሎ ደረጃውን ወረደ፡፡ "ወጣቱ ራሱን መግደሉ ሊዋጥልኝ አልቻለም፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ሳስበው ነበር" በማለት ብሎር መልሶ በጥያቄ አስተያየት ሁለቱንም ተመለከታቸው

"ሌላ መላ -ምት አገኘህ ታዲያ?" በማለት ሎምባርድ ጠየቀው

"የተወሰነ መረጃ ያስፈልገኛል፡፡ እስከዚያው ግን ራሱን ገደለ በሚለው መቀጠሉን እመርጣለሁ" ሲል መለሰለት፡፡

የእንግዳ ማረፊያው በር አጠገብ ሲደርሱ ከወ/ሮ ኤሚሊ ጋር ተገጣጠሙ፡፡ ወይዘሮዋም ከሰላምታቸው አስቀድመው ነበር "ጀልባው መጥቷል?" ሲሉ የጠየቋቸው፡ "ገና አልመጣም" በማለት ቬራ መለሰችላቸው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የምግብ ጠረጴዛው ላይ ትኩስ የእንቁላል ጥብስ ፣ አይብ ፣ ሻይ እና ቡና ቀርቧል፡፡ ሮጀርስ የእንግዶቹን ቦታ መያዝ ተመልክቶ በሩን ከኋላው ዘግቶ ሄደ፡፡

"ይሄ ሰው የታመመ ይመስላል" አሉ ወ/ሮ ኤሚሊ፡፡

"ብቻውን ነው ቁርስ ያዘጋጀልን፡፡ የጐደለ ነገር ካለ እንዳታዝኑበት" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ መለሰላቸው፡፡

"ሚስቱ እንዴት አደረች?"

"አሁን እንቁላሉ ሳይቀዘቀዝ እንብላ፡፡ ከቁርስ በኋላ የምንነጋገርበት ጉዳይ አለኝ" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ፍንጭ ሰጣቸው፡፡ እነርሱም ቁርስ መብላታቸውን ቀጠሉ፡፡

በቁርስ ላይ አንዳቸውም ስለምሽቱ አስደንጋጭ ክስተት ለማውራት አልፈለጉም ወይም አልደፈሩም ነበር፡፡ ስለ ፖለቲካ ፣ ፋሽን ፣ ስፖርት እና ከበርቴ እንግሊዛውያን እያወሩ ቁርሳቸውን ተመግበው አበቁ፡፡ ገበታው ከፍ እንዳለ ነበር ዶ/ሩ መናገር የጀመረው፡፡

"ቁርስ እስኪበላ ያቆየሁት አንድ መጥፎ ዜና አለ፡፡ ወ/ሮ ሮጀርስ በእንቅልፍ ላይ ሳለች ሞታለች፡፡"

ቬራ አፏን ይዛ "በአንድ ምሽት ሁለት ሞት?" በማለት ጮኸች፡፡

ዳኛውም በእርምሞ ዶ/ሩን በመመልከት "ለመሆኑ የሞቷ ምክንያት ምንድን ነው?" በማለት ጠየቁት

"ለመናገር ይከብዳል" ሲል መለሰላቸው፡፡

"መቼም ምርመራ ሳታደርግ አልቀረህም"

"ልክ ነው፡፡ ነገር ግን ማረጋገጫ ለመስጠት የሴትየዋን የጤና ሁኔታ ማወቅ ይኖርብኛል፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

ቬራ ዶ/ሩን አቋርጣ "መጀመሪያ ስመለከታት የተደናገጠች ትመስል ነበር፡፡ ምናልባት የልብ ምቷ ተቋርጦ ይሆናል የሞተችው" በማለት ገመተች፡፡

ዶ/ሩም "የልብ ምቷ ተቋርጦ እንደሞተችማ እናውቃለን፡፡ ጥያቄው የልብ ምቷን ምን አቋረጠው የሚለው ነው" በማለት አሽሞረ፡፡

"ልቦናዋ " የሚለው አንድ ቃል በድንገት ከወ/ሮ ኤሚሊ አፍ ሲወጣ ሁሉም እሳቸው ላይ አፈጠጡ፡፡

"ምን ማለትዎ ነው ወ/ሮ ኤሚሊ?"

"ከባሏ ጋር ሆና አሰሪዋን እንደገደለች ሁላችሁም ሰምታችሁ የለ እንዴ?" መልሰው አፈጠጡ፡፡

"እናስ?"

"እንደሚመስለኝ የቀረበባቸው ክስ ትክክለኛ ነው፡፡ በወቅቱ አቅሏን እንደሳተችም ተመልክታችኋል፡፡ ስለዚህ ሴትየዋን የገደላት ፍራቻ ነው" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ አስረግጠው ተናገሩ፡፡

"ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባት ሴትየዋ ቀድሞውንም የልብ ህመምተኛ ከነበረች " በማለት ዶ/ሩ ማስረዳት ሲጀምር ወ/ሮ ኤሚሊ በማልጉምጉም አቋረጡት፡፡

"አንተ ምንም ልትለው ትችላለህ፡፡ ይሄ ግን የፈጣሪ ድርጊት ነው" ሲሉ ሁሉም አፈጠጡባቸው፡፡

"ወ/ሮ ኤሚሊ ነገሩን በጣም አካበዱት"

ወ/ሮዋም ሌሎቹን በፈገግታ ገርመም አድርገው "ፈጣሪ ሃጥአንን ይቀጣል፡፡ ለእናንተ ባይመስልም ቅሉ እኔ ግን በዚህ እምናለሁ፡፡" በማለት ተናገሩ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ጸኛ ዋርግሬቭ ፒግቻቸውን ዳበስ አድርገው በትህትና መናገር ጀመሩ፡፡ "ውድ እመቤቴ በዘመኔ እንደተመለከትኩት ፈጣሪ ሃቀኛን ለመቅጣት ወርዶ አያውቅም፡፡ ፍርዱንም ሆነ ቅጣቱን የሚያስተላልፈው በሰው በኩል ነው፡፡"

ወ/ሮዋ ለመቀበል አለመፈለጋቸውን ትከሻቸውን በመስበቅ መለሱላቸው፡፡

ብሎር በፍጥነት ለዶክተሩ ጥያቄ አቀረበለት፡- "ለመሆኑ ከተኛች በኋላ የበላችው ወይም የጠጣችው ነገር ነበር?"

"ምንም አልቀመሰችም፡፡" ሲል ዶ/ር አርመስትሮንግ መለሰ፡፡

"ውሃም ሆነ ሻይ?" መልሶ ጠየቀው

"ባለቤቷ ምንም አለመቅመሷን ነግሮኛል" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ አረጋገጠለት

"እህ እንደ'ዛ እንደሚልማ ግልፅ ነው" በማለት ብሎር ዶ/ሩ ያቀረበውን የባልየውን ማረጋገጫ አጣጣለው፡፡ ዶ/ሩ በጥያቄ አይናቹ አየው፡፡

ፊሊፕ ሎምባርድ "ሚስቱን ገድሏታል ብለህ ነው የምታስበው?" በማለት ብሎርን ጠየቀው፡፡

"ሊሆን ይችላል፡፡ የቀረበባቸውን ክስ ሰምታችኋል፡፡ ሁላችንም የሰማነውን ድምፅ ላለማመን እየጣርን ነው" ነገር ግን እውነት ቢሆንስ በማለት አስቡት እስኪ፡፡ ሮጀርስ ሚስቱን ከመግደል ውጪ ምን አማራጭ አለው?" በማለት ብሎር ገምቱን አስቀድሞ ጠየቃቸው፡፡ ከቤቱ መልስ ሲያጣ ገለፃውን ቀጠለ፡፡ "እስከ ትናንት ማታ ድረስ ባልና ሚስቱ በነፃነት ይኖሩ ነበር ፍፁም ተረጋግተው"

ቬራ ነበረች ብሎርን ያቋረጠችው "አይመስለኝም፡፡ ጊዷ ወ/ሮ ሮጀርስ ነፃነት የሚሰማት አትመስልም ነበር፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎርን ንግግሩን ስላቋረጠችው ገላመጣት፡፡"ሊሆን ይችላል፡፡ ሌጋታ ከርስቲ አደጋ ውስጥ መውደቃቸውን የሰማነው ድምፅ አረጋግጠላቸዋል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ሴትየዋ በድንጋጤ አቅሏን ስታ ነበር፡፡ ባልየውም ደካማ ሚስቱ ወንጀላቸውን አሳልፋ እንደምትሰጥበት ስለሚያውቅ ፍርሃት ውስጥ ወደቀ፡፡ በሚስቱም መተማመን አልቻለም"

"አንተ የምታስበው እንደ'ዛ ነው? ባልና ሚስቱ አሰሪያቸውን ገድለው ማምለጣቸውን እኛ ብናውቅ ምን ይፈጠርባቸዋል?"

"እሃ ሚስትየዋ ስታስበው ጨዋታው አንድ ለ እስር ሆኗል፡፡ ሁኔታው አስፈራት፡፡ ባሏም የሚስቱን መደናበር ተመለከተ፡፡ ሚስቱም ለህይወታቸው አደጋ መሆኗን በማረጋገጡ ሊያስወግዳት ወሰነ፡፡ ከዚያም ኩባያዋ ውስጥ የሆነ ነገር ጨምሮ ጋታት እና አፏን እስከወዲያኛው ዘጋው፡፡" በማለት ብሎር መላ-ምቱን ዘረዘረላቸው፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ በዝግታ መለሰለት "አልጋዋ አጠገብ ምንም አይነት ኩባያ አልነበረም፡፡ ዙሪያውንም ቢሆንም ተመልክቼ ነበር"

"አልጋዋ አጠገብማ እንዴት መረጃ ያስቀምጣል? ካጠጣት በኋላ ኩባያውን ያጠፋዋል" በማለት ብሎር መልሶ ተከራከረ፡፡ በዚህ መሃል ጀነራል ማካርተር ጣልቃ በመግባት ጥርጣሬውን ገለፀ፡፡

"ግምትህ ትክክል ሊሆን ቢችልም አንድ ባል በሚስቱ ላይ እንደዚህ አይነት ርምጃ ሊወስድ አይችልም" በማለት ጀነራሉ ሊከራከር ሲሞክር ብሎር የለበጣ ሳቁን አስቀድሞ፡-

"ወንድ ልጅ አደጋ ላይ ሲወድቅ ስለ ስሜታዊ ፍቅር ማሰብ ያቆማል" በማለት መለሰለት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በመካከላቸው አስፈሪ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ በዚያ መሃል ሮጀርስ በሩን ከፍቶ ገባና "የጐደላችሁ ነገር ይኖራል ክቡራን?" በማለት በጠረጴዛው ዙሪያ ያሉትን እንግዶች በትህትና በመመልከት "ትኩስ ዳቦ ስላልደረሰልኝ ነው ያደረ ያቀረብኩላችሁ" በማለት ዳቦ በጠዋት አለመድረሱን አሳወቃቸው፡፡

ዳኛው ወንበራቸው ላይ እየተመቻቹ ሮጀርስን ወደ ላይ ተመለከቱና "ሌላ ግዜ ጀልባው እዚህ የሚደርሰው በስንት ሰአት ነበር ፤ ሮጀርስ?" ሲሉ ጠየቁት

"ከአንድ እስከ ሁለት ሰአት ይደርስ ነበር" ባለጀልባው ፍሬድ ናርኮት ዛሬ ምን እንዳጋጠመው አላውቅም፡፡ ለወትሮው እርሱ እንኳን ቢያመው ወንድሙን ይልክልን ነበር፡፡" በማለት መለሰላቸው፡፡

"አሁን ስንት ሰአት ነው?" በማለት ሎምባርድ ጠየቀ

"ለአራት አስር ጉዳይ ሆኗል ጌታዬ"

ሎምባርድ ቅንድቡን ወደ ላይ ከፍ አድርጐ ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምፅ አጉተመተመ፡፡ ሮጀርስ ለአንድ ደቂቃ ያህል ቆሞ ተጨማሪ ጥያቄ ተጠባበቀ፡፡

ጀነራል ማካርተር በድንገት ፀጥታውን በመስበር "በሚስትህ ሞት በጣም አዝነናል ሮጀርስ፡፡ አሁን ነው ዶ/ር የነገረን" በማለት አስተዛዝኖ ተናገረ፡፡

"አመሰግናለሁ ጌታዬ" በማለት መለሰለት፡፡ በመቀጠልም የቁርስ ሰሃንና የሻይ ብርጭቆዎቹን አነሳስቶ ክፍሉን ለቅቆ ወጣ፡፡ በሌሎቹ መካከልም አስፈሪው ፀጥታ ተመለሰ፡፡

* * *

ፊሊፕ ሎምባርድ ከብሎር ጋር በረንዳው ላይ ቆሞ ነበር፡፡"የጀልባው ነገር " በማለት መናገር ሲጀምር ብሎር አቋርጦት፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን እያሰብክ እንደሆነ አውቃለሁ አቶ ፌሊፐ፡፡ እኔም እንዳንተ ሳስብ ነበር፡፡ ጀልባው ከሁለት ሰአታት በፊት መምጣት ነበረበት፡፡ ለምን አልመጣም?"

"ታዲያ መልሱን አገኘኸው?" በማለት ሎምባርድ መልሰ ጠየቀው፡፡

"ይሄ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአጠቃላይ ሴራው አካል ነው፡፡" በማለት መለሰለት፡፡

"ስለዚህ አይመጣም ብለህ ታስባለህ?" የሚል አዲስ ድምፅ ከኋላቸው ሰምተው ሁለቱም ዞሩ፡፡

"አይመስልህም ጀነራል?" በማለት ፊቱን አኮማትሮ የቆመውን ጀነራል ብሎር ጠየቀው፡፡

"ጀልባው እንደማይመጣማ አውቃለሁ፡፡ የሴራው አንድ አካል እኮ ነው፡፡ ማናችንም ከዚህች ደሴት ላይ እንዳናመልጥ የታቀደ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ መጨረሻችንም እዚሁ ይሆናል ...." በማለት ጀነራሉ ትንሽ ቆም አድርጐ እያቅማማ መናገሩን ቀጠለ፡፡ በተለየ ድምፅ "ሰላም ነው ታላቅ ግልግል፡፡ ማምለጥ ሳትችል መጨረሻህን መጠበቅ .... አዎ - ግልግል ነው..."

ጀነራሉ ከበረንዳው ወርዶ ወደ ባህሩ ዳርቻ ሲራመድ ቁልቁል ተመለከቱት፡፡ የጀነራሉ እግሮች እርስ በርሳቸው እየተጋጩ ሲራመድ ሲመለከቱት በእንቅልፍ ልቡ ያለ ይመስል ነበር፡፡

"ምስኪን ሽማግሌ፡፡ በቀላሉ የሚጠናቀቅ መስሎታል" በማለት ብሎር ወደ ባህሩ ዳርቻ የተቃረበውን የጀነራል ማካርተር ምስል በሃዘኔታ ተመለከተ፡፡

"አንተ እንደ'ሱ የምታስብ አይመስለኝም" በማለት ለዘብ ያለ አስተያየቱን አቀረበለት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የቀድሞው ወንጀል መርማሪ ብሎር ፈገግ ብሎ "በቀላሉ እጅ የሚሰጥ ልብ የለኝም፡፡ አንተም ብትሆን እንደ'ኔ ትመስለኛለህ" በማለት መለሰለት፡፡

"ለደቂቃም ቢሆን አረጋግተኸኛል ፤ አመሰግናለሁ" በማለት ሎምባርድ በፈገግታ አፀፋውን መለሰ፡፡

• • •

ዶ/ር አርመስትሮንግ ወደ በረንዳው ወጣ፡፡ በግራ በኩል ብሎር እና ሎምባርድ ወሬ ይዘዋል፡፡ በቀኝ በኩል ደግሞ ሽማግሌው ዳኛ ብቻቸውን ቆመው ተመለከተ፡፡ ወደ ሽማግሌው ለመሔድ ወስኖ ከመንቀሳቀሱ በፊት ግን አገልጋዩ ሮጀርስ እየተጣደፈ ከኋላው ጠራው፡፡

ከደቂቃዎች በፊት ጤነኛ የነበረው አስተናጋጅ ፊቱ ኩበት መስሎ እየተንቀጠቀጠ ነበር፡፡ ዶ/ር አርመስትሮንግ በተመለከተው ሮጀርስ ድንጋጤ ተደናበረ፡፡

"አንድ ግዜ ላናግርህ ፤ ጌታዬ ለብቻህ?" እየተንቀጠቀጠ ነበር አገልጋዩ የሚናገረው፡፡

"ምን ሆነሃል ፤ ሮጀርስ?"

"ወደ ውስጥ እንግባ ፤ ዶ/ር ወደ ውስጥ " በማለት እየተርበተበ ዶ/ሩን አስቀድሞ ወደ እልፍኙ ገባ፡፡

የምግብ ጠረጴዛው አጠገብ እንደደረሱ ዶ/ሩ እየተጣደፈ ጠየቀው፡፡ "ምንድን ነው የሆንከው?"

የሮጀርስ ወፋፍራም የደም ስሮች አንገቱ ላይ ተጋድመው ይታያሉ፡፡ እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ለመናገር ሲሞክርም ምላሱ እየደረቀበት ምራቁን ደጋግሞ ለመዋጥ ይሞክራል፡፡

"ጌታዬ አንድ ግልፅ ያልሆነ ነገር አለ፡፡"


t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንድን ነው? ለምን ተረጋግተህ አትነግረኝም?"

በድጋሚ ምራቁን ዋጠና መናገር ጀመረ

"ጌታዬ እዚህ ሰሃት ላይ የነበሩት አሻንጉሊቶች ትናንት ማታ አስር ነበሩ፡፡ በፈጣሪ ስም እምላለሁ አስር ነበሩ፡፡"

"አዎን፡፡ አስር እንደነበሩ ራት እየበላን ሁላችንም አይተናል"

"አየህ ዶ/ር ችግሩ ይሄ ነው፡፡ ትናንት ማታ ጠረጴዛውን ሳፀዳ የነበሩት ዘጠኝ ናቸው፡፡ እኔም ብዙ ሳልገረም ነበር ያለፍኩት፡፡ አሁን ግን ተመልከት ጌታዬ! ቁርስ ሰአት ላይ ልብ አላልኩም ነበር፡፡ ካላመንከኝ ራስህ ተመልከት፡፡ አሁን ያሉት ስምንት ብቻ ናቸው፡፡ ስምንት! ይሄ በጣም ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ስምንት ብቻ!"

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሰባት

ወ/ሮ ኤሚሊ ቬራን ጠርተው ወደ ባህሩ ዳርቻ በመሔድ በዚያውም የጀልባውን መምጣት እንዲመለከቱ ጠየቋት፡፡ ቬራም ወ/ሮዋን ሳለማስቀየም ስትል አብራቸው ሄደች፡፡

ሰፊው ባህር ላይ ምንም አይነት የሞተር ጀልባ አይታይም ነበር፡፡ ንፋስ እየተነሳ መሆኑን የሚያመላክተው ነጭ አረፋ የባህሩ ዳርቻ ላይ መታየት ጀምሮ ነበር፡፡ ከደሴቷ አቅራቢያ የምትገኘው የስቲክል ሃቫን መንደር አትታይም፡፡ ከመንደሯ በላይ የሚገኘው ቀይ ኮረብታ ብቻ ነበር በርቀት የሚታያቸው፡፡

"ባለጀልባው ሰው ታማኝ ይመስል ነበር፡፡ ትናንትና እንዳየሁት ከሆነ የሚያረፍድ አይመስልም ነበር" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ቀዝቀዝ ብለው ተናገሩ፡፡

ቬራ ምን መመለስ እንዳለባት ግራ ተጋባች፡፡ ውስጧ የሚተራመሰውን ፍራቻ ለማረጋጋት እየጣረች ቆየች፡፡ በመጨረሻም ለመረጋጋት በመሞከር "ቶሎ በመጣና ከዚህ ቦታ በወሰደን" በማለት እየተብረከረከች መለሰችላቸው፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ ረጋ ባለ ድምፅ "እሱማ ቢሆን የሁላችንም ምኞት ነበር፡፡" አሉ፡፡

"ሁሉም ነገር የተሳሳተ ነው ያስፈራል" አለች

ወ/ሮዋ በቁጭት ጥርሳቸውን ነክሰው እኔ እንኳን የተናደድኩት በራስ ሞኝነት ነው፡፡ የደረሰኝ ደብዳቤ ግልፅ አልነበረም፡፡ መጠራጠር ነበረብኝ አሉ፡፡

ቬራ "የእኔ እንኳን አጠራጣሪ አልነበረም" በማለት አጉተመተመች፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"በቀላሉ ማመን አልነበረብኝም"

ቬራ ወ/ሮዋን ወደ ጐን ተመለከተቻቸውና "ለመሆኑ ቁርስ ላይ የተናገሩት የምሮትን ነበር?" ስትል ጠየቀቻቸው፡፡

"የትኛውን?"

"ሮጀርስ እና ሚስቱ አሰሪያቸውን እንደገደሉ የቀረበባቸውን ክስ ያምኑበታል?"

ወ/ሮዋ ፈርጠም ብለው "እኔ በግሌ አምናለሁ፡፡ አንቺስ?" በማለት ጠየቋት

"እኔ ምን ማመን እንዳለብኝ እርግጠኛ አይደለሁም"

"መረጃዎችን ስትመለከቺ ግን የእኔ ግምት ትክክል መሆኑን ትረጂያለሽ፡፡ የሚስተየዋ አቅሏን መሳት እና የባልየው ተርበትብቶ ትሪውን መጣል ...፡፡ አዎ በርግጥም የቀረበባቸው ክስ እውነተኛ ነበር" በማለት ወ/ሮዋ በረጅሙ ተነፈሱ፡፡

"ነገር ግን ሚስትየዋ እኮ ከመጀመሪያውም የተሸበረች እና የተደናበረች ነበረች፡፡" በማለት ወ/ሮ ሮጀርስን በመጀመሪያ ስትመለከታት የነበራትን ግምት ነገረቻቸው፡፡

"ሃጢያቷ እያሳደዳት ነበር፡፡" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ምስጢራዊ ፈገግታቸውን አስቀድመው በረጅሙ አየር ሳቡና መናገር ቀጠሉ፡፡ "በህፃንነቴ መዋዕለ - ህፃን ውስጥ ሳለሁ "ሃጢያታችሁ ያሳድዳችኋል፤ በኋላም ይይዛችኋል የሚል ጥቅስ ግድግዳ ላይ መስቀሉ ትዝ ይለኛል፡፡" አሉ፡፡

ቬራ በድንጋጤ እግሮቿ ሲንቀጠቀጡ ተሰማት፡፡ "ግን እኮ ወ/ሮ ኤሚሊ ..." በማለት በረጅሙ ተንፍሳ "ስለሌሎቹስ ምን ያስባሉ? ማለቴ ባለፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስቱ የተከሰሱበት እውነት እንደሆነ ካመኑ የሌሎቻችንስ?" ስትል ጠየቀቻቸው፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ የተሸበሸበ ግንባራቸውን ፈታ አድርገው "ለምሳሌ ሎምባርድ የተባለው ሰው ሃያ አንዱን የጐሳ አባላት ለሞት ጥሏቸው መሔዱን አምኗል" አሉ፡፡

'እነርሱማ ተራ ዜጐች እኮ ናቸው '

'ተይ ልጅ ጥቁርም ሆኑ ነጮች ወንድሞቻችን ናቸው" በማለት ሲመልሱላት 'ጥቁር ወንድሞቻችን' በማለት አሰበችና በድንገት ፍርሃት ወረራት፡፡

ወ/ሮ አሚሊ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡ "የተወሰኑት ክሶች በርግጥ የተሳሳቱ ይመስላሉ፡፡ ለምሳሌ ዳኛው የተጣለበትን ግዴታ በመወጣቱ ነው የተከሰሰው፡፡ ጡረተኛው ወታደር እና እኔም ብንሆን እንዲሁ ...፡፡" በማለት ለአፍታ ያህል ቆም ብለው በተለየ ድምፅ መናገር ጀመሩ፡፡ "ትናንት ማታ ምንም ላለመናገር ፈልጌ ነበር፡፡ በተፈጥሮዬ ከወንድ ጋር መነጋገር አይመቸኝም" አሉ፡፡

"እንዴት?" በማለት ጠየቀቻቸውና በመቀጠል የሚነግሯትን ለመስማት ጓጓች፡፡ ወ/ሮዋም ቃላቶቻቸውን በጥንቃቄ በመምረጥ መናገር ጀመሩ፡፡ "ቤትሪስ ቴይለር አብራኝ በምትሰራበት ወቅት ጥሩ ሴት መስላኝ ነበር፡፡ ንፅህናዋን እና ንግግሯን በመስማት ነበር የተሸወድኩት፡፡ መጥፎ ሴት መሆኗን የተረዳሁት በጣም ዘግይቼ ነበር፡፡ ምንም አይነት ስርአት የማታውቅ ባለጌ ሴት ናት፡፡ ቤተሰቦቿ የተከበሩ በመሆናቸው እንደ'ዚ አይነት ምግባረ-ብልሹ ልጅ እንዴት እንዳሳደጉ ገርሞኝ ነበር፡፡"

"ከዛስ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ያንን መጥፎ ባህርይ ይዛ ለአንዲት ሰአትም አጠገቤ እንድትቆይ አልፈለግሁም ነበር፡፡ በፍፁም አልፈቀድኩም"

"ከዚያስ ምን ሆነች?"

"ያው መጥፎ ሰዎች መጨረሻቸው ይታወቃል ራሷን ገደለች፡፡"

ቬራ በድንጋጤ ተሞልታ "ራሷን ገደለች?" ስትል ጠየቀቻቸው፡፡

"አዎን፡፡ ራሷን ወንዝ ውስጥ ወርውራ ሞተች"

ቬራ የበለጠ እየተርገፈገፈች ጠየቀቻቸው፡፡ "እርስዎስ ምን ተሰማዎት? ማለቴ እርስዎ ባያባርሯት ኖሮ ... ራስዎትን አልወቀሱም?"

"ለምን ራሴን እወቅሳለሁ? አጠገቧ አልደረስኩም"

"ግን እኮ እርስዎ ባያባርሯት..."

ወ/ሮ ኤሚሊ ፈርጠም ብለው "የገዛው ሃጢያቷና ክፋቷ ናቸው ገፋፍተው የገደሏት፡፡ እንደ መልካም ሴት መኖር ብትችል ኖሮ አትሞትም ነበር" በማለት መለሱላት፡፡

ወደ ቬራ ዞረው ተመለከቷት፡፡ የሴትየዋ አይኖች ውስጥ የሚያስፈራ ቅዝቃዜ መኖሩን ተመለከተች፡፡ ባህሩ ዳርቻ ከሚገኘው አግዳሚ ወንበር ላይ ከተቀመጡ በኋላም ቬራ መረጋጋት አልቻለችም ነበር፡፡ ቀድሞ ምስኪን የመሰሏት አሮጊት በድንገት አደገኛ እንደሆኑ ገባት፡፡

• • •

ዶ/ር አርመስትሮንግ ወደ በረንዳው ተመልሶ ወጣ፡፡ ሽማግሌው ዳኛ ቀድሞ የተቀመጡበት ቦታ ሆነው ወደ ባህሩ እየተመለከቱ ሲሆን ብሎር እና ሎምባርድ ደግሞ በተቃራኒው አቅጣጫ ቆመው ቃላት ሳይለዋወጡ ሲጋራ እያጨሱ ነበር፡፡ ከሮጀርስ የደረሰውን ጥቆማ ለማን ማዋየት እንዳለበት አሰበ፡፡ ዳኛ ዋርግሬቭ ብልህ እና አስተዋይ እንደሆኑ ቢያውቅም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታዎች ብልሃተኛን ሳይሆን ለድርጊት ዝግጁ የሆነን ሰው እንዲያስቀድም ገፋፉት፡፡

በመሆኑም በቀጥታ ያመራው ወደ ወጣቶቹ ነበር፡፡ "ሎምባርድ አንድ ግዜ ላናግርህ?" በማለት ጠራውና ከብሎር ነጥሎ ወደ ሜዳው ይዞት ወረደ፡፡ ከበረንዳው ርቀው መሔዳቸውን አረጋገጠና ዶ/ር አርመስትሮንግ በለዘቡ ቃላት "ምክር ብጤ ፈልጌ ነበር" በማለት ጠየቀው፡፡

"የህክምና እውቀት እንደሌለኝ ታውቃለህ" በማለት ሎምባርድ ፈገግ ብሎ መለሰለት፡፡

"ስለ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ የሴትየዋን ሞት በተመለከተ ምን ታስባለህ? የብሎርን መላ- ምት ትቀበለዋለህ?" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ጠየቀው፡፡

ሎምባርድ ሲጋራውን በረጅሙ ስቦ ጭሱን ወደ ውጪ በማስወጣት መለሰለት "እንደ መላ- ምት ከተመለከትነው ታማኝነት ያለው ይመስለኛል፡፡"

"ልክ ብለሃል" በማለት ዶ/ሩ ተስማማ፡፡ ፊሊፕ ሎምባርድ በቀላሉ የሚታለል ሰው አለመሆኑን ተረዳ፡፡

ሎምባርድ ማስረዳቱን ቀጠለ፡፡ "ሮጀርስ እና ሚስቱ ቀጣሪያቸውን በመግደል በቀላሉ ሊያመልጡ እንደሚችሉ ምንም አያጠራጥርም፡፡ ለመሆኑ እመቤታቸውን እንዴት የገደሏት ይመስልሃል? በመርዝ ወይስ....?"

አርመስትሮንግ ተረጋግቶ መመለስ እንዳለበት ገብቶታል፡፡ "ጠዋት ላይ ሮጀርስን ስለ ቀጣሪው የጤንነት ሁኔታ ጠይቄው የሰጠኝ መልስ ጠቋሚ ነበር፡፡ ሰፊ የህክምና ማስረጃ የሚያስፈልገው አልነበረም፡፡ ቀጣሪያቸው ወ/ሮ ብራዲ በመተንፈሻ አካል ህመም ትሰቃይ ነበር፡፡ ህመሟ ሲያገረሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወይም በድንገት ሲያጣድፉት በአቅራቢያዋ የነበሩ ሰዎች እርዳታ ከርሰዋ የኖይትሬት እንክብል በቶሎ ካልሰጧት በቀር መሞቷ አይቀሬ ነው፡፡"

ፊሊፕ ሎምባርድ አሰብ አድርጎ "እንደዚያ በቀላሉ?" በማለት ዶ/ሩን ጠየቀው

"መድሃኒቱን በቶሎ አለመስጠት ብቻ! በቃ ሌላ እርምጃ መውሰድ አይጠበቅባቸውም፡፡ እመቤቲቷ በጠና በታመመችበት ምሽት ሮጀርስ ዶ/ር ለመጥራት ረጅም ግዜ እንደወሰደበት ስታስበው ግልፅ ይሆንልሃል፡፡ ስለዚህ ማንም ሳያውቅባቸው በቀላሉ አስወግደዋታል" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ዘረዘረለት፡፡

"ቢያውቅባቸውም ደግሞ ማረጋገጥ አይቻልም" በማለት ሎምባርድ አከለ፡፡ ዶ/ሩም ከሎምባርድ በተሰነዘረው ማጠናከሪያ ሃሳብ ተገርሞ ተመለከተው፡፡

"ሁኔታው እዚህ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው" በማለት ሎምባርድ ጨምሮ ተናገረ፡፡

"አልገባኝም "

"በዚህቹ ህንድ ደሴት የተሰባሰብነውን ማለቴ ነው፡፡ ህግ ፊት አቅርበህ የማታረጋግጣቸው ወንጀሎች ልክ ሮጀርስ እና ሚስቱ እንዳደረጉት! ለምሳሌ ሽማግሌው ዳኛ ዋርግሬቭ ግድያ የፈፀሙት ህግን በመጠቀም ነው፡፡" በማለት ሎምባርድ ምሳሌ ሰጠ፡፡

"ያንን ታምናለህ?" ዶ/ሩ ጠየቀው

ሎምባርድም ፈገግ ብሎ "በሚገባ እንጂ! ሽማግሌው ዳኛ ኤድዋርድ ሴተንን የገደሉት አስገራሚ የሆነ ብልሃትን ተጠቅመው ነው፡፡ በዳኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው የፈፀሙትን ግድያ በምንም አይነት ለፍርድ ሊያቀርበው አትችልም" በማለት መለሰለት፡፡

ዶ/ሩ የሎምባርድን ንግግር የሰማው በከፊል ድንጋጤ ውስጥ ሆኖ ነበር፡፡ በሃሳቡም 'በሆስፒታል ውስጥ ፤ በኦፕራሲዮን አልጋ ላይ የተፈፀመ ግድያ የተደበቀ እና የማይደረስበት ነው' ሲል ማሰቡ ሞኝነት መሆኑ ገባው፡፡

"ስለዚህ ጋባዣችን አቶ ኦውን እና የህንድ ደሴት " በማለት ሎምባርድ ሲቀጥል ዶ/ሩ በረጅሙ ተንፍሶ አቋረጠውና ጥያቄ አቀረበለት

"ሁላችንን እዚህ ደሴት ላይ መሰብሰቡ ለምን አስፈለገው?" በማለት ጠየቀው፡፡

"ለምን ይመስልሃል?" ሲል ሎምባርድ መልሶ ጠየቀው

"ይሄንን ጥያቄ ወደ ወ/ሮ ሮጀርስ ሞት እንመለስና እንመልከተው፡፡" በማለት ነበር ሮጀርስ መመለስ የጀመረው፡፡ "የመጀመሪያው ግምት ሮጀርስ በሴትየዋ ስላልተማመነባት ገደላት የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከድንጋጤ ጋር በተያያዘ ሞተች የሚለው ነው፡፡"

"ማለት? ራሷን አጠፋች ልትል ነው?" በማለት ሎምባርድ ጠየቀው፡፡

"አይመስልህም?"

ሎምባርድ ተረጋግቶ ነበር የመለሰለት፡፡ "ምናልባት ማሪስተን ራሱን አጠፋ ብለን ልንገምት እንችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአስራ ሁለት ሰአታት ውስጥ ሁለት ሰዎች ራሳቸውን አጠፉ ብለን መቀበል ይከብዳል፡፡ አንቶኒ ማሪስተን ምንም ያህል ስሜታዊ ወጣት ቢሆን ህፃናትን አውቆ በመኪና አይገጭም፡፡ ስለዚህ የሰራው ወንጀል ፀፅቶት ራሱን አጠፋ በማለት ብንገምት እንኳን መርዙን ከየት አመጣው? እንደሰማሁት ፖታሲየም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያናይድ ማንም ሰው በጃኬቱ ኪስ ይዞት የሚዞር አይነት መርዝ አይደለም፡፡"

"ልክ ነህ፡፡ የተባይ ማጥፊያ ይዘህ ለመዞር የግድ ወደ እርሻ ቦታህ በመሔድ ላይ የምትገኝ ገበሬ መሆን ይኖርብሃል" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ግምቱን አጠናከረለት፡፡

"ስለዚህ ማሪስተንም ራሱን ማጥፋቱ አጠራጣሪ ነው፡፡ ይህ ፖታሲየም ሳይናይድ መጣራት ያለበት ነገር ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ልንገምት የምንችለው አንቶኒ ማሪስተን ወደዚህ ደሴት የመጣው ራሱን ለማጥፋት ተዘጋጅቶ መርዙን ይዞ ነበር፤ አሊያም ደግሞ "

"አሊያም ደግሞ ምን ?" ዶ/ር አርመስትሮንግ ለማረጋገጥ ያህል ጠየቀው እንጂ መልሱን ያውቀዋል፡፡

"ይሄ እኮ ግልፅ ነው ዶ/ር- አሊያም ደግሞ አንቶኒ ማርስተን በሰው ተገድሏል ማለት ነው፡፡"

• • •

"ወ/ሮ ሮጀርስስ?" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ጠየቀው፡፡

"አየህ? አንቶኒ ማሪስተን ራሱን ገድሏል በሚለው መላ-ምት በቀላሉ አምን ነበር፡፡ ነገር ግን የወ/ሮዋ ሞት እንድጠራጠር ያደርገኛል፡፡ በተናጠል የሁለቱም አሟሟት ራስን ከማጥፋት ጋር ይገናኛል፡፡ ነገር ግ ተከታታይ ሁለት ሞቶችን መቀበል ያዳግታል፡፡" በማለት ሎምባርድ መለሰለት

"ጥርጣሬህን የበለጠ የሚያዳብር አንድ መረጃ ልስጥህ" በማለት ሮጀርስ ስለጠፉት ሁለት የቻይና ጥቋቁር አሻንጉሊቶች የነገረውን ደገመለት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"ማታ አስር እንደነበሩ አስታውሳለሁ፡፡ አሁን ስምንት ቀርተዋል እያልከኝ ነው?" ሎምባርድ ተገርሞ ጠየቀው፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ግድግዳ ላይ ከተሰቀለው የህፃናት የተረት ግጥም የመጀመሪያዎቹን ስንኞች በቃሉ አነበነበለት፡-

.....አስር የህንድ ህፃናት ለራት ተጠሩ

አንዱ ታፍና ሲሞት ዘጠኝ ቀሩ

ዘጠኙ ልጆች ሳይተኙ አደሩ

አንዱ ሲያንቀላፋ ስምንቱ ቀሩ...

ሁለቱም በአግራሞት ተያዩ፡፡ ሎምባርድ ሲጋራውን በሃይል ስቦለት በታፈነ ድምፅ "ይሄማ አጋጣሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ማርስተን ራት ላይ አየር አጥቶ ሲሞት ወ/ሮ ሮጀርስ ደግሞ በተኛችበት ነው የቀረችው...." አለ፡፡

"ስለዚህ?" ዶ/ር አርመስትሮንግ ለማረጋገጥ ጠየቀው

"ስለዚህማ እንቆቅልሹ ተፈትቷል፡፡ አሁን የሚቀረን ዋናው እና የተሰወረውን ጥቁር ሰው - ሚስተር ኦውንን-ማግኘት ነው፡፡ የሚቀረው እንቆቅልሽም እርሱ ነው"

ዶ/ር አርመስትሮንግ ለእፎይታ ተንፍሶ "መስማማታችን ጥሩ ነው፡፡ ዋናው ችግር ግን ሮጀርስ እንደነገረኝ እዚህ ደሴት ላይ ከእኛ በቀር ሌላ ሰው የለም" በማለት የእንቆቅልሹን አስቸጋሪነት አስታወሰው፡፡

"ተወው! ሮጀርስ ዋሽቷል አሊያም ተሸውዷል!"

ዶ/ሩ አንገቱን አወዛውዞ "የሚዋሽ አይመስለኝም፡፡ በጣም ስለደነገጠ...."

t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድ መከራከሩን ቀጠለ፡፡ "ዛሬ ጠዋት የሞተር ጀልባው አለመሟላ በራሱ የአቶ አውን እቅድ አንዱ አካል ነው፡፡ የህንድ ደሴትን ከውጪ ምድር ጋር በመነጠል አቶ አውን ስራውን ለመጨረስ ማቀዱን ያጠናክራል የአርመስትሮንግ ፊት ገረጣ፡፡ በፍርሃት ድምፁ እየተርገበገበ "ሰውየ የለየለት እብድ እንደሆነ ተመለከትክ?!" አለው፡፡

ሎምባርድ በተረጋጋ ሁኔታ ነበር የመለሰለት፡፡ "አቶ አውን ያልተረዳ አንድ ነገር አለ፡፡"

"ምንድን ነው?"

"ደሴቷ ብዙም ሩቅ አለመሆኗ ነዋ፡፡ የሆነ ነገር አመቻችተን በቀላሉ የአቶ አውንን ወጥመድ መና እናስቀረዋለን "

"ግን እኮ ሰውየው አደገኛ ሊሆን ይችላል"

ሎምባርድ በረጅሙ ሰቆ "አደገኛ ተኩላ አፍጥጦ ከመጣብህ አንተም ያለህ ብቸኛ አማራጭ አደገኛ መሆን ነው፡፡ ይልቅስ በፍጥነት ለብሎር እንንገረውና እንንቀሳቀስ፡፡ እርሱ ቀልጣፋ ነው፡፡" በማለት እቅዱን ገለፀለት፡፡ በመቀጠልም

"ለሴቶቹ ፣ ለዳኛው እና ለጀነራሉ መናገር የለብንም፡፡ ከመደናበር የተሻለ ርዳታ አያደርጉልንም፡፡ ሶስታችን እንበቃለን፡፡"

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ስምንት

ብሎር በፍጥነት ነበር የተስማማው፡፡ "እንዳላችሁት የቻይና አሻንጉሊቶቹ መሰወር ስሜት ይሰጣል፡፡ በጣም ይገርማል፡፡ ምናልባት አቶ አውን ስራውን በወኪል ወይም በመልዕክተኛ እያሰራ አይመስላችሁም?" በማለት ጠየቃቸው፡፡

"ግልፅ አድርገው"

"ወጣቱ ማርስተን ትናንት ማታ ራሱን አጠፋ፡፡ በመቀጠል ደግሞ አቶ ሮጀርስ የሚስቱን አፍ ዘጋላት" በማለት ግምቱን ግልፅ ለማድረግ ሞከረ፡፡ ዶ/ር አርመስትሮንግ ወጣቱ ራሱን ለማጥፋት የሳይናይድ መርዝ ይዞ መምጣቱን እንደማይቀበል በማንሳት ተከራከረው፡፡

"ምናልባት መርዝ ይዞ መምጣቱ ላያከራክረን ይችላል፡፡ ዋናው ጥያቄ ግን መርዙን ብርጭቆው ውስጥ ማን ሊጨምረው ይችላል የሚለው ነው" በማለት ብሎር ፈርጠም አለ፡፡

መልስ የሰጠው ሎምባርድ ነበር፡፡ "ትናንት ማታ ወጣቱ ማርስተን ብዙ ነበር የጠጣው፡፡ የመጨረሻውን መጠጥ ከመቅዳቱ በፊት ግን የተወሰነ የግዜ ክፍተት ነበር፡፡ በዚያ መሃል ብርጭቆው መስኮቱ አጠገብ የነበረው ጠረጴዛ ላይ የነበረ ይመስለኛል፡፡ መስኮቱ ደግሞ ክፍት ስለነበር የሆነ ሰው በዚያ በኩል የሳይናይድ መርዙን ብርጭቆው ላይ ሊጨምር ይችላል፡፡"

ብሎር ባለማመን ሳቅ ብሎ "እኛ ሳናይ?" በማለት ጠየቀው፡፡

"ሁላችንም ክፍሉ ውስጥ ተወዛግበን እንደነበር አስታውስ" በማለት ሎምባርድ መለሰለት፡፡ ግምቱ ትክክል ሊሆን እንደሚችል አርመስትሮንግ አከለ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዲያውስ በግዜ እንንቀሳቀስ፡፡ ምናልባት ሽጉጥ የያዘ ሰው ከመካከላችን ይኖር ይሆን?" በማለት ብሎር በጥርጣሬ ጠየቀ፡፡

"እኔ ይዣለሁ" በማለት ሎምባርድ ወደ ጃኬቱ ኪስ ጠቆመው፡፡ ሁሉቱም ባለማመን ተመለከቱት፡፡

"በሄድክበት ቦታ ሁሉ ሽጉጥ ይዘህ ነው የምትዞረው?"

"ብዙ ግዜ ችግር ያለባቸው ሁኔታዎች ያጋጥሙኛል፡፡ ስለዚህ ይዤ ነው የምንቀሳቀሰው"

"መቼም ከዚህ የበለጠ አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞህ የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ ለማንኛውም እብዱ አጥማጃችን አዲስ መሳሪያ እና ሳንጃ ሊኖረው እንደሚችል እገምታለሁ፡፡" በማለት ብሎር ተናገረ፡፡

"አይመስለኝም፡፡ ቀውስ ነብሰ-ገዳዮች ብዙ ግዜ ድመፅ ሳያሰሙ ነው እርምጃቸውን የሚወስዱት" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ተከራከረው፡፡

"ይሄኛው እንደዚያ አይነት አይመስለኝም ፤ ዶ/ር" በማለት ብሎር መለሰለት፡፡

• • •

ሶስቱ ወንዶች ስራቸውን የጀመሩት ደሴቷን ዞረው በመቃኘት ነበር፡፡ የደሴቷ አብዛኛው ክፍል ገላጣ ሜዳ ነበር፡፡ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ከነበሩት አነስተኛ ጉብታዎች እና ቁጥቋጦዎች በስተቀር ሰው ሊደበቅባቸው የሚችሉ ስፍራዎችም ሆኑ ዋሻዎች እንደሌሉ ዞረው ተመለከቱ፡፡

ቅኝታቸውን ወደ ማጠናቀቁ ሲቃረቡ ነበር ጀነራል ማካርተር ሃይቁ ዳር ዞሮ ተቀምጦ ውሃውን በትኩረት ሲመለከት ያገኙት፡፡ ከጀርባው ሲጠጉት ዞሮ የመመልከት ፍላጐት እንኳን አልነበረውም፡፡ ብሎር በአግራሞት ተመልክቶት ጉሮሮውን ጠራርጐ፡-


t.me/OLDBOOKSPDF

"ሰላማዊ የዕሞና ስፍራ አግኝተሃል" አለው።

ጀነራሉ ዞር ብሎ አየውና "ብዙ ግዜ የለም ግዜ የለም። ባትረብሹኝ ደስ ይለኛል" በማለት ተቆናጠረ።

"ይቅርታ ! ጀነራል። ደሴቷን በመቃኘት ላይ ሳለን ነው ድንገት የተመለከትንህ። ምናልባት ሰው ሊደበቅበት የሚችል ስፍራ ቢኖር ብለን " በማለት ብሎር በይቅርታ ድምፀት መለሰለት።

"ፈፅሞ አልገባችሁም ! አልገባችሁም። አሁን ከአጠገቤ ሂዱልኝ" በማለት ጀነራሉ ጮኸበት። ብሎርም ወደ ሁለቱ ጓደኞቹ ተመለሰ። ለጥያቄያዊ አስተያየታቸው መልስ መስጠት እንዳለበት ተሰማው።

"ሰውየው እብድ ነገር ነው"

"ምንድን ነው ያለህ?"

"ጊዜ የለም ! አትረብሹኝ ምናምን ይላል"

"ባይልህ ነበር የሚገርመው" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ በግዴለሽነት አንገቱን አወዛወዘ።

• • •

ሶስቱ ወንዶች አጠቃላይ ቅኝታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት በደሴቷ ደቡባዊ ጫፍ ከሚገኘው ጉብታ ላይ ሆነው በአቅራቢያ የነበረውን መንደር ለመመልከት ሞከሩ። ባህሩ ላይ ምንም አይነት የአሳ አጥማጆች ጀልባ አልነበረም። በዚያ ላይ ዝናብ እየመጣ ስለነበር ከጥቂት ሰአታት በኋላ ባህሩ በማዕበል መናወጡ አይቀሬ ነበር።

"ማታ ከፍ ያለ ችቦ አቀጣጥለን የመንደሩን ነዋሪዎች ምልክት ብንሰጣቸውስ?" በማለት ብሎር ሃሳብ አቀረበ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድን ትንሽ አቅማምቶ "ምናልባት መኖራችንን ማሳወቅ በራሱ አደጋ ቢኖረውስ? እዚህ ቦታ ምን እየተካሔደ እንደሆነ እኮ ገና አላወቅንም" በማለት ተናገረ፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ግራ ተጋብቷል፡፡ "በዚህ ሁኔታ ምን ማድረግ እንዳለብን እርግጠኛ አይደለንም፡፡ " በማለት የበኩሉን አስተያየት አከለ፡፡ ብሎር ከጉበታው ጫፍ ላይ ሆኖ ወደ ባህሩ ቁልቁል እየተመለከተ፡-

"እዚህ ስር ምናልባት መደበቂያ ሊኖር ይችላል" በማለት ብሎር ሲናገር አርመስትሮንግ በጥርጣሬ እያየው ፡-

"ጀልባ ቢኖር ኖሮ ደሴቷን በመዞር መደበቂያ ጉድጓዶች እንዳሉ መመልከት እንችል ነበር" አለ

"ጀልባ ቢኖርማ ከዚህ ሁሉ ጣጣ ማምለጥ እንችል ነበር፡፡" በማለት ብሎር ሳቅ ብሎ መለሰለት፡፡

ሎምባርድ ወደታች ተመለከተና "የሆነ መንጠልጠያ ነገር ብናገኝ ምናልባት እዚህ ስር መደበቂያ መኖሩን ማየት እንችል ነበር" አለ፡፡ ብሎርም ቀና ብሎ ተመልክቶት፡-

"መጣሁ ገመድ ነገር ፈልጌ-" በማለት ወደ ቤቱ አቅጣጫ አመራ፡፡

ሎምባርድ ዶ/ር አርመስትሮንግን ገርመም አድርጎት

"ዶ/ር ምን እያሰብክ ነው?" በማለት ጠየቀው፡፡

"ጀነራሉ ምን ነክቶት ይሆን ብዬ እያሰብኩ ነው" በማለት ዶ/ሩ አይኖቹን ከባህሩ ላይ ሳይነቅል መለሰለት፡፡

• • •

ቬራ በማለዳ ተነስታ ነበር፡፡ መረጋጋት ስላልቻለች በየቦታው መዘዋወር ነበር የመረጠችው፡፡ በተቻላት መጠን ከወ/ሮ ኤሚሊ ለመራቅ ሞከረች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶ/ር ኤሚሊም ከሰው ጋር መገናኘት ስላልፈለጉ ከቤቱ ጀርባ በሚገኝ ወንበር ላይ ተቀምጠው ሹራብ መጥለፍን ነበር የመረጡት፡፡

ድንጋጤ እና ግራ መጋባት የሚያምረውን የቬራ ፊት አጠየሙት፡፡ በረንዳው ላይ ስትደርስ ዳኛ ዋርግሬቭን ተመለከተቻቸው፡፡ የሚወዛወዘው የእዛውንት ወንበር ላይ አንገታቸውን ቀብረው የተቀጡትን ዳኛ ስትመለከት ፍርድ ለመስጠት የዳኛ ካባ የደረቡ መሰላት፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ በወጣቱ ኤድዋርድ ሴተን ላይ ሞት ሲፈርዱ በምናቧ ታያት፡፡ በፍጥነት ከበረንዳው ላይ በመውረድ ወደ ባህሩ ዳርቻ አመራች፡፡

በዝግታ እየተራመደች ሳለ ባህሩ ዳርቻ የተቀመጠውን ጀነራል ማካርተር ከርቀት ተመልክታ ወደር'ሱ አመራች፡፡ አጠገቡ መድረሷን የተመለከተው ጀነራል አፍጥጦ ከእግር እስከ ፀጉሯ ገመገማት፡፡ "እስተያየቱ የሚያውቀኝ ይመስላል" በማለት አሰበች፡፡

"ኦ- አንቺ ነሽ ለካ፡፡ መጣሽ አይደል?" አሉ ጀነራሉ፡፡

"ባህር መመልከት ያስደስትሃል ማለት ነው?"

"አዎን፡፡ በተለይ ለመጠበቅ የተሻለ ስፍራ ነው"

"መጠበቅ?" በማለት ግራ ተጋብታ ጠየቀችው

"አዎና፡፡ ሁላችንም መጨረሻውን እየጠበቅን አይደለም እንዴ?" በማለት መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ አቀረበላት፡፡

"ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም"

ጀነራሉ አይናቹን ጠበብ አድርጎ ነበር የመለሰላት፡፡ "አንዳችንም ከዚህ ደሴት በሰላም አናመልጥም፡፡ እቅዱ ይሄ እንደሆነ ደግሞ ሁላችንም እውቀናል፡፡ አንቺ ያልገባሽ ነገር ቢኖር ይህ ምን አይነት እረፍት መሆኑን ነው፡፡"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እረፍት?"

"ታዲያስ? ለነገሩ አንቺ ገና ወጣት ስለሆንሽ ሰላማዊውን እረፍት ለመቀበል እና ሽክምሽኑ ለማራገፍ አልቀረብሽ፡፡ አንድ ቀን ይሀ ይሰማሻል፡፡"

"አልተረዳሁህም" በማለት በፍርሃት ጣቶቿን እያፍተለተለች ጠየቀችው፡፡

ጀነራሉ ፍፁም ተረጋግቶ "ሌስሊን እወዳት ነበር፡፡ በጣም ነበር የማፈቅራት" አላት

"ሌስሊን ባለቤትህ ነበረች

"አዎ፡፡ የምወዳት እና የማከብራት ቆንጆ ሚስቴ" በማለት ለአንድ ደቂቃ ያህል በፍፁም ፀጥታ ውስጥ ቆይቶ ንግግሩን ቀጠለ፡-

"በጣም ስለምወዳት ነበር ያደረግሁት"

"ምኑን?" ጠየቀችው

ጀነራሉ አንገቱን ቀልበስ አድርጎ ተመለከታት፡፡ "አሁን የምከድበት ሁኔታ ላይ አይደለሁም፡፡ ወጣቱን ሪችሞንድ አውቄ ነበር ለሞት የሸኘሁት፡፡ ይሄ ደግሞ ግልፅ ግድያ ነው፡፡ ዘመኔን በሙሉ ህግ ስጣስ ኖሬአለሁ፡፡ ነገር ግን የሪችሞንድን ሞት በተመለከተ አልፀፀትም፡፡ ከዚህ በኋላ ግን "

"ከዚያ በኋላ ምን?"

"ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር ተቀየረ፡፡ ሌስሊ ያወቀች አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ተቀየረችብኝ፡፡ በአካል አብራኝ ብትሆንም ልደርስባት አልቻልኩም ነበር፡፡ በኋላም ሞተች ፤ እኔም ብቸኛ ሆንኩኝ፡፡ "ብቸኛ የሚለው ቃል እንደ ገደል ማሚቱ ተደጋገመባት፡፡

"መጨረሻው ሲደርስ በጣም ደስ ይልሻል"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም፡፡" በማለት ከአጠገቡ ለመሄድ ተነሳች

"አውቃለሁ ፣ ልጄ፡፡ ፊፅሞ ሊገባሽ አይችልም" በማለት ጀነራሉ ፊቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ባህሩ አዞረ፡፡ ከጀርባው ለቆመችው ቬራ ምንም ትኩረት አልሰጣትም ነበር፡፡

"ሊስሊ ማለት...." ማጉተምተም ጀመረ፡፡

• • •

ብሎር ገመዱን ይዞ ሲመለስ አርመስትሮንግን ብቻ ነበር ያገኘው፡፡

"ሎምባርድስ?"

"ለሽንቱ ዞር ብሎ ነው፡፡ ስለ ጀነራል ማካርተር እያሳብኩ ነበር" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ብሎርን ፍዝዝ ብሎ አየው፡፡

"ገዳዩ እሱ እንደሆነ ተጠራጠርክ እንዴ?"

"እንደሱም ባይሆን ሰውየው የሚጨንቅ ነገር አለው፡፡ አእምሮው ጤነኛ አይመስለኝም፡፡" በማለት ዶ/ሩ ገመተ፡፡

"ጤነኛማ አይመስልም፡፡ እና ተጠራጠርከው?"

"እኔ እንጃ፡፡ ግን በደሴቷ የተደበቀ ሌላ ሰው መኖሩን መጠርጠሩ ይሻላል፡፡ ያው ሎምባርድ መጣ "

ከአፍታ በኋላ ዶ/ሩ እና ብሎር ገመዱን ሲይዙለት ሎምባርድ በቀላሉ ተንጠልጥሎ ወረደ፡፡

"ይሄ ሰው እንደ ድመት ነው የሚንጠለጠለው" በማለት ብሎር ተገርሞ ቁልቁል ተመለከተው፡፡

"ተራራ የመውጣት ልምድ ያለው ይመስለኛል" በማለት ዶ/ሩ የራሱን ግምት አቀረበለት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"በበኩሌ ይሄ ሰው የሚረብሽ ነገር እንዳለው ይሰማኛል፡፡ የምናገረዉ ገብቶሃል?" በማለት ጠየቀው

"እንዴት ጠረጠርከው?"

"እኔ እንጃ፡፡ ነገር ግን በርቀት ልጠብቀው የምፈልግ አይነት ሰው ነው"

"ከአገር አገር ሲዘዋወር የኖረ ይመስላል እንጂ ጉዳት ያለው አይመስለኝም" በማለት ዶ/ሩ ግምቱን አቀረበለት፡፡

"መዘዋወሩ አይደለም ችግሩ፡፡ ለምሳሌ ዶ/ር አንተ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ ሽጉጥ ይዘህ ትሄዳለህ?"

"ሽጉጥ? የፈጣሪ ያለህ? ምን ሊያደርግልኝ?" በማለት ዶክተሩ በጥያቄ መለሰለት፡፡

"ሎምባርድ ታዲያ ምን ሊያደርግለት ያዘው?"

"እንዲያው ልምድ ሆኖበት ይሆናላ "

"ልምድ አይመስለኝም፡፡ ሰዎች በአስፈላጊ ስፍራ ሽጉጥ ይዘው የሚገኙበት አጋጣሚ ልብ - ወለድ መፅሃፍ ውስጥ ብቻ ነው ያለው" በማለት ብሎር ክርክሩን ቀጠለበት፡፡

ብሎር አጉንብሶ ሲመለከተው ሎምባርድ በቦታው ምንም አይነት መደበቂያ አለመኖሩን አረጋገጠለት፡፡ ወዲያውኑ በፍጥነት ተንጠለጥሎ በመመለስ ሁለቱ የቆሙበት ቦታ ደረሰ፡፡ ግንባሩ ላይ ችፈፍ ያለውን ላብ በአይበሉባው እየጠራረገ፡-

"እንግዲህ ምንም መደበቂያ እንደሌለ አረጋግጠናል፡፡ ስለዚህ አጥጋኙ ሊሸሸግ የሚችለው ቤት ውስጥ ነው፡፡ አሊያም ደግሞ የትም ስፍራ የለም ማለት ነው፡፡" በማለት ውጤቱን አሳወቃቸው፡፡

• • •

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶስቱ ወንዶች በቀጣይ ያመሩት ወደ ቤት ነበር፡፡ ከዋናው ቤት አጠገብ የሚገኙትን ትናንሽ ቤቶች ፈትሸው እንዳበቁ በቀጥታ ወደ ትልቁ ቤት አመሩ፡፡ ቤቱ ዘመናዊ ግንባታ ከመሆኑም በላይ ሰፊ እና ግልፅ በመሆኑ ለመደበቂያ የሚሆን ስፍራ አልነበረውም፡፡ ሶስቱ ወንዶች ምድር ቤቱን አጣርተው ወደ ላይኛው ወለል በመውጣት የመኝታ ክፍሎችን ለመመልከት ተንቀሳቀሱ፡፡ ከርቀት ባለው መስኮት በኩል ሮጀርስ ብስኩት በሰሃን ይዞ ወደ በረንዳው ሲወጣ አዩት፡፡

'መልካም አስተናጋጅ" በማለት ሎምባርድ አደነቀ፡፡ አርመስትሮንግም መሰከረለት፡፡ ብሎር በበኩሉ "ሚስቱ ምርጥ ባለሙያ ነበረች፡፡ የቀረበልንን ራት አስታውሱ " በማለት አዳነቀ፡፡ ሶስቱም ተያይዘው ወደ መጀመሪያው መኝታ ክፍል በመግባት ፍለጋቸውን ቀጠሉ፡፡

ከአምስት ደቂቃ በኋላ ፍለጋቸውን አጠናቅቀው ወጡ፡፡ በመቀጠል የሚበረብሩትን ክፍል ከመወሰናቸው በፊት ወደ ጣሪያው የሚያወጣውን መሰላል ተመለከቱ፡፡ ምናልባት የተደበቀ ሰው ቢኖር ሊመርጥ የሚችለው ስፍራ የቤቱን ጣሪያ እንደሚሆን በመገመት ወደዚያው ሊወጡ ሲሉ ድምፅ ሰምተው ቆሙ፡፡

ድምፁ በድጋሚ ሲመጣ ሶስቱም ወንዶች ፍለጋቸው መጠናቀቁን ገመቱ፡፡ 'ጣሪያ ላይ ነው በማለት ሎምባርድ ለመውጣት ተዘጋጀ፡፡ ወዲያውኑ ድምፁ በግልፅ ሲሰማቸው ብሎር ወደ ሁለቱ ጠጋ ብሎ በሹክሹክታ፡-

"ድምፁ የወጣው ከወ/ሮ ሮጀርስ መኝታ ቤት ነው" በማለት ነገራቸው፡፡

"ትክክለኛ የመደበቂያ ስፍራ ነው የመረጠው፡፡ ግንም አይጠረጥረውም፡፡" በማለት ሎምባርድን አስቀድመው ወደ መኝታ ቤቱ በር ተጠጉ፡፡ በዚህን ግዜ የሚንቀሳቀስ ሰው ኮቴ በግልጽ ተሰማቸው፡፡ ሎምባርድ በእጁ ምልክት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰማቸው፡፡ ብሎር በሩን በፍጥነት ሲበረግደው ሰሱቅም እየተከፈተ ተከታተለ
በፍጥነት ገቡ፡፡ ሰሱቅም በድንገቴ ደርቆው ቆመ፡፡

ሮጀርስ በርካታ ልብሶችን ይዞ ከፍሉ መሃል ላይ ቆሞ ነበር፡፡

• • •

ብሎር ነበር ቀድሞ የተረጋጋው፡፡ "ይቅርታ ሮጀርስ ድምፅ ሰምተን ነ
•

"የሌሊት ልብሶቹን ለመውሰድ መጥቼ ነው፡፡ ምድር ቤት አንድ ክፍል ከፍል ስላለ እዛው ለመሆን ብዬ ነበር " በማለት ሮጀርስ ተራ ተመለከታቸው፡፡

"እ ትችላለህ" በማለት አርመስትሮንግ ሲያሳለፈው መንገድ ለቀቀለት፡፡ አልጋው ላይ አንሶላ ለብሶ የተኛውን የሚስቱን አስከሬን ሳለማየት እየሞከረ ልብሶቹን ይዞ ከክፍሉ ሲወጣ ከኋላው ተመለከቱት፡፡

አርመስትሮንግ የሚስትየዋን አስከሬን ገልጦ ተመለከተ፡፡ ፊቷ ፍፁም ሰላማዊ እንቅልፍ ላይ ያለች ነበር ያስመስላት፡፡

"የህክምና ቁሳቁስ ይዤ መጥቼ ቢሆን ጥሩ ነበር፡፡ በምን እንደሞተች ማወቅ ፈልጌ ነበር፡፡" በማለት ወደ ሁለቱ በመዞር ፊቱን ቅጭም አድርጎ "ፍለጋው ቢበቃን ይሻላል፡፡ ምንም የምናገኝ አይመስለኝም" አላቸው፡፡

ብሎር በአግራሞት ራሱን እነቃንቆ "አቶ ሮጀርስ በዝግታ የሚራመድ አይነት ሰው ነው፡፡ ከደቂቃ በፊት ነበር አይደል ወደ በረንዳው ሲወጣ በመስኮት የተመለከትነው?"

"ለዛ ነበር እኮ የሆነ ሰው መኖሩን ተጠራጥረን እዚህ የገባነው" በማለት ሎምባርድ አስታወሳቸው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎር ፍሊጋውን ለማጠናቀቅ በመጓጓት ከወ/ሮ ሮጀርስ አልጋ አልፎ ደሚገኘው በር አመራ። ጭለማው መተላለፊያ የት እንደሚያወጣ ያውቅም በቀጥታ ወደ ውስጥ ገቡ። ሎምባርድም ባትሪ ከኪሱ አውጥቶ ብራና ተከተለው።

ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ሶስቱ ወንዶች የቤቱ ጣሪ ላይ ተገናኙ። ልብሳቸው ብቻ ሳይሆን ፊታቸውም በአቧራና በጥላሸት ቆሽሾ ነበር። ሬውን አሰሳ አጠናቅቀው ሲገናኙ ከስምንቱ በቀር በደሴቷ ላይ ሌላ ሰው አለመኖሩን አርግጠኛ ሆነዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድ በዝግታ 'ሁላችንም ተሳስተናል ፤ የሁለት ሰዎችን ድንገተኛ ሞት መሰረት አድርገን በማይሆን ምናባዊ ትዝብት ውስጥ ገባን...' አለ።
አርመስትሮንግ ፊርጠም ብሎ 'ተረጋጉ ይሄ ትዝብት አይደለም። ዶክተር እንደመሆኔ ስለ ሞት የተሻለ አውቃለሁ። አንቶኒ ማርተንም ራሱን አልገደለም' አለ።
ሎምባርድ በጥርጣሬ ተሞልቶ 'አጟጟቱ ድንገተኛ አደጋ አይደለም ማለት ነው?' አለ።
ብሎር በረጅሙ ተንፍሶ 'የእርሱ የአጋጣሚ ሞት ሊሆን ይችላል። የሴትየዋ ግን....'
'ወ/ሮ ሮጀርስ?'
"አዎ የእሷ ሞት ግን ያጠራጥራል' አለ ብሎር
'ምን እያልክ ነው?'
ብሎር ፊቱ ቀላ። ድምፁ እየተርገበገበ ዶክተር የሆነ መድሃኒት ሰጥተሃት ነበር" አለ።
አርመስትሮንግም "የምን መድሃኒት?" ሲል ጠየቀው
"ትናንት ማታ የእንቅልፍ ኪኒን ሰጥተሃታል' ብሎ አስታወሰው
"ኦ እሱማ ምንም ጉዳት የማያመጣ የእንቅልፍ እንክብል ነው።" በማለት ዶ/ሩ መለሰለት።
"በትክክል የሰጠሃትን መድሃኒት ንገረኝ"
"የተመጠነ ትሪዮናል ነው። ምንም ጉዳት አያስከትልም"
የብሎር ፊት የበለጠ ገረጣ። "ከመጠን በላይ እንዳልሰጠሃት እርግጠኛ ነህ?"


t.me/OLDBOOKSPDF

'ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም?' ዶ/ር አርመስተሮንግ መልሶ ጠየቀው

'ልትሳሳት ትችላለህ፡፡ ከስንት እንዴ የሚያጋጥሙ የህክምና ስህተቶች አሉ አይደል?' ብሎር ለማሳመን ተከራከረ

'እኔ አልተሳሳትኩም' በማለት አርመስትሮንግ ተቆጣ 'ከመጠን ያለፈ መድሃኒት የሰጠዋት መስሎህ ነው?' በማለት ጠየቀው፡፡

በዚህ መሃል ሎምባርድ ቆጣ ብሎ 'ሁለታችሁም አቁሙ! መወነጃጀሉ አይጠቅመንም' በማለት የሁለቱን ክርክር አስቆመ፡፡

'ዶ/ር ሊሳሳት እንደሚችል ብቻ ነው ያስታወስኩት' በማለት ብሎር ረገብ ለማለት ሞከረ፡፡

አርመስትሮንግ ፈገግ ለማለት እየሞከረ 'ዶ/ሮች መሳሳት የለባቸውም ወዳጄ፡፡ በተለይ አሁን አንተ ያልከው አይነት ስህተት....' አለ፡፡

'ይህ የመጀመሪያው ስህተትህ አይደለም ዶ/ር  በተለይ ከቴፑ የሰማነውን እምነን ከተቀበልን ' በማለት ብሎር ዶ/ሩን ነቀረው፡፡

አርመስትሮንግ በድንጋጤ ፊቱ ቀላ፡፡ ሎምባርድ በድጋሚ ጣልቃ ገብቶ 'መወነጃጀሉ ምን ዋጋ አለው? ሁላችንም እኮ በተመሳሳይ ወጥመድ ውስጥ ነን፡፡ አንተስ ብትሆን  ስለ ሃሰተኛ ምስክርነትህ ሰምተናል እኮ' በማለት ብሎር ላይ ጮኸበት፡፡

"ተራ ወሬ ነው!" በማለት ብሎር ተቆጣ፡፡ 'ከተራ ወሬ አፌን ልታዘጋ አትሞክር ፤ ሎምባርድ፡፡ ማወቅ ከምፈልገው ነገር ውስጥ አንዱ አንተን ይመለከታል፡፡

'ስለ እኔ ምን?'

'በዚህ ሰላማዊ ግብዣ ላይ ለምን ሽጉጥ ይዘህ መጣህ?'

'እሱን ነው ማወቅ የምትፈልገው?'



t.me/OLDBOOKSPDF

"በትክክል"

"እንደገመትኩት የዋህ አይደለህም ብሎር" አለ

"እሱን ተውና አሁን ስለ ሽጉጡ ንገረን"

"ምናልባት ችግር ቢያጋጥመኝ ብዬ ነው የያዝኩት"

ብሎር አይኖቹን ጠበብ አድርጎ እየተመለከተው "ለምን ትናንት ማታ አልነገርከንም?" በማለት ጠየቀው

ሎምባርድ በረጅሙ ተንፍሶ "እንደ ሁላችሁም ተጋብዤ የመጣሁ ለመምሰል ፈልጌ ነበር፡፡ ወደ'ዚህ የላከኝ አንድ አይሁድ ቀጣሪ ነው፡፡ አንድ መቶ የወርቅ ፍራንክ እንደሚከፍለኝ ቃል ገብቶ በድግሱ ላይ እንድታደም ላከኝ

"እናስ?" በማለት ብሎር ትረካውን እንዲቀጥል ጠየቀው

"በቃ ይኸው ነው" በማለት ሎምባርድ መለሰለት፡፡

"አይሁዱ ቀጣሪህ ሌላ ምንም አልነገረህም?" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ጠየቀው

"ምንም ተጨማሪ ነገር አልነገረኝም፡፡ እፌን ዘግቼ እንድመጣ ላከኝ፡፡ የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመኝ ሳልከራከረው ነበር የተቀበልኩት፡፡" በማለት መለሰለት

ብሎር የበለጠ ተጠራጠረው "ታዲያ ለምን ትናንት ማታ አልተናገርክም?"

"ይሄ እንደሚመጣ መች አውቄ? ራሴን በመደበቅ የውሸት ታሪክ መናገር እንደሚሻል አስቤ ነበር" በማለት ሎምባርድ መለሰለት፡፡

"አሁን ምን የተለየ ነገር ተሰማህ?" በማለት አርመስትሮንግ መስቀለኛ ጥያቄ ጠየቀው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የሎምባርድ ፊት ተለዋወጠ፡፡ ኮስተር ብሎ "አሁንማ እንደ እናንተ በተመሳሳይ ወጥመድ መያዜን አረጋግጫለሁ፡፡ ቃል የተገባልኝ መቶ የወርቅ ፍራንክም የአቶ አውን ወጥመድ እንደሆነ አውቄአለሁ፡፡" በማለት መለሰለት፡፡ በመቀጠል ድምፁን ከፍ አድርጐ "ወጥመድ ውስጥ ገብተናል፡፡ የሁለቱ ሞት ፣ የአሻንጉሊቶቹ መሰወር- በአጠቃላይ የአቶ አውን ስራ ናቸው፡፡ ጥያቄው ይሄ ሰይጣን አቶ አውን የት አለ የሚል ነው "

ከምድር ቤት የሰሃን ደወል ድምፅ ተሰማቸው፡፡ የምሳ ሰአት ደርሶ ነበር፡፡

* * *

ሶስቱ ተከታትለው ወደ ምድር ቤት ወረዱ፡፡ ምሳ አዘጋጃጅቶ የጨረሰው አገልጋዩ ሮጀርስ ከበር ተቀበላቸው፡፡ "ምሳው እንደሚያረካችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የተጠበሰ ስጋ ፣ የተቀቀለ ድንች ፣ አይብ ፣ ብስኩት እንዲሁም በቂ ፍራፍሬ አዘጋጅቻለሁ" በማለት ወደ አልፍኙ መራቸው፡፡

"ከበቂ በላይ ይመስላል፡፡ ለመሆኑ በቂ የምግብ ክምችት አላችሁ?" በማለት ሎምባረድ ጠየቀው፡፡

"የደሴት ነዋሪዎች በቂ መጠባበቂያ የማስቀመጥ ልምድ አላቸው ፣ ጌታዬ፡፡ በአስቸጋሪ ግዕበል ለቀናት መንቀሳቀስ ባይቻል እንኳን በቂ ክምችት አለ፡፡" በማለት ሮጀርስ አረጋገጠለት፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ ፍሬድ ናርኮት እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዛሬ እረፍት ነው፡፡ እድለ-ቢስ መገጣጠም ሆነብዎት" አለው

"ልክ ብለሃል- እድለቢስነት ነው" በማለት ሎምባርድ ተስማማ፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት የዐንገት ልብሳቸውን እያስተካከሉ ወደ አልፍኙ ገቡ፡፡ "ንፋሱ አስቸጋሪ እየሆነ ነው፡፡ ባህሩን ሲያገላብጠው አደረ" በማለት ከሶስቱ ጋር ተቀላቀሉ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኛው ጀስቲ ዋግሬቭ በዝግታ እተራመዱ ወደ ምግብ ጠረጴዛው ተጠጉ፡፡ በጠባብ አይኖቻቸው እንግዶቹን አንድ ግዜ አየት አድርገው "መልካም ማለዳ እንደሳለፋችሁ እምናለሁ" በማለት አፋቸውን በከፊል ከፍተው አሸሞሩ፡፡

ቬራ ከሌይትሮን እየተጣደፈች ገባች፡፡ "ይቅርታ አላስጠበቅኳችሁም አይደል" በማለት ቁና ቁና እየተነሰፈች ተቀላቀለቻቸው፡፡

"እንዲያውም፡፡ ጀነራሉ ገና አልደረሰም እኮ" በማለት ወ/ሮ ብሬንት አረጋጓት፡፡

አስተናጋጁ ሮጀርስ ወ/ሮ ኤሚሊን እየተመለከተ "መአዱን ይባርኩልናል እመቤቴ ፤ ወይስ እንጠብቅ?" አለ

"ጀነራሉ ባህሩ ዳርቻ ላይ ተቀምጦ ነበር፡፡ የሰሃኑን ድምፅ የሰማ አይመስለኝም፡፡ በዚያ ላይ ዛሬ ትንሽ የደበረው ይመስላል" በማለት ቬራ ምግቡ እንዲጀመር ወተወተች

"ምሳ እንደቀረበ እነግራቸዋለሁ" በማለት ሮጀርስ ለመሔድ ሲዞር ዶ/ር አርመስትሮንግ ከወንበሩ ተፈናጥሮ በመነሳት "እኔ እጠራዋለሁ፡፡ እስከዚያ እናንተ ጀምሩ" በማለት ወጥቶ ሲሄድ አስተናጋጁ ሮጀርስ "ቀዝቃዛ የምሳ ጥብስ ይሁንልዎት ወይስ የአሳማ?" በማለት መስተንግዶውን ሲጀምር ሰማው

• • •

አምስቱ እንግዶች ቃላት ሳይለዋወጡ ተቀምጠዋል፡፡ ከቤቱ ውጪ ሃይለኛ የንፋስ ድምፅ እየቀየ ይሰማ ነበር፡፡

"ማዕበል እየመጣ ነው" በማለት ቬራ ፀጥታውን ሰበረች፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ፎ ገዳይ

ገርማችኋል ትናንትና ባቡር ላይ አንዱ ሽማግሌ ማዕበል እየመጣ ሆነ ሲናገር ነበር፡፡ እንዴት እንዳወቀው ገርሞኛል በማለት ብሎር ለበት፡፡

ስተናጋጁ ሮጀርስ የምግብ ሰሃኖቹን እያቀራረበ ሳለ በድንገት ቆም ርጐ "የሚሮጥ ሰው ይሰማኛል" አላቸው፡፡ በረንዳው ላይ የሚሮጥ ሰው ዳለ ሁሉም ይሰማቸዋል፡፡ ሁሉም ከወንበራቸው ተነሱ፡፡ ማንም ነገራቸው አውቀዋል፡፡ በሩን እየተመለከቱ መጠበቅ ያዙ፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ በሩ ላይ ሲደርስ ትንፋሹ እየተቆራረጠ ነበር፡፡ ንራል ማካርተር "

"ሞተ!" በማለት የጀመረውን ዓረፍተ ነገር የጨረሰችለት ቬራ ነበረች፡፡

"አዎ ሞቷል" በማለት አረጋገጠላቸው

ለባቱ ሰዎች ምንም ቃል ሳይተነፍሱ እርስ በርስ ተፋጥጠው ቆሙ፡፡

ብሎር እና አርመስትሮንግ የጀነራሉን አስከሬን ወደ ቤት እንዳስገቡ ይለኛው አውሎ ንፋስ ተነሳ፡፡ የቀሩት የእልፍኙ በር ላይ ሆነው ሲመለከቱ ለቱ አስከሬኑን ይዘው አለፉ፡፡ ቬራ በፍጥነት ዞራ ወደ ምግብ አዳራሹ መራች፡፡ ጠረጴዛው በፍራፍሬ እና ብስኩት የተሞላ ሲሆን ገና ልተቀመሰለትም ነበር፡፡

የምግቡ ጠረጴዛ አጠገብ በሁለት ደቂቃ ያህል ቆማ ነበር፡፡ ከኋላዋ ዘገታ የሚራመደው ሮጀርስ ቬራን በጥያቄ አስተያየት እየተመለከታት ይትርታ ወይዘሪት- የምትፈልጊው ነገር እንዳለ ብዬ ነው፡፡" በማለት ትህትና ጠየቃት፡፡

ቬራ ያወጣችው ድምፅ ጩኸት ለራሷም አስገረማት፡፡ "ልክ ነህ ፤ ሮጀርስ ፡፡ ራስህን ጠብቅ፡፡ የቀረነው ሰባት ብቻ... " በማለት ተደናበረች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የጀነራሉን አስከሬን መርምሮ እንደጨረሰ ነበር ዶ/ር አርስትሮንግ ውጤቱን ወደሚጠብቁት እንግዶች ያመራው፡፡ ከእልፍኙ አጠገብ በሚገኘ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ወ/ሮ ኤሚሊ ሹራባቸውን እየጠለፉ ተቀምጠዋል፡፡ ቬራ በመስኮት ሃይለኛውን ንፋሳማ ዝናብ እየተመለከተች ሲሆን ብሎር ወንበሩ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀምጧል፡፡ ሎምባርድ ወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠ ሲሆን ዳኛው ጀስቲስ ዋርግሬቭ ደግሞ አይናቸውን እንደወትሮ ገርበብ አድርገው ጥግ ላይ ተቀምጠዋል፡፡

ዶ/ሩ እንደደረሰ ነበር ዳኛው በአስገምጋሚ ድምፃቸው "እህስ ፣ ዶ/ር?" በማለት የጠየቁት

ዶ/ር አርመስትሮንግ ፊቱ ገርጥቷል፡፡ "የልብ ድካምም ሆነ መሰል ችግር አላገኘሁበትም፡፡ ጀነራሉ የሞተው ከጀርባው ጭንቅላቱን በሆነ ነገር ተመትቶ ነው" በማለት የአስከሬን ምርመራ ውጤቱን ገለፀላቸው፡፡

በክፍሉ የነበሩት ሰዎች አጉረመረሙ፡፡ ከሁሉም ድምፅ በላይ የሚሰማው የዳኛው ጥያቄ ነበር፡፡ "በትክክል የተመታበትን መሳሪያ አውቀሽዋል?"

"አላወቅሁም"

"መመታቱን ግን እርግጠኛ ነህ?"

"በሚገባ" በማለት አረጋገጠላቸው፡፡

"አሁን ያለንበትን ሁኔታ ማወቅ ችለናል " በማለት ዳኛው በዝግታ ተናገሩ፡፡ በመቀጠል የተናገሩበት ሁኔታ በሙሉ ለችሎት የተቀመጡ አስመስሏቸዋል፡- ሁላችንም በተመሳሳይ ፍርሃት ውስጥ እንገኛለን፡፡ በመሆኑም የየራሳችንን ቃል የምንናገርበት ሰአት ላይ ደርሰናል፡፡" በማለት



t.me/OLDBOOKSPDF

...ፊት አንገታቸውን መዘዝ አድርገው "በእጃችን ካለው መረጃ በመነሳት ...ምንከተለው ሂደት አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ከመካከላችን ተጠርጣሪ ...ሆኑ የማይችሉትን መለየት ነው፡፡" አሉ፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ በጥድፊያ "እኔ የተከበርኩ ባለሙያ ነኝ፡፡ በዚህ ...ጉዳይ የምጠረጠርበት አግባብ ....." በማለት የራሱን ነፃ መሆን መናገር ...ሲጀምር ዳኛው በእጃቸው ምልክት አስቆሙት

"እኔም የተከበርኩ ባለሙያ ነኝ፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻውን ከተጠርጣሪነት ነፃ አያወጣም፡፡ ዶክተሮችም ሆኑ ዳኞች ያልተገባ ድርጊት ፈፅመው አይተናል፡፡" በማለት ዳኛው ብሎርን ወደ ጐን አየት አድርገው "ፖሊሶችም እንዲሁ" አሉ፡፡

ሎምባርድ ነበር በመቀጠል የተናገረው፡፡ "እንደ እኔ እምነት ሴቶቹን ከተጠርጣሪ ዝርዝር ብናወጣቸው ጥሩ ነው" አለ፡፡

ዳኛው በተለመደው አስገምጋሚ ድምፃቸው "ሴቶች ግድያ ሲፈፅሙ አይችሉም እያልከን ነው?" በማለት ጠየቁት፡፡

"ሳይሆን የመፈፀም እድላቸው አነስተኛ..." በማለት የጀመረውን ማስረጃ ሳይጨርስ አቆመ፡፡

ዳኛው ወደ አርመስትሮንግ በመዞር በተመሳሳይ ድምፅ "ዶ/ር አንዲት ሴት ማካርተርን ከጀርባው በመምታት ልትገድል የሚያስችል አቅም አላት?" በማለት ጠየቁት

"የፖሊስ ዱላ የሚመስል ቀላል የፕላስቲክ መምቻ ከተጠቀመች በርግጥም ብዙ ጉልበት ሳታወጣ ልትገድለው ትችላለች" በማለት ዶ/ሩ የመሳሪያው አይነት ወሳኝ እንደሆነ ገለፁላቸው፡፡

" ከፍተኛ ጉልበት ሳትጠቀም?" ዳኛው ጠየቁት

t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎ" በማለት አረጋገጠላቸው፡፡

በመቀጠል ዳኛው ወፍራም አንገታቸውን በማዘዋወር "የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች በመድሃኒት ተገድለዋል፡፡ ድርጊቱን ለመፈፀም ደግሞ የግድ የወንድ ጉልበት አያስፈልግም" በማለት ተናገሩ፡፡

"ይሄ እብደት ነው" በማለት ቬራ አምባረቀች

ዳኛው በጠባብ አይናቸው ቬራን ገረመሟት፡፡ አስተያየታቸው ረበሻት፡፡ ለምንድን ነው እንደዚህ የሚያተኩሩብኝ? ለነገሩ ድሮም አልወደዱኝም ነበር በማለት አሰበች፡፡

"ክብርት እመቤቴ ስሜትሽን ተቆጣጣሪ፡፡ እየወነጀልኩሽ አይደለም፡፡" በማለት ዳኛው አይናቸውን ከቬራ ላይ አንስተው ወደ ወ/ሮ ኤሚሊ በመዞር "እርስዎም እመቤቴ በድርጊቱ እንዳይበሳጩ እለምናታለሁ፡፡ ሁላችንንም ተጠርጣሪዎች ማድረጌ አስቀይሞት ይሆን?" በማለት በትህትና ጠየቁ፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ ሹራባቸውን መጥለፍ ሳያቆሙ ነበር ለዳኛው መልስ የሰጧቸው፡፡ "ባህርዬን የሚያውቅ ሰው በምንም መንገድ በሶስቱ ሰዎች ሞት ቀርቶ በምንም አይነት አነስተኛ ወንጀል አይጠረጥረኝም፡፡ ነገር ግን ሁላችንም እንግዶች በመሆናችን ያለሙሉ መረጃ ማንንም ነፃ ወይም ወንጀለኛ ማድረግ እንደማይቻል እረዳለሁ፡፡ ቀድሞ እንደተናገርኩት ግን አሁንም ቢሆን ከመካከላችን ሴጣን አለ፡፡" በማለት ምላሽ ሰጡ፡፡

"ስለዚህ ከመካከላችን ተጠርጣሪ የማይሆን ሰው እንደሌለ ሁላችንም ተስማምተናል ማለት ነው" አሉ ዳኛው፡፡

"ሮጀርስስ?" በማለት ሎምባርድ ጠየቀ፡፡

"ሮጀርስ ምን?" በማለት ዳኛው መልሰው ጠየቁት

"መልካም ሰው ይመስላል" በማለት ሎምባርድ ተናገረ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት እንደዛ ልትል ቻልክ?"

"በመጀመሪያ ከፉ አስተሳሰብ ያለው አይመስልም፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ...ቱ ከሚችቹ አንዱ ናት፡፡" በማለት ሉምባርድ መለሰ፡፡

...ኛው ማንባሬቸውን ጭጥረው "በርካታ ወንዶች ሚስቶቻቸውን በመግደል ...ጥረው ፊቱ ቀርበው አይቻለሁ፡፡ አብዛኞቹም በስተመጨረሻ ...ጀለኞች ሆነው አግኝቻቸዋለሁ" በማለት ተከራከሩት፡፡ በመቀጠል ...ምባርድ ተከራከሬቸው፡፡ "በርግጥ በተለያየ ምክንያት ሚስቶቻቸውን ...ደሉ ባሎችን አይቻለሁ፡፡ ሮጀርስም አንዱ የማይሆንበት ምክንያት ...ም፡፡ ነገር ግን ከራሱ ሚስት በመጀመር ፍትህ ለመስጠት ገድያ ...ሚፈፅመው አቶ እውን ማለት ሮጀርስ ነው የሚል እምነት የለኝም" ...ማለት ነበር ሉምባርድ ለሮጀርስ የተከራከረለት፡፡

...ኛው ክርክራቸውን ቀጠሉ፡፡ "በቂ ማረጋገጫ እስከሌለን ድረስ ባልና ...ስቱ ሮጀርስ ቀጣሪያቸውን ለመግደል አሲረዋል ለማለት አንችልም፡፡ ...ህንን መላምት ውድቅ ካደረግን ደግሞ ባልና ሚስቱ እንደሌሎቻችን ሁሉ ...ጠርጣሪ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ወ/ሮ ሮጀርስ ትናንት ማታ የተሸበረችው ...ናልባት የባሏን ቀጣይ እርምጃ በመገመት ሊሆን እንደሚችልም ...ገመት እንችላለን፡፡

"ስለዚህ ገዳዩ አቶ እውን ከእኛ መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል ማለት ...ው፡፡ ያለምንም ልዩነት ሁላችንም በቂ ተጠርጣሪ ነን" በማለት ሉምባርድ ...አረገጠ፡፡

ዳኛው ዋርግሬቭ በመቀጠል "በቀላሉ ለማስረዳት ያህል እኔ ያቀረብኩት ...ሳብ ተጠርጣሪዎችን መቀነስ የሚል ነው፡፡ ይህም ማለት ከመካከላችን ...ለአንቶኒ ማርስተን የሳይናይድ መርዝ የማይሰጡ ፣ ለወ/ሮ ሮጀርስ መጠት



t.me/OLDBOOKSPDF

ከፍ ያለ የእንቅልፍ መድሃኒት ሊሰጡ የማይችሉ እና ጀነራል ሊጋታ ከርሰቲ ሊገድሉ የማይችሉትን ከመካከላችን እንለይ፡፡" በማለት አስረዱ፡፡ ማካርተን

ብሎር ወደፊት ተንጠራርቶ "አሁን ገና ገባኝ የማሪስተንን ሞት በተመለከተ ትናንት ስንነጋገር መርዝ ሊጨምርበት የሚችል ሰው ከቤት ውጪ የነበረ ሊሆን እንደሚችል ደምድመናል፡፡ ነገር ግን እዚያው ክፍል ውስጥ የነበረ ሰው በቀላሉ መርዙን ብርጭቆው ውስጥ ሊጨምርበት ይችላል፡፡ ሮጀርስ ክፍል ውስጥ መኖሩን አላስታውስም፡፡ ነገር ግን ሌሎቻችን በሙሉ መርዙን መጨመር እንችላለን፡፡"

ብሎር ለአፍታ ያህል ትንፋሽ ወስዶ ቀጠለ፡፡ "ወ/ሮ ሮጀርስን በተመለከተ ደግሞ አጠገቧ የነበሩት ባሏ እና ዶ/ሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ እንዳቸው በቅፅበት
.

ዶ/ር አርመስትሮንግ ከወንበሩ ተፈናጥሮ በመነሳት "ተቃውሞ!" በማለት ጮሆ አቋረጠው፡፡ "ይሄ ፈፅሞ የተሳሳተ ነው፡፡ ለሴትየዋ የተመረዘ መድሃኒት እንደሰጠኋት በመሃላ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ" በማለት አስተባበለ፡፡

"ዶ/ር አርመስትሮንግ" የሚለው የዳኛው ቀዝቃዛ ድምፅ አቋረጠው፡፡ "ቁጣህ የሚጠበቅ ነው፡፡ ነገር ግን እውነታውን መቀበል እንዳለብ አስታውስ፡፡ ለሟቿ ከመጠን ያለፈ እንክብል ለመስጠት የተሻለ እድል የነበራችሁ አንተ እና ባሏ ሮጀርስ ናችሁ፡፡ አሁን ደግሞ ሌሎቻችን የነበረንንእድል እንመርምር፡፡ ሌሎቻችን ከተጠርጣሪነት ነጻ ነን ግልፅ ነው? አይመስለኝም" በማለት ዳኛው ከቤቱ መልስ ጠበቁ

ቬራ ቆጣ ብላ "እኔ ሴትየዋ አጠገብ እንዳልነበርኩ ሁላችሁም አይታችኋል" አለች

t.me/OLDBOOKSPDF

ማስታወስውን ልንገራችሁ፡፡ ከተሳሳትኩኝ አርሙኝ" በማለት ዳኛው ነገር ጀመሩ፡፡ "እንደማስታውሰው ወ/ር ሮጀርስን ሰፋ ላይ ያስተኟት ብሉስተን እና ሎምባርድ ሲሆን በመቀጠል የደረሰው ዶ/ር አርምስትሮንግ ነበር፡፡ ዶ/ሩ ባልየው አቶ ሮጀርስን ብራንዲ እንዲያመጣ ላከው፡፡ በመቀጠል ከየት እንደመጣ ያላወቅነውን ድምፅ ሰምተን ሁላችንም ወደ ሚቀጥለው ክፍል ሄድን፡፡ ራሷን ከሳተችው ወ/ሮ ሮጀርስ ጋር እዚሁ የቀሩት ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት ብቻ ነበሩ፡፡"

የወ/ሮ ኤሚሊ ጉንጭ ተንቀጠቀጠ፡፡ ሹራባቸውን መጥለፍ አቁመው ቀና በማለት "ፈፅሞ የተሳሳተ ነው!" በማለት ተቃወሙ፡፡

ተመልሰን ስንመጣ ሶፋው አጠገብ እጉንብበሰው ነበር"

"ሰብአዊ አዘኔታ ከመቼ ጀምሮ ነው ወንጀል የሆነው?" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ መልሰው ጠየቁ

ዳኛው ግምታቸውን ቀጠሉ፡፡ "በመቀጠል ሮጀርስ የታዘዘውን ብራንዲ ይዞ መጣ፡፡ በነገራችን ላይ ብራንዲው ውስጥ መድሃኒቱን ጨምሮ ሊሆንም ይችላል፡፡ በዶ/ሩ እና በባለቤቷ ተደግፋ ቀና ካለች በኋላ ብራንዲውን ጠጣች፡፡ ከዚያም ዶ/ሩ ወደ መኝታዋ ወሰዳት እና እንቅልፍ መድሃኒቱን ሰጣት፡፡"

ብሎር በፍጥነት ተቀበላቸው እና "በትክክል የሆነውን ነው የነገሩት፡፡ ስለዚህ እኔ ፣ ዳኛው ፣ ሎምባርድ እና ወ/ት ቬራ ነፃ ነን" በማለት ደመደመ፡፡

ዳኛው በቀዝቃዛ አይኖቻቸው እያዩት "እንደዚያ ነው? ከመደምደማችን በፊት መመልከት ያለብን ነገር አለ" አሉ፡፡

ብሎር ግራ ተጋብቶ "አልገባኝም" አለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኛው ቀጠሉ፡፡ "ለወ/ሮ ሮጀርስ ዶ/ሩ የሰጣት መድሃኒት ስራውን በጀመረበት ወቅት በከፊል እንቅልፍ ወስዷታል፡፡ በዚያ ቅፅበት ታዲያ አንድ ሰው የተወሰኑ እንክብሎችን ይዞ ክፍሏ በመግባት ዶ/ሩ እንድትውጠው ማዘዙን በመንገር ቢሰጣት ምንም አይነት ጥያቄ ሳታነሳ በእንቅልፍ ላይ ሳለች መድሃኒቱን ልትውጥ ትችላለች"

በመካከላቸው ለአፍታ ያህል ፀጥታ ሰፈነ፡፡ በመጨረሻም ፊሊፕ ሎምባርድ ተናገረ፡፡ "በዚህ መላ-ምት አልስማማም፡፡ ሁላችንም በወቅቱ ከዚህ ክፍል አልወጣንም ነበር፡፡ በዚያ ላይ የማርስተን ሞት እስከደነገጥን እዚሁ ደንዝዘን ተቀምጠን ነበር፡፡" በማለት ለማሳመን ሞከረ፡፡

"ሁላችንም ከተኛን በኋላ አንድ ሰው ምናልባትም ተነስቶ ወደ ጓዷ መኝታ ቤት ሊሔድ ይችላል"

"በፍፁም እንደዚያ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በዚያ ሰአት ሚ/ር ሮጀርስ አጠገቧ ይሆናል" በማለት ሎምባርድ የዳኛውን መላምት ውድቅ አደረገው፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ ነበር ምላሽ የሰጠው፡፡ "ሮጀርስ ምግብ የተበላበትን ጠረጴዛ ለማፅዳት ወደ እልፍኙ ወርዶ ነበር፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ማንም ሳያየው ወደ ጓዷ ክፍል መግባት ይችላል፡፡"

ወ/ሮ ኤሚሊ "ለመሆኑ የሰጠሃት መድሃኒት በዚያ ፍጥነት ያስተኛታል?" በማለት ዶ/ሩን ጠየቁት፡፡

"ህመምተኛውን በቅርበት የማናውቀው ከሆነ የመድሃኒቱን ውጤት ለመግለፅ ይከብዳል፡፡ አንዳንድ ህመምተኞች ላይ መድሃኒቱ በፍጥነት ለሲራ ሲችል ሌሎች ላይ ደግሞ ይዘገያል" በማለት ዶ/ሩ መለሰላቸው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ'ሱ ነው የተማርከው ፣ ዶ/ር?" በማለት ሎምባርድ ሲያሾፍ ግጥመው ከተሩ ፈቱ ቀላ፡፡ ሌላ ቃላት ከመናገሩ በፊት ግን የዳኛው ቀዝቃዛ ምፅ አቋረጠው፡፡

ሽሙጡን አቁመን ወደ ምክንያታዊ ግምታችን እንመለሳለን፡፡ ጊዜ በፊል ስመመን ውስጥ ሳለች ወ/ሮ ኤሚሊን ወይም ወ/ት ቬራን ከፍሏ ውስጥ ብታያቸው ላያስደነግጣት ይችላል፡፡ በተቃራኒው ግን እኔ ፣ ብሎር ወይም ሎምባርድ በክፍሏ ብንገኝ የተለየ ስሜት ይፈጥርባታል፡፡ እኔ ምገነው አሁንም ቢሆን ጊዜ ከፍሏ ውስጥ በተመለከተችው ሰው ለመደንገጧን እና ፈፅሞ ጥርጣሬ እንዳልተሰማት ነው፡፡" በማለት ዳኛው ደመደሙ፡፡

ብሎር ቀበል ብሎ "እና ይሄ ወደየት ይመራናል?" በማለት ጠየቀ፡፡

• • •

ዳኛው በተመሳሳይ ቀዝቃዛ ስሜት ውስጥ ሆነው መናገር ቀጠሉ፡፡ "ዛሬ ማለዳ ደግሞ ሁላችንንም ያስገረመ ሁለተኛ ሞት አጋጥሞናል፡፡ የጀነራሉን ሞት በተመለከተ ሁላችንም በግድያው ሰፍራ እንዳልነበርን ቃላችንን እንሰጣለን እንጂ መረጃ ማግኘት የምንችል አይመስለኝም፡፡ በዚህኛው ግድያ ማናችንም ከጥርጣሬ ነፃ እንዳልሆንን በመቀበል የየራሳችንን ነፃ መሆን እናስረዳ፡፡" በማለት ገልፀው ስለ ራሳቸው የግማሽ ቀን ውሎ መዘርዘር ጀመሩ፡፡

"እኔ በበኩሌ ማለዳውን በሙሉ ያሳለፍኩት በረንዳ ላይ ነበር፡፡ የምሳ ሰአት መድረሱን የሚጠቁመውን የሰሃን ደውል ከመስማቴ በፊት ከወንበሬ አልተነሳሁም ነበር፡፡ ነገር ግን በመሃል ወደ ባህሩ ዳርቻ በመሔድ ጀነራሉን ገድዬ ተመልሼም ሊሆን ይችላል፡፡ ሙሉውን ሰአት የተከታተለኝ ሰው



t.me/OLDBOOKSPDF

አልነበረም፡፡ ከበረንዳው ላይ አለመነሳቴን የሚመሰክረው የእኔ ቃል ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ላለመነሳቴ በቂ ማስረጃ መኖር አለበት፡፡"

ከዳኛው በመቀጠል ብሎር ተናገረ፡፡ "ማለዳውን ያሳለፍኩት ከዶ/ር አርመስትሮንግ እና ከሎምባርድ ጋር ነበር፡፡ እነርሱም ይህንን ይመሰክራሉ፡፡"

ዶ/ር አርመስትሮንግ ነጠቅ አድርጎ "ገመድ ልታመጣ ወደ ቤት ሄደህ ነበር" አለው፡፡ "ቀጥታ ወደ ቤት ሄጄ መመለሴን እኮ አይታችኋል" በማለት ብሎርተከራከረ፡፡

"ቤት ውስጥ ቆይተሃል" አለው ዶ/ሩ

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው ፤ ዶ/ር? ገመዱን ፈልጌ እኮ ነው ያመጣሁት" በማለት ብሎር ተቆጣ

"እኔ መቆየትህን ብቻ ነው የተናገርኩት" በማለት ዶ/ሩ ቀላል መልስ ሰጠው

"ብሎር ገመድ ለማምጣት በሄደበት ወቅት ሁለታችሁ አንድ ላይ ነበር የቆያችሁት?" በማለት ዳኛው ጠየቋቸው፡፡

"በአብዛኛው አብረን ነበር፡፡ ሎምባርድ ለደቂቃዎች ያህል ባልነበረበት ወቅትም ከቦታዬ አልተንቀሳቀስኩም" በማለት ዶክተሩ መለሰላቸው

ሎምባርድም ፈገግ ብሎ "ከደሴቷ ውጪ ላለው ምድር የነፀብራቅ ምልክት ለማሳየት የሚሆን ቦታ ፍለጋ ዞር ብዬ ነበር፡፡ አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ያህል ብቻ " በማለት አስረዳ፡፡

ዶ/ሩም በመቀጠል "ትክክል ነው፡፡ በዚያች ቅፅበት ውስጥ ግድያ መፈፀም እንደማይቻል ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ፡፡" አለ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ በወቅቱ ከሁለት አንዳችሁ ሰአት ተመልክታችሁ ነበር?" በማለት ዳኛው ጠየቋቸው፡፡

ዶ/ሩ አለመመልከቱን ሲናገር ሎምባርድ ደግሞ "ሰአት የለኝም" በማለት መለሰ፡፡

ዳኛውም ረጋ ባለ ድምፅ "አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ያላችሁት ግምት ተቀባይነት የለውም" አሏቸው፡፡ ጭናቸው ላይ ሹራብ ወደ ስቀመጡት ወይዘር በመዞር "ወ/ሮ ኤሚሊ?" በማለት ጠየቁ፡፡

"ከወይዘሪት ቬራ ጋር ስንሸራሸር ቆይቼ በመመለስ በረንዳው ላይ ተቀምጬ ፀሃይ ስሞቅ ነበር" በማለት መለሱ

"በረንዳው ላይ ግን አላየሁትም"

"ንፋሱ ስላስቸገረኝ በምስራቃዊ አቅጣጫ ነበር የተቀመጥኩት፡፡"

"እስከ ምሳ ሰአት እዛው ነበሩ?"

"አዎ"

"አንቺስ ቬራ?"

"ከወ/ሮ ኤሚሊ ጋር ከተያየሁ በኋላ እዚሁ አካባቢ ዞር ዞር ብዬ በኋላ ላይ ጀነራሉን ለማናገር ወረድኩ፡፡" በማለት ቬራ መለሰች፡፡

"ሰአቱ ስንት ነበር?"

"እኔ እንጃ፡፡ ከምሳ አንድ ሰአት በፊት ወይም ከዚያ በታች ይሆናል" በማለት ግልፅ ያልሆነ ግምቷን አቀረበች፡፡

ብሎር ጣልቃ በመግባት "እኛ ካገኘነው በኋላ ነበር ያናገርሽው?" በማለት ጠየቃት

"እሱን አላውቅም፡፡ ሳገኘው ግን በጣም ተረብሾ ነበር"

"ምን እንደረበሸው ጠይቀሽዋል?" ዳኛው ጠየቋት

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሁላችንም መሞታችን እንደማይቀር ነገረኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ስለፈራሁ በቀጥታ ወደቤት ተመለከስኩ፡፡ ከዚያም ከምሳ በፊት ወደ ጋር ዞሬ ነበር፡፡ ቀኑ እስኪያልቅ ነበር ዳኛው ጉንጫቸውን ዳበስ አድርገው "የሚቀረን የሮጀርስ ቃል ነው፡፡ ምን ያህል እንደሚጠቅመን ባላውቅም" በማለት ሮጀርስ እንዲናገር አዘዙ፡፡

ሮጀርስም ሙሉውን የማለዳ ግዜ ምሳ ለማዘጋጀት በስራው ተጠምዶ መቆየቱን እና በመስኮቱ በኩል እንኳን ወደ ውጪ አለመመልከቱን ተናገረ፡፡ በማያያዝም የምግብ ጠረጴዛው ላይ ከምሳ በፊት የነበሩት የቻይና አሻንጉሊቶች ቁጥር ስምንት እንደነበር በመሃላ አረጋገጠላቸው፡፡

የሮጀርስን ቃል ሰምተው እንዳበቁ በመካከላቸው ፀጥታ ሰፈነ፡፡ በመጨረሻም ዳኛው ለመናገር ጉሮሮአቸውን ሲጠራርጉ ሎምባርድ ወደ ቬራ ጠጋ ብሎ "የማጠቃለያ ንግግር ሊደረግ ነው" አላት፡፡

ዳኛው የማጠቃለያ ንግግራቸውን ጀመሩ፡፡ "የሶስቱን ሰዎች ግድያ በተለመለከተ ምክንያታዊ የግንኙነት መስመሮችን ለመመርመር ሞክረናል፡፡ አንዳንዶቹ በቀጥታ የሚጠቁሙን ተጠርጣሪ ቢኖሩም ግንንም ለመወንጀል የሚያስችል መረጃ አላገኘንም፡፡ ለግዜው እጅግ አደገኛ ገዳይ መሆኑን ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ከዋናው ምድር ጋር በመገናኘት እርዳታ እስከናገኝ ድረስ በደሴቷ ላይ የሚኖረን ቆይታ በየራሳችን ጥንቃቄ ላይ መመስረት አለበት፡፡

እስካሁን የተገደሉት ሶስት ሰዎች በቂ ማስጠንቀቂያ አልነበራቸውም፡፡ የቀረነው ግን ራሳችንን በየራሳችን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ቅድሙ ማስጠንቀቂያ ከትጥቅ እኩል ነው፡፡ በመሆኑም ለግዜው ነቅተን ራሳችንን እንጠብቅ፡፡" በማለት ዳኛው ንግግራቸውን ቋጩ፡፡

ሎምባርድም ዝግ ባለ ድምፅ "ችሎቱ በዚህ ይደመደማል" አለ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አስር

"ታምነዋለህ?" በማለት ቬራ ጠየቀችው፡፡ መስኮቱ አጠገብ ከሎምባርድ ጋ ተቀምጠው ንፋስ የቀላቀለውን አስፈሪ ዝናብ እየተመለከቱ ነበር፡፡

ዶክተር ዋርግሬቭ ገዳዩ ከመካከላችን አንዱ መሆኑን የተናገሩትን ነው" በማለት መልሶ ጠየቃት

"አዎ"

"ዳኛው ትክክል ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ለማመን "

"ለማመን ይከብዳል አይደል?" በማለት አቋረጠችው፡፡

"ሁሉም ነገር ይገርማል፡፡ ከጀነራሉ ሞት በኋላ ግን ቢያንስ ራሱን ገደለ ወይም በአደጋ ሞተ ማለት አቁመናል፡፡ ገድያ መፈፀሙን እርግጠኛ መሆን ችለናል፡፡ እስከ አሁንም ሶስት ተገድለዋል፡፡" አላት

ቬራ እየተንቀጠቀጠች "አስፈሪ ህልም የማይ ነው የመሰለኝ" አለች፡፡

ሎምባርድም በተመሳሳይ ፍራቻ ስሜት ውስጥ ሆኖ "ሁላችንም እንደዚያ ቢሆን ደስ ባለን፡፡ ለግዜው ግን ራሳችንን መጠበቅ ብቸኛው መንገድ እንደሆነ አስታውሺ" አላት፡፡

"ለመሆኑ ከእነርሱ መካከል ማንን ትጠረጥራለህ?"

"ሁለታችንን ነፃ ማድረግሽ ጥሩ ነው፡፡ እኔ ገዳይ አለመሆኔን አረጋግጥልሻለሁ፡፡ አንቺም የገዳይ አይን የለሽም፡፡ በንፁህነቴ በማመንሽ አንቺንም ማመን አለብኝ"

ቬራ ፈገግ ብላ "አመሰግናለሁ" አለችው፡፡ በማያያዝም "ሰው እንደማትገድል መናገርህን እምናለሁ፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ የቴፑ ቅጂ ያንተ ድምፅ አይደለም" በማለት በተራዋ የሎምባርድን ነፃ መሆን መሰከረች፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዲያውስ ሁለታችንን ከተጠርጣሪዎቹ ዝርዝር ውስጥ ካወጣን በቀጥታ ወደ ግምቴ ልሒድ፡፡ ገዳዩ አቶ እውን ማን ሊሆን ይችላል? ያለ ምንም ጥርጥር የእኔ ግምት ዳኛ ዋርግሬቭ የሚል ነው፡፡" በማለት ነገሬት

ቬራ በድንጋጤ እና አግራሞት ውስጥ ሆና "እንዴት እሳቸውን ጠረጠርክ?" አለችው

"በቀላሉ ማስረዳት ያስቸግረኛል፡፡ ነገር ግን ሽማግሌው ለአመታት በዳኝነት ሰርቷል፡፡ በብዙ ሰዎች ላይ ሲፈርድ መኖሩ ምናልባትም በሰው ልጅ ነብስ ላይ ስልጣን እንዳለው እንዲሰማው አድርጉታል፡፡ ስለዚህ አንድ እርምጃ ወደፊት በመራመድ ራሱን ፈራጅ እና ፍርድ ፈፃሚ አድርጉ ተመልክቷል"

"ሊሆን ይችላል" አለች

"አንቺስ ማንን ትጠርጥሪያለሽ?"

"ዶ/ር አርመስትሮንግን" በማለት ስትመልስለት በአግራሞት አፏዉና "እንዴት ጠረጠርሽው? እኔ በበኩሌ የመጨረሻው ተጠርጣሪዬ እሱ ነው" አላት፡፡

ቬራ ራሷን በአሉታ አወዛወዘች፡፡ "ሁለቱ ሰዎች በመርዝ ነው የተገደሉት፡፡ ይሄ በቂ መረጃ ባይሆን እንኳን ወ/ሮ ሮጀርስን በእንቅልፍ ኪኒን ያስተኛት ዶ/ሩ ነው፡፡" አለችው

"ትክክል ነሽ"

"በዚያ ላይ ዶክተሮች የአእምሮ መታወክ ቢያጋጥማቸው እንኳን አያስታውቁም፡፡ ከስራቸው አድካሚነት አንፃር ደግሞ ያጋጥማል፡፡" በማለት አስረዳችው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"ነገር ግን ጀነራሉን እሱ ገድሎታል ማለት አይቻልም፡፡ ከእኔ አጠገብ ዘይደበት ቅፅበት ገድሎት ሊመጣ አይችልም፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ሰው ለመግደል የሚያስችል ስልጠናም ሆነ ልምድ ያለው አይመስለኝም" በማለት ተከራከረች፡፡

"በዚያ ቅፅበት ባይገድለውም በኋላ ላይ ግን ግዜ አግኝቷል" አለች

"መቼ?"

"ምሳ እንደቀረበ ሊነግረው ሲሄድ"

ሎምባርድ በድጋሚ በአግራሞት አፏጨ፡፡ "በዚያ ግዜ እንደገደለው ታምኛለሽ? ይገርማል" አላት፡፡

"ምን የሚያሳስበው ነገር አለ? ብቸኛው ሃኪም እሱ ነው፡፡ ጀነራሉ ከአንድ ለሊት በፊት እንደተገደለ ማረጋገጫ ቢያቀርብ ማን ይከራከረዋል?" በማለት መልሳ ጠየቀችው፡፡

" በጣም ይገርማል፡፡ እንዴት አሰብሽው?"

• • •

"ማን ሊሆን ይችላል ሚስተር ብሎር?" በማለት አስተናጋጁ ሮጀርስ ጠየቀው፡፡

"የሁላችንም ጥያቄ እርሱ ነው፡፡ ከመካከላችን አንዱ የሞት ጌታ ነው፡፡ ይህ ሰው ማን ይሆን?" በማለት የቀድሞው ወንጀል መርማሪ ብሎር በጥያቄ መለሰለት

"ግን አንተ የሆነ ፍንጭ አለህ አይደል?" በማለት ግራ የተጋባው አገልጋይ ጠየቀው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም፡፡ እንደ ግምቴ ከሆነ ግን ስውየው ከእንግዶችህ መካከል በጣም የተረጋጋው እንደሚሆን ይሰማኛል" በማለት ብሎር መለሰለት

ሮጀርስ የግምባሩን ላብ በመዳፉ እየጠራረገ "ይሔ ነገር ህልም ቢሆን ደስ ባለኝ " በማለት ግራ ተጋብቶ ብሎርን አየው፡፡

"ለመሆኑ በውስጥህ የሆነ ፍንጭ ነገር አለህ?" በማለት ብሎር ጠየቀው፡፡

"የበለጠ ያስፈራኝ እኮ ምንም አይነት ፍንጭ ማጣቴ ነው፡፡" በማለት ሮጀርስ መለሰለት፡፡

• • •

ዶ/ር አርመስትሮንግ መረጋጋት አቃተው፡፡ "በየትኛው መንገድ ከዚህ ደሴት መውጣት ይኖርብናል፡፡" በማለት ተናገረ፡፡

ዳኛ ዋርግሬቭ በመነፅራቸው አናት በኩል እየተመለከቱት መለሱለት፡፡ "የአየር ሁኔታ ትንበያ ባልሆንም በዚህ አየር ምንም አይነት ጀልባ ወደዚህ ሊመጣልን የሚችል አይመስለኝም፡፡ ቢያንስ ለሃያ ሰአታት ያህል እዚሁ መቆየታችን የግድ ነው፡፡"

ዶ/ሩ የበለጠ ተርበተበተ፡፡ "ስለዚህ በየአልጋዎቻችን ውስጥ ሳለን ተራ በተራ መገደላችን ነዋ?"

. "እንዳንሞት ተስፋ ማድረግ አለብን፡፡ በተቻለን መጠን በቂ ጥንቃቄ እንድናደርግ አስጠነቅቃችኋለሁ " በማለት ዳኛው እየቀፈፋቸው መለሱለት፡፡ በእርጅና እድሜያቸው እንኳን ሞትን መፍራታቸው አስገረመው፡፡ በህክምና ስራው የተመለከታቸው በርካታ አዛውንት ሀመግ ላለመሞት የሚያደርጉት ትግል ከወጣቶች የበለጠ መሆኑን በተደጋጋሚ ተመለከቶ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እስከ አሁን ድረስ ብቻ ሶስት ሰዎች መገደላቸውን አስታውሱ" በማለት ዶ/ሩ ዳኛውን ተከራከራቸው፡፡

ትክክል ነህ፡፡ ነገር ግን ሶስቱንም ያስጠነቀቃቸው ሰው እንዳልነበረ ትርሳ፡፡ እኛ ግን ቢያንስ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ደርሶናል፡፡" በማለት ዳኛው መለሱለት፡፡

"ለማንኛውም እንዴት ነው መጠንቀቅስ የምንችለው? በዚያ ላይ ገዳዩን እንኳን ብናውቅ" በማለት ዶ/ሩ በጭንቀት ጠየቀ፡፡

"ገዳዩን አናውቅም ማለት እንኳን አንችልም" በማለት ዳኛው አወዛጋቢ መልስ ሲሰጡት ዶ/ሩ አፍጥጦ እየተመለከታቸው፦

"አውቃለሁ እያሉኝ ነው?" ሲል ጠየቃቸው፡፡

ዳኛው በጥንቃቄ ቃላት መርጠው መለሱለት፡፡ "በቂ መረጃ ባይኖረኝም እስከ አሁኑን አጠቃላይ ሁኔታ በመገምገም አንድ ተጠርጣሪን መለየት ችያለሁ፡፡"

ዶ/ሩ አሁንም አፍጥጦ እያያቸው "አልገባኝም" አለ

• • •

ወ/ሮ ኤሚሊ ብሬንት መኝታ ቤታቸው ውስጥ ከመስኮቱ አጠገብ ተቀምጠው መፅሃፍ ቅዱስ ለማንበብ ሞከሩ፡፡ መረጋጋት ስላቃታቸው መፅሃፍ ቅዱሱን ዘግተው ከመሳቢያቸው ውስጥ ጥቁር ሽፋን ያለውን የግል ማስታወሻ አውጥተው መፃፍ ጀመሩ፡፡

"አስፈሪ ነገሮች እየተከሰቱ ነው፡፡ ጀነራል ማካርተር ሞተ፡፡ የጀነራሉን የአጎት ልጅ ኤልሲ ማክፋርሰንን እንዳገባ አስታውሳለሁ፡፡

"ጀነራሉ በሰው እንደተገደለ አልጠራጠርም..."



t.me/OLDBOOKSPDF

ከምሳ በኋላ ጡረተኛው ዳኛ ሲናገር ገዳዩ ከመካከላችን እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

ይህም እንዳችን ላይ ሰይጣን ሰፍሮብናል ማለት ነው፡፡ የእኔም ግምት ይኸው ነበር፡፡ ሁሉም ማን ሊሆን እንደሚችል አያውቁም፡፡

እኔ ግን አውቃለሁ.....

እጃቸው ሲንቀጠቀጥ ነበር ወ/ሮዋ መፃፍ ያቋረጡት፡፡ እጃቸው እንደሰካራም ዛለ፡፡ ጣቶቻቸው እርሳሱን መያዝ አልቻሉም ነበር፡፡ በሚንቀጠቀጥ እጃቸው እንደምንም ታግለው የጀመሩትን ዓ.ነገር ጨረሱት፡፡ "...የገዳዩ ስም ቢትሪስ ታይለር ነው፡፡" የመዝጊያውን አረፍተ ነገር እንደፃፉ አይኖቻቸው ተከደኑ፡፡ ከእፍታ በኋላ ከገቡበት ቅዐብታዊ ሰመመን በርግገው ሲወጡ የፃፉትን ነገር ተመለከቱት፡፡

በድንጋጤ ማስታወሻው ላይ አፈጠጡ፡፡ "እኔ ነኝ ይህንን የፃፍኩት? እያበድኩ መሆን አለበት፡፡" በማለት ለራሳቸው በማይሰማ የፍርሃት ድምፅ እንሾካሾኩ፡፡

• • •

ንፋሱ የበለጠ እየበረታ ቀጠለ፡፡ የባህሩ ማዕበል ድምፅ እና ከቤቱ ግድግዳ ጋር የሚላተመው አውሎ ንፋስ ያስፈራ ነበር፡፡ ሁሉም ሰዎች ሰፊው ሳሎን ጥግ ላይ ካለው ጠረጴዛ ዙሪያ ተጠጋግተው ተቀምጠዋል። እርስ በርሳቸው ከመተያየት ሌላ ቃላት ለመለዋወጥ እንኳን አልደፈሩም።

በመሃል ሮጀርስ ሻይ ይዞላቸው ሲገባ ሁሉም ከወንበራቸው በመነሳት ነበር የተቀበሉት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

'መጋረጃዎቹን ሊመልሳቸው፡፡ መብራት ቢበራ ደግሞ የተሻለ ይመስለኛል፡፡' በማለት አገልጋይ ሮጀርስ የእነርሱን መልስ ሳይጠብቅ መጋረጃውን በመልቀቅ መብራት ሲያበራ ሳሎኑ ነብስ ዘራ፡፡

ቬራ በትህትና 'ወ/ሮ ኤሚሊ ሻዩን ይቀዱልናል?' በማለት ጠየቀቻቸው፡፡

'አንቺው ብትቀጂው ይሻላል የእኔ ልጅ፡፡ የሻይ ጀበናውን ለመያዝ የሚበቃ ጉልበት የለኝም፡፡ በዚያ ላይ ሹራብ የምሰራበት ኪሮሽ ጠፍቶብኝ ተናድጃለሁ' በማለት መለሱላት፡፡

ቬራ ለሁሉም ሻይ ቀዳችላቸው፡፡ በመካከላቸውም የቀድሞው ሞቅ ያለ ጨዋታ ቀስ በቀስ ተመለሰ፡፡ ሎምባርድ እና ብሎር ሻዩን ሲያዳንቁ ዶ/ር አርመስትሮንግ ደግሞ የተለያዩ ቀልዶችን አወራላቸው፡፡ በደህናውም ቀን ሻይ የማይወዱት ዳኛ ዋርግሬቭ አንድ ስኒ መጠጣቱ ጥሩ ስለመሰላቸው ከሌሎቹ ጋር ተመሳሰለዋል፡፡

በሞቀ ጨዋታቸው መካከል ሮጀርስ እየተጣደፈ ገባ፡፡ ፊቱ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ ይታይበታል፡፡

"ይቅርታ ጌቶች፡፡ የመታጠቢያ ቤቱን መጋረጃ ያየ አለ?" በማለት ሲጠይቃቸው ሎምባርድ ቀና ብሎ እየውና "የምን መጋረጃ ነው ሮጀርስ?" ሲል ጠየቀው፡፡

"የመታጠቢያ ቤቱ መጋረጃ በቦታው የለም ጌታዬ፡፡ ጠፍቷል"

"ጠዋት ነበር" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ አገልጋዩን ጠየቁት

"አዎን ጌታዬ"

"ምን አይነት መጋረጃ ነበር?" ብሎር ጠየቀው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሣምራዊ የሃር መጋረጃ ነበር ጌታዬ፡፡ ቀለሙ ከግድግዳው እና ከወለሉ ጋር ይመሳሰል ነበር-"

"እና አሁን የለም እያልክ ነው?" ሎምባርድ ደግሞ በተራው ጠየቀ፡፡

"አዎ ጌታዬ የለም"

"ተወው ይጥፋ ፤ አትጨነቅ፡፡ ቢያንስ በመጋረጃ ሰው አይገደልም፡፡ እርሳው" በማለት ብሎር ሲናገር ሮጀርስ ጉንበስ ብሎ "እሺ ጌታዬ አመሰግናለሁ፡፡" በማለት በሩን ከኋላው ዘግቶ ወጣላቸው፡፡

የሮጀርስን መውጣት ተከትሎ አስፈሪው ፀጥታ በመካከላቸው ነገሠ፡፡ በድጋሚ እርስ በርሳቸው ተፋጥጠው ተቀመጡ፡፡

• • •

ራት የተመገቡት በግዜ ነበር፡፡ ሶስት ሰአት ከመሆኑ በፊትም ሁሉም ተነስቶ በመካከላቸው አስፈሪው ፀጥታ ቀጠለ፡፡

"መተኛት እፈልጋለሁ" በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ወደመኝታ ክፍላቸው ለመሄድ ሲነሱ ቬራም ለመተኛት ወስና ተከተለቻቸው፡፡ ሴቶቹን ወደ ክፍላቸው ለመሸኘት ሎምባርድ እና ብሎር ከኋላ ተከተሏቸው፡፡ ሴቶቹ በየክፍሎቻቸው በመግባት በራቸውን ሲቆልፉ ሰሙና ወንዶቹ ወደ ሳሎን መመለስ ጀመሩ፡፡

"በራቸውን መቆለፋቸው ጥሩ ነው" በማለት ብሎር ደረጃውን መውረድ ሲጀምር ከኋላው የተከተለው ሎምባርድ ሳቅ ብሎ፡-

"ቢያንስ ለዚህ ምሽት ደህና ናቸው" አለ፡፡

• • •

አራቱ ወንዶች ወደ መኝታ ክፍሎቻቸው ለመሄድ የተነሱት በአንድ ላይ ሆነው ነበር፡፡ ሮጀርስ ሳሎኑ ውስጥ ለቁርስ የሚሆኑ መመገቢያ ሳህኖችን



t.me/OLDBOOKSPDF

የደረደረ አራቱ ደረጃውን ሲወጡ ተመለከታቸው፡፡ አንደኛው ፎቅ ላይ ደርሱ አራቱም ቆመው ሲያወሩ ሳሎኑ ውስጥ ሆኖ ይሰማቸው ነበር፡፡

ዳኛ ዋርግሬቭ ከፍ ባለ ድምፅ "ሁላችሁም በራችሁን ቆልፉ" በማለት ሲናገሩ ይሰማል፡፡

ብሎርም በተመሳሳይ ድምፅ "ቁልፉ ሊከፈት ስለሚችል ወንበር ማስደገፉ ይከፋም" በማለት አከለ፡፡

"ብሎር ትልቁ ችግር ብዙ ነገር ማወቁ ነው" በማለት ሎምባርድ አሽሟጠጠ፡፡

"ብሉ ደህና እደሩ፡፡ በጠዋት ለመገናኘት ያብቃን" በማለት ዳኛው ወደ ክፍላቸው ሲገቡ የቀሩትም በየክፍላቸው ገብተው በራቸውን ከውስጥ ሲቆልፉ ሮጀርስ የነበረበት ሳሎን ድረስ ይሰማ ነበር፡፡

ሁሉም ነገር ለቁርስ ዝግጁ መሆኑን በማረጋገጥ ነበር ሮጀርስ ከሳሎኑ ለመውጣት የተዘጋጀው፡፡ የምግብ ጠረጴዛው ላይ በመስተዋት ሰሃን ላይ የተቀመጡትን የቻይና አሻንጉሊቶች ተመለከታቸው፡፡ ቁጥራቸው ሰባት ነበር፡፡

"ዛሬ ማታ ድብብቆሽ የሚጫወት የለም ማለት ነው " በማለት በረጅሙ ተነፈሰና የሳሎኑን በር ከኋላው ዘግቶ ወደ አዲሱ መኝታ ክፍሉ አመራ፡፡ የበሩን ቁልፍ ጃኬቱ ኪስ ውስጥ ከተተ፡፡

መኝታ ቤቱ ቀለል ያለ እይታ ነበረው፡፡ ሰው ሊደበቅበት የሚችል ስፍራ ቢኖር የቁም ሳጥኑ ነበር፡፡ ሮጀርስም የቁም ሳጥኑ ባዶ መሆኑን አረጋግጦ እንደጨረሰ ለመተኛት ተሰናዳ፡፡

"የህንድ ሸወዳ ጨዋታ ዛሬ እንደሌለ አረጋግጫለሁ...." በማለት በረጅሙ ተንፍሶ ለመተኛት ተደላደለ፡፡

• • •



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አስራ አንድ

ፊሊፕ ሎምባርድ ፀሃይ ከመውጣቷ በፊት ከእንቅልፉ የመንቃት ልምድ ነበረው፡፡ እንደ ሁሌው በጠዋት ነቅቶ ከአልጋው ወረደና ወለሉ ላይ በርከክ በማለት ከውጪ የሚሰማ ድምፅ እንዳለ ለማጣራት ሞከረ፡፡ ሃይለኛው ንፋስ ከምሽቱ በበለጠ እየጨኸ ነበር፡፡ የዝናብ ድምፅ ግን አልተሰማውም.....

ከጠዋቱ ሁለት ሰአት አካባቢ ንፋሱ ሃይሉን ጨምሮ እያፏጨ ነበር፡፡ ነገር ግን ሎምባርድ ተመልሶ ስለተኛ ድምፁን አልሰማውም፡፡ ሶስት ሰአት ተኩል ላይ ከእንቅልፉ ነቅቶ የአልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጠ ሰአቱን ተመለከተ፡፡ ሰአቱን ወደ ጆሮው አስጠግቶ በማዳመጥ መስራቱን አረጋገጠ፡፡ የታችኛው ከንፈሩን ነክሶ ለአደን እንደተዘጋጀ ተኩላ በሙሉ ንቃት ላይ ሆኖ ከአልጋው ላይ ተነሳ፡፡ ለሌላ ሰው የሚያወራ ይመስል በትህትና እንዲህ አለ፦

"ለዚህ ነገር ምላሽ የምንሰጥበት የእንቅስቃሴ ግዜ የደረሰ ይመስለኛል፡፡"

ለአራት ሃያ አምስት ጉዳይ ሲሆን ሎምባርድ የተዘጋው የብሎር መኝታ ቤት በር አጠገብ ደርሶ አንኳኳ፡፡ ብሎር በሩን ከፈተለት፡፡ የብሎር አይኖች ከመቅላታቸውም በላይ የሚገለጡት በትግል ነበር፡፡

ሎምባርድ ወዳጃዊ ፈገግታውን አስቀድሞ "ቀኑን ሙሉ ልትተኛ ነበር? እንዴት ደልቶሃል ፤ ወዳጄ" አለው፡፡

"ምን ሆነሃል?" በማለት ብሎር ገርበብ ባሉ የጠዋት አይኖቹ እያሉ ተመለከተው፡፡

"ለመሆኑ ከነጋ የቀሰቀሰህ ወይም ሻይ ያመጣልህ ሰው ነበር? ስንት ሰአት እንደሆነስ እውቀሃል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎር ከአሊጋው አጠገብ ያለውን የትራስጌ ሰአት ተመለከተ፡፡ "የፈጣሪ ያለህ እስከዚህ ሰአት ተኝቻለሁ?" በማለት ተገርሞ ጠየቀውና መልስ ከማግኘቱ በፊት "ምነው ሮጀርስ የለም እንዴ? እንዴት ሳይቀሰቅሰኝ?" በማለት እየተጨናበሰ ሎምባርድን ጠየቀው፡፡

"አሁን ገና እየነቃህ ነው" በማለት ሎምባርድ ፈገግ ብሎ መለሰለት ፡፡

"ምን እያልከኝ ነው?" ብሎር ግራ ተጋብቶ ጠየቀው፡፡

"ሮጀርስ ጠፍቷል፡፡ ክፍሉም ሆነ ማብሰያው ክፍል ውስጥ የለም፡፡ የተጣደ ነገር የለም፡፡ ምድጃው እንኳን አልተለኮሰም" በማለት ሲመልስለት ብሎር ደንገጥ አለ፡፡

"የት ሄዶ ሊሆን ይችላል" ምናልባት ወጣ ብሎ "

ሎምባርድ መልስ ሳይሰጠው በሩ ላይ እንደቆመ አለፈውና ወደ ሌሎቹ መኝታ ቤቶች አመራ፡፡ አርመስትሮንግ ከእንቅልፉ ተነስቶ በመለባበስ ላይ ሲሆን ዳኛ ዋርግሬቭ ግን እንደ ብሎር ከእንቅልፋቸው ጋር እየታገሉ ነበር፡፡ ቬራ ክሌይትሮን ልብሷን ለብሳ ነበር ያገኛት፡፡ የወ/ሮ ብሬንት መኝታ ቤት ግን ባዶ ነበር፡፡

በአንድ ላይ ሆነው ፍለጋውን ተያያዙት፡፡ የሮጀርስን ክፍል ሲመለከቱት አልጋው ሰው እንዳደረበት ያስታውቅ ነበር፡፡ የጺም መላጫውን እና ሳሙናውንም በቅርብ ሰአት የተጠቀመባቸው ሲሆን ፊቱን ያደረቀበት ፎጣም እርጥብ ነበር፡፡

"ከአልጋው በሰላም ወርዷል›› አለ ሎምባርድ

ቬራ በፍርሃት ተሞልታ ዝቅ ባለ ድምፅ "የሆነ ቦታ ተደብቆ እየጠበቀ ሊሆን አይችልም?" በማለት ጠየቀች፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

'ሊሆን ይችላል ፤ የእኔ ቆንጆ፡፡ እስከምናገኘው ድረስ ግን ሁላችንም በአንድ ላይ ብንሆን የተሻለ ነው፡፡' በማለት ሎምባርድ አስጠነቀቃቸው፡፡

አርመስትሮንግ 'ከቤት ውጪ የሆነቦታ ይሆናል' በማለት እንደተናገረ ሎምባርድ ልብሱን እያስተካከለ መጥቶ ተቀላቀላቸው፡፡

'ለመሆኑ ወ/ሮ ኤሚሊስ የት ናቸው?'

ሶስቱ እየተከታተሉ ወደ ሳሎን ለመሔድ መተላለፊያው አጠገብ ሲደርሱ ወ/ሮ ኤሚሊ የፊተኛውን በር ከፍተው ገቡ፡፡ የለበሱትን የዝናብ ልብስ እያወለቁ ሶስቱን ቀና ብለው አዩና

"ማዕበሉ እንደቀጠለ ነው፡፡ ዛሬ ምንም አይነት ጀልባ የሚመጣ አይመስለኝም፡፡" አሉ፡፡

"ወ/ሮ ኤሚሊ ብቻዎትን ደሴቷ ላይ መዘዋወሩ አያስፈራዎትም? በማለት ብሎር ጠየቃቸው፡፡

"ምን ያስፈራኛል? ከርቀት የማየት ችሎታዬ ዛሬም አብሮኝ አለ ፤ አቶ ብሎር" በማለት ወ/ሮዋ ቆፍጠን ያለ መልስ ሰጡት፡፡

"ምናልባት ሮጀርስን ከርቀት አይተውት ይሆን?"

ወ/ሮዋ ትንድባቸውን ወደ ላይ ሰቅለው "አላየሁትም፡፡ ምነው?" በማለት ገራ የተጋቡ መሰሉ፡፡

በዚህ መሃል ነበር ዳኛው ጀስቲስ ዋርግሬቭ ጺማቸውን ተላጭተው እና ሰው ሰራሽ ጥርሳቸውን አጥልቀው የደረሱት፡፡ ደረጃውን በመውረድ ወደ ሳሎኑ በር አመሩ፡፡

"ጠረጴዛው ለቁርስ ተዘጋጅቷልና" ዳኛው ወደ ሳሎን እንደገቡ ነበር ከኋላ ለተከተሏቸው የገለፁት፡፡

"ግታ አዘጋጅቶት ሊሆን ይችላል" በማለት ሎምባርድ ንግግሩን አቋረጠ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF
Scanned by TapSca

ሁሉም በየአቅጣጫው ሰፊው ሳሎን ውስጥ መዘዋወር ያዙ፡፡ ጠረጴዛው ላይ ሰሃን እና የሻይ ብርጭቆዎች በአግባቡ ተደርድረዋል፡፡ ዳኛ ዋርግሬቭ ምግብ ጠረጴዛው አጠገብ ቆመው ቁልቁል ሲመለከቱ ከኋላቸው ቆማ ነበረችው ቬራ በድንጋጤ አንዳቸውን ያዘቻቸው እና ክፍሉን በሚሞላ ጩኸት "ተመልከቱ! አሻንጉሊቶቹን!" በማለት አምባረቀች፡፡

ጠረጴዛው መሃል ላይ የነበሩት የቻይና አሻንጉሊቶች ቁጥር ስድስት ብቻ ነበር፡፡

• • •

ከጥቂት ፍለጋ በኋላ ነበር ሮጀርስን ያገኙት፡፡ ከዋናው ቤት ጀርባ ከሚገኘው የልብስ ማጠቢያ ክፍል ውስጥ ለማገዶ የሚሆን እንጨት ለመፍለጥ ገብቶ ነበር፡፡ አነስተኛ መጠን ያለውን መጥረቢያ በእጁ እንደያዘ ሲሆን ሌላ ትልቅ መጥረቢያ ደግሞ ከጀርባው ገርበብ ያለው በር ላይ ተደግፎ ነበር፡፡ የመጥረቢያው ስለት እስከ ግማሽ ድረስ ደም ተቀብቷል፡፡ የቅቡ መጠን መጥረቢያው ሮጀርስ ጭንቅላት ላይ የጠለቀበትን ርቀት ያከላል፡፡

• • •

"ግልፅ ነው፡፡ ገዳዩ ከጀርባው ሆኖ አንድ ግዜ ብቻ ነበር በመጥረቢያው ስለት የሮጀርስን የራስ ቅል የመታው፡፡ ከዚያም ሮጀርስ ሲንበረከክ ወይም ሲወድቅ መጥረቢውን ነቀለው" በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ የሬሳ ምርመራ ውጤቱን ገለፀ፡፡

ብሎር በበኩሉ ከምግብ ማብሰያው ክፍል ያገኘውን የዱቄት ወንፊት በመጠቀም ትልቁ መጥረቢያ እጀታ ላይ የእጅ አሻራ መኖሩን እተመለከተ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጉዳቱን ለማድረስ ከፍተኛ ጉልበት አስፈልጎ ነበር፤ ዶ/ርም በማለት ጳኛ ዋርግሬቭ ጠየቁ፡፡

"ምን ማለትዎ እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ አንዲት ሴት በቀላሉ ልታደርገው ትችላለች" በማለት ዶ/ር አርመስተሮንግ ወደ ኋላ ዞሮ በርቀት ያሉትን ቬራ እና ወ/ሮ ኤሚሊ በመመልከት ድምፁን ዝቅ አድርጎ ቀጠለ፡፡ "ወጣቷ ልጅ የተሻለ ጥንካሬ ቢኖራትም ወ/ሮ አሜሊም በቀላሉ ሊያደርጉት እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ ሰይጣናዊ ድርጊት ለመፈፀም ዝግጁ ከሆነ ደካማ አካልን የሚያበረታ ሃይል ከየትም ይመጣል፡፡"

ብሎር የመጥረቢያውን እጀታ በጠቅጣቃው ወንፊት ውስጥ ለመዉረጃ ግዜ አትኩሮ ተመለከተና ቀና አለ፡፡

"ምንም አይነት አሻራ የለበትም፡፡ ገዳዩ እጀታውን ጠራርጎ ሳያስቀምጠው አይቀርም፡፡"

በድንገት የቬራ ሃይለኛ ጩኸት አካባቢውን አደባለቀው፡፡ ወንዶቹ ወደ እርሷ ሮጡ፡፡ "እዚህ ደሴት ላይ ንብ አለ? የንብ ቀፎስ? ለመሆን ማር የሚያገኙት ከየት ነው?" በማለት ለሁሉም ትርጉም ያልሰጣቸውን የንብ ቀፎ ወሬ በጩኸት ቀጠለች፡፡

ሁሉም ግራ ተጋብተው አፍጥጠው እየተመለከቷት ነበር፡፡ ቬራ የበለጠ ተናደደችባቸው፡፡ ለምን እኔ ላይ ታፈጥላችሁ? እንደ እብድ አትመልከቱኝ" በድጋሚ ብትጮህባቸውም ግራ እንደታጋቡ ነበር የሚያይዋት፡፡ ንብ እና የንብ ቀፎ እኮ ነው የምላችሁ አሁንም አልገባችሁም በየመኝታ ቤታችሁ ግድግዳ የተሰቀለላችሁን ግጥም አላነበባችሁትም እንዴ

"ሰባቱ ልጆች እንጨት ሲፈልጡ ፤"

"አንዱ ራሱን ሲፈልጥ ስድስቱ አመለጡ፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሿራ የግጥሙን ሁለት ስንኞች በቃሏ አነበነበችላቸው፡፡ ግራ የተጋቡት ሰዎች ላይ በቁጣ አፈጠጠችና ፡- ግጥሙን ሙሉ በሙሉ በቃ ደገምለሁ፡፡

ቀጣዩን ስንኝ ልበልላችሁ

ስድስቱ ልጆች በንብ ቀፎ ሲጫወቱ

አንዱ ሲነድፍ ተረፉ አምስቱ፡፡

አሁንስ ገባችሁ የንብ ቀፎ የት እንዳለ የጠየቅኋችሁ ለዚሁ ነበር፡፡ ይሄ ነገር ቀልድ መሆን አለበት.... ቀልድ... ድምጿ እየቀነሰ በአንገቱ ደገሞ የአገራሞት ሳቅ እየሳቀች ነበር፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ አንገቷን ዳበስ አድርጎ በለስላሳ ቃላት እንድትረጋጋ አበረታታት፡፡ በመጨረሻም በረጅሙ ተንፍሳ አመሰግናለሁ ዶ/ር፡፡ አሁን ደህና ነኝ በማለት ራሷን ተቆጣጠረች፡፡ ከደቂቃ በኋላም ወደ ምግብ ማብሰያ ክፍል በመሔድ እየተዘጋጀች እኔና ወ/ሮ ኤሚሊ ቁርስ እንስራለን፡፡ የማገዶ እንጨቱን ልታመጡልን ትችላላችሁ አለቻቸው፡፡ ቬራ ስትሔድ የዶ/ሩ የእጅ ምልክት ጉንጯ ላይ ተቀምጦ ነበረ፡፡ የሮጀርስን አስከሬን በነካካበት እጁ ነበር ሲያባብላት የነካት፡፡

ዶ/ር ጥሩ የማረጋጋት ችሎታ አለህ- አለው ብሎር

ዶ/ሩ ቬራን ደም በማስነካቱ የይቅርታ አስተያየት እያየው ነበር የመለሰለት፡፡ በዚህ ችግር ላይ ወፈፈነት ከተጨመረ ከባድ ይሆንብናል ብዬ እኮ ነው፡፡

ወፈፌ እንኳን አትመስለኝም፡

ጤነኛ ናት፡፡ ማንም ላይ ሊደርስ የሚችል ድንገተኛ መታወክ ነው ያጋጠማት፡፡ በማለት ዶ/ሩ የብሎርን ግምት አጠናከረለት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮጀርስ ከመሞቱ በፊት በቂ የማገዶ እንጨት ፈልጦ ነበር፡፡ ቬራ እና ወ/ሮ ኤሚሊ ለወንዶቹ ቁርስ ለማድረስ ተፍ ተፍ ማለቱን ተያያዙት፡፡ ቬራ ስጋ ስትከትፍ ወ/ሮዋ ደግሞ እሳት ለማቀጣጠል እየታገሉ ነበር፡፡ ቶና ብለው ወንዶቹን እየት አደረጉና አይዟችሁ በግማሽ ሰአት ውስጥ ይደርሳል በማለት አፅናኗቸው፡፡

የቀድሞው ወንጀል መርማሪ ብሎር ድምፁን ዝቅ አድርጉ ምን እየውብኬ እንደሆነ ትገምታለህ በማለት ሎምባርን ጠየቀው፡፡

ንገረኝ እስኪ

መርማሪው ነገሮችን በአጭሩ መግለፅ አይሆንለትም ነበር፡፡ ረጅም ገለፃውን ለመጀመር በረጅሙ አየር ሳበ፡፡

አሜሪካን ውስጥ ስለተከሰተ አንድ ወንጀል የሰማሁት ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ሽማግሌ ባልና ሚስቶች በመጥረቢያ ይገደላሉ፡፡ በወቅቱ ቤት ውስጥ የኖበሩት የቤት ሰራተኛዋ እና ያላገባችው የማቾች ሴት ልጅ ነበሩ፡፡ በማለት አየር ወሰደና ቀጠለ፡፡

ኩሽና ውስጥ መጥረቢያውን ስመለከት ያቺን ያላገባች ሴት ምስል ተመለከትኩኝ፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ የእኛዋን ወጣት ቬራ በድንገት ወፈፍ አደረጋት እና ጮኸች፡፡ ጩኸት የሚገመት ነበር፡፡ አይመስልህም

ሎምባርድ አጭር መልስ ሰጠው ሊሆን ይችላል፡፡

ብሎር ትንተናውን ቀጠለ፡፡ ሴላዋን ደግሞ ተመልከት፡፡ የሮጀርስን ሚስት የዝናብ ልብስ ለብሰው በጠዋት የተመለከትካቸው ወ/ሮ ኤሚሊ እንዳላቸው አስታውስ፡፡ ይሄ ደግሞ ነብሰ-ገዳይ ባያደርጋቸው እንኳን ቢያንስ አእምሮአቸውን ዞር ለማድረግ በቂ ይመስለኛል፡፡ አሮጊቷ ሃይማኖተኛ ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው፡፡ የፈጣሪ መሳሪያ እንደሆኑ ያምናሉ፡፡ ከፍላቸውን ዘንትው የሚቀመጡት መፅሃፍ ቅዱስ እያነበቡ እንደሆነስ ታውቃለህ

ሎምባርድ በረጅሙ ተንፍሶ መፅሃፍ ቅዱስ ማንበባቸው የእእምሮ መቃወስን እያረጋግጥም በማለት የብሎርን ግምታዊ ትንተና ውድቅ ለማድረግ ሞከረ፡፡

የዝናብ ልብሱስ በዚያ ላይ ብቻቸውን ባህሩ ዳርቻ ደርሰው እንደተመለሱ ነግረውናል፡፡ በማለት ብሎር ክርክሩን ቀጠለበት፡፡

ሎምባርድ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ክርክሩን ቀጠለ፡፡ ወ/ሮ ኤሚሊ ሮጀርስ እንደገደሉ ብናምን እንኳን ከገደሉት በኋላ በቀጥታ ወደ ባህሩ አቅራቢያ ከመሔድ ይልቅ በቀጥታ ተመልሰው ወደ መኝታ ቤታቸው ሊገቡ እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡ ገዳይነታቸው እንዳይታወቅ ሲሉ የተኙ ለመምሰል ይሞክራሉ እንጂ....

ብሎር አቋረጠው፡፡ ተሳስተሃል ሎምባርድ፡፡ ሴትየዋ ገዳይ ባይሆኑ ኖሮ ብቻቸውን በጠዋት ደሴቷ ላይ ለመዘዋወር የሚያስችል ድፍረት አያገኙም ነበር፡፡ ምንም ነገር የማትፈራ ከሆነ ደግሞ ወንጀለኛ ነህ ማለት ነው

ሎምባርድ በመስማማት አሁን ገባኝ- እንደሱ አልተመለከትኩትም ነበር ብሎ ክርክሩን ጋብ አደረገ፡፡ በመቀጠልም ቢያንስ እኔን በገዳይነት ስላልጠረጠርከኝ ደስ ብሎኛል አለው፡፡

ብሎር እንደማፈር ብሎ እየውና ሽጉጥ መያዝህንና የሃሰት ታሪክ መናገርህንበማስታወስ መጀመሪያ ላይ ጠርጥሬህ ነበር፡፡ በኋላ ግን መሳሳቴን ተረዳሁ አለው፡፡

ሎምባርድ ፈገግ ብሎ ተረድቼሃለሁ፡፡ በነገራችን ላይ ጉበዝ ወንጀል መርማሪ ነህ፡፡ ምናልባት ወንጀለኛ ብትሆን በተሳካ ሁኔታ ማስመሰል


t.me/OLDBOOKSPDF

የምትችል ይመስለኛል፡፡ ችሎታህን አደንቃለሁ በማለት ጉንበሰ አለለት፡፡ በመቀጠልም ትናንት ማታ እየዋሸህ እንደነበር አውቃለሁ በማለት እውነተኛ ማንነቱን እንደነገረው ገርመም አደረገው፡፡

ብሎር መዋሸት ማቆም እንዳለበት ተሰማውና የምሽቱን ሃሰቱን ቃል ለማስተባበል ወሰነ፡፡ እንግዲያውስ እውነቱን ልንገርህ፡፡ ላንዶር ነፃ ሰው ነበር፡፡ በወንበዴዎቹ መከበቤን የተናገርኩት የውሸቱን ነበር፡፡ ላንዶርን በመያዝ ያቀረብኩትም ያለ ወንጀሉ ነበር፡፡ ምስክር ቢኖር ኖሮ ግን

በሃሰት ላንዶር ወህኒ አይወርድም ነበር በማለት ሎምባርድ የብሎርን ንዛዜ ጨረሰለት፡፡ እርሱን ወህኒ በማውረድ ያገኘኸው ጥቅም ነበር አይደል በማለት ጠየቀው፡፡

የማዕረግ እና የደረጃ እድገት አገኘሁ በማለት ብሎር የተፀፀተ መሰለ፡፡

ላንዶር ደግሞ በተወረወረበት ወህኒ ሳለሞተ በማለት ሎምባርድ አሁንም በጥያቄ አስተያየት ብሎርን ተመለከተው፡፡

እንደሚሞት በምን አውቅ ነበር በማለት ብሎር የልምምጥ ጥያቄ ሰነዘረለት፡፡

መሞቱ ላንተ መዘዝ አስከተለ-

የምን መዘዝ እርሱ የሞተው ተጉዳ እንጂ እኔማ ምን ሆንኩኝ

ይኸው የህይወትህ ፍፃሜ እንዲህ እንዲሆን በቃህ፡፡ አስቀያሚ ፍፃሜ አሉ- እንደ ሮጀርስ እና ሌሎቹ በቀላሉ የምሞት መስሎህ ነው ተጠንቅቄ ራሴን መጠበቅ እችላለሁ፡፡ በፈለግኸው ነገር መወራረድ እንችላለን

መወራረድ አልወድም፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ አንተ ከሞትክ ዐለ የተወራረድንበትን ማን ይከፍለኛል

ምን ለማለጽ ፈልገህ ነው ሎምባረድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድ ፈገግ ብሎ የመትረፍ እድልህ አነስተኛ እንደሆነው እየነገርኩህ ነው በማለት መለሰለት፡፡

ሞገ

እርግጠኛነትህ ቀላል ኢላማ ያደርግሃል፡፡ ገዳዩ አቶ ወይም ወ/ሮ እውን በቀላሉ ሊያጠምዱህ ይችላሉ፡፡

ብሎር በቁጣ አፈጠጠና አንተስ የመዳን እድል አለህ በማለት ጠየቀው

ፊሊፕ ሎምባርድ ፊቱን ከሰከሰ፡፡ በራሴ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ከዚህ የበለጠ አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ገብቼ ወጥቻለሁ፡፡ ብዙ መናገር ባልፈልግም ከዚህኛው አደጋ ግን መውጣት እችላለሁ፡፡

ቬራ ስጋውን መጥበሻ ላይ አድርጋ ምድጃው ላይ ጣደች፡፡ በድንገት ሃሳብ ውስጥ ሰጠመች፡፡ ከደቂቃዎች በፊት ራሷን መቆጣጠር አቅቷት እንደነበር አሰበች፡፡ ራሷን ለማጠናከርም የተለያዩ የማበረታቻ ሃሳቦችን በውስጧ አመላለሰች፡፡ በድንገት ግን የተለየ ትውስታ ውስጥ ገባች፡፡ ህፃኑ ሳይረልን ለማትረፍ ወደ እርሱ እየዋኘች ስትሄድ ታሰባት፡፡ለምንድን ነው ስለ ሳይረል አሁን የምታስበው፣

ሁሉም ነገር አልፏል፡፡ ሳይረል እርሷ ከመድረሷ በፊት ነበር የሞተው..... እርሷም በማዕበሉ ሃይል እየተገፋች ወደ ዳር ተመለሰች.... በመጨረሻም ጀልባው ደረሰላት....

ህፃኑን ለማትረፍ ላደረገችው ሙከራ ሁሉም ከፍተኛ አድናቆት አቀረቡላት፡፡ ሁጐ ግን በዝምታ ነበር የተመለከታት፡፡ ሁጐን ማስታወስ በጣም ይጐዳል... ለመሆኑ አሁን የት ይሆን ያለው እግዚብሔር ይሆን

ቬራ ስጋው አረረ የሚለው የወ/ሮ ኤሚሊ ድምፅ ነበር ከሃሳቧ ያወጣት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ምን አይነት ጣጣ ነው፡ በማለት መጥበሻውን ከምድጃው ላይ አወረደችው፡፡ ስጋው ከማረር አልፎ ሙሉ በሙሉ ተቃጥሎ ነበር፡፡ ሌላ የተከተፈ ስጋ መጥበሻ ላይ አድርጋ እየጣደች ወ/ሮ ኤሚሊ እርስዎ በጣም የተረጋጉ ሴት ኖት አለቻቸው፡፡

በስነ ስርዓት ነው ወላጆቼ ያሳደጉኝ በማለት ወ/ሮ ኤሚሊ ረጋ አድርገው ተናገሩ፡፡

ምንም ነገር አያስፈራዎትም ሞትም ቢሆን በማለት ቬራ ጠየቀቻቸው፡፡

ሞት የሚለው ቃል እንደ ስለት ሲወጋቸው ተሰማቸው፡፡ ወዲያውኑ ጥልቅ ሃሳብ ውስጥ ገቡ፡፡

ወ/ሮ ኤሚሊ ሞት አይፈሩም፡፡ በርግጥም ዘራቸው በሙሉ ለሞት የማይሸነፍ ነበር፡፡ ቬራ ይሄንን እንደማታውቅ ነበር የገባቸው፡፡

የወ/ሮ ኤሚሊ ቤተሰቦች በሙሉ ሞትን በጀግንነት የመጋፈጥ ልምድ ነበራቸው፡፡ በምንም አይነት አይፈሩም፡፡ ጀነራል ማካርተር ከመሞቱ በፊት ማናቸውም ከደሴቷ በሰላም እንደማያመልጡ መናገሩን ወ/ሮዋ አስታወሱ፡፡ ጀነራሉ የአጐታቸው ልጅ የሆነችውን ኤልሲ ማክፈርሰን እንዳገባ ሲያስታውሱ ነበር ዘራቸው ሞት እንደማይፈራ ያረጋገጡት፡፡ ጀነራሉ ሞትን በድፍረት ተቀብሏል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሞትን በመዳፈር ራሳቸውንም ያጠፋሉ - ልክ እንደ ቢትሪስ ቴይለር፡፡

ሌሊት በህልማቸው ቢትሪስን አይተዋት ነበር፡፡ ከመኝታ ቤታቸው መስኮት ጋር በጭንቅላቷ እየተጋጨች እንዲያስገቧት ስትለምናቸው ነበር ያለሙት፡፡ ወ/ሮ ኤሚሊ ሊስገቧት አልፈለጉም ነበር፡፡ ምክንያቱም ካስገቧት መጥፎ ነገር ይከሰት ነበር...

ወ/ሮ ኤሚሊ ከጥልቅ ሃሳባቸው ሲባንኑ ቬራ አፍጥጣ እያየቻቸው መሆኑን ተመለከቱ፡፡ የቬራ አስተያየት ስላልጣማቸው ትኩረቷን ማስቀየር ነበረባቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁርሱ ደርሷል አይደል እናቀራርብባቸው፡፡ በማለት ተንቀሳቀሱ፡፡

ስድስቱ ቁርሳቸውን የበሉት በፍፁም መረጋጋት ነበር፡፡ ሁሉም በየራሳቸው ሃሳብ ተጠምደው ስለነበር ብዙም የረባ ቃል አልተለዋወጡም ነበር፡፡ በወጥመዱ ውስጥ እንደምገኝ ጥንቸል እየተሽረከሩ በሚመላለሱ ሃሳቦች ተጠምደዋል

......ቀጥሎስ ማን ምን እንዴት.......

......ይሻል ይሆን ወይስ.... ገዜ ቢኖር ጥሩ ነበር....

...... ይሂ ሞኝ ደግሞ የነገርኩትን በሙሉ አምኗል...

...... ሃይማኖተኛ መምሰል አቀራረብ ነው.......

......ስድስቱ አሻንጉሊቶች ያድሩ ይሆን

በየራሳቸው ሃሳብ ተወጥረው ስድስቱም ቁርሳቸውን የተመገቡት በፀጥታ ነበር፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

ቁርሱ ተበልቶ እንዳበቃ ዳኛው ጀስቲስ ዋርግሬቭ በተረጋጋ ድምፅ ከአስራ ደቂቃ በኋላ እንግዳ ማረፊያው ውስጥ ተገናኝተን ብንነጋገር ጥሩ ይመስለኛል በማለት ሃሳብ ሲያቀርቡ ሁሉም ተስማሙ፡፡

ቬራ የተበላባቸውን እቃዎች እስከዛ ድረስ ልጠብ በማለት እቃ ማንሳት ጀመረች፡፡ ሎምባርድ ሊረዳት ሲነሳ ወ/ሮ ኤሚሊም ከወንበራቸው ተነስተው ከቆሙ በኋላ አ-ፈጣሪዬ በማለት ግንባራቸውን ደገፈው ተመልሰው ተቀመጡ፡፡

ምነው ወ/ሮ ኤሚሊ ዳኛው ነበሩ የጠየቋቸው፡፡

እኔ እንጃ፡፡ ቬራን ለመርዳት ብዬ ነበር የተነሳሁት ግን አዞረኝ እና ልወድቅ ነበር... ኧረ አጥወለወለኝ

ማዞር ከሆነ ችግር የለውም፡፡ አንድ መድሃኒት እሰጥታለሁ፡፡ ይሻሎታል በማለት ዶ/ር አርመስትሮንግ ሲጠጋቸው በእጃቸው ተከላከሉትና አልፈልግም በማለት አምባረቁበት፡፡

ሁሉም ደንግጠው ቆሙ፡፡ የወ/ሮዋ ጩኸት የጥርጣሬ ብቻ አልመሰላቸውም ነበር፡፡ በተለይ ዶ/ሩ በጣም ነበር የደነገጠው፡፡

ምንም እንድትሰጠኝ አልፈልግም፡፡ ማዞሩም በራሱ ይተወኛል፡፡ አትጠጋኝ

እሺ ወ/ሮ ኤሚሊ- እንዳሉት ይሁን በማለት ዶ/ሩ ገለል አለ፡፡

ብሎር ትኩረቱን ለማስቀየር ብሎ እኔ ላግዝሽ ቬራ፡፡ በቤት ስራ ጉበዝ ነኝ በማለት ተነስቶ አብሯት እቃ ይዞ ወጣ፡፡

ሳሎኑ ውስጥ ብቻቸውን የቀሩት ወ/ሮ ኤሚሊ ከደቂቃዎች በኋላ መረጋጋት ጀመሩ፡፡ ከምግብ ማብሰያው ክፍል የሚወጣ የሰዎች ድምፅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቃስ በቀስ ይሰማቸው ጀመር፡፡ ወዲያውን ደግሞ እንቅልፍ ተጫጫናቸው፡፡ ሰመመን ውስጥ ያሉ ያህል ነበር የሚሰማቸው፡፡

የንብ ድምፅ ተሰማቸው፡፡ እዚህ ክፍል ውስጥ ንብ እንዴት ገባ በማለት ተገርመው አሰቡ፡፡ ወዲውኑ መስኮቱ አጠገብ የሚበር ንብ ያዩ መሰላቸው፡፡ ቬራ ስለ ንቦች ስትናገር የነበረው በከፊል ትዝ አላቸው፡፡

ክፍሉ ውስጥ ብቻቸውን አልነበሩም፡፡ ከጀርባቸው የኮቴ ድምፅ ይሰማቸዋል፡፡ ቤትሪስ ታይለር ከወንዝ ወጥታ እየተራመደች መሰላቸው፡፡ ነገር ግን ዞረው ሊያይዋት አልቻሉም፡፡ በፍርሃት የድረሱልኝ ጩኸት ማሰማት ቢፈልጉም ማንም እንደማይደርስላቸው አውቀው ተስፋ ቆረጡ፡፡ክፍሉ ውስጥ ሌላ ሰው አልነበረም፡፡

ቤትሪስ ከተደፈቀችበት ወንዝ ወጥታ ስትራመድ ከሰውነቷ ላይ የሚወርደው ውሃ ወለሉ ላይ ሲደርስ ይሰማቸዋል፡፡ የበሰበሰ ውሃ እና የቤትሪስ ገላ ሽታ አፍንጫቸውን ሰነፈጣቸው፡፡

መስኮቱ አጠገብ የሚበረው ንብ ድምፅ ተሰማቸው፡፡ ወዲውኑ ደግሞ አጠገባቸው ደርሶ መብረር ጀመረ፡፡ በዚያው ቅፅበት ንቡ አንገታቸው ላይ ሲነድፋቸው ተሰማቸው፡፡

እንግዳ ማረፊያው ክፍል ውስጥ ተሰባስበው ወ/ር ኤሚሊን እየጠበቁ ነበር፡፡

"ሔጂ ልጥራቸው" በማለት ቬራ ተነሳች፡፡

"ቆይ!" በማለት ብሎር በእጁ እንድትቀመጥ አዘዛትና ድምፁን ዝቅ አድርጎ መናገር ጀመረ፡፡ "ሁላችሁም አዳምጡኝ፡፡ እስከአሁን ድረስ ገዳዩን ስንፈልግ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰአት ግን አግኝተነዋል፡፡ ወ/ሮ ኤሚሊ ናቸው፡፡" አለ



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምክንያታቸውስ" በማለት አርመስትሮንግ ጠየቀው

"ሃይማኖተኛነታቸው ወደ እብደት ተሸጋግሮባቸዋል"

"ግምትህ ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ማረጋገጫ የለንም"

ቬራ ጣልቃ በመግባት "ቁርስ በምናበስልበት ወቅት ሁኔታቸው ጥሩ አልነበረም፡፡ አይኖቻቸው ያስፈሩ ነበር" አለች፡፡

"እሱ መረጃ ሊሆን አይችልም፡፡ የሁላችንም ሁኔታ ጥሩ አይደለም" በማለት ሎምባርድ ተቃወመ፡፡

"ሌላም ነገር አለ" በማለት ብሎር በጥድፊያ መናገሩን ቀጠለ፡፡ "በግራምፎኑ ከተዘረዘሩት ክሶች መካከል ማስተባበያ ያልሰጡት ወ/ሮ ኤሚሊ ብቻ ነበሩ፡፡ ለምን? ምክንያቱም ማስተባበል ስለሌለባቸው!"

ቬራ በፍጥነት "ተሳስተሃል! ማስተባበያቸውን ነግረውኛል" አለች፡፡

"በትክክል ምን ነበር የነገሩሽ?" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ ጠየቁት፡፡ ቬራም ወ/ሮ ኤሚሊ ስለ ቤትሪስ ታይለር የነገሯትን ደገመችላቸው፡፡

"አስገራሚ ነው፡፡ እኔም በርሳቸው ቦታ ብሆን የሚሰማኝ ስሜት ያ ነበር" በማለት ዳኛው አስተያየት ሰጡ እና "ለመሆኑ ሲነግሩሽ የነበራቸው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?" በማለት ጠየቋት፡፡

"ምንም የተለየ ነገር አላሳዩም" በማለት መለሰች፡፡

"ያላገቡ አሮጊቶች ደረቆች ናቸው! በቅናት እና በክፋት የደነደነ ልብ አላቸው" በማለት ብሎር ለፈለፈ፡፡

ዳኛ ዋርግሬቭ ሰአታቸውን ተመልክተው "ለስብሰባችን የቀረው አምስት ደቂቃ ስለሆነ ወ/ሮ ኤሚሊን ብንጠራቸው ጥሩ ነው" አሉ

"እርምጃ ብንወስድ አይሻልም?" ብሎር ነበር የጠየቀው፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኛውም በተረጋጋ ሁኔታ "ለግዜው ከጥርጣሬ ያለፈ በቂ መረጃ ስለሌለ እርምጃ መውሰድ አንችልም፡፡ ዶ/ር የወ/ሮዋን የባህሪ ለውጦች በቅርብ ተከታተል፡፡ አሁን ወደ ሳሎኑ እንሒድ እና እሳቸው ያሉበት እንሰብሰብ" በማለት ዳኛው ሌሎቹን አስከትለው ወ/ሮ ኤሚሊ ብቻቸውን ወደተቀመጡበት ሳሎን ገቡ፡፡

ወ/ሮዋ ጀርባቸውን ለበሩ ሰጥተው ተቀምጠዋል፡፡ አጠገባቸው ምንም ነገር የለም፡፡ ከጀርባቸው አምስቱ ሰዎች ሲጠጉ እንኳን ዞር አላሉም ነበር፡፡ አጠገባቸው ደርሰው ፊታቸውን ተመለከቱ፡፡ የወ/ሮ ኤሚሊ ፊት በደም ተጨማልቋል፡፡ ከናፍራቸው ጠቁሮ ገርበብ ያለ ሲሆን አይኖቻቸው እንደተከፈቱ ነበረ፡፡

"የፈጣሪ ያለህ! ሞተዋል!" በማለት በድንጋጤ የጮኸው ብሎር ነበር፡፡

• • •

ዳኛ ጀስቲስ ዋርግሬቭ በቀዝቃዛ ድምፅ "ከመካከላችን እንዷ ነፃ ወጣች፡፡ ዘግይተናል!" አሉ፡፡

አርመስትሮንግ የወ/ሮ ኤሚሊን በደም የተሸፈነ ፊት አጉንብሶ ተመለከተ፡፡ የታችኛው ከንፈራቸውን ገለጥ አድርጐ ከተመለከተ በኋላ ጭንቅላቱን አነቃንቆ ቀና አለ፡፡

"ምንድን ነው የገደላቸው ፤ ዶ/ር? ስንወጣ ደህና አልነበሩም እንዴ? በማለት ሎምባርድ ጠየቀው፡፡

ዶ/ር አርምስትሮንግ የሟቿ ወ/ር ኤሚሊን አንገት ተጠግቶ እየተመለከተ ነበር፡፡ በቀኝ አንገታቸው በኩል የውግ ምልክት ነበረበት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንገታቸው ላይ በመርፌ የተወጉ ይመስለኛል፡፡ ምልክቱ የመርፌ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ" በማለት ዶ/ሩ መለሰ፡፡ መስኮቱ አጠገብ አንዲት ንብ ለመውጣት በመታገል እየበረረች ድምፅ ታሰማ ነበር፡፡

"ተመልከቱ! ንቧን አያችኋት? ጠዋት የተናገርኩትን አስታወሳችሁን" በማለት ቬራ ጮኸች፡፡

"ንብ አይደለም ወ/ሮ ኤሚሊን የነደፉቸው፡፡ የሆነ ሰው አንገታቸውን በመርፌ ወግቶታል" በማለት ዶ/ሩ ሊያረጋጋት ሞከረ፡፡

ዳኛው አሁንም በቀዝቃዛ ድምፅ "ምን አይነት መርዝ የተወጋች ይመስልሃል ዶ/ር?" በማለት ጠየቁት፡፡

"ከሳይናይድ የመርዝ አይነቶች አንዱን ፤ ምናልባትም ፖታሲየም ሳይናይድ ፤ አንቶኒ ማርስተን ከተገደለበት ጋር ተመሳሳይ ቢሆን ነው ወዲያውኑ የገደላቸው፡፡ እንደምናያቸው ከሆነ እንደወጣን የሞቱ ይመስለኛል"

"ንቡስ? ይሄማ አጋጣሚ ሊሆን አይችልም!" ቬራ በድጋሚ ጮኸች፡፡

ሎምባርድ ጥርሱን ነክሶ እየተነፈሰ "አጋጣሚ አይደለም፡፡ ነገር ግን የእኛ ሰው ገድያውን ብቻ ሳይሆን ምልክቶቹንም በጥንቃቄ መጠቀም የሚፈልግ አይነት ነው፡፡ የህፃናቱን የተረት መዝሙር እስከመጨረሻው ሙጥኝ ማለቱ ነዋ! ...." በማለት በቁጣ አፍጥጦ ድምፁን ከፍ በማድረግ "ይሄ ፈፅሞ የለየለት እብደት ነው! ሁላችንም አብደናል" አለ

"ሁላችንም ጤነኛ ነን፡፡ ለማንኛውም ከመካከላችን የህክምና መርፌ ይዞ የመጣ ሰው አለ?" በማለት ዳኛው ጠየቁ፡፡

እርግጠኛነት በማይታይበት ድምፅ ዶ/ር አርመስትሮንግ "እኔ ይዣለሁ" በማለት መለሰ፡፡ የአራቱም ጥንድ አይኖች እርሱ ላይ አፈጠጡ፡፡ በፍርሃት

t.me/OLDBOOKSPDF

እየተመለከተችው 'ሁሉም ዶ/ር በጉዞ ላይ የህክምና መሳሪያዎችን መያዙ የተለመደ እኮ ነው' በማለት መለሰላቸው።

'አሁን መርፌው የት ነው ያለው ዶ/ር?'

'መኝታ ቤት ፣ የጉዞ ሻንጣዬ ውስጥ' በማለት እንደመለሰላቸው አምስቱም ተያይዘው ወደ ዶ/ሩ መኝታ ክፍል አመሩ።

የዶ/ሩን የጉዞ ሻንጣ ወለሉ ላይ ዘርግፈው ውስጡን ባዶ አደረጉት። የተባለው የህክምና መርፌ በርሳው ውስጥ የለም።

• • •

ዶ/ር አርመስትሮንግ አፍጥጠው የሚመለከቱትን አራት ጥንድ አይኖች መሸሽ አቃተው። እየተንተባተበ "የሆነ ሰው ወስዶታል ማለት ነው" አለ። የአራቱ ምላሽ አስፈሪ ፀጥታ ነበር። አፍጥጠው መመልከታቸውን ቀጠሉ። አይኖቹን ከዳኛው ወደ ቬራ እያንከባለለ በተማፅኖ ድምፅ "በፈጣሪ ስም እምላለሁ የሆነ ሰው ወስዶት ይሆናል እንጂ ....' በማለት ወደ ሎምባርድ እና ብሎር ደግሞ ዞረ።

ሎምባርድ እና ብሎር በአይናቸው ተነጋግረው ተግባብተዋል።

ዳኛ ዋርግሬቭ መናገር ጀመሩ። "እንግዲህ አምስታችንም እዚሁ ክፍል ውስጥ እንገኛለን። አንዳችን ገዳይ ነን ማለት ነው። ስለዚህ የአራት ንፁሃንን ነብስ ለመታደግ ሲባል ማናቸውንም ነገር ማድረግ ይኖርብናል። ዶ/ር አርመስትሮንግ በእጅህ የሚገኙ መድሃኒቶች ምን ምን እንደሆኑ ንገረን?"

ዶ/ሩ በተረጋጋ ድምፅ ለመናገር ሞከረ። "የያዝኩትን የመድሃኒት ሳጥን መመልከት ትችላላችሁ። ትሪዮናል እና ሰልፎናል የእንቅልፍ እንክብሎች ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

አስፐሪን እና ብሮማይድ ፤ ብቻ ነው ያሉት፡፡ ምንም አይነት ሳይናይድ አልያዙም፡፡

"እኔም የእንቅልፍ እንክብሎች ይዣለሁ፡፡ እንክብሎቹ ከመጠን ካለፉ ገዳይ መሆናቸውን አውቃለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ተራው የሎምባርድ ነው፡፡ ሽጉጥ ይዘሃል፡፡" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ ወደ ሎምባርድ ዞሩ፡፡

"እና ብይዝስ?" ሎምባርድ ተቆጣቸው

"የዶ/ር እና የእኔን የእንቅልፍ መድሃኒቶች ጨምሮ እንዳንድ ሽጉጥ ያሉ ነገሮችን በሙሉ ሰብስበን አንድ ቦታ ማስቀመጥ አለብን፡፡ ከዛ በኋላ ሁላችንም ለመፈተሽ ፍቃደኛ እንሆናለን፡፡ ምናልባት ሌሎችን የሚጎዱ ቁሳቁሶች ከተገኙ ማስረከብ ይኖርብናል" በማለት ዳኛው ገለፁት፡፡

"ሽጉጤንማ ፈፅሞ አልሰጣችሁም!"

ዳኛው ቆም ብለው፡- "አቶ ሎምባርድ ቀልጣፋ እና ጉልበተኛ ወጣት እንደሆንክ አውቃለሁ፡፡ ብሎር ያንተን ያህል እንኳን ባይሆን የሚናቅ አይደለም፡፡ ከሁለታችሁ ማን እንደሚያይል መናገር ይከብደኛል፡፡ ነገር ግን እኔ ፤ ዶ/ር አርመስተሮንግ እና ቬራ ከብሎር ጐን ከቆምን ምን ሊመጣ እንደሚችል መገመቱ ቀላል ነው" በማለት አስጠነቀቁት፡፡

ሎምባርድ ጥርሱን ገጥሞ በፍጥነት እየተነፈሰ ፈገግ ለማለት ሞከረ፡፡

"እንግዲያውስ ምንም አማራጭ የለኝም፡፡ እሰጣችኋለሁ፡፡

"መልካም ወጣት ነህ፡፡ ለመሆኑ ሽጉጥህ የታለ?" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ በትህትና ጠየቁት፡፡

"መኝታ ክፍሌ ፤ ከአልጋዬ አጠገብ ያለው መሳቢያ ውስጥ" በማለት መለሰላቸው፡፡

"በጣም ጥሩ"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውሯ ገዳይ

ሟጂ ላምባጡ"

"አብረን መሄድ ያለብን ይመስለኛል"

ሎምባርድ የንዴት ሳቅ እየሳቀ "ጥርጣሬያችሁ ከመጠን ያለፈ አልመሰላችሁም?" በማለት ጠየቃቸው፡፡ ወዲያውኑ ሁሉም ተያይዘው ወደ ሎምባርድ ክፍል አመሩ፡፡ እንደደረሱም ሎምባርድ እየተጣደፈ አልጋው አጠገብ ያለውን መሳቢያ በሃይል ጎትቶ ከፈተው፡፡ ወዲያውኑ ፊቱ በድንጋጤ ጨው መሰለ እና በጥያቄ እስተያየት እየጠበቁት ወደነበሩት አራቱ ሰዎች ዞሮ የመሃላ መአት መደርደር ጀመረ፡፡

ሽጉጡ መሳቢያው ውስጥ አልነበረም፡፡

• • •

"ብርበራችሁ እንዴት ነው ፣ ረካችሁ?" በማለት ሎምባርድ በትግስት ፈትሸው እስኪጨርሱ ጠብቆ ጠየቃቸው፡፡ ብሎር ፣ ዶ/ር አርመስትሮንግ እና ዳኛ ዋርግሬብ የሎምባርድን ክፍል ፈትሸው እስኪያጠናቅቁ ድረስ ቬራ ክሌይትሮን ከክፍሉ ውጪ መተላለፊያው ላይ ቆማ ነበር፡፡ በመቀጠል የቀሩት ሶስት ወንዶች ክፍል በየተራ ተበረበረ፡፡

ፍተሻውን አጠናቀው ሲጨርሱ ቬራ ወደነበረችበት መተላለፊያ አመሩ፡፡ ዳኛ ዋርግሬብ በትህትና "አንቺም ለተመሳሳይ ፍተሻ ፍቃደኛ እንደማትሆኚ እምናለሁ፡፡ ወደ ክፍልሽ በመግባት የውስጥ ልብስሽን ብቻ ለብሰሽ ብትወጪልን?" በማለት ጠየቋት፡፡

ቬራ ከክፍሏ ስትወጣ የለበሰችው ጠባብ የሃር ውስጥ ልብስ ሰውነቷ ላይ ተጣብቆ ሙሉ ቅርጿን ያሳያል፡፡ ወንዶቹ ፍተሻውን አጠናቅቀው እስኪመለሱ ጠበቀቻቸው፡፡ በመጨረሻም ሲወጡላት ልብስ ለመደረብ ወደ ክፍሏ ገባች፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ልብሷን ለብሳ እስክትመለስ በመጠበቅ ዳኛ ዋርግሬቭ "በመቀጠል ያገኘናቸውን መድሃኒት እና ማናቸውንም ጉጂ ቁሳቁሶች እናስቀምጣለን። እቃ ቤት ውስጥ የሚገኘው ትንሽ የብረት ሳጥን ቁልፍ ያለው ይመስለኛል" በማለት ከአራቱ ወንዶች መልስ ጠበቁ።

"ጥሩ ነው። ቁልፉን እርስዎ ቢይዙት የሚሻል ይመስለኛል" በማለት ብሎር አስተያየቱን አቀረበ።

ዳኛው መልስ አልሰጡትም። በቀጥታ ያመሩት ወደ እቃ ማስቀመጫው ቤት ነበር። በተባለው ሳጥን ውስጥ መድሃኒቶቹን እና ቁሳቁሶቹን አስገብተው ቆለፉባቸው። በመቀጠልም ትንሿን ሳጥን በሎምባርድ እና ብሎር አማካኝነት አስነስተው ትልቁ የዕቃ መደርደሪያ ውስጥ በማስገባት ቆለፉበት። ከዚያም የሳጥኗን ቁልፍ ለሎምባርድ የትልቁን ቁም ሳጥን ቁልፍ ደግሞ ለብሎር ሰጧቸው።

"ቁልፉን ለሁለታችሁ ያካፈልኳችሁ ከመካከላችን ጠንካሮች ሁለታችሁ በመሆናችሁ እርስ በርስ መነጣጠቁ ከባድ ሊሆን እንደሚችል በመገመት ነው። የቀረነውም ብንሆን ከእናንተ ላይ የመቀማት ጉልበት የለንም።" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ ንግግራቸውን ለአፍታ ያህል ቆም አድርገው ቀጠሉ፡- "ሳጥናቹን ለመክፈትም ሆነ ለመስበር የሚሞክር ቢኖር ውጤቱ ጥሩ ላይሆን ይችላል። አሁን የሚቀረን ሌላ ከባድ ያልተፈታ እንቆቅልሽ አለ። ይኸውም የሎምባርድ ሽጉጥ የት አለ የሚለው ነው"

ብሎር ቀለል አድርጎ "እንግዲህ ከባለቤቱ የተሻለ የሽጉጡን መኖሪያ የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም" አለ።

የፊሊፕ ሎምባርድ ፊት በንዴት ቀላ። "አሳማ የውሻ ልጅ! እንደነገርኩሽ ስናገር አልሰማኸኝም እንዴ?" በማለት ተሳደበ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጳኛ ዋርግሬቭ የሉምባርድን ቁጣ ችላ በማለት "ለመሆኑ ለመጨረሻ ግዜ መኖሩን ያየኸው መቼ ነበር?" በማለት ጠየቁት፡፡

"ትናንት ማታ ከመተኛቴ በፊት መኖሩን አይቼ ነበር፡፡" ሲመልስላቸው ዳኛው ብዙም ሳይገረሙ ነበር የተመለከቱት፡፡

"ስለዚህ ዛሬ ጠዋት ሮጀርስን ፍለጋ ስንዞር ሊሆን ይችላል የተወሰደው " አሉ ዳኛው፡፡

"እዚሁ ብንፈልግ ልናገኘው እንችላለን "

ዳኛው ፊማቸውን ዳበስ አድርገው "ፍለጋችን ውጤታማ አይሆንም፡፡ ገዳዩ ሽጉጡን ለመደበቅ በቂ ግዜ ነበረው፡፡ ስለዚህ የምናገኘው አይመስለኝም፡፡" አሉ፡፡

"ሽጉጡ የት እንዳለ ማወቅ ባይቻልም ወ/ሮ ኤሚሊ የተወጉበት መርፌ የት እንደሚገኝ ግን አውቃለሁ-" በማለት ብሎር በሩን ከፍቶ ሲወጣ አራቱ ተከተሉት፡፡ ቤቱን በመዞር ከምግብ ቤቱ መስኮት ትይዩ መሬት ላይ መርፌ እና ስሪንጁ ወድቀው ተገኙ፡፡ ከመርፌው አጠገብ ደግሞ አምስተኛው የቻይና አሻንጉሊት ተሰብሮ ተጥሏል፡፡

"አሮጊቷን ከወጋ በኋላ በመስኮት ሊወረውረው እንደሚችል ገምቼ ነበር፡፡ ከዚያም ከጠረጴዛው ላይ አሻንጉሊቱን አንስቶ ለቀጣዩ ስራ ተዘጋጀ ማለት ነው፡፡ በማለት ብሎር በርካታ ተነፈሰ፡፡

የቀድሞው መርማሪ ፖሊስ ብሎር ሲሪንጁን በጥልቀት መርምሮ ምንም አይነት አሻራ እንደሌለበት አረጋገጠላቸው፡፡

"እሺ አሁን ደግሞ ሽጉጡን እንፈልግ" በማለት ቬራ ሃሳብ አቀረበች፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"መልካም፡፡ ነገር ግን በፍለጋችን ወቅት አንድ ላይ ብንሆን ይመረጣል፡፡ ከተለያየን ለገዳዩ አመቺ ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡" በማለት ላኛው አስጠነቀቋቸው፡፡

• • •

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመካከላችን አንዳችን ....' የሚለው ቃል በአምስቱም አእምሮ ውስጥ ተመላለሰ፡፡ በመካከላቸው ምንም አይነት የቃላት ልውውጥ አልተደረገም፡፡ አምስቱም በፍርሃት ተወጥረው እርስ በርሳቸው ከመጠባበቅ የተለየ ነገር ማድረግ አልቻሉም ነበር፡፡

የሁሉም ሰውነት የዛለ ሲሆን በየራሳቸው ሃሳብ ውስጥ በመሆን በህይወት ለመቆየት መታገል ጀምረዋል፡፡ ዳኛ ዋርግሬቭ ከወንበራቸው የመነሳት ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ ሰውነታቸው መንቀሳቀስ ባይችልም አይኖቻቸው ግን ንቁ ነበሩ፡፡ ብሎርም ድካም የተጫጫነው ሲሆን አይኖቹ ቀልተዋል፡፡ ፊሊፕ ሉምባርድ ከርቀት የሚመጣን ድምፅ ለመስማት ያቆበቆበ ይመስል አንገቱን ዘመም አድርጐ ይጠባበቃል፡፡ በተደጋጋሚ ለመሳቅ ይሞክርና ይተወዋል፡፡

ቬራ ከሌይትሮን ወንበሯ ላይ ተጨብጣ ተቀምጣለች፡፡ ከመስታወት ጋር ተጋጭታ እንደወደቀች ትንሽ ወፍ ስብርብር ብላ እግሯን አቅፋ ነበር የተቀመጠችው፡፡ ዶ/ር አርመስትሮንግ ከሁሉም በላይ መረጋጋት አቅቶት ነበር፡፡ በሚንቀጠቀጡ እጆቹ ደጋግሞ የሚለኩሰውን ሲጋራ መያዝ አቅቶት ነበር፡፡ በዚያ ላይ እየደጋገመ ብዙም የማይገቡ ነገሮችን ይቀባጥራል፡፡

ዶ/ሩ ከወንበሩ ተፈናጥሮ ተነሳ፡፡ "እዚህ በመቀመጥ የምናመጣው ነገር የለም፡፡ የሆነ ነገር ማድረግ አለብን፡፡ ለምን ውጪ እሳት አንድደን ከደሴቷ ውጪ ያሉ ሰዎች እንዲያዩን...."

"በዚህ ዝናብ?" በማለት አጭር ጥያቄ በማቅረብ ያስቆመው ብሎር ነበር፡፡ ሃይለኛ ንፋስ የቀላቀለው ዝናብ ከመስኮቱ ጋር በመጋጨት የሚፈጥረው ድምፅ በጣም ነበር የሚረብሸው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ከአጭር ውይይት በኋላ ሁሉም በጋራ የተስማሙበትን እቅድ አወጡ፡፡ አራቱ ሰዎች እንግዳ ማረፊያው ውስጥ ሲቀመጡ አንዱ ብቻ ወጥቶ ሄደ፡፡

ብሎር ራሱን ለማረጋጋት ያሰበ ይመስል "አይዟችሁ ፤ በቂ ግዜ አለን፡፡ የእሳት ምልክት በማሳየት እርዳታ መጥራት እንችላለን፡፡ ካልሆነ ደግሞ አነስተኛ ጀልባ ገንብተን እንሔዳለን" አላቸው፡፡

አርመስትሮንግ የለበጣ ሳቅ አስቀድሞ "ግዜ ቢኖር ነበረ! ግዜ የለንም ሁላችንም መሞታችን አይቀርም" አለ፡፡

ዳኛ ዋርግሬቭ በርጋታ ነበር አስተያየት የሰጡት "ሁላችንም ከተጠነቀቅን ምንም አንሆንም፡፡"

ምግብ ማብሰያው መደርደሪያ ውስጥ በርካታ የታሸጉ የቆርቆሮ ምግቦችን አገኙ፡፡ አምስቱም በቁማቸው እንደነገሩ በላልተው ወደ እንግዳ መቀበያው ተመለሱ፡፡ በመካከላቸው ምንም ቃላት ሳይለዋወጡ ደንዝዘው ተቀመጡ፡፡ በየምናባቸው እርስ በራስ መካሰስ ቀጠሉ፡፡

"...አርመስትሮንግ አስተያየቱ አላማረኝም..... በዚያ ላይ ትክክለኛ ዶ/ር አይመስልም.... ለሌሎቹ ልንገራቸው ወይስ ልጨሀ? .... የሚያምኑኝ ግን አይመስለኝም.... በዚያ ላይ ገና ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ነው.... ፈጣሪዬ.... መሞቴ ነው ማለት ነው...".

"..... በቀላሉ አልሞትላቸውም.... ከብዙ አስቸጋሪ ወጥመዶች አምልጫለሁ .... ለመሆኑ ያንን ሽጉጥ ማን ይሆን የወሰደው ... ማንም የወሰደው አይመስለኝም .... የሁላችንም ክፍል ተፈትሿል..."

"..... ሁሉም ሞት ይፈራሉ .... ፍራቻቸው የሚያስቀረው ይመስል ... ልጅቷ ምኗም አልተመቸኝም፡፡ ከወንዶቹ ይልቅ እርሷን መከታተል አለብኝ፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

...ግና ለአስር ሃያ ጉዳይ ነው? ምንም ሊገባኝ አልቻለም።

ሌቱ ቆንጆ እንዴ? ....ወይኔ ራሴ ሊፈነዳብኝ ነው። ሽሬ መቼ

የምነቃው...'

'... ነቶቹ መጠበቅ አለብኝ። ሁሉም ነገር በእቅዱ መሰረት

እየሄደ ነው።...አንዳቸውም አልጠረጠሩም። ሽወዳውም መታወቅ

የለበትም። ምናልባት አንድ የሆነ ሽወዳ ግድረግ ሳይኖርብኝ

አይቀርም... ከየትኛቸው ልጀምር ይሆን?....ሺ! ከእሱ መጀመር

ያለበት...'

ለቱ ከምሽቱ አስራ አንድ ሲሆን ሁሉም ለመንቀሳቀስ ተነሱ። ቬራ

ፍድሬያ ተነስታ "ሻይ ሳፈላ ነው። የሚፈልግ አለ?"

"እኔ እጠጣለሁ" ብሎር ነበር የመለሰላት

"እንገዲያው አፍልቼ እስከመጣ እዚሁ ጠብቁኝ"

"የለም ፣ ውዴ። አብረንሽ መሆን አለብን" በማለት ዳኛ ዋርግሬቭ ሲነሱ

ሌሎቹም ተከተሏቸው። ቬራ በአግራሞት ሳቀችና ወደ ግዕድ ቤቱ

አመራች።

ሻይ አፍልታ ለራሷ እና ለብሎር ቀዳች። ሶስቱ ወንዶች አዲስ ውስኪ

ከመጋዘን አውጥተው እየጠጡ ነበር።

ተያይዘው ወደ ሳሎኑ ሲመለሱ ዳኛ ዋርግሬቭ በአባታዊ ድምፅ

"ሁላችንም መጠንቀቅ ይኖርብናል።" አሉ።

ብሎር የሳሎኑን መብራት ቢያበራውም ከፍሉ በጭለግ እንደተዋጠ

ነበር። የመብራት ጄነሬተሩ አለመብራቱን ያስታወሱት ያኔ ነበር።

"ሮጀርስ ከሞተ በኋላ ጄነሬተሩን ያበራው የለም ለካ" በማለት ሎምባርድ

አስታወሰ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምን ሂደን ጀነሬተሩን አናስነሳውም?" በማለት ብሎር ርግጠኛነት በማይታይበት ድምፅ ጠየቃቸው፡፡

"የተወሰኑ ሻማዎች የዕቃ መደርደሪያው ውስጥ እንደነበሩ አይቻለሁ፡፡ እነርሱን ብናበራ ይሻላል" ዳኛ ዋርግሬቭ አማራጭ አቀረቡ፡፡ ሎምባርድ የታሸጉ ሻማዎች አመጣ፡፡ አምስት ሻማዎችን አብርተው ተቀመጡ፡፡ ሰአቱም ለስድስት ሩብ ጉዳይ ሆኖ ነበር፡፡

• • •

ለአስራ ሁለት ሃያ ጉዳይ ሲሆን ቬራ ሳሎኑ ውስጥ መቀመጡ ስላሰለቻት ወደ ክፍሏ በመሄድ ገላዋን ለመታጠብ ወሰነች፡፡ አንድ ሻማ አብርታ ይዛ አራቱን ወንዶች ሳሎን ውስጥ በመተው ወደ ክፍሏ አመራች፡፡

የመኝታ ክፍሏን በር ከፍታ ስትገባ የባህር ዳርቻ ሽታ አፍንጫዋን ሞላው፡፡ ሽታው የሴንት ትሬዴኒክን የባህር ዳርቻ ይመስል ነበር፡፡ በምናቧ የሳለችው መሆኑን ለራሷ በመንገር ለመረጋጋት ሞከረች፡፡ በዚያ ላይ ቤቱ ደሴት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ቀኑን ሙሉ በማዕበል ሲናጥ የዋለው ባህር ያለችበት ድረስ ሊሸት እንደሚችል በማስታወስ ራሷን አበረታታች፡፡

'ወደ ዳር ልዋኝ ፣ ቬራ ...'

'ለምን ወደ ዳር አልዋኝም?'

የማይረባ ህፃን! እርሱ ባይኖር ኖሮ ሁጎ በቀላሉ ሃብታም መሆን በቻለና ባገባት ነበር....

ሁጎ ........

ሁጎ በርግጥ አጠገቧ ነበር? መኝታ ቤቷ እየጠበቃት ይሆን? ይህን እያሰበች ወደ ክፍሏ መሃል ስትዘልቅ በመስኮት የገባው ሃይለኛ ንፋስ ሻማዋን አጠፋባት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በድንጋጤ ደርቃ ቀረች፡፡ ክፍሉ ውስጥ ከርሷ ሌላ ሰው ያለ መሰላት፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ ራሷን በመቆጣጠር ወንዶቹ ሳሎን ውስጥ መሆናቸውን ለራሷ ደጋግማ በመንገር ለመረጋጋት ሞከረች፡፡

ሴንት ትራዴኒክን ያስታወሳት የባህር ሽታ ምናልባ የሳለው ሳይሆን የእውነት ነበር፡፡ ክፍሏ ውስጥ ሌላ ሰው አለ .....፡፡ በእርግጠኝነት የሆነ ድምፅ መስማቷን አወቀች፡፡

ከዚያም በቆመችበት በጣም የሚቀዘቅዝ እጅ አንገቷ ላይ አነቃት፡፡ ቀዝቃዛ እጅ ... የባህሩ ሽታ .....

• • •

ቬራ የቻለችውን ያህል ጮኸች፡፡ ነገር ግን ወንዶቹ ሰምተው መንቀሳቀስ አልጀመሩም ነበር፡፡ የወንበር ኳኳታ ፣ የበር ድምፅ እንዲሁም የሚሮጡ ሰዎች ኮቴ አልተሰማትም፡፡ በድጋሚ ጮኸች እና ወለሉ ላይ ወደቀች፡፡ በወደቀችበት ቅፅበት የኮቴዎች ድምፅ ተሰማት፡፡ ክፍሏ ውስጥ ብርሃን እንዳየች ወደ ኋላዋ አፈገፈገች፡፡

'ምንድን ነው?'

'ምን ሆንሽ?'

ወደ ኋላ ለመሸሽ ሞከረችና ወዲያውኑ ራሷን ሳተች፡፡ ከእፍታ በኋላ ስትነቃ ወንዶቹ ሻማ ይዘው አጠገቧ ቆመው ነበር፡፡

"ምንድን ነው ያ?" በማለት አንዱ ሻማውን ወዳስጠጋበት አቅጣጫ ተመለከተች፡፡ ረጅም ሃረግ መሰል የባህር ውስጥ አረም የክፍሏ ኮርኒስ ላይ ተሰቅሎ ወደ ታች ተንጠልጥሏል፡፡ ቀዝቃዛ እጅ ያነቃት የመሰላትም አረሙ አንገቷ ላይ ሲነካት ነበር፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች ለመሳቅ ሞከረች ፡- "አረም .... የባህር አረም ነበር ለካ የሸተተኝ ..." በማለት ወዲያውኑ ራሷን ሳተች፡፡

ከወደቀችበት አንስተው የሚጠጣ ነገር ሲያቀምሷት በመጠኑ ነቃች፡፡ ብራንዲ ሽተታት፡፡ ብርጭቆውን ገፋ አደረገችና በርጋታ ተነሳች፡፡

"ከየት ነው ያመጣኸው?"

ብሎር ቆየት ብሎ መለሰላት "ከሳሎን ነዋ!"

" አልጠጣም"

ሎምባርድ በረጅሙ ሰቆ "አትጠጪ፡፡ መንቃትሽ በራሱ ጥሩ ዜና ነው፡፡ ያልተከፈተ ጠርሙስ ይገኝ ልምጣ" በማለት ክፍሉን ለቅቆ ወጣ፡፡

ቬራ ግራ እንደተጋባች "አሁን ደህና ነኝ፡፡ የሚጠጣ ውሃ ብቻ ስጡኝ" አለች

አርመስትሮንግ ደገፍ ወደ መታጠቢያ ክፍሏ ወሰዳት፡፡ ብርጭቆ እንስታ ውሃ ሞላች፡፡

"ብራንዲው እኮ ንፁህ ነበር" በማለት ብሎር በስጨት ብሎ ተናገረ

"በምን አወቅህ?" አርመስትሮንግ ነበር የጠየቀው፡፡

"የሆነ ነገር የጨመርኩበት መስሎሃል አይደል?"

"አንተ ልትጨምርበት ትችላለህ አላልኩም፡፡ ነገር ግን የሆነ ሰው ጠርሙስ ውስጥ የሆነ ነገር ጨምሮበት ሊሆን ይችላል-"

በዚህ መሃል ሎምባርድ ያልተከፈተ ብራንዲ ይዞ ገባ፡፡ ጠርሙሱን ወደ ቬራ አፍንጫ አስጠጋላትና "ይኸው ያልተከፈተ አምጥቻለሁ፡፡" በማለት አሽጉን እየከፈተ "እድሜ ባልታወቀው ገዳያችን ቤቱ ሙሉ መጠጥ ነው" በማለት በብርጭቆ ቀዳ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

...ቬራ ላለመጠጣት ወደ ኋላ ስታፈገፍግ ዶ/ር አርመስትሮንግ ትከሻዋን ...ዝ አድርጐ እንድትጠጣ አግባባት፡፡ አንድ ጉንጭ ቀመሰች፡፡ ወዲያውኑ ...ሷ ተመለሰ፡፡

...ፊፕ ሎምባርድ በእርካታ ፈገግ ብሎ "በእቅዱ መሰረት ያልተሳካ አንድ ...ድያ " አለ

...ቅዱ ራሴን እንድስት እና በዚያው እንድሞት ነበር?" በማለት ...ጠየቀችው

"በድንጋጤ እንድትሞቺ አስቦ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን መሰል አጋጣሚ ...ለም እንዴ ዶ/ር?" በማለት ሎምባርድ ጠየቀ፡፡

"ጤነኛ እና ወጣት ከሆነች በድንጋጤ ላትሞት ትችላለች፡፡ ነገር ግን ...ምናልባት " በማለት ዶ/ሩ የብራንዲውን ብርጭቆ አንስቶ በጣቱ ጫፍ ቀመሰ፡፡ አረፍተ ነገሩን ከመጨረሱ በፊት ብሎር በቁጣ አምባረቀበት፡፡

"አንተ ጤና ቢስ! አሁንም የሆነ ነገር የጨመርኩበት መስሎህ ከሆነ የምትናገረውን ነገር ምረጥ፡፡ አዋርድሃለሁ!"

"ለመሆኑ ዳኛ ዋርግሬቭ የታሉ?" ሙሉ በሙሉ ንቃቷ የተመለሰላት ቬራ ነበረች የጠየቀቻቸው፡፡ ሶስቱ በድንጋጤ ተያዩ

"እንዴ? አብረውን የመጡ መስሎኝ ነበር እኮ..."

"ዶ/ር ከኋላዬ ነበርክ፡፡ ሲመጡ አላየሃቸውም?" በማለት ብሎር ጠየቀው

"የተከተለኝ መስሎኝ ነበር፡፡ ሽማግሌ ስለሆነ ከእኛ እኩል ሮጦ ላይደርስ ይችላል፡፡

ሶስቱ ወንዶች በድጋሚ ተፋጠጡ፡፡ ከዚያም ሎምባርድ "ምን ይባላል?" በማለት ተገርሞ ሲጠይቅ ብሎር "እንፈልጋቸው " በማለት ቀድሞ ሲወጣ ሁለቱ ወንዶች ተከተሉት፡፡ ቬራም ከኋላ በዝግታ ተከተለቻቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ተከታትለው ሳሎኑ ውስጥ ሲገቡ ዳኛ ዋርግሬቭ አልነበሩም፡፡ ወደ ጠባቧ እንግዳ መቀበያ በማምራት በሩ ላይ ደርሰው ቆሙ፡፡ ከፊት የነበረው አርመስትሮንግ ወደኋላ ዞሮ ሌሎቹ ድምፅ እንዳያሰሙ በእጁ ምልክት ሰጥቷቸው ወደ ውስጥ ዘለቀ፡፡

ዳኛ ዋርግሬቭ ረጅም መደገፊያ ያለው ወንበራቸው ላይ ተቀምጠዋል፡፡ በወንበራቸው የግራ እና የቀኝ መደገፊያዎች ላይ ሻማዎች በርተዋል፡፡ ረጅም መጋረጃ በዳኛ ጋውን መልኩ የለበሱ ሲሆን ሰው ሰራሽ የዳኛ ፀጉርም ጭንቅላታቸው ላይ ተደርጓል፡፡

ዶ/ር አርመስትሮን በዝግታ ወደ ዳኛው ተጠጋ፡፡ ጎንበስ ብሎ ተመለከታቸው፡፡ ሰው ሰራሹን ፀጉር አንስቶ ጣለው፡፡ መሳጣ ግንባራቸው መሃል ላይ ትንሽ ቀዳዳ ተመለከተና በጣቱ ዳበሰው፡፡

"በጥይት ተመትቶ ሞቷል" በማለት ተናገረ፡፡

"የፈጣሪ ያለህ! የጠፋው ሽጉጥ" በማለት ብሎር ተናገረ፡፡

"መሃል ግንባሩን ነው የመታው"

ቬራ የወደቀውን ሰው ሰራሽ ፀጉር አንስታ ተመለከተችውና "ይሄ ፀጉር የወ/ሮ ኤሚሊ ነው፡፡ እንደጠፋባቸው ሲናገሩ ሰምቻለሁ" በማለት በፍርሃት ተንቀጠቀጠች፡፡

"የለበሱት መጋረጃ ደግሞ ሮጀርስ መጥፋቱን የተናገረው ነው!"

በዚህ መሃል የፊሊፕ ሎምባርድ ረጅም ሳቅ ክፍሉን ሞላው፡፡

"አምስቱ ልጆች ህግ ተፈተኑ ፤

አንዱ ሲመረጥ አራቱ ተበተኑ፡፡..."

t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት የህፃናት መዝሙሩን ግጥም ሁለት ስንኞች በቃሉ አለ፡፡ "የአደገኛው ዳኛ ጀስቲስ ዋርግሬቭ ፍፃሜ ይህ ነው፡፡ ከእንግዲህ በኋላ በሰይጣናዊ ፍርዱ ወደ ሞት የሚልካቸው ሰዎች የሉም፡፡ ወጣቱ ኤድዋርድ ሴተን ይሄንን ቢያይ ምን ያህል ይስቅ ነበር ..." በማለት ከጣሪያ በላይ ሳቀ፡፡

"ዛሬ ጠዋት ዳኛው ገዳይ እንደማይሆኑ ስትናገር አልነበር እንዴ?" በማለት ቬራ ጠየቀችው፡፡

ሎምባርድ ሳቁን አቁሞ አፈጠጠባትና "ያኔ ተሳስቼ ነበራ ፡፡ ከመካከላችን በነፃ የተሰናበተው አንዱ ሰው ይኸው!" በማለት በሁለት እጆቹ ወንበር ላይ የተቀመጠውን የዳኛ ዋርግሬቭ ራስ ጠቆማት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አስራ አራት

የዳኛ ጀስቲስ ዋርግሬቭን አስከሬን ወደ መኝታ ቤታቸው ተጋግዘው በመውሰድ አልጋው ላይ አስተኙ፡፡ ከዚያም አራቱ ተያይዘው ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል በመውረድ ተቀምጠው መተያየት ቀጠሉ፡፡

"ምንድን ነው ቀጥሎ የምናደርገው?" በማለት ብሎር አስፈሪውን ፀጥታ ገፈፈው፡፡

"ምግብ መብላት አለብን" በማለት ሎምባርድ ሃሳብ አቀረበ፡፡ በቆርቆሮ የታሸገ ምላስ እና ሰምበር አገኙ፡፡ ምንም ቃል ሳይለዋወጡ ተመግበው ጨረሱ፡፡

"ከዚህ በኋላ ምላስ የሚባል ነገር የምንበላ አይመስለኝም" በማለት ቬራ አማረረች፡፡

ከአፍታ ዝምታ በኋላ ብሎር ፈገግ ብሎ "እንግዲህ አራታችን ቀርተናል፡፡ ቀጣዩ ማን ይሆን?" በማለት ጠየቀ፡፡

አርመስትሮንግ "መጠንቀቅ ይኖርብናል" ሲል ብሎር ቀበል ብሎ "ዳኛው ከመሞቱ በፊት አሁን እንዳልከው ነበር የተናገረው" አለ፡፡

"ለመሆኑ እንዴት ይሆን ዳኛውን ያስወገዳቸው?? በማለት ዳኛው ተገርሞ ጠየቀ፡፡

"አስገራሚ ጨዋታ! በመጀመሪያ ቬራ ክፍል ውስጥ የባህሩን አረም አስቀመጠ፡፡ እርሷ ስትጮህ ሁላችንም ሮጠን ወደ ላይ ወጣን፡፡ በዚያ ወቅት ሽማግሌውን በግላጭ አገኛቸው" በማለት ሎምባርድ የገዳዩን የተቀነባበረ ዘዴ አደነቀ

"የተኩስ ድምፅ እንዴት ሳንሰማ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

ቬራ እየሰሙኸች ነበር፡፡ እኛም ስንፈራራ ነበር፡፡" በማለት ሎምባርድ መለሰለት፡፡ ንግግሩን በመቀጠልም "ያ ዘዴው ከዚህ በኋላ እንደማይሰራ ስለሚያውቅ ቀጥሎ ሌላ ነገር መጠቀሙ አይቀርም" አላቸው፡፡

'ቀጥሎ ምን ሊያደርግ ይችል ይሆን?' በማለት አርመስትሮንግ ከአራቱ የተሻለ ግምት ያለው ሰው ቢኖር በሚል ተመለከታቸው፡፡

ቬራ ፦ "ማሰብ አልቻልኩም" ስትል ፤ ሎምባርድ ፈርጠም ብሎ "የራሴ የሆነ ግምት አለኝ ....." አላቸው፡፡ ከዚያም አራቱ እርስ በርስ መተያየት ጀመሩ፡፡

ቬራ 'በጣም ደክሞኛል፡፡ መተኛት አለብኝ" በማለት ለመሄድ ተነሳች፡፡

ሎምባርድም ከወንበሩ በመነሳት "ተቀምጠን መፋጠጡ ምንም ጥቅም የለውም' ሲል ብሎርም ለመሄድ አብሮ ተነሳ፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ በመጨረሻ ተነስቶ "ሁላችንም በቀላሉ እንደማንተኛ ብናውቅም ወደየመኝታችን ከመሄድ የተሻለ ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡" አለ፡፡

በሩ አጠገበብ ሲደርሱ ብሎር ብዙም በማይሰማ ድምፁ "ለመሆኑ ያ ሽጉጥ የት ይሆን?" በማለት ጠየቀ፡፡

• • •

አራቱ በየመኝታ ቤታቸው በር ላይ ሳይደርሱ የበራቸውን እጀታ በመያዝ ለመግባት መጠባበቅ ጀመሩ፡፡ ምንም ቃላት ሳይለዋወጡ እርስ በርሳቸው ተያዩ፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ከፍተው ገቡ፡፡

ከአፍታ በኋላ የበር ቁልፍ እና የወንበር እንቅስቃሴ ከአራቱም ክፍል ተሰማ፡፡ በፍርሃት የተዋጡት አራቱ ቀረኛ ሂቆች እስከ ጠዋት ድረስ በየክፍላቸው መሸጉ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

• • •

ፊሊፕ ሎምባርድ በሩን በመንበሩ አስደገፎ ወደ መልበሻ ጠረጴዛው ተራመደ፡፡ በደብዛዛው የሻማ መብራት እማካኘኑት ፊቱን በመስታወት ተመለከተ፡፡ በድካም የዛለ ቢመስልም የአዳኝ አይኖቹ አሁንም ንቁ ነበሩ፡፡

"ይሄ ስራ ደህን ወጥሮሃል!" በማለት በመስታወቱ ውስጥ ላለው የራሱ ምስል ተናገረና ልብሱን አወላለቀ፡፡ የእጅ ሰአቱን ከአልጋው ጎን በሚገኘው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና ከመተኛቱ በፊት የጠረጴዛውን መሳቢያ ከፈተ፡፡

ቁልቁል አፍጥጦ እየተመለከተ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ አንድ ሽጉጥ መሳቢያው ውስጥ ነበር፡፡

• • •

ቬራ አልጋዋ ውስጥ ገብታለች፡፡ ከትራሷ አጠገብ የበራውን ሻማ ለማጥፋት አልደፈረችም፡፡ ምንም እንደማትሆን ለራሷ ደጋግማ በመናገር ለመድፈር ሞከረች፡፡

"ለምን እዚሁ ክፍል ውስጥ አልቆይም፡፡ ቢነጋም አልወጣም፡፡ ምግብ አልፈልግም፡፡ የሚረዳን ሰው እስኪመጣ እዚሁ በመደበቅ በህይወት እቆያለሁ ..." በማለት ስለመጪው እቅድ አወጣች፡፡

ወዲያው ደግሞ ኮርንዎል ፣ ሁጐ እና ለህፃኑ ሲሪል ያለችው ነገር በሃሳቧ ተመላለሱባት፡፡ የሲሪል ውትወታ ጆሮዋ ላይ አቃጨለባት፡፡

"ወደ መሃል ልዋኝ ቬራ? ወደ ድንጋዩ ብዋኝስ?"

"እናትህ ወደ መሃል መዋኘትህን ካየች ትቆጣኛለች፡፡ ባይሆን ነገ ስትዋኝ እሷን አዋራልሃለሁ፡፡ አንተም በፍጥነት ወደ መሃል ተዋኝተህ ድንጋዩ ላይ ደርሰህ ታስገርማታለህ" በማለት የተናገረችው ትዝ አላት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በወቅቱ ያሰበችውን መላልሳ አስታወሰችው፡፡ በማግስቱ ሁጐ ወደ ከተማ እንደሚሄድ ታውቃለች፡፡ ሲመለስ ሁሉም ነገር ተጠናቅቆ ይጠብቀዋል፡፡ እንዳሰበችው ባይሆንስ? ሴሪል ቢተርፍስ? 'ቬራ ቀኝ ብላኝ ነው' ማለት ቢያጋልጣትስ? ይሄንን የመሰለ ነገር ቢሆን እንኳን ሀቱ መቆሸቱን ትናገራለች፡፡ ከሴሪል ይልቅ እርሷን እንደሚያምኗት ታውቃለች፡፡ ከዚያ ሁሉ ሃሳብ የሚገላግላት ሌላው ነገር ደግሞ ሴሪልን ለማትረፍ በመሞከር የቃታት አስመስላ ሰጥሞ እስኪሞት ድረስ በዝግታ ወደ'ርሱ መዋኘት ነበር፡፡ ማንም ሊጠረጥራት አይችልም ...

ሁጐ ጠርጥራት ነበር? ለምንድን ነበር እንደዚያ ያያት? አውቆባት ይሆን? ከፍርድ ቤት በጥድፊያ ወጥቶ የሄደው ስላወቀ ይሆን?

ለምንድን ነው ሁጐ ለደብዳቤዋ መልስ ያልሰጣት?

ሁጐ ....

ሁጐ ........

ስለ ሁጐ ማሰብ የለባትም፡፡ ሁጐ የለም ! ሁሉም ነገር አልፏል፡፡ ለምንድን ነው ሁጐ ክፍሉ ውስጥ ያለ የሚመስላት?

ቬራ በሃሳብ ተወጥራ ስትገላበጥ ቆየች፡፡ በመጨረሻም ኮርኒሱ ላይ አፍጥጣ እንቅልፏን መጠባበቅ ጀመረች፡፡ በድንገት ግን ኮርኒሱ ላይ የተንጠለጠለ ሜንጦ አየች፡፡ ያስደነገጣት የባህር ሃረግ የተንጠለጠለበት ሜንጦ ክፍሉ ውስጥ ያልነበረ መሆኑን አስታወሰች፡፡

በፍርሃት ተንቀጠቀጠች፡፡ ከሰአታት በፊት ያስደነገጣት ቀዝቃዛ እጅ እና የባህሩ ሽታ ተመለሱባት .....፡፡ ሁጐ.....

የተሰቀለውን ሜንጦ አልወደደችውም፡፡ በቀላሉ የሰውን አይን የሚስብ ..... አስፈሪ ሜንጦ .......

t.me/OLDBOOKSPDF

* * *

የቀድሞው መርማሪ ብሎር አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጧል፡፡ ትናንት አይኖቹ ደም ቢመስሉም የመተኛት ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ከአስሩ መካከል ስድስቱ ተወግደዋል፡፡ አብሪተኛው ዳኛም ጓቾችን ተከትሏል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚያስጠነቅቃቸው ሌላ አስፈሪ ዳኛ የለም....

አሁን አራቱ ብቻ ቀርተዋል ፣ ሴቷ ፣ ሎምባርድ ፣ ዶ/ሩ እና ራሱ ብሎር፡፡ ቀጣዩ ሟች ማን ይሆን? ማንም ቢሆን ቅሉ ብሎር አይሆንም፡፡

ለመሆኑ ያ ሽጉጥ የት ይሆን? በሃሳብ ተወጥሮ ከአስፈሪው ፀጥታ ጋር በመታገል ላይ ሳለ እኩለ- ሌሊት መሆኑን ከሳሎን የሚሰማው የግድግዳ ሰአት ደወል ነገረው፡፡

ልብሱን ሳያወልቅ አልጋው ላይ ጋደም በማለት ደሴቷ ላይ ከደረሰ ጀምሮ የተከሰቱትን ነገሮች አንድ በአንድ መላልሶ አሰባቸው፡፡ ከብሪት መናሩን ሳያረጋግጥ ወደ ጐን ተንጠራርቶ ሻማውን አጠፋው፡፡ በአስፈሪው ጭለማ ውስጥ ለዘለአለም የሚቆይ መስሎት ተጨነቀ፡፡

በድቅድቅ ጭለማው ውስጥ የዳኛ ዋርግሬቭ ለዘብተኛ ፊት ፣ የወ/ሮ ኤሚሊ በደም የተጨማለቀ ምስል እንዲሁም የጠወለገው የአንቶኒ ማርስተን ምስሎች እየተሽከረከሩ ይታዩታል፡፡

በመቀጠል ደግሞ በቅርቡ የማያስታውሰው አንድ ፂማም ምስል ታየው፡፡ ምስሉን እዚህ ደሴት ላይ አላየውም፡፡ በቅርብ ግዜ የሚያውቀው ሰው ምስልም አይደለም፡፡ ለማስታወስ ሞከረ ....፡፡

ምስሉን ሲያስታውስ ደነገጠ፡፡ ላንዶር ነበር፡፡ ከቀናት በፊት የላንዶርን መልክ ለማስታወስ ሞክሮ አቅቶት ነበር፡፡ በዚህ ጭለማ ውስጥ ግን ሙሉ ምስሉ ተከሰተለት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ምት ነፍና
የላንደር ዝምተኛ ሚስት እንዲሁም የአስራ አራት አመት እድሜ ባለራት ልጁ ምስልም ታየው፡፡ ሚስት እና ልጁ በአሁኑ ሰአት የት ይሆኑ? የሽጉጡ መሰወር ከላንደር ትዝታ ነቅሎ አወጣው፡፡ የሽጉጡ ነገር ፈፅሞ ሊዋለት አልቻለም፡፡ ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች አንዱ እጅ ላይ ሽጉጡ እንዳለ ይሰማዋል፡፡ ዕረፍት የነሳውም ይኸው ነበር፡፡

የሳሎኑ የግድግዳ ሰአት ደወል ተሰማው፡፡ ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ሆኗል፡፡ በዚያው ቅፅበት የሆነ ድምፅ መኝታ ቤቱ በር አጠገብ ተሰማውና ከአልጋው ላይ ተፈናጥሮ ተነሳ፡፡ በዚህ ሰአት ቤቱ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ሰው መኖሩ አስደንግጦታል፡፡ በድንገት ግንባሩን የሸፈነውን ላብ ጠራርጎ ማዳመጥ ቀጠለ፡፡

ወደ በሩ ተጠግቶ ለማዳመጥ ሞከረ፡፡ ድምፁ ጠፍቷል፡፡ ብሎር የእግር ኮቴ መስማቱን እርግጠኛ ሆኗል፡፡ ከፍቶ በመውጣት ለማጣራት ፈለገ፡፡ ነገር ግን ከውጪ ምን እንደሚጠብቀው አለማወቁ አስፈራው፡፡ ምናልባትም ድምፅ ያሰማው ሰው እንዲወጣ ፈልጎ ቢሆንስ?

ብሎር ማዳመጡን ቀጠለ፡፡ የተለያዩ ድምፆች ተመሳለሱበት፡፡ ምናባዊ ድምፆች መሆናቸውን አውቋል፡፡ ራሱን ለማረጋጋት ሲሞክር ግን ምናባዊ ያልሆነ ሌላ ድምፅ ሰማ፡፡ ለስላሳው የእግር ኮቴ ድምፅ በሩን አልፎ ወደ ደረጃዎቹ አመራ፡፡ የአርመስትሮንግ እና ሎምባርድ ክፍል ከእርሱ አልፈው ነበር የሚገኙት፡፡ የኮቴው ድምፅ ግን ሳይቆም ነበር ያለፈው፡፡

ብሎር ማየት ፈለገ፡፡ የሰውየውን ማንነት እንዲሁም ወደ የት እንደሚሔድ ...፡፡

በቀጣይ ብሎር በፍጥነት ነበር የተንቀሳቀሰው፡፡ ወደ አልጋው በመመለስ ከግድግዳው ጋር የተጣበቀውን የሶኬት ገመድ በመንቀል እጁ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠመጠመው፡፡ በፍጥነት ወደ በሩ በመመለስ ያስደገፈውን ወንበር አነሳና በሩን ድምፅ ሳያሰማ ከፍቶ ወደ ኮሪደሩ ወጣ፡፡

ወደ ደረጃው ሲራመድ ነበር ከሰአታት በፊት ቤቱን ሲያናውጠው የነበረው ንፋስ እንደቆመ የተረዳው ከአስፈሪው ፀጥታ በተጨማሪ ደግሞ ደመናውን ሙሉ በሙሉ በመግፈፍ የወጣችው ጨረቃ የቤቱን ኮሪደር እንዲሁም ምድር ቤቱን በወጋገን ሞልታው ነበር፡፡

ብሎር ደረጃውን ሲጀምር ነበር ዋናው በር አጠገብ የሰው ምስል ውልብ ሲል ያየው፡፡ ወደ በሩ ለመራመድ አሰበና የሆነ ነገር ትዝ ብሎት ቆመ፡፡ ወጥመድ ቢሆንስ? ከክፍሉ እንዲወጣ በማሰብ ድምፁን አሰምተውት ቢሆንስ?

ምናልባት ከሶስቱ እንግዶች አንዱ ቢሆንስ? ከክፍሉ የወጣውን ሰው ማንነት ለማረጋገጥ ወደ ፎቁ ተመለሰ፡፡ በመጀመሪያ ያንኳኳው የዶ/ር አርመስትሮንግ ክፍል ነበር፡፡ መልስ የለም፡፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል ጠበቀና ወደ ሎምባርድ ክፍል አለፈ፡፡ የሎምባርድ በር ሲቆረቆር ፈጣን ምላሽ አገኘ፡፡

"ማነው?"

"ብሎር ነኝ፡፡ ዶ/ር አርመስትሮንግ ክፍሉ ውስጥ የለም፡፡ እንደ ጠብቀኝ፡፡" አለና ወደ ቬራ ክፍል አመራ፡፡ ቬራም ቶሎ ነበር የመለሰችለት፡፡

"ማነህ?"

"እኔ ነኝ፡፡ መጣሁ ጠብቂኝ" በማለት ወደ ሎምባርድ ተመለሰ፡፡ ሎምባርድ በአንድ እጁ ሻማ ይዞ ሌላኛውን እጁን ደግሞ የፒጃማ ጃኬቱ ኪስ ውስጥ አድርጎ በሩ ላይ ቆሟል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንድን ነው?" በማለት ብሎርን ጠየቀው፡፡ ብሎርም ስለሰማው ድምፅ እንዲሁም ዶ/ሩ ክፍሉ ውስጥ አለመኖሩን አስረዳው፡፡ ሎምባርድ በቀጥታ ወደ ዶ/ሩ ክፍል በማምራት እያንኳኳ ተጣራ፡፡

"አርመስትሮንግ ! አርመስትሮንግ ......" መልስ አልነበረም፡፡

ሎምባርድ በርከክ ብሎ በትንሹ ጣቱ የቁልፉን ቀዳዳ ገፍቶ ሞከረው፡፡ "ቁልፉ የለም፡፡ ይሄ ማለት ከውጪ ቆልፎት ሄዷል" አለ፡፡

"ይገርማል"

"ብሎር ቶሎ እንንቀሳቀስ፡፡ አሁኑኑ እንደዘዋለን" በማለት ወደ ቬራ ክፍል ሮጠ፡፡

"ቬራ"

"አቤት"

"አርመስትሮንግ ክፍሉ ውስጥ የለም፡፡ ልንፈልገው ወጥተናል፡፡ እስክንመለስ በምንም አይነት በሩን እንዳትከፍቺ፡፡ ገባሽ?"

"ገብቶኛል"

"ራሱ አርመስትሮንግ መጥቶ እኔ ወይም ብሎር መሞታችንን ከነገረሽም አትመኚ፡፡ ከሁለት አንዳችን ሳንሆን ሁለታችንም ካልመጣን በቀር በሩን አትክፈቺ ! ገባሽ?"

"ገብቶኛል ! ሞኝ አይደለሁም"

"በጣም ጥሩ ! አሁን አደኑን እንጀምር" በማለት ሎምባርድ በሩጫ ወደ ደረጃው አመራ፡፡

"መጠንቀቅ አለብን፡፡ ሽጉጡን ይዞት ሊሆን ይችላል" በማለት ብሎር አስጠነቀቀው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድ ደረጃውን በፍጥነት እየወረደ "ተሳስተሃል ፤ ሽጉጡን አልያዘም" አለው፡፡ ዋናው በር አልተዘጋም ነበር፡፡ ወጥተው በረንዳው ላይ እንደደረሱ ከኋላው ወደነበረው ብሎር ዞረና "ሽጉጡ እኔ ጋ ነው" በማለት ከጃኬቱ ኪስ ወጣ አድርጎ ሣቃን አሳየው፡፡ "ማታ አገኘሁት እና መሳቢያዩ ውስጥ አስቀመጥኩት፡፡" አለው፡፡

ብሎር በድንጋጤ ደንዝዞ ቆመ፡፡

"ምን ሆነሃል? የምገድልህ መስሎህ ከሆነ ተሳስተሃል፡፡ ካላመንከኝ ወደ ውስጥ ተመለስና ተደበቅ፡፡ እኔ አርመስትሮንግን እፈልገዋለሁ" በማለት ሎምባርድ ብሎርን የቆመበት ትቶት ለመሄድ ተዘጋጀ፡፡

ብሎር ትንሽ አቅማምቶ ብሎርን ተከተለው፡፡ ሽጉጡን ሊጠይቀው አሰበና ተወው፡፡ በስራ ዘመኑ ከበርካታ የታጠቁ ወንጀለኞች ጋር ተጋፍጦ አልፏል፡፡ ሁሉንም በግልፅ አግኝቶ የተጋፈጣቸው ሲሆን ስኬታማም ነበር፡፡ የሚያስፈራው ነገር ቢኖር የተደበቀ አጥቂ ብቻ ነው፡፡ በግልፅ የሚመጣበትን የመከላከል አቅሙ አብሮት ነበር፡፡

• • •

ቬራ ልብስ ደርባ መልሰ መጠባበቅ ጀመረች፡፡ በሯን ደጋግማ በመመልከት በዶ/ር አርመስትሮንግ አቅም በቀላሉ እንደማይከፈት አረጋገጠች፡፡ ምናልባት ዶ/ሩ መጥቶ ሁለቱ ወንዶች መሞታቸው አሊያም መቁሰሉን እያቃሳተ ቢነግራት ምን ማድረግ ይኖርባታል? ዶ/ሩ ሊጠቀም የሚችለውን ዘዴ አንድ በአንድ አውጠነጠነች፡፡

የሁለቱን ወንዶች መውጣት አረጋግጠ ቤቱ በእሳት መያያዙን ቢነግራት አሊያም በእሳት ቢያያይዘውስ? እንዴት መወጣት እንዳለባት እያሰላሰለች ከመስኮቱ ወደ መሬት ያለውን ርቀት በጨረቃ ብርሃን ተመለከተች፡፡ ርቀት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎሬ ጉዳይ ቢኖረውም ከስር አበባው ላይ ብታርፍ ብዙ ጉዳት እንደማይደርስባት አረጋገጠች፡፡

ወንዶቹ እስኪመለሱ ግዜው እየተንቀራፈፈ ስላስጨነቃት ማስታወሻዋን አውጥታ የሆነ ነገር ለመፃፍ ሞከረች፡፡ ወዲያውኑ የሆነ ድምፅ ተሰማትና ቀና አለች፡፡ መጀመሪያ ላይ በሃሳቧ የፈጠረችው ድምፅ መስሏት ነበር፡፡ ነገር ግን እውነተኛ ነበር፡፡

ምድር ቤቱ ውስጥ የበር መስታወት ሲሰበር ሰማች፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የሰው ኮቴ ደረጃዎቹን ሲያስጮሃቸው ፤ በኋላም የበሮች መከፈትና መዘጋት ድምፅ ተሰማት፡፡ ድምፁ የበለጠ ወደ ክፍሉ ሲቃረብ ተነስታ ቆመች፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባት እርግጠኛ ባለመሆን መጠባበቅ ቀጠለች፡፡

በሩ አጠገብ የደረሰው የኮቴ ድምፅ በመጨረሻም ወደ በር ማንኳኳት ተቀየረ፡፡

"ማነህ?"

"ሎምባርድ ነኝ ደህና ነሽ?"

"ደህና ነኝ፡፡ ምን ተፈጠረ?"

"በሩን ክፈቺልን" በማለት ብሎር መኖሩን አረጋገጠላት፡፡ በፍጥነት በሩን ከፍታ ጎን ለጎን የቆሙትን ሁለት ወንዶች ከላይ እስከታች ተመለከተቻቸው፡፡ እስከ ጉልበታቸው ድረስ በውሃ ረጥበዋል፡፡

"ምንድን ነው?"

"አርመስትሮንግ ጠፍቷል"

"ምን?"

"አዎ፡፡ ተሰውሯል ማለቱ ይሻላል፡፡" ብሎር መለሰላት፡፡

"እንዴት ይሰወራል? ተደብቆ ይሆናል ..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"ደሴቷ ምንም መደበቂያ የላትም፡፡ ሁሉንም ስፍራ በጨረታው ብርሃን ተጉዘን አይተናል፡፡ የለም"

"እናንተ ስትወጡለት ወደ ቤት ገብቶ ተደብቆስ ቢሆን?"

"እኛም እሱን ገምተን ቤቱን አንድ በአንድ ፈትሸነዋል፡፡ መቼም ሳትሰጊ አትቀሪም፡፡ ዶ/ሩ አንድም ቦታ የለም፡፡፡ ተሰውሯል፡፡"

"ይሄ የማይታመን ነው!" አለች

"ልክ ነሽ" በማለት ሎምባርድ "አንድ ያልነገርንሽ ነገር ብቻ ይቀራል፡፡ ይኸውም የሳሎኑ የመስታወት መስኮት የተሰበሩ ሲሆን የምግብ ጠረጴዛው ላይ የቀሩት አሻንጉሊቶች ሶስት ብቻ ናቸው" ብለው ነገሯት፡፡

• • •

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ አምስት

ግለጻ ላይ ሶስቱ ማዕድ ቤት ተቀምጠው ቁርሳቸውን በሉ፡፡ ግታ የነበረው ግለበአ እና ንፋስ ሙሉ በሙሉ ቁሟል፡፡ ደግቅ ፀሃይ ደሴቷን ሞልታዋለች፡፡ የሶስቱ እስረኞች ፍርሃትም ሙሉ በሙሉ የተገፈፈ ይመስላል፡፡ ሀይወታቸው አደጋ ላይ እንደሆነ ቢያውቁም ቢያንስ ጭለግ ባለመሆኑ ለመጋፈጥ ደፍረዋል፡፡

ሎምባርድ በተረጋጋ ድምፅ "ከፍ ያለ ስፍራ ላይ ሆነን በመስታወት ምልክት እርዳታ እንጠራለን፡፡ የሆነ ሰው ከደሴቷ ውጪ ሆኖ ሊያየን ይችላል፡፡ ካልሆነ ደግሞ ግታ ላይ እሳት እናንዳለን፡፡ መቼም ጭፈራ ላይ ያለን አይመስላቸውም" በማለት ሁለቱን ለማበረታታት ሞከረ፡፡

ቬራ በተበረታታ ሁኔታ "እርግጠኛ ነኝ እስከ ግታ ድረስ በጀልባ ይመጡልናል" አለች፡፡

"ንፋሱ ቢቆምም ባህሩ ገና ስላልተረጋጋ እስከ ነገ ድረስ ጀልባ አያስኬድም"

"እና እዚሁ ልናድር?" በፍርሃት ተሞልታ ነበር ሎምባርድ ላይ ያፈጠጠችበት፡፡

"እንደምንም ብለን ሃያ አራት ሰአት መቆየት አያቅተንም" አላት፡፡

ብሎር ጉሮሮውን ጠራረገና "አርመስትሮንግ ምን እንደሆነ ግጣራት አለብን" አላቸው፡፡

"የእሻንጉሊቶቹ ቁጥር ሶስት መሆን መሞቱን ያሳያል " በማለት ሎምባርድ ተናገረ

"ሬሳውስ?" ቬራ ጠየቀች

"እም! ሬሳው የታለ?" ብሎር አከለ፡፡

"እሱ ነው የሚገርመው " በማለት ሎምባርድ ትከሻውን ሰበቀ፡፡

"ምናልባት ባህር ውስጥ ተወርውሮስ ቢሆንን?" ብሎር በጥርጣሬ ጠየቀው፡፡

"ማን ይወረውረዋል? እኔ? በሩን ከፍቶ ሲወጣ አይተኸው ወደ እኔ ክፍል ርጠህ መምጣትህን ተናግረህ የለ? ከዚያም አብረን ነው ለፍለጋ የወጣነው፡፡ በዚያ መሃል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬሳ ተሸክሜ ባህር ድረስ እንዴት ልሄድ እችላለሁ?" በማለት ሎምባርድ ቆጣ ብሎ ጠየቀው፡፡

"እሱን አላውቅም፡፡ ግን አንድ ነገር አውቃለሁ"

"ምን?"

"ሽጉጡ፡፡ መጀመሪያም ሆነ አሁን በአንተ እጅ ይገኛል፡፡ በመሃልም እንተው ጋር ላለመሆኑ በምን እርግጠኛ መሆን እንችላለን?" በማለት ብሎር ጠየቀው፡፡

"ተው እንጂ ብሎር ፣ ሁላችንም ተፈትሸን ነበር እኮ"

"እዎን ግን ከፍተሻው በፊት ደብቀኸው በኋላ መልሰህ ወስደኸውስ ቢሆንም"

"በፈጣሪ ስም እምልልሃለሁ መሳቢያው ውስጥ ተመልሶ ነው ያገኘሁት፡፡ በህይወቴ እንደዚህ ያለ አስገራሚ ነገር ገጥሞኝ አያውቅም፡፡" በማለት ሎምባርድ መለሰለት፡፡

"እንድናምንህ ትፈልጋለሁ ማለት ነው? አርመስትሮንግም ሆነ ሌላ ሰው ለምን ብሎ ሽጉጡን መልሶ ያስቀምጥልሃል?"

"ምን አውቄ? ለመገመት የሚከብድ ነገር ነው፡፡ ግን ሆኗል" በማለት ሎምባርድ ትከሻውን ሰበቀ፡፡

ብሎርም ትከሻውን ሰብቆ "ስለዚህ የተሳሳተ ነገር አውርተህልናል ማለት ነው፡፡" አለ

"አላመንከኝም?"

"ይኸውልህ ሎምባርድ ፣ እውነተኛ ሰው ብትሆን ኖሮ "

"እውነተኛ ሰው ነኝ አላልኩም" በማለት አቋረጠው፡፡

"እሺ እውነቱን መነጋገር ካለብን አንድ ነገር በግልፅ ማውራት [illegible] ይኸውም አንተ ሽጉጡን በመያዝህ የእኔ እና የቬራ ህልውና ባንተ ፍላጎት [illegible] የተመሰረተ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ሽጉጡን መድሃኒቶቹን ያደረግንበት ሳጥን [illegible] አስገብተን ቁልፉን ለሁለት እንይዛለን" በማለት ብሎር ሃሳብ አቀረበ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

ሎምባርድ ሲገራ ለኩሶ በሃይል ሳበለትና "ያግ ፈፅሞ አይሆንም፡፡ ሽጉጡ ከእጇ አይወጣም" በማለት እቅጩን ነገረው፡፡

"ስለዚህ በአንድ ነገር እርግጠኛ ሆነናል ማለት ነው" በማለት ብሎር በጥልቀት ተመለከተው፡፡

"ማይታወቀው ገዳይ እኔ እንደሆንኩ?" በማለት ሎምባርድ በረጅሙ ተንፍሶ ጠየቀው፡፡ "ገዳዩ እኔ ብሆን ለምን ትናንት ማታ አልገድልህም ነበር፡፡ ከዛያ ግዜ በላይ አንተን የመግደል አጋጣሚው ነበረኝ፡፡"

"ምናልባት የሆነ ምክንያት ይኖርሃል" በማለት ብሎር መለሰለት፡፡

በፀጥታ ስታዳምጣቸው የቆየችው ቬራ ቆጣ ብላ ነበር ክርክራቸውን ያቋረጠችው፡፡ "ሁለታችሁም በማያከራክር ነገር ላይ ግዜ ትፈጃላችሁ፡፡ ሞኞች!"

"ምን ማለት ነው?"

"እንዴት የህፃናቱን የተረት ግጥም አታስታውሱም?"

አራቱ ልጆች ባህር ሲቀዝፉ !

እንዱን አሳ በላው ! ሶስቱ ተረፉ፡፡

በማለት የግጥሙን ሁለት ስንኞች አስታወሳቸው ቀጠለች፡- "አሳ በላው የሚለው ጥሩ መሸወጃ ነው፡፡ አርመስትሮንግ አሁንም ደሴቷ ላይ እንደሚገኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ የሞተ እንዲመስለን ብሎ እንዱን እሻንጉሊት ይዞ ሔዷል"

"ሊሆን ይችላል"

"የት ሊደበቅ ይችላል? ደሴቷን ሙሉ በሙሉ በርብረናል" በማለት ብሎር ተከራከረ፡፡

"ሽጉጡን ፍለጋ በርብረን ነበር" በማለት ቬራ ፊቷን ቋጠረችና ሎምባርድን ተመለከተችው፡፡

"አዎ ! ግን በሽጉጡ እና በሰው ልጅ መካከል የመጠን ልዩነት አለ" በማለት ሎምባርድ ተቃወማት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ህዝቡን መመልከት አስደሰተኝ፡፡ ህይወቴ አደጋ ላይ እንደሆነ ባውቅም ፍርሃት አልተሰማኝም፡፡' በማለት ዘና አለች፡፡

ብሎር ሰአቱን አየና "ምሳ ብንበላስ?" አላቸው፡፡

"እኔ አልበላም፡፡ በተለየይ ያንን የታሸገ ምላስ እና ሰምበር ድጋሚ ከበላሁ ሞኛል' በማለት ቬራ ውጪ ለመቆየት ወሰነች

"አንተስ ፣ ሎምባርድ?"

"እኔም ምግቡ አስጠልቶኛል፡፡ ከቬራ ጋር እዚሁ እቆያለሁ፡፡' በማለት ሲመልስለት ብሎር በፈገግታ ተመለከተው፡፡

ቬራ አስተያየቱ ስለገባት "ምንም አያደርገኝም፡፡ ምናልባት እንዳይገድለኝ ትጠብቀኛል አይደል?" አለችና በፈገግታ ጠየቀችው፡፡

"እንደዚያ ሳይሆን ሳንለያይ ብንቆይ ይሻላል ብዬ ነው' በማለት ብሎር አፈር ብሎ አስተባበለ፡፡

"ሽጉጥህን ወደ ቤቱ መሄድ ፈርተህ ከሆነ አብሬህ ልምጣ' በማለት ሎምባርድ ወደ ብሎር ተመለከተው፡፡

"አይ .... አይ! አትምጣ' በማለት ተከላከለው፡፡

"ምነው ፈራኸኝ? ልገድልህ ከፈለግሁ እኮ አሁንም እችላለሁ' በማለት ብሎር ሳቅ አለ፡፡

"ትችላለህ፡፡ ነገር ግን በእቅዱ መሰረት አንድ በአንድ መወገድ ያለብን ይመስለኛል' በማለት ብሎር ሲመልስለት ሎምባርድ በአፀፋው ገርመም አድርጎት "ትክክል ይመስለኛል' አለው፡፡

"ቤቱ ብቻዬን ብገባበት ይቀፋል ብዬ ነው' በማለት ብሎር ለመሄድ ተዘጋጀ፡፡

"ሽጉጤን ባውስህ ጥሩ ነበር ፣ ግን ....' በማለት ሎምባርድ ሲያሽሟጥጥ መልስ ሳይሰጠው ሄደ፡፡

"የአውሬው መመገቢያ ሰአት ደርሷል' በማለት ብሎርን ከጀርባ እየተመለከተው ተናገረ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"ብቻውን መሄድ ግን አደገኛ ነው" በማለት ቬራ እየቀፈፋት ብሎርን ከጀርባው ተመለከተችው፡

"ምን ይሆናል ብለሽ ነው? አርመስትሮንግ ምንም መሳሪያ አልያዘም፡፡ በዛ ላይ ብሎር የተሻለ ጥንካሬ ስላለው ሊቋቋመው ይችላል፡፡ ከምንም በላይ ግን አርመስትሮንግ ቤቱ ውስጥ አለመኖሩ ይሰማኛል"

"ምን እያልክ ነው? ብሎርን ጠርጥረኸው እንዳይሆን?" በማለት ቬራ ተገርማ ጠየቀችው፡፡

"እስቢው እስኪ የአርመስትሮንግ መጥፋት የነገረን ብሎር ነው፡፡ እኛን ከመቀስቀሱ በፊት አስወግዶትስ ቢሆንስ?"

"እንዴት?"

"እሱን አላውቅም፡፡ ነገር ግን መፍራት ካለብኝ ብሎርን ነው፡፡ ከመጀመሪያ ጀምሮ ስለራሱ የተናገረው ታሪክ የውሸት ቢሆንስ? ምናልባት እኮ ያበደ ቱጃር አሊያም የለየለት እብድ ሊሆን ይችላል፡፡"

ቬራ በድንጋጤ ፊቷ ቀላ፡፡ "ታዲያ እኛንም ሊያስወግደን ይችላል....." በማለት በፍርሃት ተሞላች፡፡

ሎምባርድ ሽጉጡን እያሳያት "እንዳያስወግደን በተቻለኝ መጠን እጠባበቃለሁ" በማለት በጥልቀት ተመለከታትና "ትተማመኚብኛለሽ አይደል? ቢያንስ እንደማልገድልሽ ይሰማሻል?" በማለት ጠየቃት፡፡

"ቢያንስ አንደኛችሁን ማመን ያለብኝ ይመስለኛል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከብሎር ይልቅ አርመስትሮንግ የበለጠ ያጠራጥረኛል፡፡ በማለት እየት አደረገችውና "የሆነ ሰው ተደብቆ የሚከታተለን ይመስለኛል" አለችው፡፡

"ወ/ሪት ቬራ እኔ ተደብቆ ከሰማይ ወደ ምድር በሚመለከት መለኮታዊ ፍጡር አላምንም፡፡ እዚህ ደሴት ላይ የሚደረገው በሙሉ የሰው ልጅ ተግባር ነው" በማለት አስረግጦ ነገራት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሎሮ ነጻ
በአግራሞት ተመለከታትና "እስኪ ደግሞ ስለራስሽ ንገሪኝ፡፡ እንደተባለው ሀገሩን ጉርለሽዋል?" በማለት ድንገተኛ ጥያቄ ጠየቃት፡፡

ቬራ በሐሳብ ኸትት ነበር የመለሰችለት "በፍፁም! አልገደልኩትም! ምን ለማለት ፈልገህ ነው?"

ሎምባርድ ሳቅ ለማለት ሞከረ፡፡ "እንደገደልሽው ያስታውቃል፡፡ ይልቅስ ከገድያው ጋር ምናልባት የተያያዘ አንድ ወንድ ይኖር ይሆን?" በማለት አሽሟጦ ጠየቃት፡፡

ቬራ ፊት ላይ የተዘበራረቀ ስሜት ተነበበ፡፡ በረጅሙ ተነፈሰችና "አዎን ፡፡ አንድ ሰው ነበር-" አለች፡፡

"አመሰግናለሁ፡፡ እሱን ነበር ለማወቅ የምፈልገው፡፡" በማለት መለሰላት፡፡

ቬራ በድንጋጤ ተፈናጥራ ተነሳችና "የምን ድምፅ ነው? ሰማኸው?" በማለት ጠየቀችው፡፡

"የሆነ ነገር የወደቀ መሰለኝ፡፡ ጩኸቱንስ ሰምተሽዋል?" በማለት ወደ ቤቱ አቅጣጫ እያየ ጠየቃት፡፡ ሁለቱም ድምፁ ከቤቱ እንደመጣ አረጋግጠዋል፡፡

"ወደዛው ሄደን እናረጋግጥ" አላት

"ወደዚያ ቤት አልሄድም" በማለት ወደ ኋላዋ ስታፈገፍግ ክንዷን ያዘና ጐተታት፡፡

"ባንሔድ ይሻላል፡፡ ሁለታችን ብቻ ከቀረን ቢያንስ ራሳችንን እንጠብቅ" በማለት ተማፀነችው፡፡

"እዛ ቤት አንድ ሌላ ሰው አለ፡፡ ምናልባትም አርመስትሮንግ " በማለት ለመሄድ ሲሰናዳ ተመለከተችና "አሁን ገና አመንከኝ አይደል? ብሎርን አትጠራጠር ስልህ ነበር" አለችው፡፡

"ለማንኛውም በድጋሚ እንፈልገዋለን" አላት፡፡

"ግታ ካላገኛችሁት አሁን የምናገኘው አይመስለኝም" በማለት በተስፋ መቁረጥ ተመለከተችው እና "እሺ አብሬህ እሄዳለሁ" በማለት ተያይዘው ወደ ቤቱ አመሩ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀጥታ በሩን ከፍተው ከመግባት ይልቅ ቤቱን እንዲ ለመዞር ነበር ሉምባርድ የወሰነው፡፡ የቤቱ ምስራቃዊ በር ደረጃ ላይ ብሎር ሁለት እግሮቹን አንፈራግጦ ወድቋል፡፡ ጭንቅላቱ በነጭ የእምነበረድ ቅርፅ ተፈልጦ ነበር፡፡

ሉምባርድ ወደ ላይ ቀና በማለት የተከፈተውን መስኮት ተመለከተ፡፡ 'የማን መኝታ ክፍል ነው?' በማለት በድንጋጤ የምትንቀጠቀጠውን ቬራ ጠየቃት፡፡

'የእኔ፡፡ እምነበረዱም ክፍሌ ውስጥ የነበረ የድብ ቅርፅ ያለው ሰአት ነው፡፡' በማለት እየተንቀጠቀጠች መለሰለችለት፡፡

'የድብ ቅርፅ ....'

• • •

'ክፍልሽ ውስጥ ምንም መደበቂያ የለም አይደል?'

'በደንብ ፈትሸነው ነበር፡፡ መቼም እንደ መናኝ ገድገዳውን ካልቦረረው በቀር' በማለት በድንጋጤ እንደተሞላች መለሰችለት፡፡

'ለማንኛውም ሄጀ እመለከታለሁ' በማለት ለመሄድ ሲዘጋጅ አስቆመችው፡

'ለመመልከት እንደምትወጣ ስለሚያውቅ እዛው ይጠብቅሃል ' በማለት አስጠነቀቀችው፡፡

ሽጉጡን አሳያትና 'ይሄንን ይዣለሁ' አላት፡፡

'ብሎር ከአርመስትሮንግ የተሻለ ጠንካራ እና ንቁ እንደነበር ተናግረህ ነበር፡፡ ነገር ግን ልብ ያላልከው አርመስትሮንግ የለየለት እብድ መሆኑን ነው፡፡ እብድ [illegible] ደግሞ ከማንም የተሻለ ድፍረት እና ብልጠት አለው' በማለት [illegible] አለመሆኑን ገለፀችለት፡፡

ሽጉጡን ወደ ኪሱ መለሰና 'እንገዲያውስ ነይ እንሂድ' አላት፡፡

• • •

'ሲመሽ ምንድን ነው የምናደርገው?' በማለት ቬራን ጠየቃት፡፡ ምንም [illegible] ሳትሰጠው ተብሳጨ፡፡ 'ምንም አላሰብሽበትም?' በማለት በቁጣ ጠየቃት፡፡

'ምንም ማሰብ አልቻልኩም፡፡ ፍርሃቱ ሊገድለኝ ነው፡፡' በማለት መለሰችለት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ምሽቱን ወደ ጉብኝታው ሄደን እናሳልፋለን፡፡ ንፋሱ ስለቀነሰ ብዙም አይበርድም፡፡ በጠዋት እርዳታ ሊደርስልን ይችላል፡፡ ይበርደኝ ይሆን? በማለት ስስ ልብሷን እያየ ጠየቃት፡፡

'መኖትም ስላለ ስለ ብርዱ አታስብ፡፡ ይልቅ ዞር ዞር እንበል፡፡ እዚህ ቦታ ለዘለዑ ማበዴ አይቀርም፡፡' አለችው፡፡ ተያይዘው ወደ ባህሩ ዳርቻ አመሩ፡፡

'ገላችንን ለመታጠብ የሚመች ቦታ ቢኖር ጥሩ ነበር' አለች፡

ፀሐይ በመጥለቅ ላይ ነበረች፡፡ የጀምበሯ ወርቃማ ብርሃን ከባህሩ ጋር ተቀናጅቶ የፈጠረው እይታ በጣም ያስደስታል፡፡ ከርቀት ባህሩ ዳርቻ ላይ የሆነ ነገር ተመለከቱ፡፡

'የመዋኛ ልብስ ይመስላል ፣' አለና ገላዋን ለመታጠብ የተመቻቸ እድል ማግኘቷን ነገራት ልብሱን ወዳዩበት ቦታ አመሩ፡፡

ወደ ቦታው ሲጠጉ የተመለከቱት የመዋኛ ልብስ አለመሆኑን አረጋገጠው ተደናገጡ፡፡

'የሚታየው የወንድ ጫማ ነው?' በማለት በፍርሃት ጠየቀችው፡፡ መልስ ሳይሰጣት ወደ ፊት ተራመደ፡፡ ልብሱና ጫማው ብቻ የሚታየው የሰው ምስል ከሁለት ድንጋዮች መካከል ተወሽቆ በጥገዱ እየተንቀሳቀሰ ነበር፡፡

ሎምባርድ ተጠግቶ ሲመለከተው ደነገጠ፡፡ ቬራ በትከሻው ላይ አሻግራ ምስሉን አየችው፡፡

'ግፊማሬ ያለዉ አርምስትሮንግ ነው' አለች

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አስራ ስድስት

በርካታ አመታት እና ዘመናት ያለፉ ይመስላል፡፡ ግዜ መንቀሳቀስ አቁሞ ሙሉ በሙሉ ለሺህ ዘመናት የቀዘቀዘ ነበር የሚመስለው፡፡ ነገር ግን አንድ ደቂቃ ያህል እንኳን አልሞላቸውም ነበር፡፡

ቬራ ክሌይትሮን እና ፊሊፕ ሎምባርድ ወደታች አፍጥጠው ሬሳውን እያዩ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቀና ብለው እርስ በርስ ተያዩ፡፡

• • •

ሎምባርድ ትርጉም የሌለው ሳቅ ሳቀ፡፡ "ይኸው ነው ማለት ነው ፤ ቬራ?"

"ከእኔ እና ከአንተ በቀር ደሴቷ ላይ ሌላ ሰው የለም " በማለት አንሾካሾከች፡፡

"ትክክል፡፡ አሁን ያለንበት ሁኔታ አውቀናል መሰለኝ ፤ አይደል?" በማለት ጠየቃት

ቬራ በአገራሞት "የእምብነበረዱ የድብ ቅርፅ እንዴት በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ?" አለች፡፡

"የተጠና እንቅስቃሴ ነው ፤ ውዴ " አላት፡፡

የሁለቱ አይኖች ተገጣጠሙ፡፡ አስፈሪ የአዳኝ አውሬ አይኖች እንደነበሩት እስከዚያ ድረስ ልብ አለማለቷ አስገረማት፡፡

"ይሄ መጨረሻው ነው ፤ ገባሽ? በመጨረሻም ከእውነታው ጋር የምንፋጠጥበት ሰአት ላይ ደርሰናል"

"ገባኝ፡፡" በማለት ወደ ባህሩ ተመለከተች፡፡ በዚሁ ስፍራ ያገኘችው ጀነራል ማካርተር መጨረሻው መሆኑን የነገራት በልበ ሙሉነት ነበር፡፡ ሞቱን በፀጋ ተቀብሏል፡፡

የአርመስትሮንግ አስከሬን ቁልቁል እያየች በሃዘን ተሞልታ "ምስኪን ሰው " አለች

"ምን የሚሉት አዘኔታ ነው?"

"ሰብአዊነት! አንተስ ለሰው አታዝንም?"

"ከሞተ በኋላ ምን ማዘን ያስፈልጋል?" በማለት አሽሟጠጠ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

'ራሳውን ከዚህ ማውጣት አለብን' በማለት በሃዘን የተሞላ ልምምጥ አሰማች፡፡

'እመኖተንበ? ወደ ቤት ወስደን ከሌሎች ሰለባዎች ጋር ልንቀላቅለው?' በሹፈት ጠየቃት፡፡

'ቢያንስ ወደ ዳር እናውጣው ' በማለት ተለማመጠችው፡፡

'እሺ ይሁንልሽ፡፡' በማለት ራሳውን ለመጐተት ሲያጐንብስ ቬራም ልትረዳው አብራው አጐነበሰች፡፡ የአቅሟን ያህል ስትጐትት ቆየች፡፡ በመጨረሻም ወደ ዳር አወጡት፡፡

'ደስ አለሽ?' በማለት ጠየቃት፡፡

'በጣም እንጂ'

መልሷ የደስታ ብቻ አልመሰለውም፡፡ ድምጿ በተለየ መልኩ አስፈሪ ሆነበት፡፡ በፍጥነት እጁን ወደ ጃኬቱ ኪስ ሲወረውር ሽጉጡን እንደማያገኘው አውቆ ነበር፡፡ በዚያው ቅፅበት ቬራ ሁለት ርምጃ ወደኋላ በማፈግፈግ ሽጉጡን ደቅናበት ቆመች፡፡

'ያ ሁሉ አዘኔታሽ ኪሴ ለመግባት ነበር?'

መልስ አልሰጠችውም፡፡ ሽጉጡን አጥብቃ ስትይዝ ለመጀመሪያ ግዜ ሎምባርድ ፍርሃት ተሰማው፡፡ ብዙ ግዜ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ነገር ግን የአሁኑን ያህል ፈርቶ አያውቅም ነበር፡፡ መፍራቱን ሳለማሳወቅ እምክሮ "ሽጉጡን ስጪኝ" በማለት በቁጣ አዘዛት፡፡

ቬራ ሳቀች፡፡ ሳቋ የበለጠ ስላስፈራው በተለየ መንገድ ለመሞከር በልምምጥ መናገር ጀመረ፡፡

"ይኸውልሽ ውዴ እዚህ ላይ እኔ እና አንቺ በተቻለን መጠን ካልተግባባን "

ባልገመተችው ፍጥነት ልምምጡን አቋርጦ ወደ'ርሷ ሲወረወር ደነገጠች፡፡ በዚያው ፍጥነት ምላጩን ሳበች፡፡ የሎምባርድ ሰውነት ተጣጥፎ እግሯ ስር ወደቀ፡፡ ሁለተኛውን ጥይት ለመተኮስ ቁልቁል እያየችው አለመች፡፡ በመጀመሪያው ጥይት ልቡን ስላገኘችው ወዲያውኑ ፀጥ አለ፡፡

• • •

t.me/OLDBOOKSPDF

ቬራ ከፍተኛ የደስታ እና የእርካታ ስሜት ውስጧን ሲሞላው ተሰማት፡፡ የሚያስፈራት ነገር በሙሉ ተወገደ፡፡ ደሴቷ ላይ ብቸኛዋ ሰው እንደሆነች አረጋገጠች፡፡ ከእርሷ ሌላ ዘጠኝ አስከሬኖች ቢኖሩም የእርሷ በህይወት መቆየት በራሱ በቂ ስለነበር የሙታኑ መኖር አላስጨነቃትም፡፡

በከፍተኛ እፎይታ ተሞልታ ቁጭ አለች፡፡

• • •

በምዕራቡ አድማስ ጥግ ፀሃይዋ ሙሉ በሙሉ ገባች፡፡ የሰማዩ ቀለም ከወርቃማነት ወደ ብርቱካንማ ሲቀየር በደስታ ተመልክታ ለመሄድ ተነሳች፡፡ የሚያስፈራት ነገር ተወግዷል፡፡ በደሴቷ ብቻዋን ነች፡፡ ስጋት የለባትም፡፡

የርሃብ እና የእንቅልፍ ስሜቷን ያወቀችው ለመሄድ ስትነሳ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰአት ምግቧን መብላትም ሆነ መተኛት ትችላለች፡፡

በተለይ መተኛት......

መተኛት .......

በደሴቷ አንዷት አሻንጉሊት ብቻ ቀርታለች፡፡ ስለዚህ ያለምንም ፍርሃት መተኛት ትችላለች፡፡ በጠዋት ሰዎች እንደሚደርሱላት ገመተች፡፡ ባይመጡ እንኳን በደሴቷ ላይ ባማረው ቤት ተመቻችታ መቆየት ትችላለች፡፡

የቤቱ ዋና በር ላይ ስትደርስ ምግብ የመብላት ፍላጐቷ በድንገት ጠፋ፡፡ በአስከሬን የተሞላ ቤት ውስጥ ከመመገብ ይልቅ መተኛት የተሻለ እንደሆነ ተሰማት፡፡ በርግጥም ሰውነቷ በድካም ዝሎ ነበር፡፡

የምግብ ጠረጴዛው አጠገብ ደርሳ ቆመች፡፡ ሶስቱ አሻንጉሊቶች ሰሃኑ ላይ ነበሩ፡፡ በረጅሙ ሳቀችና "ውድ ጓደኞቼ አርፍዳችኋል" በማለት ሁለቱን በመስኮት በኩል ወረወረቻቸው፡፡ በረንዳው ላይ ወድቀው ሲሰባበሩ ተሰማት፡፡ ሶስተኛውን እንስታ ወደ መኝታዋ እየሄደች "አንተ ግን ከእኔ ጋር ትሆናለህ፡፡ አሸንፈናል!" አለች፡፡

ደረጃውን በመውጣት ላይ ሳለች እግሮቿ ዛሉባት፡፡

"አንዱ የህንድ ልጅ ቀረ...."



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚለውን ስንኝ አስታወሰች፡፡ ከዚያስ? ከዚያም አገባት ፤ በሰላምም ኖሩ - በማለት አሰበችና በድንገት ሃሳቧ ተግባበጠባት፡፡ ሁጐ ቤቱ ውስጥ እንዳለ ተሰማት፡፡ ሁጐ መኝታ ቤት እየጠበቃት ነው፡፡

'የለም! በጣም ስለደከመኝ በቁሜ እየቃዠሁ ነው...' በማለት ለራሷ ማስታወስ ሞከረች፡፡ በዝግታ ደረጃውን እየወጣች ሳለ የሆነ ነገር ከእጇ ላይ ወደቀ፡፡ ሽጉጡ ነበር፡፡ የቻይና አሻንጉሊቱን ብቻ አጥብቃ ያዘች፡፡ ቤቱ ጨለምለም ያለ ሲሆን ወደ ላይ ስትጠጋ ቀፈፋት፡፡ ቤቱ ውስጥ ብቻዋን አለመሆኗ ተሰማት፡፡ ሁጐ አብሯት ነበር.....

'እንዱ የህንድ ልጅ ብቻ ቀረ .....'

ከዚያስ መጨረሻው እንዴት ነበር? ለማስታወስ ሞከረች፡፡ በሯ ላይ ደረሰችና ከፍታ ገባች፡፡ ክፍሏ ውስጥ ጣሪያ ላይ የተንጠላጠለው ሜንጦ ትዝ አላት፡፡ ቀና ብላ ስታየው ገመድ ተንጠልጥሎበታል፡፡ ከገመዱ ስር ደግሞ አንድ ወንበር ነበር፡፡ ወንበሩን በኋላ ወደ ጐን ትገፋዋለች፡፡

ሁጐ የሚፈልገው ያንን ነበር፡፡

ወዲያውኑ የግጥሙ የመጨረሻ ስንኝ ትዝ አላት፡፡

.... የተረፈውም ልጅ ራሱን አነቀ፡፡

ትንሹ የቻይና አሻንጉሊት ከእጇ ላይ አምልጧት እርቧም ወደ ፊት ተንደረደረች፡፡ ቀዝቃዛው እጅ ፤ የሲሪል እጅ አንገቷን ነካት፡፡

"ወደ ድንጋዩ ዋኝ ፤ ሲሪል ..."

ቀስ ብላ ወንበሩ ላይ ቆመች፡፡ የተንጠለጠለውን ገመድ አስተካክላ አንገቷ ላይ አስገባችው፡፡

ሁጐ ቁጭ ብሎ እያያት ነበር፡፡ ወዲያውኑ ወንበሩን በእግሯ ወርውራ ጣለችው፡፡

• • •

የስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነሩ የሆኑት ሰር ቶማስ ሌጌ በቁጣ እና ባለማመን ነበር የሚናገሩት፡፡

"ሁሉም ነገር የማይታመን ነው!"



t.me/OLDBOOKSPDF

መርማሪ ሜይን በትህትና ነበር የሚመልስላቸው፡፡

"አዎን ጌታዬ ፤ የማይታመን ነው፡፡"

"አስር ሰው ደሴቱ ላይ ሞቷል እያልክ ነው፡፡ ምንም ስሜት አልሰጠኝም" አሉ ሰር ቶማስ፡፡

"አስሩም ሞተዋል ፤ ጌታዬ"

"የሆነ ሰው ገድሏቸዋል፡፡ ካልሆነማ እንዴት አስሩም ...?"

"ችግሩ እንዴት እንደሆነ አለማወቃችን ነው ፤ ጌታዬ"

"ለመሆኑ የዶ/ሩ ምርመራ ምን ያሳያል?"

"ምንም አያሳይም፡፡ ዋርግሬቭ እና ሎምባርድ በጥይት ሲገደሉ ወደ ኤሚሊ እና ማሪስተን ደግሞ በሳይናይድ መርዝ ሞተዋል፡፡ ወ/ሮ ሮጀርስ ከመጠን ያለፈ የእንቅልፍ ኪኒን የገደላቸው ሲሆን ባለቤታቸው ሮጀርስ ደግሞ በመጥረቢያ ተፈልጦ ሞቷል፡፡ ብሎርም አናቱን ተፈንክቶ የሞተ ሲሆን ዶ/ር አርመስትሮንግ ደግሞ ውሃ ውስጥ ተዘፍቆ ሞቷል፡፡ ወ/ሪት ቬራ ታንቃ ሞታለች፡፡" በማለት መርማሪው ለረዳት ኮሚሽኑ ገለፀላቸው፡፡

"የሚገርም ነው፡፡ ለመሆኑ ከስቲክልሃቨን መንደር ነዋሪዎችስ ምንም አላገኘህም? መቼም የሆነ ነገር ሳያዩ አይቀርም-"

"ነዋሪዎቹ ምስኪን አሳ አጥማጆች ናቸው ፤ ጌታዬ፡፡ የሰሙት ነገር ቢኖር ደሴቷን አውን የተባሉ ቱጃር እንደገዛት ብቻ ነው፡፡"

• • •



t.me/OLDBOOKSPDF

## ድህረ - ታሪክ

"ለመሆኑ የደሴቱን ሽያጭ እና ድግሱን ያመቻቸው ሰው ማን ነበር?" ረዳት ኮሚሽኑ ጠየቁ፡፡

"አይዛክ ሞሪስ የተባለ ሰው ነው ! ጌታዬ" መርማሪ ሜይን መለሰላቸው፡፡

"ስለ ሞሪስ የሚታወቅ ነገር አለ?"

"ከሰስት አመት በፊት ከቤኒቶ ጋር በመተባበር የማጭበርበር ወንጀል ላይ የተሳተፈ ቢሆንም ማረጋገጫ ግን አልተገኘበትም፡፡ በዚያ ሌላ በአደንዛዥ እፅ ዝውውር የሚጠረጠር ነበር፡፡ ነገር ግን ለዚህም ማረጋገጫ የለንም"

"ለምን ስለ ደሴቱ አትጠይቁትም?"

"አንችልም ! ጌታዬ፡፡ ሞሪስ ሞቷል፡፡"

"የደሴቷን ሽያጭ እንዴት ነበር ያስፈፀመው"

"ግዢውን የፈፀመው ራሱ ሲሆን ስሙን ሳልጠቀሰው ሶስተኛ ወገን ነበር በውክልና የተቆጣጠረው፡፡"

" የሂሳብ አያያዙ ላይ የሆነ ፍንጭስ የለም?"

መርማሪ ሜይን ፈገግ ብሎ "ጌታዬ ሞሪስ ስህተት የሚያሳልፍ ሰው አይደለም፡፡ ከቤኒቶ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሂሳብ ምርመራ አድርገንበት ምንም አላገኘንም፡፡" በማለት አረጋገጠላቸው፡፡ በመቀጠልም "ሞሪስ ነበር ስቲክል ሃቫን በማምራት የደሴቷ ባለቤት - አቶ ኦውን - ራሱ መሆኑን የተናገረው፡፡ ለነዋሪዎቹ ደሴቱ ላይ ለአንድ ሳምንት የሚዘልቅ ድግስ እና የመዝናኛ ውድድር እንደሚደረግ ተናግሮ ነበር፡፡"

"ነዋሪዎቹ ምንም አልጠረጠሩም ታዲያ?" ረዳት ኮሚሽነሩ ተገርመው ጠየቁት፡፡

መርማሪው ፈገግ በማለት ነበር የመለሰላቸው፡፡

"ጌታዬ ! የሀንድ ደሴት ከኦውን በፊት የወጣቱ ኤልመር ሮብሰን ንብረት ነበረች፡፡ ወጣቱ በርካታ ድግስ እና ጨዋታ በማድረጉ ነበር በመንደሩ ነዋሪ የሚታወቀው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ በደሴቷ ላይ ምንም ቢደረግ የመንደሩ ነዋሪዎች ጨዋታ ነው የሚመስላቸው፡፡"

ረዳት ኮሚሽነሩ በተሰጣቸው ማብራሪያ አልረኩም ነበር፡፡ መርማሪ ሚይን ገለፃውን ቀጠለ፡፡

"ፍሬድ ናርኮት የተባለ ሰው ነበር ሚቾቹን ወደ ደሴቷ ያደረሳቸው፡፡ ከቀድሞ የወጣቱ ኤልመር ሮብሰን እንግዶች የተለዩ እንነደበሩ ተናግሯል፡፡"

"ለመሆኑ መቼ ነበር ወደ ደሴቷ የነብስ አድን የሄደው?" በማለት ረዳት ኮምሺነሩ ጠየቁ፡፡

"ነሐሴ 11 ቀን የመስታወት ምልክት መታየቱን አንድ ወጣት አሳወቀ፡፡ በ12 የባህሩ ማዕበል ጋብ ሲል ነበር የደረሱት፡፡ ከዛ በፊት ግን ምንም አይነት ጀልባ ለመሳክ አልተቻለም፡፡"

"ከደሴቷ በዋና ለማምለጥ የቻለ ሰው የለም?"

"ጌታዬ ከ1 ማይል የሚበልጥ ርቀት ሲኖር አስቸጋሪውን ንፋስ የሚቋቋም ዋነናተኛም የለም፡፡ ሰው በዋና ቢያቋርጥም እንኳን ዳር ላይ ሰዎች ሲያዩት ይችላሉ፡፡"

"ቤቱ ውስጥ ያገኛችሁት የተቀዳ ድምፅስ ምን ጠቁሟችኋል?"

"ሸክላው በአንድ ታዋቂ የፊልምና የዘፈን ኩባንያ የተመረተ ሲሆን ለአቶ አውን በአይዛክ ሞሪስ በኩል እንዲደርስ የተላከ ነበር፡፡"

"የተቀረፀበት መልክትስ?"

"የክስ ዝርዝሮች ናቸው ጌታዬ፡፡ ደሴቷ ላይ ቀድመው ከደረሱት የሮጀርስ ባልና ሚስት ይጀምራል፡፡ ባልና ሚስቱ ለቀጣሪያቸው ወ/ሮ ብራንዲ ሞት ተጠያቂ እንደሆኑ ያትታል፡፡ በወቅቱ ዳኛ ሁለቱን ነፃ ቢለቃቸውም የሟቿ ዶክተር የተለየ ወንጀል ሊኖር እንደሚችል ግምቱን አስቀምጦ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጀመሪያ አንድ ሰው ራሱን በዛ ሁኔታ አይገድልም፡፡ በመቀጠል ስናስበው ብሎር የገዳይነት ባህርይ የለውም፡፡"

"በግምትህ እስማማለሁ" አሉ ረዳት ኮምሽነሩ፡፡

"ስለዚህ ሁሉም በሞቱበት ወቅት ሌላ አንድ ሰው ደሴቷ ላይ ነበር፡፡ ያ ሰው ግድያውን ከፈጸመ በኋላ የት ሄደ? የመንደሯ ነዋሪዎች በምንም አይነት ሰው ከደሴቷ ሊያመልጥ እንደማይችል አረጋግጠውልናል፡፡ ስለዚህ ጥያቄ አሁንም ይቀራል፡፡ ማን ገደላቸው?"

• • •

ኤማ፡ጀን የተባለች የአሳ አጥማጅ ጀልባ እንዳገኘቺው የተገለፀ አንድ መረጃ ለስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ ተላከ፡፡ መረጃውም የሚከተለው ደብዳቤ ነበር፡፡

ከልጅነቴ ጀምሮ የተለያዩ ታሪኮችን ሳነብ ሰዎች ደብዳቤ ፅፈው ጠርሙስ ውስጥ በመጨመር ውቅያኖስ ውስጥ ይወረውሩታል፡፡ ደብዳቤው የመገኘት እድሉ በጣም ጠባብ ነው፡፡ እኔም የግድያ ኑዛዜዬን ፅፌ ውሃ ውስጥ የጨመርኩት አንድም ምስጢራዊ ግድያዬን ለመግለፅ ሲሆን ካልተገኘ ደግሞ ምስጢሩ ተዳፍኖ ይቀራል በማለት ነው፡፡

የሰው ልጅ ተሰቃይቶ ሲሞት መመልከት ያስደስተኛል፡፡ ከዚህ የስነ ልቦና ቀውስ ውጪ ደግሞ ለፍትህ ልዩ ፍቅር ነበረኝ፡፡ ወንጀለኞች እንዲቀጡ ካለኝ ፅኑ ፍላጐት በመነሳት ነበር ህግ መማር የወሰንኩት፡፡

በዳኝነት ስራዬ የተመለከትኩት በርካታ ነገር ቢኖርም በተደጋጋሚ ለፍርድ የሚቀርቡ ሰዎች ያለ ጥፋታቸው በአቃቤ ህግ እና ፖሊስ ምስጢራዊ ትስስር እና በመረጃ ጉድለት ብቻ ይፈረድባቸዋል፡፡ እንደ ኤድዋርድ ሴተን ያሉ ሰዎች ያለ ጥፋታቸው የተፈረደባቸው ብዙ ናቸው፡፡

በዳኝነት ስራዬ ወቅት ህግን በታማኝነት አስፈፅሜያለሁ፡፡ ነገር ግን ከጊዜያት በኋላ በድንገት የመግደል ፍላጐት ሞላኝ፡፡ ለመግደል ስል ብቻ ነፃ ሰዎችን መጉዳት አልፈለግሁምና መሞት ያለባቸውን ሰዎች ፈለግሁ፡፡ ለዚህም ወንጀል ፈፅመው ከፍትህ ያመለጡ ሰዎችን አገኘሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ደሴቷን በሞሪስ ስም ገዛሁ፡፡ አስሩ እንግዶች ነሐሴ 8 ቀን ደሴቷ ላይ እንዲመጡ በተለያዩ አሳማኝ መንገዶች ጠራኋቸው፡፡ ሞሪስ ከለንደን ሳይነሳ ነበር በመርዝ የገደልኩት፡፡ ምንም አይነት መረጃ እንደማያስቀር እርግጠኛ ነበርኩኝ፡፡

ቀላል ወንጀል የፈፀሙትን ነበር በመጀመሪያ የገደልኳቸው፡፡ ማረስተን እና ሮጀርስ ብዙ ሳይሰቃዩ ሞቱ፡፡ የማረስተን እና ወ/ሮ ሮጀርስ ብርጭቆ ውስጥ መርዝ ጨምሬ ነበር የገደልኳቸው፡፡ ጀነራል ማካርተርም ሳይሰቃይ ነበር የሞተው፡፡

ደሴቷ ላይ ሰባታችን ብቻ ስንቀር ነበር ዶ/ር አርመስትሮንግን የመለመልኩት፡፡ እንደ እኔ ያለ ሰው ግድያ እንደማይፈፅም በመገመቱ አመነኝ፡፡ ሎምባርድን ነበር ሁሉም የጠረጠሩት፡፡

ነሐሴ 10 ቀን ሮጀርስን በመጥረቢያ ከገደልኩት በኋላ የመኝታ ቤቶቹን ቁልፍ ከኪሱ ወሰድኩኝ፡፡ በመቀጠል የሮጀርስ ሬሳ ተገኝቶ ሁሉም ግራ በተጋቡበት ወቅት ወደ ሎምባርድ ክፍል ገብቼ ሽጉጡን ሰረቅሁት፡፡ ሽጉጥ እንደያዘ የነገረኝ ሞሪስ ነበር፡፡

የወ/ሮ ኤሚሊ ብርጭቆ ውስጥ ቀላል መርዝ ጨምሬ ነበር ያዳከምኳቸው፡፡ በሞቱበት ወቅት ንብ ያስገባሁት ለጨዋታው ማግር ብዬ ነበር፡፡

ከአርመስትሮንግ ጋር ባቀድነው መሰረት የራሴን ሃሰተኛ ሞት አቀነባበርን፡፡ ፕላስተር እና ቀለም በመጠቀም ግንባሬን በጥይት የተመታሁ አስመሰለኝ፡፡ ሬሳውን በመጠጋት የምርመራ ውጤት የሚያቀርበው እርሱ በመሆኑ ሌሎቹ እንደማይጠረጥሩ እርግጠኛ ነበርን፡፡

ዶ/ር አርመስትሮንግ መሞቴን አረጋግጠላቸው አስከሬኔን ወደ መኝታ ክፍሌ አስገባልኝ፡፡ ከዚያ ጀምሮ በነፃነት መንቀሳቀስ ቻልኩኝ፡፡

በዚያው ሌሊት ለስምንት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ከአርመስትሮንግ ጋር ባህር ዳርቻ ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝን፡፡ በሰአቱ ነበር የተገናኘነው፡፡ ባህሩን ቁልቁል ስንመለከተው በጣም አስፈሪ ርቀት ነበረው፡፡ በዚያን ሁሉ ወቅት አርመስትሮንግ


t.me/OLDBOOKSPDF

